# ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ህብረት
የቲዎሪ መፅሄት
በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሁኔታና የደርግ የምርት ዘመቻ

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ሚያዝያ 1971

# መ ግ ቢ ያ

ከየካቲት አብዮት ወዲህ በኢኮኖሚያዊና በታሪካዊ ይዘቶቻቸው የረዥም በርቀቀውን ኢኮኖሚ መሠረት የሚያናጉና የካፒታሊዝምን እድገት የሚያሰናክሉ፣የምርት ሃይሎችን እድገት የሚያፋጥኑ፣የአገሪቱን ኢኮኖሚ የሚያሳድጉ፣የሰፊውን ህዝብ ኑሮ የሚያሻሽሉ፣የአገሪቱን በሒሳዊ ነፃነት የሚያስከብሩ፣ወዘተ ብዙ የኢኮኖሚ ለውጦች ተደርገዋል፡፡ እነዚሁ ለውጦች በአብዮት ጄልነታቸው በሰፊ ት አመታት በሰፊው ህዝብና በተራማጅ ሃይሎች ሁሉ ቢሰተጋቡ ቆይተዋል፡፡

በሌላ በኩል ግን የተደረጉት ለውጦች ምን ያህል እንደተረጋገጡ/በስራ ላይ እንደዋሉ/፣የካፒታሊዝምን እድገት ምን ያህል እንዳሰናከሉ፣የምርት ሃይሎችን እድገት ምን ያህል እንዳፋጠኑ፣የአገሪቱን ኢኮኖሚ ምን ያህል እንዳሳደጉ፣የሰፊውን ህዝብ ኢኮኖሚ ችግር ምን ያህል እንደፈቱ፣የአገሪቱን በሒሳዊ ነፃነት ምን ያህል እንዳስከበሩ፣በተለይ በህብረተሰቡ ውስጥ ያስከተሏቸውን አሉታና አወንታ ውጤቶች የሚያብራ ኢኮኖሚ—ነክ ጥናቶች አልተካሄዱም፡፡ እንዲህ አይነቱ ጥናት ካልተካሄደ ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚከናወኑትን አዲስ የኢኮኖሚ ግንኙነቶችና ህጋጋት በሚገባ መጠበቅና ትክክለኛ የፖለቲካ ትግል ማካሄድ ያስቸግራል፡፡ ፖለቲካ የኢኮኖሚ ክምችት ነውና፡፡

በኢት ኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ ጥናት እንዲያዘጋጅ ያነሳሳን ዋናው ምክንያት ይህ ሲሆን ኢ ወ ፓ ከመስከረም 1970 ዓ ም ጀምሮ ''ሶሺሊዝምን ለመገንባት'' ''ነፍስ ለማዳን''፣ ወዘተ እያለ የሚያደርገው ''የአረንጓዴ''ዘመቻ መፍጠር የጀመረው ውዥንብር ሁኔታዊ ተጨማሪ መነሻ ሆኖናል፡፡

በእነዚሁና በሌሎች ምክንያቶች በጥያቄው ላይ ''አንድ አይነት'' ጥናት ማቅረብ አስፈላጊና ሁኔታዊ ስለመሰለን ለውይይት መነሻ ይሆን ዘንድ እነሆ ይህን ጥናት አቅርበናል፡፡ ጥናቱ በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሏል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ቅድሚያና ታሪካዊ መንደርደሪያ ይሰጣል፡፡ ሁለተኛው ክፍል የዛሬይቱ ኢት የኢኮኖሚ ስርአት ምን አይነት እንደሆነና የህብረተሰቡን እድገት ሁኔታ ችግሮች፣ጥልቀቶቻቸውን ምክንያቶቻቸውንና መፍትሄዎቻቸውን ያጠናል፡፡ ሶስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ በደርግ የምርት ዘመቻ ላይ ሂሳዊ ትችት ካቀረበ በኋላ ተራማጆች ማድረግ የሚገባቸው አንዳንድ ተግባሮች ይሰነዝራል፡፡

ጥናቱ በአይነቱ የመጀመሪያ በመሆኑ፣ በማቴሪያል እጥረት፣ በእስታትስቲክስ ጉድለት፣ በዜና ማነስ፣ ወዘተ የተነሳ ብዙ ጉድለቶች የሚኖሩት ለመሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ስለሆነም አንባቢያን አስተያየት እንዲሰጡን እንጠይቃለን፡፡

# ክፍል አንድ

## የኢኮኖሚ ሥርዓትና ህብረተሰብ

"... The mode of production of material life conditions the social, political and intellectual life process in general,..... all the social and political relations, all religions and legal systems, all the theoretical outlooks which emerge in history, are tobe comprehended only when the material conditions of life of the respectively corresponding epochs are understood and the former are drived from these material conditions".[1]

''ያንዱን ህብረተሰብ የውስጥ ትግሎችና ከነዚህም ትግሎች የሚፈልቀውን የወደፊት ገስጋሲ የሚወስነው ሃይል ህብረተሰቡ የቆመበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው::''[2]

ከአራት አመት በፊት ጀምራ ኢት በሶሻሊዝም የምትታወቀው ''ህብረተሰቢት'' ቀብላ ነው:: ከ1970 ዓ ም መጠረሻ ገደማ በተለይም ከመስከረም 1971 ዓ ም ደግሞ ''የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ለመገንባት'' ከፍተኛ ዘመቻ እየተካሄደ ነው:: አሁን በለችበት ሁኔታ ኢት ህብረተሰቢት ልትባል ትችላለች ወይ? በአሁኒቷ ኢትስ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ለመገንባት ይቻላል ወይ? ኢት በአሁኑ ጊዜ የምትገኝበት የህብረተሰብ እድገት ደረጃ ምንድነው? ኢኮኖሚዋንስ ለመገንባት በአሁኑ ወቅት ማድረግ የሚቻለው ትክለኛ ዘመቻ ምንድን ነው?

1፡ እነዚህን የመሰሰሉትን ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ የሚቻለው ማርክስና ታጠቀ ከሰጠ አንጻሉት በእያንዳንዱ የህብረተሰብ የእድገት ደረጃ የሚገኙትን የምርት ሁኔታዎች የኢኮኖሚ ሥርዓት እና የህብረተሰብ ኢኮኖሚ እድገት ህገጋት በሚገባ መረዳት ሲቻል ስለሆነ፣

2፡ ሙሉ በሙሉ በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ላይ ያተኮረው ጽሑፋችንን በሶፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሠረታዊ ወይም ብዙ እውቀት ያለው ብቻ ሳይሆን ብዙ ወይም ምንም እውቀት የሌለው ማንኛውም አንባቢ ከሳንባች ችገር እንዲረዳውና ከዚህም በመነሳት በኢት ያለውን የኢኮኖሚ ሥርዓት ምንነት እንዲሁም የሚካሄዱትን ኢኮኖሚያዊ ድርጊቶች/ዘመቻዎች/በቀላሉ ለያይ የሚችልበት ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ስለመሰለን ስለኢኮኖሚ ሥርዓትና ህብረተሰብ ፒያሊቲካዊ ግንኙነት በመገደርደሪያ ደረጃ አስቀድመን እናቀርባለን::

ስለሆነም በዚህ አርእስት ስር በመጀመሪያ የኢኮኖሚ ሥርዓት ምን ማለት እንደሆነ እናብራራለን:: ከዚህም በኋላ አንድ የኢኮኖሚ ሥርዓት በአንድ ህብረተሰብ እድ



ገትና በፖለቲካዊ ነፃነት ላይ ያለውን ተጽእኖ በአጭር ትንተና እናመለከታለን:: ስለሆነም የመጀመሪያው የጽሑፍ ክፍል በሶስት ንዑስ ክፍሎች ይናፋታል:: እነርሱም:-

1 — የኢኮኖሚ ሥርዓት /ኢኮኖሚክ አስትራክቸር/ ትርጉም
2 — " "ና የህብረተሰብ እድገት
3 — " "ና ፖለቲካዊ ነፃነት የሚሉ ይሆናሉ::

### 1፡ 1 የኢኮኖሚ ሥርዓት ትርጉም

የኢኮኖሚ ሥርዓት የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ሳይንሳዊ ትርጉም እንደማንኛውም ተራ ታል በመዝገበ ቃላት በሚሰጥ ገለፃ ብቻ ለመረዳት ያስቸግራል:: በእንደዚህ አይነት አጭር ጽሑፍም በሚያረካና በሚያጠግብ ደረጃ ለማቅረብ ያስቸግራል:: እኛ የምናቀርበው አጭር ገለጻ ሁለትን ነጥቦች በመረዳት ላይ የተመሠረተ ነው:: በመዝገበ ቃላት ውስጥ በሚገኝ ትርጉም ላይ ብቻ አይወሰንም:: የጽንሱ ሐሳቡን ሙሉ ሳይንሳዊ ትርጉም እናቀርባለሁ ብለንም አያምንም::

ለኢኮኖሚ ሥርዓት ሳይንሳዊ ትርጉም ለመጀመሪያ ጊዜ የሰጠው ማርክስ ነው:: ስለሆነም መሠረታዊ በሆነው በማርክስ ገለፃ እንጀምራለን::

"In the social production of their life, men enter into definite relations that are indespensable and independent of their will, relations of production which corrospond to a definite stage of development of their material productive forces. The sum total of these relations of production constitutes the economic structure of society".[3]

በማርክስ አባባል የአንድ ህብረተሰብ የኢኮኖሚ ሥርዓት በዚያ ህብረተሰብ ውስጥ በአንድ የተወሰነ ታሪካዊ ወቅት የሚገኙ የምርት ሃይሎችና የእድገት ደረጃቸውን የሚያንፀባርቁ የምርት ግንኙነቶች ጠቅላላ ድምር ማለት ነው:: ይህን መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ትርጉም ለመረዳት በውስጡ የታቀፉትን ጽንሰ ሐሳቦች ዘርዘር አድርጎ መረዳት ያስፈልጋል:: የምርት ግንኙነትም የምርት ሃይሎች፣ የምርት ሃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ጠቅላላ ድምር የተሰኙት ያዘሉትን ሳይንሳዊ ትርጉም ለመረዳት እንሞክር::

በመጀመሪያ ምርት /ፕሮዳክሽን/ ምን ማለት ነው:: ምርት ማለት የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሳዊ ጥቅሞች ከተፈጥሮ ለማግኘት ተፈጥሮ በሰገኘለት ነገሮች/ናቹራል ኦብጀክትስ/ ላይ ጉልበቱን በማፍሰስ የሚያካሂደው የስራ ሂደት ወይም

ከነውን ማለት ነው። በሌላ አነጋገር በተፈጥሮ ውስጥ ያሉትን ነገሮች ቅርፃቸውን በመለወጥ ለእርሱ ኑሮ ለህብረተሰብ መኖር እንዲያገለግሉ የሰው ልጅ የሚፈጽመው ሥራ ማለት ነው። ራሱንና ህብረተሰቡን ለማኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማግኘት የሰው ልጅ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ የሚያከናውነው ሥራ ወይም ምርት በሁለት ክፍሎች የሚጠቃለሉ ንኡስ ክፍሎች አሉት። አንደኛው ክፍል የምርት መሣሪያዎችን ማጭድ፣ ማረሻ፣ በሬ፣ ትራክተር፣ መዶሻ፣ የኢንዱስትሪ መኪናዎች ወዘተ ቢይዝ ሁለተኛው ደግሞ ለወዲያው ጥቅም የሚውሉ እቃዎች/ኮንሰምሽን ጉድስ/ለማምረት የሚደረገውን ሥራ ይይዛል።

የሰው ልጅ የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሳዊ/ማቴሪያል/ ነገሮች እንደሁ በዘፈቃደ ሊያመርት አይችልም። በሌላ አነጋገር ተፈጥሮ ያቀረበችለትን ሁሉ እንደ አቅሙና እውቀቱ ቅርፃቸውን በሥራው እየለወጠ እንዲያገለግሉት ለማድረግ ሥራውን /ሌበሩን/ በተግባር ለመገዘር የሚያስችሉት ሁኔታዎች መኖር አለባቸው። የሚሠሩ/የሚለወጡ/ እና የሚለወጡባቸው ነገሮች ያስፈልጋሉ። የሚሠሩ ነገሮች ማለት ቅርፃቸውን በመለወጥ ለማምረት ጉልበትን የሚያፈስባቸው ማለት ነው። ጥሬ እቃ፣ ውሃ፣ መሬት፣ ወዘተ እንደምሳሌ ሆነው ሊወሰዱ ይችላሉ። የሚሠራባቸው ያልናቸው ሰው ተፈጥሮ ያቀረበችለትን ጉልበትን በመጠቀም ለማምረት የሚገለገልባቸውን መሣሪያዎች ይይዛሉ። እንደምሳሌ የኢንዱስትሪ መኪናዎች፣ መሣሪያዎች፣ የማምረቻ ህንጻዎች፣ ወዘተ ለመጥቀስ ይቻላል። ሁለቱ ማለት የሰው ልጅ ለጥቅሙ ቅርፃቸውን ለመለወጥ ጉልበትን የሚያፈስባቸው የሚሠራባቸው ና ይህን ለማከናወን የሚገለገልባቸው ነገሮች ተደምረው የምርት መሣሪያዎች ይባላሉ።

የሰው ልጅ ተፈጥሮ የሰጠው አልምቶ ሊጠቀም የሚችለው መሬት ቢኖረው፣ ቆፍሮ ሊያቀልጠው የሚችለው የማእድን ሀብት ቢኖረው፣ ወዘተ ወዘተ በእጆችና በእግሮች ብቻ ወደሬት ፈቅ ሊያደርገው ማለት ተፈጥሮ ያቀረበለትን ሁሉ በፈለገው መንገድ እየለወጠ ለጥቅም ሊያውለው አይችልም። ይህን ለማድረግ ከጉልበቱ ሌላ የጉልበቱ መገልገያ መሣሪያዎች እጅግ አድርገው ያስፈልጉታል። ምርት ከላ ምርት መሣሪያዎች ፈጽሞ የማይቻል ከመሆኑም ሌላ መጠንና አይነቱ በመሣሪያዎች አይነት ጥራትና መጥፎነት ይወሰናል። በዶማ ከሚቆፍር በበሬ የሚያርስ የበለጠ ያመርታል። በበሬ ከሚያርስ በትራክተር የሚያርስ የበለጠ ያመርታል። ሰውም ለኑሮው የሚያስፈልጉት ነገሮች ከዚህ ጋር ተያይዘው ይጨምራሉ ወይም ይሟላሉ። ስለሆነም ከሁለቱ ማለት የሰው ልጅ በጉልበቱ ከሚለውጣቸውና በጉልበቱ ለመለወጥ ከሚገለገልባቸው ነገሮች የሥራ መሣሪያዎች በምርት ሂደት ውስጥ የበለጠ አይነተኛ ቦታ ይይዛሉ።



ምርት ከላምርት መሣሪያዎች አይቻልም። በሌላ አነጋገር መሬት ቢኖር ማረሻ ከሌለ እህል ማምረት አይቻልም። የብረት ማቅለጫ መኪና ከሌለ ብረታ ብረት ማምረት አይቻልም። ይህ አንዱ ሃቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በጉልበት የነገሮችን ቅርጽ ለውጦ የምርት መሣሪያዎች ለመሥራትም ሆነ ከተሠራም በኋላ እንዲንቀሳቀሱና ጥቅም እንዲሰጡ ለማድረግ የሚችለው የሰው ልጅ ከሌለ የምርት መሣሪያዎች በራሳቸው በአርባታ ውስጥ ብዙ አያበረክቱም። የመኪናው ሞተር በሰው ልጅ ካልተከፈተ መኪናው ተገትሮ ከጥቅም ውጭ ይውላል ማለት ነው። በምርት ሂደት ውስጥ የሰው ልጅ እጅግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ስለዚህም ነው ማርክስ ''ሥራ የሀብት ሁሉ ምንጭ ነው'' ሲል ኤንገሊስ በዚህ ላይ በመጨመር ''ሥራ የራሱ የሰው ፈጣሪም ነው'' ያሉት።

በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ወደ አገልግሎት ለመለወጥ የሰው ጉልበት የሚፈስባቸው ተፈጥሮአዊ ነገሮች፣ እነዚህን ተፈጥሮአዊ ነገሮች ለጥቅም ለማዋል ቅርፃቸውን ለመለወጥ የሰው ልጅ የሚገለገልባቸው የምርት መሣሪያዎችና አምራች ሰው ራሱ ተደምረው የዚያን ህብረተሰብ የምርት ሃይሎች ያስገኛሉ። በሌላ አነጋገር የምርት ሃይሎች ማለት ለሰው ልጅ አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሳዊ ነገሮች ለማምረት የሚያስፈልጉት መሣሪያዎችና እነዚህን መሣሪያዎች በማንቀሳቀስ የምርት ሂደት እንዲሰራ የሚያደርጉት ሰዎች ድምር ማለት ነው።

ሰዎች ጉልበታቸውንና የምርት መሣሪያዎችን በመጠቀም በተፈጥሮ ላይ ከነውን ቢፈጽሙ በተናጠል ወይም በብቸኝነት አይደለም። በጋራ ወይም በማህበር ነው። ምርት በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ ማህበራዊ ነው የሚባለውም ለዚሁ ነው። አንድ ሸቀጥ ለማምረት የብዙ ሰዎች ተሳትፎን ይጠይቃል። በተለይ አሁን ባለንበት የኢንዱስትሪ ዘመን አንድ ሰው በተናጠል አንድ ሸቀጥ ሊያመርት አይችልም። ከዚህም ሌላ አንድ ሰው የሚሠራውን ሌላው ሰው ሳይሠራው ይችላል። አንድ ፋብሪካ የሚያመርተውን ሌላው ሳያመርተው ይችላል። አንድ አገር የሚያመርተውን ሁሉ ሌላው አገር ሳያመርተው ይችላል። በአንድ አገር ውስጥም የገጠሩ ክፍል የሚያመርተውን የከተማው ክፍል ሊያመርተው አይችልም። በዚህ ሁኔታ ሰዎች ለመኖር የሚያስፈልጓቸውን ቁሳቁሳዊ ነገሮች ሁሉ ለማምረት ይችሉ ዘንድ ያለውድ በግድ የተወሰነ ግንኙነት መፍጠር አለባቸው ማለት ነው። ለማምረት ብቻ ሳይሆን በየረድፉ የሚመረቱትን ለማግኘት በመካከላቸው ለመከፋፈልና ለመለዋወጥም የተወሰነ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። በሌላ አነጋገር በምርት ሂደት ውስጥ የሰዎች የጋራ ተሳትፎ፣ የስራ ክፍፍል የሃብት/የማቴሪያል ዌልዝ/ ክፍፍልና ልውውጥ አይነተኛ ቦታን ይይዛሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ ሰዎች እርስ በእርሳቸው አንድነት ይፈጥራሉ፣ ይያያዛሉ። በእያንዳንዳቸው ላይ ይመካሉ። በሱም ከፍላጎታቸው

ነፃ የሆነ አንድ የተወሰነ ግንኙነት ውስጥ ይገባሉ:: ማርክስ

> "In the social production of their life, men enter into definite relations that are indispensable and independent of their will". ይላል::

በማርክስ አባባል በምርት፣ በክፍፍል ዲስትሪቡሽን እና በልውውጥ ኤክስቼንጅ ሂደት ውስጥ ሰዎች የሚፈጥሩአቸው ግንኙነቶች የምርት ወይም የኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ይባላሉ::

የምርት ግንኙነቶች የተለያዩ ባህሪያት አሏቸው:: እነዚህ ልዩ ልዩ ባህሪያት የሚወሰኑት በምርት መሣሪያዎች ባለቤትነት ቅርፆች አይነት ነው:: በሌላ አነጋገር የአምራቾች ከምርት መሣሪያዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት የምርት ግንኙነቶችን መልክና አይነት ባህሪ ይወስናል:: በምርት ግንኙነት ውስጥ ሰዎች ከምርት መሣሪያዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት መሠረታዊና ዋናው ክፍል ነው:: በምርት መሣሪያዎች ባለቤትነት ላይ ተመስርተው የምርት ግንኙነቶች ወይ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ወይ ደግሞ ከብዝበዛ ነፃ የሆኑ ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህ የሚወሰነው የምርት መሣሪያዎች ባለቤትነት በማን ስር እንደሆነ ነው::

የምርት መሣሪያዎች በጥቂት ግለሰቦች ወይም መደቦች ግላዊ ባለቤትነት ስር ከሆኑ የምርት ግንኙነቱ ሀብት ያለው/ያላቸው/መደብ/መደቦች/ሀብት የሌላውን/የሌላቸውን/መደብ/መደቦች/የሚበዘብዙበት ዘበት ይሆናል:: የህብረተሰቡ ሀብት በግላዊ ባለቤትነት ስር የሆነባቸው የባሪያ፣ የጉልታዊና የከበርቴው የምርት ግንኙነቶች ለዚህ ምሳሌ ናቸው:: በተቃራኒው ደግሞ የምርት መሣሪያዎች በህብረተሰቡ የጋራ ቁጥጥር ስር ከሆኑ የምርት ግንኙነቱ ሰው በሰው የማይበዘበዝበት ይሆናል:: የጋርዮሽና የሶሻሊስት የምርት ግንኙነቶች ለዚህ ምሳሌዎች ናቸው:: እነዚህ በምርት መሣሪያዎች ባለቤትነት ልዩነቶች ላይ የተመሠረተ አምስት ልዩ ልዩ የምርት ግንኙነቶች በህብረተሰብ እድገት ታሪክ ውስጥ ይገኛሉ ማለት ነው::

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት የሚገኙ የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች ጠቅላላ ድምር የዚያን ህብረተሰብ ስልተ ምርት ያስገኛሉ:: ይህ ስልተ ምርት ደግሞ በመጀመሪያ የጠቀስነው የኢኮኖሚ ስርአት ማለት ነው:: በዚህ አይነት በህብረተሰብ እድገት ታሪክ ውስጥ የጋርዮሽ፣ የባሪያ፣ የጉልታዊ፣ የከበርቴና የሶሻሊስት የኢኮኖሚ ስርአቶች ይገኛሉ::



ከዚህ በላይ በቀረብነው አጭር ገለጻ የኢኮኖሚ ስርአት የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች ጠቅላላ ድምር መሆኑን ለማሳየት ሞክረናል:: አሁን ደግሞ አንዱ የኢኮኖሚ ስርአትና የህብረተሰብ እድገት ምን አይነት ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት እንዳላቸው እናሳያለን::

## 1፡ 2 የኢኮኖሚ ስርአትና የህብረተሰብ እድገት

አንድ ቤት ከለመሠረትና ጣራ አይሠራም:: መሠረት ኖሮም ጣራ ከሌለ ወይም ጣራ ኖሮ መሠረት ከሌለ ቤት አይኖርም:: እርግጥ የአንድ ቤት መሠረት ከለጣራ ሊኖር ይችላል:: ጣራው ግን ከለመሠረቱ ሊኖር አይችልም:: ይህም ማለት ለአንድ ቤት መኖር የቤቱ መሠረት ወሳኝ ነው ማለት ነው:: መሠረትና ጣራው በአንድ ላይ ገን ቤቱን ይፈጥራሉ:: ህብረተሰብም እንደዚሁ ነው:: ለመኖር መሠረትና ጣራ ያስፈልገዋል:: የህብረተሰብ መሠረት የኢኮኖሚው ስርአት ሲሆን ጣራው ደግሞ ላእላይ መዋቅሩ ነው:: ሁለቱ በአንድ ላይ የአንዱን ህብረተሰብ አይነትና እድገት ይወስናሉ:: የኢኮኖሚ ስርአት ምን ማለት እንደሆነ ከላይ ገልጠናል:: ላእላይ መዋቅሩን በአጭሩ እንገልጥ:: እስታሊን

> "The superstructure is the political legal, religious,artistic, phylosophical views of society and the political, legal and other instit-utions corresponding to them"[5] ይላል::

የአንድ ህብረተሰብ ላእላይ መዋቅር የህብረተሰቡ መሠረት የኢኮኖሚው ስርአት ነፀብራቅ ወይም ውጤት ነው:: የላእላይ መዋቅሩ አይነትና እድገት በመሠረቱ አይነት ይወሰናል:: መሠረቱ/የኢኮኖሚው ስርአት/ጉልታዊ ከሆነ ላእላይ መዋቅሩ ማለት በህብረተሰቡ ውስጥ የሚኖረው ፖለቲካ፣ ርእዮተአለም፣ ህግና ስርአትና ልዩ ልዩ ተቋሞች ጉልታዊ ይሆናሉ:: የከበርቴም ሆነ የሶሻሊስት መሠረቶች እንደዚሁ የየራሳቸው ላእላይ መዋቅሮች ይኖራቸዋል ማለት ነው:: ላእላይ መዋቅሩ እድሜ ከመሠረቱ እድሜ ጋር የተያያዘ ነው:: አሮጌ መሠረት በአዲስ ሲተካ አሮጌው ላእላይ መዋቅር በአዲስ ይተካል::

> "The superstructure is the product of one epoch, the epoch in which the given economic base exists and operates. The superstructure is therefore short lived, it is eliminated and disappears with the elimination and disappearance of the given base". 6

በመደብ በተከፋፈለ ህብረተሰብ ውስጥ እንደመሠረቱ ላእላይ መዋቅሩም መደባዊ ባህሪ ይኖረዋል፡፡ ይህ ማለት ገዥ መደቦች አስተሳሰባቸውን የሚያንፀባርቁትና የመደብ ጥቅማቸው የሚያስጠብቁ ህጎች፣ ደንቦች፣ ልምዶች፣ ተቋሞች፣ ወዘተ ይፈጥራሉ ማለት ነው፡፡ የላእላይ መዋቅሩ ፈጣሪ መሠረቱ ነው ማለት ግን ለመሠረቱ በህብረተሰብ እድገት ውስጥ የወሳኝነትን ቦታን ይሰጠዋል እንጂ በኋለኛው ላይ ተጽእኖ አይኖረውም ማለት አይደለም፡፡ ተጽእኖ አለው፡፡ ሁለቱ ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት አላቸው፡፡ አንዱ በሌላው ላይ እንደሁኔታው ቦታው ተጽእኖ ያደርጋል፡፡ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በገጽ 5 ላይ እስታሊን የሚከተለውን ይናገራል፡፡

> "The superstructure is a product of the base, but this by no means implies that it merely reflects the base, that it is passive, neutral, indifferent to the fate of its base, to the fate of the classes, to the character of the system. On the contrary, having come into being, it becomes an exceedingly active force actively assisting its base to take shape and consolidate itself, and doing its utmost to help the new system to finish off and eliminate the old base and the old classes". 7

የህብረተሰብ እድገት ታሪክ እንደሚያመለክተው በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ላእላይ መዋቅር የተወሰነ ቅርጽ ይዞ የሚፈጠረው የህብረተሰቡን መሠረት እንዲያገለግል ነው፡፡ ጥንካሬውና እድሜውም መሠረቱን ለማገልገል ከሚጫወተው ሚና ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በእድሜውም ውስጥ አሮጌውን የህብረተሰብ መሠረት ለመደምሰስ አዲሱን ለመገንባትና ለማጠናከር ጠንካራ ሚና ከተጫወተ በኋላ በአንድ በተወሰነ ደረጃ በህብረተሰቡ ውስጥ በሚገኙት መደቦችና መሠረቱም ጭምር ላይ የመሃል ሰፋሪነት ቦታ ይይዛል፡፡ ቀስ በቀስም ምንም አይነት ሚና ሊጫወት የማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርስና ላእላይ መዋቅርነቱ ይሰረዛል፡፡ ነገሩን ዘርዘር አድርገን እንመልከተው፡፡

የፊውዳሉ መሠረት የኢኮኖሚ ስርአት በከበርቴው ሲለወጥ የፊውዳሉ ላእላይ መዋቅር በከበርቴው ላእላይ መዋቅር ተተካ፡፡ የከበርቴው ላእላይ መዋቅር ለተወሰነ ጊዜ አሮጌውን የፊውዳሉን መሠረት ላእላይ መዋቅርና መደቦች ለመደምሰስና አዲሱን ማለት የከበርቴውን መሠረት ቅርጽ ለማስያዝና ለማጠናከር ጠንካራ ሚና ተጫውቷል፡፡ የኋላ የኋላ ግን ራሱ የሚያረጅበት ደረጃ ላይ ይደርስና የህብረተሰቡን መሠረት በማገልገል ፈንታ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በዚህን ወቅት የከበርቴው ህብረተሰብ መሠረትና ላእላይ መዋቅር ቅራኔ ውስጥ ይገባሉ፡፡ መሠረቱ ያረጀውን የከበርቴ ላእላይ መዋቅር ይጥልና አዲስ የሶሻሊስት ላእላይ መዋቅር ይፈጥራል፡፡ አዲሱ የሶሻሊስት ላእላይ መዋቅር አሮጌው የከበርቴ መሠረት ላእላይ መዋቅርና አሮጌ መደቦች ለመደምሰስና አዲሱን የሶሻሊ



ስት መሠረት ለማጠናከር ጠንካራ ሚና ይጫወታል፡፡ ይሁን እንጂ አሮጌ መደቦችና ላእላይ መዋቅር ጠርሰው ሲደመሰሱና ሲጠፉ፣ አዲሱ መሠረት ሲጠናከር ላእላይ መዋቅር በህብረተሰቡ ውስጥ ባሉት መደቦች ላይ እኩል አመለካከት ይኖረዋል፡፡ በመሠረቱም ላይ የመሃል ሰፋሪነት ቦታ ይይዛል፡፡

> "The superstructure has only to renounce this role of auxilury, it has only to pass from a position of active defence of its base to one of indifference towards it to adopt an equal attitude to all classes, and it loses its virtue and ceases to be a superstructure". 8

ከዚህ በላይ ያደረግነውን አጭር ገለፃ እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፡፡ የኢኮኖሚ ስርአት የህብረተሰብ እውነተኛና ዋና መሠረት ነው፡፡ በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት የአንድ ህብረተሰብ ላእላይ መዋቅር/ፖለቲካ፣ ህግ፣ ሃይማኖት፣ ባህል/ የኢኮኖሚው ስርአት እድገት ነፀብራቅ ነው፡፡ ላእላይ መዋቅሩ የኢኮኖሚውን ስርአት/መሠረቱን/ እንዲያገለግል በመሠረቱ የሚፈጠር ነው፡፡ በሁለቱ መካከል በሚፈጠር ቅራኔ አሮጌ መሠረትና ላእላይ መዋቅር በአዲስ መሠረትና ላእላይ መዋቅር የህብረተሰቡ የኢኮኖሚ መሠረት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስ ላእላይ መዋቅሩ ይደመሰሳል ይጠፋልም፡፡ የገለጣውን መሠረታዊ አሳቡን ብንወስድ የህብረተሰቡን እድገት የሚወስነው በመሠረቱ/የኢኮኖሚው ስርአት/እና በላእላይ መዋቅሩ መካከል ያለው ቅራኔ ነው፣ በዚህ ቅራኔ ውስጥ አብዛኛው ጊዜ ዋናውና ወሳኙ የኢኮኖሚው ስርአት/መሠረቱ/ነው የሚለው ሆኖ እናገኛለን፡፡ በማርክስ አነጋገር፣

> "the mode of production of material life conditions the social, political and intellectual life process in general". 9

የአንድ ህብረተሰብ የኢኮኖሚ ስርአት መሠረት በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በዚያ ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች ድምር መሆኑንና ምርት፣ የአርባታ/ምርት/ ሃይሎችና ግንኙነቶች ያዘሉትን ትርጉም ከላይ ገልጠናል፡፡ አንመለስበትም፡፡ አሁን የምናደርገው የሁለቱን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በመተንተን ድምራቸው የኢኮኖሚው ስርአት በህብረተሰብ እድገት ላይ የሚጫወተውን ሚና ማሳየት ይሆናል፡፡

ከታሪካዊ ቁስአካላዊነት እንደምንገነዘበው ሰዎች ለመኖር ምግብ፣ ልብስ፣ መጠለያና ሌሎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሳዊ ነገሮች ያስፈልጓቸዋል፡፡ እነዚህን ለማግኘት ደግሞ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ አነጋገር በተፈጥሮ ላይ ጉልበታቸውን በማፍሰስ የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች ማምረት አለባቸው፡፡ ካልሰሩ ማለት ካላረሱ/ካላመረቱ/ ተፈ

ጥሮ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ የያዘች ብትሆንም ሰዎች በፈለጉት መንገድ ልታቀርብላቸው አትችልም፡፡ ስለዚህ ምርት ሰዎች በምንም መንገድ ሊያስወግዱት የማይችሉት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለአንድ ህብረተሰብ ኑሮና እድገት መሠረት ነው፡፡ እንግዲህ የምርት አይነትና የእድገት ደረጃ በአንድ የተወሰነ ወቅት አንድ ህብረተሰብ የሚኖረውን የእድገት ደረጃ ይወስናል ማለት ነው፡፡

የሰዎች ኑሮና ቁሳቁሳዊ ፍላጎት ከትውልድ ትውልድ ከዘመን ዘመን ያለማቋረጥ ያድጋሉ፡፡ በአይነትም ሆነ በመጠን እየተለዋወጠና እየጨመረ የሚሄደውን ቁሳቁሳዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሰዎች በተፈጥሮ ውስጥ ያሉትን ሀብቶች ቅርፃቸውን በመለወጥ እንዲያገለግሏቸው ይበልጥ ይሠራሉ፡፡ ከተፈጥሮ የበለጠ ሀብት ለማምረት ይበልጥ ይታከታሉ፡፡ የሚያረቡት የሚያመርቱት ሀብት ዓይነትና መጠን በሚገለገሉባቸው መሣሪያዎች ስለሚወሰኑ የምርት መሣሪያዎቻቸውንም በያደርጡ ለማሻሻል ይገደዳሉ፡፡ በስራቸው ከሚያገኙት ልምድና ምርምር አሮጌ መሣሪያዎቻቸውን ማሻሻል ብቻ ሳይሆን አዳዲስ መሣሪያዎች ይፈጥራሉ፡፡ እውቀታቸው እየዳበረ ይሄዳል፡፡ እያደገ በሚሄደው እውቀታቸውም ተፈጥሮን ይበልጥ እያወቁት ይሄዳሉ፡፡ በተፈጥሮ ላይ የሚኖራቸው እውቀት እየጨመረ መሄዱና የአርበታ/የምርት/መሣሪያዎቻቸው በመጠንም ሆነ በአይነት እየተለዋወጡ መሄድ ይበልጥ ሀብት እንዲያፈሩ ያደርጋቸዋል፡፡

> "It is people, because of the knowledge they have acquired their experience and labour skills, who set in motion the instruments of production, who improve them invent machins, and add to their knowledge. In this way development of the productive forces is insured, and an ever-inereasing volume of material wealth obtained". 10

ማርክስ አንድ ህብረተሰብ ቁሳቁሳዊ ሀብት ማቴሪያል ዌልዝ ማፍራት ከቶ አንደሚጠፋና የቁሳቁሳዊ ሀብት ማምረት ለህብረተሰብ ህልውናና እድገት መሠረት እንደሆነ ይናገራል፡፡ ከዚህና አላይ ከጠቀስነው አባብ በሀብት ምርት ሂደት ውስጥ ከፍተኛና ወሳኝ ቦታ የሚጫወቱት ሰዎች በህብረተሰብም ህልውናና እድገት ላይ ተመሳሳይ ሚና እንዳላቸው ልንረዳ እንችላለን፡፡ ከለሰዎች ጥረት ሀብት ሊመረት ከልቻሉና ያለኗለኛው ደግሞ የህብረተሰብን ህልውና የሚወስን ከሆነ ሰዎችም የህብረተሰብን መኖርና አለመኖር እንዲሁም ማደግና አለማደግ ይወስናሉ ማለት ነው፡፡

ሰዎች የህብረተሰብን እድገት የሚወስኑት አሮጌ ምርት መሣሪያዎቻቸውን ያለማቋረጥ በማሻሻልና አዳዲስ በመፍጠር የቁሳቁሳዊ ሀብት አርበታን/ምርትን/ ለማሳደግ በሚያ



የአርበታ/ምርት/ግንኙነቶች አንደየጊዜውና ቦታው በመፍጠርም ጭምር ነው፡፡

> "In order to produce, they enter into definite connections and relations with one another and only within these social connections and relations does their action on nature, does production, take place".11

በምርት ሂደት ውስጥ ሰዎች በተናጠል ሀብት ሊያመርቱ እንደማይችሉና ምርት ማህበራዊ እንደሆነ፣ እንዲሁም ሰዎች በዚህ ሂደት ውስጥ የሚፈጥሯቸው ግንኙነቶች የሀብት ምርት የማይነጠሉ ክፍሎች በመሆናቸው ምርት ግንኙነቶችን እንደሚያስገኙ ከላይ ጠቅሰናል፡፡ እነዚህም ግንኙነቶች ከጋርዮሽ አንስቶ እስከ ሶሻሊስት ህብረተሰብ እንደሚኖር ይበልጥ እያደጉና እየተወሳሰቡ እንደሚሄዱ ተናገረናል፡፡

የምርት ግንኙነቶች የሚፈጠሩት በምርት ሃይሎች ነው፡፡ የምርት ሃይሎች የምርት ግንኙቶች የሚፈጥሩት የወደፊት እድገታቸውን ለማመቻቸት ነው፡፡ አፈጣጠሩ በታ የሚወስነው እንዴትና መቼ ነው?

የምርት ግንኙነቶች መሠረታቸው ሰዎች ከምርት መሣሪያዎች ባለቤትነት ጋር ያላቸው ግንኙነት ነው፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉት የምርት መሣሪያዎች በጥቂት ቡድኖች ወይም መደቦች ገላዊ ባለቤትነት ስር ከሆኑ አብዛኛው ሀብት የሌለው ይሆናል፡፡ ይህ ሀብት የሌለው የህዝብ ክፍል ለመኖር ሲል በባሪያ ህብረተሰብ በባሪያነት፣ በጉልታዊ ህብረተሰብ ስር በጭሰኝነት፣ በከበርቴው ህብረተሰብ ደግሞ በወዝ አደርነት ሀብት ላላቸው መደቦች ይሰራል፡፡ ሀብት ያላቸውና የሌላቸው መደቦች በምርት ሥራ ውስጥ የሚኖራቸው ግንኙነት የአሠሪና የሠሪ፣ የተቀማጭ በላና የሠርቶ በላ፣ የበላይና የበታች፣ የበዝባዥና የተበዝባዥ፣ የጨቋኝና የተጨቋኝ ይሆናል፡፡ ሀብት በህብረተሰቡ ባለቤትነት ቁጥጥር ሥር በሆነባቸው በጋርዮሽና በሶሻሊስት ህብረተሰብ ውስጥ ደግሞ በምርት ሂደት ውስጥ የሚኖሩት የሰዎች ግንኙነቶች የምርት ግንኙነቶች በህብረትና በጋራ መረዳዳት ላይ የተመሠረቱ አንዱ ቡድን መደብ ሌላውን የማይበዘብዝባቸው ይሆናሉ፡፡

የምርት ሃይሎች የምርት ግንኙነቶች የሚፈጥሩት ለእድገታቸው አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ነው ብለናል፡፡ አንዱ የምርት ግንኙነት ከተፈጠረ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ በተለይ በልጅነት እድሜው አዲስ እንደተፈጠረ የምርት ሃይሎችን እድገት ያበረታታል፡፡ ለሰዎች እድገት፣ ለምርት መሣሪያዎች መሻሻል፣ ብሎም ለቁሳቁሳዊ ምርት እድገትና ለሰው ልጆች ኑሮ መሻሻልና ለህብረተሰብ እድገት አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ይህ የሚሆን

ውም የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች የእድገት ደረጃዎች በሚጣጣሙበት ጊዜ ነው::
ይሁን እንጂ የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች ሁልጊዜ አይጣጣሙም::

እናብራራ:—

የምርት ሃይሎች በጣም የሚንቀሳቀሱ፣ ያለማቋረጥ ሁልጊዜ የሚያድጉ፣ በመጠንም
በቀጥር እየጨመሩና አርጊዎች በአዲሶች እየተተኩ ወደፊት የሚገሰግሱ ናቸው:: በዚህ
መልክ ከእነርሱ የእድገት ፍጥነት ጋር የሚስተካከል የእድገት ፍጥነት ያለው የምርት
ግንኙነት ያስፈልጋቸዋል:: የምርት ግንኙነቶች ግን የምርት ሃይሎችን ያህል ተንቀሳ
ቃሽ አይደሉም:: ይበልጥ የረጉ ናቸው:: ስለሆነም እድገታቸው ከምርት ሃይሎች ጋ
ር እኩል ሊራመድ አይችልም:: ከአንድ ከተወሰነ ደረጃ በኋላ ከምርት ሃይሎች እድገ
ት ከበስተኋር ብ ይቀራሉ:: በተለይ ወደ መጠረሻ አድሚአቸው ከአዲሶች የምርት ሃይሎ
ች ጋር ሲነፃፀሩ በጣም ከማርጀታቸው የተነሳ ለምርት ሃይሎች የወደፊት እርምጃ እንቅ
ፋት ይሆናሉ:: በዚህ ወቅት የሰዎች የመፍጠር ችሎታ፣ የስራ መንፈስ፣ ብሎም የህብ
ት ምርት የሰው ልጆች ኑሮና የህብረተሰብ እድገት ይቀጥታሉ:: የምርት ግንኙነቶች
ከምርት ሃይሎች እድገት ጋር መጣጣማቸው ያልቃል:: የምርት ሃይሎች ወደፊት ለመራመ
ድ አዲስ ተስማሚ የምርት ግንኙነቶች ለመፍጠር ትግል ያካሂዳሉ:: አርጊዎች የምርት
ግንኙነቶችም በበኩላቸው ባሉበት ረግተው ለመቆየት ከአዲሶች የምርት ሃይሎች ጋር ትን
ቅንቅ ያደርጋሉ:: አዲሶች የምርት ሃይሎችና አርጊዎች የምርት ግንኙነቶች ግጭት ው
ስጥ ይገባሉ ማለት ነው:: በሁለቱ መካከል የሚደረገው ግጭት በከፍተኛ ደረጃ የህብ
ረተሰብ እድገት አራማጅ የሆነውን ህዝባዊ አብዮትን ያስነሳል:: የምርት ሃይሎች የ
ምርት ግንኙነቶች የሚፈጥሩት ለወደፊት እድገታቸው የሚጥሙ ሁኔታዎች ለማመቻቸት ቢሆን
ድርጊታቸውንም የሚያከናውኑት በአብዮት ነው::

> "The productive forces are the most mobile element in the mode of production, they are continually changing since people are constantly improving the instruments of labour and accumulating production experience. As for the relations of production, these change according to the level of development of the productive forces and in their turn influence this development'.
>
> When the relations of production correspond to the level of development of the productive forces, the latter develop uninterruptedly....when the relations of production do not correspond to the level of development of the productive forces, they act as a brake on production....A definite level of the productive forces requires the corresponding relations of production.... when the relations of production lag behind the development of the productive forces, become outdated



> replaced by new ones. In a society divided into hostile classes the old relations of production are superseded by new ones through social revolution". 12

ይህ ከዚህ በላይ የጠቀስነው የኒኪቲን ገለጻ ማርክስ 15 ዓመት ሙሉ ፖለቲካዊ
ኢኮኖሚ አጥንቶ አ ኢ አ በ1959 ዓ ም፣

> "At.a certain stage of their development, the material productive forces of society come in conflict with the existing relations of production or....with the property relations within which they have been at work hitherto. From forms of development of the productive forces these relations turn into their fetters. Then begins an epoch of social revolution". 13 በማለት የፃፈው አብዮታዊ አባዘ ነው::

የህብረተሰብን የእድገት ታሪክ ስንመለከት በምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች መካከል
እንደየጊዜው እንደየበታው በተፈጠሩት ቅራኒዎች ሳይ ተመስርተው በተካሄዱት አብዮቶች ስቢ
ያ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃዎች እያደጉ የመጡ አምስት ልዩ ልዩ የምርት ግንኙነቶች
እንዳሉ እንገነዘባለን:: ከሁሉም ዝቅተኛ የሆነው የጋርዮሽ የምርት ግንኙነት በባሪያው
የባሪያው በበላበተ፣ የባላበቱ በከበርቴው የከበርቴው ደግሞ ከፍተኛ በሆነው በሶሻሊስት
የምርት ግንኙነቶች እየተተኩ መጥተዋል:: ህብረተሰብም ይህንን ሂደት በመከተል ከዝቅተ
ኛ ወደ ከፍተኛ እያደገ መጥቷል::

አምስቱን የምርት ግንኙነቶች ብናወዳድራቸው በቀረብነው የቀደም ተከተል አቀማመጥ
መሠረት አንዱ ከሌላው ከፍተኛና ለምርት ሃይሎች እድገት ይበልጥ ተስማሚ ሆኖ እናገኘዋለ
ን:: የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ለምርት ሃይሎች እድገት እጅግ በጣም በር ከፋች፣
አመቺ ሁኔታ ፈጣሪና ነፃነት አስገኚ ቢሆንም ሌሎችም የምርት ግንኙነቶች እንደዚሁ በአን
ድ የተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ተመሳሳይ አብዮታዊ ሚና ተጫውተዋል::

ለምሳሌ:— የከበርቴው የምርት ግንኙነት በባላበታዊው የምርት ግንኙነት ውስጥ
ለፈለቀትና የወደፊት እድገታቸው በዚህ በአረጀው የምርት ግንኙነት ታፍኖ ለተያዘው አዲስ
የምርት ሃይሎች እድገት አራሱ የኋላ ኋላ አርጅቶ እንቅፋት እስኪሆንባቸው ድረስ ለተወሰ
ነ ጊዜ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል:: ነገሩን ዘርዘር አድርገን እንመልከተው::

የምርት ግንኙነቶች መሠረት የሚወስነው በምርት መሣሪያዎች ባለቤትነት ነው ብለና
ል:: በባላበታዊ የምርት ግንኙነት ውስጥ ዋናው የምርት ማፍሪያ መሣሪያ መሬት ነው::
ስለሆነም የሰዎች ግንኙነት/የምርት ግንኙነት/የሚወስነው በመሬት ባለቤትነት ላይ በሳቸው

ግንኙነት ላይ ይሆናል:: የመሬት ባለቤትነት ያላቸው ቡድኖች ወይም መደቦች በህብረተሰቡ ውስጥ የመሬት ባለቤቶች ወይም ጌቶች ወይም ባለሀብቶች ይሆናሉ:: እነዚህ መሬትን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው የህብረተሰቡን ሀብት የግል ሃብታቸው የሚያደርጉ መደቦች ቡድኖች ከታሪክ እንደምንገነዘበው በቁጥራቸው አነስተኛ ናቸው:: ይኸም በመሆኑ በህብረሰቡ ውስጥ ያለው አብዛኛው ህዝብ መሬት የለሽ ይሆናል:: በህብረተሰቡ ውስጥ መሬት ያላቸው ጥቂት መደቦች ቡድኖችና መሬት የሌላቸው ብዙ መደቦች ቡድኖች ይኖራሉ ማለት ነው:: ይሁን እንጂ ያላቸውም ሆኑ የሌላቸው መኖር አለባቸው:: ለመኖር ደግሞ ሀብት ማርበት ያስፈልጋቸዋል:: ባይወዱ በግድ በምርት ሂደት ውስጥ የተወሰነ ግንኙነት ይፈጥራሉ:: መሬት ያለው በሀብትነት የያዘውን መሬት ለመጠቀም የሚሠራለት ይፈልጋል:: መሬት የሌለው ደግሞ ለኑሮው የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሳዊ ነገሮች ለማፍራት ጉልበቱን የሚያፈስበቸው ተፈጥሮአዊ ነገሮች ያስፈልጉታል:: እነዚህ ተፈጥሮአዊ ነገሮች ግን በመሬት ጌቶች ባለቤትነት ስር ሆነውበታል:: እንዲህ አይነቱ ሁኔታ መሬት የለሹ መሬት ላለው እንዲሰራ ያስገድደዋል:: መሬት ያላቸውና የሌላቸው ለራሳቸውና ለህብረተሰቡ መኖር አስፈላጊ የሆነውን ምርት ለማምረት ባይወዱ በግድ ግንኙነት ይፈጥራሉ:: ከለዚህ ግንኙነት መሬትን አርሶ፣ ከብትን አርብቶ፣ ወዘተ የባላባታዊውን ህብረተሰብ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ አይቻልም::

የባላባት የምርት ግንኙነት ከባሪያው የምርት ግንኙነት ከፍተኛ ነበር:: በዚህ ግንኙነት ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ቢሆንም ሰዎች እንደ እቃ ከመሸጥ ከመለወጥ ''ነፃ'' ወጥተዋል:: እንደምስር ወይም እንደበረሬ ማለት እንደማንኛውም የምርት መሣሪያ ከመታየትና ከመያዝ ድነዋል:: የምርት ሃይሎች ይበልጥ ሊያድጉ የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥረዋል:: የአረሽ ዘዴ፣ የከብት አርባታ፣ የገበሽ አጠቃቀም ወዘተ በበሬው እንዲሻሻሉ ሆነዋል:: ከብረት በተሰራ ማረሻ መጠቀም፣ ከብረታብረት የተሰሩ እቃዎች ማምረት የእጅ ጥበብ ፋብሪካዎች ማስፋፋት፣ ጥሬ እቃዎችን በልዩ ልዩ ቅርፆች መለወጥ ወዘተ ከባሪያው የምርት ግንኙነት በላቀ መንገድ እንዲከናወኑ ሆነዋል:: ጉልበትና ሁሉ የምርት መሣሪያዎችም በዚህ መልክ በማደጋቸው የሰው ልጅ ለማምረት የሚያጠፋው ከባሪያው ዘመን ቀነሷል:: የሚያመርተውም ሀብት ጨምሯል:: ይሁን እንጂ በባላባታዊ ህብረተሰብ የሚመረተው ምርት በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑም ሌላ ለራስ ጥቅም የሚውል ነበር:: በዚህም ምክንያት የተፈጥሮ ምርት /ናቹራል ፕሮዳክሽን/ በመባል ይታወቃል::

የባላባት የምርት ግንኙነት በመሬት የግል ሃብትነት ላይ የተመሠረተ፣ መሬት ባለውና በሌለው መካከል ያለ ግንኙነት ስለሆነ የፊተኛው የኋለኛውን የሚበዘብዝበት የሚፈልጥ የሚቆርጥበትና የሚጨቁንበት ግንኙነት ነው:: ይህ ባህሪው ይበልጥ ግልጽና ይፋ የሚሆነው ግንኙነቱ እያረጀ በሚሄድበት ወቅት ነው:: መሬት ያለው የመሬት ከበርቴ መሬት የሌ



ለውን በጭሰኛነት በመሬቱ ላይ በማሰረስ የምርቱን ከፍተኛውን ክፍል እየወሰደ የጉልበቱን ፍሬ ይበዘብዘዋል:: በሚያበድረው ብድር በአይነት በገንዘብ የፈለገውን ያህል ወለድ እየወሰነ ይበዘብዘዋል:: በተለይ የተፈጥሮው የባላባታዊ ኢኮኖሚ በገንዘብ ኢኮኖሚ ይበልጥ እየተለወጠ ሲሄድና የመሬት ከበርቴዎች ቅንጦታቸውን ለማሟላት ጭሰኛው የሚከፍላቸውን ምርት ከ''አይነት''ወደ ገንዘብ መለወጥ ሲጀምር ብዝበዛው ይባባሳል:: ባለመሬቱ ጭሰኛውን በፈለገው ወቅት እንደ ባሪያ የግል ስራውን ያሰራዋል አጥሩንና ጎተራውን እንዲሰራ እህሉን እንዲያገዝ፣ ጠበት ወይም ቅቤና ሌሎች ገጸ በረከቶች እንዲያበረክት ወዘተ ያደርገዋል:: ይህ በኢኮኖሚ አንፃር ነው::

በፖለቲካም የህብረተሰቡን ወግ፣ ህግ፣ ደንብ፣ ሃይማኖት፣ ተቋሞች፣ ድርጅቶች ወዘተ ለመደብ ጥቅሙ በሚስማሙ የእርሱን ርእዮተአለም በሚያንፀባርቅ መንገድ በመቀየስ ገበሬውን/አብዛኛው ህዝብ መሆኑ ነው/ይጨቁነዋል:: የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመደራጀት፣ የመንቀሳቀስ መብቱን ይነፍገዋል:: ያ ከባሪያው የምርት ግንኙነት ''ነፃ''ወጥቶ የነበረው የምርት ሃይሎች ዋና ክፍል የሆነው ሰው/አርሶ በሳው/እንደገና እንደ ባሪያ የሚገዛበት ሁኔታ ውስጥ ይገባል:: በዚህ መልክ ጭሰኛው ድህነቱ እየጨመረ ኑሮው እየተበላሸና መብቱ እየተረገጠ ይሄዳል::

በሌላ በኩል ደግሞ በከተማ መስፋፋት የጀመሩትና የከበርቴው የምርት ግንኙነት መፀነስ አይነተኛ የሚያደርጉ የባለእጅ ጥበብ ፋብሪካዎች፣ ንግድ፣ የሸቀጥ ምርት፣ የገንዘብ ኢኮኖሚ በፊውዳሉ የምርት ግንኙነት እያረጀ መሄድ እድገታቸው ይገታል:: በጥሩ የፊውዳሉ የምርት ግንኙነት እያደጉ ለመጡት የምርት ሃይሎች እንቅፋት መሆን ይጀምራል:: ወደፊት ከማራመድ ወደኋላ ይጎትታቸዋል:: አዲስ የምርት ግንኙነት ለመፍጠር መሬት ባለመያዙ የተበዘበዘው መብቱ የተረገጠውና እድገቱ የተገታው አርሶ አደሩና ገበያ በመጥበቡ፣ የገንዘብ ኢኮኖሚ ባለመስፋፋቱ፣ የምርት ሃይሎች እንደልብ ባለመንቀሳቀሳቸው የሸቀጥ አርባታ ተገበሩ የተደናቀፈበት ከበርቴው አንድ ላይ ሆነው መሬትንና ላእላይ መዋቅሩን በቁጥጥሩ ስር አድርጎ የምርት ሃይሎችን ጠቀሳሳ እድገት ማገድ በጀመረው በፊውዳሉ የምርት ግንኙነት ላይ ያምፃሉ:: ይህም አመጽ የፊውዳሉን የምርት ግንኙነት መደምሰስንና የከበርቴውን የምርት ግንኙነት መፈጠርን አስከተለ::

"With the appearance of manufacture the productive forces came into contradiction with the feudal production relations. Manufacture demanded a free world, while feudalism tied the serf to the land, manufacture needed a broad international market, the establishment of which was hampered by the closed feudal economy, its isolation and the natural economy. It became necessary to replace the feudal relations of production with new, capitalist relations. This was

> accomplished by a number of bourgeois revolutions in which which the main fighting forces was the serfs and the lower sections of the urban population led by the bourgeoisie". 14

በከበርቴው የምርት ግንኙነት ውስጥ በበላበቱ የምርት ግንኙነት አያረጀ መሄዱ ታፍነው የነበሩት የምርት ሃይሎች ነፃ ወጡ፡፡ ዘመናዊና ከባድ ኢንዱስትሪ፣ ንግድና የገንዘብ ኢኮኖሚ ዘመናዊ እርሻ፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ዘመናዊ መመላለሻና መገናኛዎች ወዘተ ከዚህ በፊት ተወዳዳሪ በማይገኝላቸው ፍጥነትና ጥልቀት ተስፋፉ፡፡ ሰዎችም ከቦታ ቦታ፣ ከፋብሪካ ፋብሪካ ለመንቀሳቀስ፣ የመፍጠርና የመፈለስፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የምርት መሣሪያዎችን ለማሻሻል የህብረተሰቡን ምርትና የኑሮአቸውን ደረጃ ለማሳደግ ይበልጥ የተሻለ ሁኔታ አገኙ፡፡

> "The bourgeoisie, during its rule of scarce one hundred years, has created more massive and more colossal productive forces than have all proceding generations together. Subjection of nature's forms to man, machinery, application of chemistry to industry and agriculture, steam-navigation, railways electrec telegraphs, clearing of whole conitinents for cultivation, canalisation of rivers, whole populations conjured out of the ground...." 15

ይሁን እንጂ ይህ በአዲሱ የከበርቴው የምርት ግንኙነት የተፈጠረው አመቺ ሁኔታ ዘላለማዊ አልነበረም፡፡ የከበርቴው የምርት ግንኙነት በቀርጽ ይለይ እንጂ በይዘቱ ከፊውዳሉ የምርት ግንኙነት ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ ሁለቱም በእርባታ መሣሪያዎች በግል ሀብትነት ላይ የተመሠረቱ ነበሩ፡፡ የከበርቴው መደብ በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ ያሉትን የምርት መሣሪያዎች የግል ሀብቱ አደረገ፡፡ ይህም ዓይነት የሀብት አያያዝ የህብረሰቡ ዋና አምራች የሆነው የወዛደሩ መደብ የከበርቴው መደብ ዋና ተቀጣሪና ሀብት አፍሪ እንዲሆን አስገደደው፡፡ በባሪያው የምርት ግንኙነት ዘመን የባሪያ መደብ እንደ ማጭድ፣ ምስር፣ በሬ፣ ወዘተ እንደታየው በከበርቴው የምርት ግንኙነትም የወዛደሩ መደብ እንደማንኛውም ተራ ሸቀጥ መታየት ጀመረ፡፡ በፊውዳሉ የምርት ግንኙነት ዋና የምርት አምራች የነበረው ጪሰኛ የፊውዳሉን የቅንጦት ኑሮ ለማዳበር በገፍ ይበዘበዝ እንደነበረው የወዛደሩ መደብም የከበርቴውን ትርፍ ብሎም ካፒታል ለማሳደግ በገፍ መበዝበዝ ጀመረ፡፡ ከበርቴው የበለጠ ሀብት ለማካበት የመበዝበዣ ዘዴዎችን እያሻሻለ በቀጠለ ቁጥር በወዛደሩ መደብ ውስጥ ጠቅላላ ድህነት ሥራ አጥነት፣ የሞራል ውድቀት የመፍጠር ችሎታ መበላሸት፣ ወዘተ ተከትሎ መጣ፡፡ በከበርቴው ቤት ሀብት ሲዘንብ በወዛደሩ ቤት ድህነት ዘነበ፡፡ በህብረተሰቡም ውስጥ ወቅታዊና ተደጋጋሚ የኢኮኖሚ ቀውሶች መታየት ጀመሩ፡፡ እነዚህም ወቅታዊና ተደጋጋሚ የኢኮኖሚ ቀውሶች የከበርቴው ስርአት መለያ ባህሪዎች ሆኑ፡፡



ይህ ብቻ አልነበረም፡፡ የከበርቴውን የምርት ግንኙነትና የምርት ሃይሎች እድገትን የሚያንፀባርቅ፣ የመደብ ጥቅሙን የሚጠብቅበት ላዕላይ መዋቅር ከፈጠረ በኋላ የትርፍና የሀብት ማካበቻው መሠረት የሆነውን ብዝበዛውን ለማረጋገጥ በምርት አምራች በወዝአደሩና በሌላው ሠርቶ አደር ላይ ጭቆናውን ማካሄድ ጀመረ፡፡

በጥሩ ያ በአንድ በተወሰነ ወቅት ለምርት ሃይሎች እድገት ታሪክ ከእርሱ በፊት መዝገበት የማያውቀ ከፍተኛ አመቺ ሁኔታ በመፍጠር የምርት ሃይሎች ብሎም ምርትና ህብረተሰብ እንዲያድጉ ያደረገው የከበርቴ የምርት ግንኙነት አረጀ፡፡ አብዮታዊ ሚናው አከተመ፡፡ የምርት ሃይሎች የምርትና የህብረተሰብ እድገት አራማጅ በመሆን ፈንታ ጎታች ሆነ፡፡ የምርት ሃይሎች ይበልጥ በፊና ነፃ በሆነ መንገድ ሊያድጉ የሚችሉበት አዲስ የምርት ግንኙነት መፍጠር ቢፈልጉ የከበርቴው መደብ ጥቅሙን ላለማስነካት አቋሙን ይዞ ለመቆየት ቢል ያረጀውን የከበርቴውን የምርት ግንኙነት ይዞ መቆየት መረጠ፡፡ ሃብትና ሥልጣኑም ይበልጥ በከበርቴው መደብ ቁጥጥር ስር እየዋሉ ሄዱ፡፡ ድህነትና ጭቆናም የወዛደሩ መደብ የዘወትር ችግር ሆኑ፡፡ በዚህ በአድሃሪ ሚናውና ፍላጎቱ የተነሳም በየደረጃው ከሚያድጉት የምርት ሃይሎች ጋር ቅራኔ ውስጥ መግባት ጀመረ፡፡ በዚህ ቅራኔ ውስጥ የምርት አምራች የወዝአደሩ መደብና የምርት መሣሪያዎች ባለቤት የሆነው የከበርቴው መደብ መፋለም ጀመሩ፡፡ በማርክስ አገላለጥ፣

> "Along with the constantly diminishing number of the magnates of capital...grows the mass of misery oppression slavery, degradation, exploitation, but with this too grows the revolt of the working class, a class always increasing in numbers, and disciplined, united, organized by the mechanism of the process of capitalist production itself. Capital becomes a feeler upon the mode of production which has sprung up and flourished along with and under it concentration of the means of production and socialization of labour at last reach a point where they become incompatible with their capitalist integumant. This integument is burst asunder. The knell of capitalist private property sounds. The expropriators are expropriated". 16

በአንዳንድ ህብረተሰቦች የወዛደሩ መደብ አሸንፎ የምርት መሣሪያዎችና የፖለቲካ ስልጣኑን ከከበርቴው መደብ በመንጠቅ አዲስና ከፍተኛ የሆነውን የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ፈጠረ፡፡ በአብዛኛው ህብረተሰብ ውስጥ ገና አሮጌውን በአዲሱ የምርት ግንኙነት ለመተካት በምርት ሃይሎች ግንኙነት መካከል የሚደረገው ትግል እንደቀጠለ ነው፡፡

የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ከሌሎች ግንኙነቶች ከፍተኛና ለምርት ሃይሎች እድገት ይበልጥ ተስማሚ ነው ብለናል፡፡ እንዲህ ያልነው ለምንድን ነው?

ከላይ የጠቀስናቸው ሌሎች የምርት ግንኙነቶች ከምርት ኃይሎች ባህሪይ ጋር የነበሯቸው መጣጣም ህሪያዊና የአይሚያቸው የመጀመሪያ ወቅቶች ብቻ ነበር። ይህ መጣጣማቸውም ከአይሚአቸው መገፋት ጋር ከጊዜ ጊዜ እየተበላሸና ጠርሶ እየጠፋ ሄደ። የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ግን ከዚህ የተለየ ባህሪ አለው። ባህሪው ከምርት ኃይሎች ባህሪ ጋር ሙሉ በሙሉ መስማማቱ ብቻ ሳይሆን ስምምነቱ አስከመጨረሻ የሚኖይ/ዘላቂ/ ነው። በሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ውስጥ ከከበርቴው የምርት ግንኙነት የበለጠ አመቺ ሁኔታ ለምርት ኃይሎች እድገት ይፈጠራል። የምርት ኃይሎች እንደልብ እንዲንቀሳቀሱና ከሳንካዎች ገደብ እንዲያዱት ይደረጋሉ። ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ እርሻ፣ ኢንዱስትሪ፣ ባህል፣ የሰዎች የማምረት ችሎታ ወዘተ ለከፍተኛ ደረጃ ያድጋሉ። እድገታቸውም የህብረተሰቡን አምራች ኃይል ፍላጎትና ጥቅም ለማሟላት በሚያስችል ሁኔታ ይቀየሳል። ለዚህ ሁኔታ መፈጠር ቀናውና መሠረታዊው ምክንያት የህብረተሰቡ የምርት መሣሪያዎች ከግል ሀብትነት ወደ ህብረተሰባዊ/ማህበራዊ/ሀብትነት መለወጣቸውና ማህበራዊ ባህሪ ያላቸው የምርት ኃይሎች ማህበራዊ ባለቤትነት ካገኙት የምርት መሣሪያዎች ጋር ተስማሚ ባህሪ ማግኘታቸው ነው። የምርት እድገት ዋና አላማው የጥቂት መደቦችን የቅንጦት ኑሮ ወይም የትርፍ ፍላጎት ከማሟላት የጠቅላላውን የህብረተሰቡን ፍላጎት ወደሟሟላት ይለወጣል። ይህም በመሆኑ ሰዎች ለየግላቸው ሳይሆን ለጠቅላላው ህብረተሰብ እንዲያስቡ የማምረትና የመፍጠር ችሎታቸው እንዲያድግና የህብረተሰቡ የምርት መሣሪያዎችና የሰዎች ጉልበት በዘገቶ በይበከት በተቀነባበረ መንገድ ከጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ይቻላል። የምርት ኃይሎች በዚህ መልክ ነፃነት አገኝተው ሲያድጉ መንቀሳቀስ መቻላቸው በህብረተሰቡ ውስጥ የሚካሄደው የምርት ተግባርና የሰዎች የኑሮ ሁኔታ ሲያድግ እንዲያድጉ ያደርጋል። ''አንዳንድ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ የቲዎሪ ችግሮች''በሚለው ጽሑፍ ውስጥ ኪም ኢል ሱንግ በ1969 እ. ኢ. አ ስለዚህ ሁኔታ የሚከተለውን ተናገሯል። ስሩ አድርገን እንጠቅሰዋለን።

"Socialist economy has unlimited potentialities to incessantly develop the economy at such a high rate as is inconceivable in capitalist society, and the further socialist construction advances and the stronger the economic basis grows the greater become these potetialities.

"In the socialist society...all the labour resources and natural wealth of the country can be most reasonably made use of and production can be incessantly raised according to plan.

"And the production relation of socialism open a wide scope for an unrestricted development of productive forces, and the socialist state by making use of this possibility can rapidly develops technology according to plan.



"In socialist society, high revolutionary zeal of the people is the decisive factor which energetically eggs the productive forces on to pollulate. The essential excellence of the socialist system lies in the fact that the working people, freed from exploitation and opperession, work with conscious enthusiasm and creative initiative for the country and the people for society and the collective, as well as their own welfare...the working people zealously work for the development of production, because they are deeply aware that the fruits of their labour belong to themselves, to their people and their country". 17

ከጠቀስነውና ሌሎችም አብዮታውያን ከፃፉት እንደምንረዳው በሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ውስጥ ለምርት እድገት ዋና እንቅፋት የሆነው የሰው በሰው መበዝበዝና መጠቀን ይጠፋሉ። መራብ፣ መታረዝና መጠለያ ማጣትም አይኖርም። የአእምሮ በሽታና የሞራል ውድቀትም በአምራች ዘንድ አይታይም። የሚፈጠረውም ሳይሰራ መኖር የህብረተሰቡን ዋና የምርት አምራች የሆነውን የወዛደሩን መደብና ሌላውን የሠርቶ አደሩን የሚያገለግል በመሆኑ ለሰዎች የአእምሮ፣ የፍልስፍና፣ የመፍጠር እድገት ብሎም ለምርት መሣሪያዎች ሲያድጉ መሸሸልና የምርት መጠመር ምንም አይነት ገደብ አይኖርም። ጠቅላላ ሁኔታው ለማምረት ለመፍጠር፣ ለመፈልሰፍ፣ የማያድጉ መሸሸሎች ለማድረግ ያመቻል። ሰዎች የሚያመርቱት ለጥቂት መደቦች ሳይሆን ለራሳቸውና ለህብረተሰቡ የጋራ ጥቅም የሚያመርቱ መሆኑን ጠንቅቀው ስለሚረዱ ከሳንካዎች ቸልተኝነት ከወኔ ጋር ከልብ ይሠራሉ። የምርትም ተግባር በዘፈቃ ሳይሆን በንቃ አቅዶ ስለሚሠራና በከፍተኛ ደረጃ ስለሚደረጁ የሀብትና የሰው ጉልበት በከንቱ አይፈሱም። ለምርትና ለህብረተሰቡ እድገት በተቀነባበረ ሁኔታ እንዲውሉ ይደረጋሉ። ሰዎችም ከብዝበዛና ከጭቆና በከፍተኛ ደረጃ ነፃ ስለሚወጡ የመፍጠርና የመሥራት ችሎታቸውን እያሸሸሉ ክብረታቸውንና የአስብ ልውጣቸውን እያጠናከሩ የምርት መሣሪያቸውን ብሎም ምርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ያሰድጋሉ።

"...Continuous inprovements and innovations will be brought about in all fields of economic managment, organization of production and labour, and development of technology". ይላል ኪም ኢል ሱንግ።

ይህ ከዚህ በላይ የጠቀስነው የሶሻሊስት የምርት ኃይሎች ግንኙነት ሲያድጉ አስከመጨረሻው መጣጣም በቲዎሪ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የሶሻሊስት ግንኙነቶች በተፈጠሩባቸው ህብረተሰቦች በተጨባጭ የታየና የተረጋገጠ ነው። እዚህ ላይ ግን ''አስከመጨረሻው''የሚለው የአብዮት ቀለበስ ካልተደረገ በሚል ገምት ላይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ''የአብዮት ቀለበስ''የሚለውንም ሁለት መልኮች እንደሚኖረው መገንዘብ ያስፈልጋል። አንደኛው መልክ የተቋቋመውን የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት በግልጽ በቀርጽም በይዘትም በሌላ/በከበርቴው/መልስ መተካት ነው። ሌላው ደግሞ በቅርጽ የሶሻሊስት መሆኑን [illegible]ት ግን የከበርቴ/በመንግሥት ደረጃ/ግንኙነት ሲሆን ነው።

''የኢኮኖሚ ስርአትና የህብረተሰብ እድገት''በሚለው ንዑስ አርእስት ስር በቀረበነው አጭር ገለጣ ህብረተሰብ በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች መካከል በሚነሳው ቅራኔ ላይ ተመስርተው በተካሄዱ ህዝባዊ አብዮቶች/በሶሻሊስት ሪቮልሽን/ከዝቅተኛ/ከጋርዮሽ/ወደ ከፍተኛ/የሶሻሊስት/የእድገት ደረጃዎች እየተሸጋገሩ መምጣታቸውን ለማሳየት ሞክረናል:: አንድ የተወሰነ የምርት ግንኙነት ለመፈጠርም ሆነ ለመኖር የሚወሰነው በምርት ሃይሎች የእድገት ደረጃ እንደሆነና በአንድ በተወሰነ ወቅት ከምርት ሃይሎች ጋር የሚጣጣም በህሪ ናሮት አብዮታዊ ሚና ከተጫወተ በኋላ እንደሚያረጅና ወደ አንቀፋትነት እንደሚለወጥ/ከሶሻሊስት ግንኙነት በስተቀር/ አሳይተናል:: ከዚህ ቀጥሎ አንድ የኢኮኖሚ ስርአት ከብሔራዊ ነፃነት ጋር ያለውን ግንኙነት በጥሩ እናሳያለን::

## 1: 3 የኢኮኖሚ ስርአትና ብሔራዊ ነፃነት

" No country can ensure its firm political independence and realize its full equality and sovereignty in international relations without building an independent national economy. Without economic independence, it is impossible for a country to guarantee its political independence, or to build its national life as master in its own house". 19

የአንድ አገር የኢኮኖሚ ስርአት በዚያ አገር ብሔራዊ ነፃነት ላይ ያለው ተጽእኖ ቀጥታ አይደለም:: ተዘዋዋሪ ነው:: አንድ አገር ነፃና ያደገ ኢኮኖሚ ካላት ብሔራዊ ነፃነቷና ክብሯ ይጠበቃል:: የሚያስፈልጓትን የቁሳቁሳዊ ነገሮች የማምረት መሣሪያዎችም ሆነ የእለት ተለት ጥቅም እቃዎች በራሷ ከመረቶች በሌሎች አገሮች ላይ አትመካም:: ካልተመካችና ራሷን ከቻለች ደግሞ የፖለቲካ ነፃነቷና የገዛ ድንበር የተጠበቁና የተከበሩ ይሆናሉ:: ከላይ ከጠቀስነው ጥቅስ የምንረዳው ይኸው ነው:: ይኸን አይነት ቀስትና የሚበቀ ነፃና ያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚቻለው የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች የሚጣጣሙበት የኢኮኖሚ ስርአት ሲኖር ነው:: ለዚህም ነው የኢኮኖሚ ስርአትና ብሔራዊ ነፃነት ግንኙነት ተዘዋዋሪ ነው ያልነው:: ከዚህ ቀጥለን ታሪክ በአጭሩ በመጥቀስ ይኸን ግንኙነት ዘርዘር ባለ መንገድ ለማሳየት እንሞክራለን::

በክፍል 1:2 ውስጥ ህብረተሰቦች ከአንድ የኢኮኖሚ ስርአት ወደ ሌላ ብሎም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ህብረተሰብ ማደጋቸው የማይቀር የህብረተሰብ ህግ መሆኑን ተናግረናል:: የሚከተሉትንም የእድገት ሂደት አሳይተናል:: ይሁን እንጂ ህብረተሰቦች ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርጉትን እድገት እንዴትና መቼ እንደሚያከናውኑ የሚወስነው የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች ቅራኔ ፍንዳታ በአለም ውስጥ በሚገኙት ህብረተሰቦች ውስጥ በአንድ ጊዜ አልተካሄደም:: አንዳንዶች በከፍተኛው የሶሻሊስት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሥርአት ውስጥ



ሲገኙ ቁጥራቸው ከጠቀሳሳው ጋር ሲወዳደር በጣም ኢምንት ነው::አብዛኛዎቹ በፊውዳሳዊና በከበርቴ ሥርአቶች ውስጥ ገና ይዋዥቃሉ:: በኋላኛዎቹ ህብረተሰቦች ውስጥ ቅራኔዎቹ በና ፉምና ትግሎችም እየተካሄዱ ቢሆኑም መሠረታዊ ለውጦች ገና አልተከናወኑም::

ለምሳሌ ምእራብ አውሮፓን ወስደን ብንመለከት የፊውዳሉ የምርት ግንኙነት በከበርቴው የተተካው በልዩ ልዩ አገሮች በተለያዩ ወቅቶችና ሁኔታዎች ሲሆን ይህ ሂደት ከተካሄደባቸው ከሌሎች ክፍለ አለማት ጋር ሲወዳደር ከሁሉ ቀደም የተፈፀመ ሆኖ እናገኘዋለን:: የከበርቴው የምርት ግንኙነት በሶሻሊስት ከተተካባቸው አገሮች ጋር ሲወዳደር ግን የምእራብ አውሮፓ አገሮች ከእነዚህ አገሮች የበለጠ ጊዜ በከበርቴ የምርት ግንኙነት ውስጥ መቆየታቸው ብቻ ሳይሆን አሁንም በእነርሱም ውስጥ የሚቀጥሉ ሆነው እናገኛቸዋለን::

ይህ ለህብረተሰቦች እድገት ወሳኝ የሆነው የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች ቅራኔ በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ መንገዶች መፈንዳትና መሠረታዊ ለውጦች አርጊውን በአዲስ መተካት ማስከተል በህብረተሰቦች ወይም አገሮች ማለት ይቻላል ዘገድ የእድገት ልዩነቶችን አስከተለ:: ከፊውዳሊዝም ወደ ከበርቴው የምርት ግንኙነቶች ቀድመው የተሸጋገሩት ይበልጥ አደጉ:: ሳይንስን ቴክኖሎጂን፣ ኢንዱስትሪን፣ እርሻን፣ ንግድን፣ መገናኛዎችን ወዘተ አጅግ አድርገው አሳደጉ:: አስፋፉ:: ተፈጥሮን በሚገባ መግዛትና መጠቀም ቻሉ:: በዚህም የምርት መሣሪያዎች መሻሻልና የምርት መጠመር ህያው ሆኑ:: እንዲያውም ከሚያስፈልገው/መሸጥ ከሚችለው/በላይ ማምረት የከበርቴው የተለመደ ህግ ሆነ:: በፊውዳሳዊ ግንኙነቶች ውስጥ የቆዩት ህብረተሰቦች ግን የእድገታቸው ፍጥነት አዝጋሚ እንደሆነ ቀረ:: በምርት ሃይሎች እድገት ወደ ኋላ መቅረት የተነሳ የሚመረተውም ምርት በዚያው መጠን ዝቅተኛና ከእጅ ወደ አፍ የሚሄድ ብቻ ሆኖ ቀረ:: ይህ ሁኔታ ሀብታምና ደሀ፣ ያደጉና ወደኋላ የቀሩ ህብረተሰቦች ጎን በጎን እንዲኖሩ አደረገ::

ስለከበርቴው የምርት ግንኙነቶች ስናወራ የምርት መሣሪያዎች በጥቂት መደቦች/በከበርቴው/ቁጥጥር ስር በመሆናቸው የሰዎች ወይም የመደቦች ግንኙነቶች የበዝባዥና የተበዝባዥ፣ የጨቋኝና የተጨቋኝ፣ የበላይና የበታች ግንኙነቶች ናቸው ብለናል:: በዝባዦች ጨቋኞችና የበላዮች የምርት መሣሪያዎች ባለቤቶች ሲሆኑ ተበዝባዦች ተጨቋኞችና የበታች ሀብት የሌላቸው ናቸውም ብለናል:: በእድገትም ሂደት ውስጥ ሃብት ያላቸው ጥሪት እየከበሩና ኑሮ እየተመቻቸው ሲሄድ ሀብት የሌላቸው ይበልጥ እየደኸዩና ኑሮአቸው እየተጎሳቆለ እንደሚሄድ ገልጠናል:: ሁኔታውም የምርት ግንኙነቶቹ እያረጁ ሲሄዱ እንደሚባባስም ተናግረናል::

ዊ ኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ የሚቐቀትን ህብረተሰቦች እየተከፋፈሉ በቀጥጥራቸው ስር አደረጋቸው:: በዚህም መልክ ከበርቴው አለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ስርአት ፈጠረ:: ካፒታል አለም አቀፋዊ ሆነ:: እነዚህን ህብረተሰቦች ከፊውዳላዊ የምርት ግንኙነቶች ጎን በጎን የሚሄዱ ግን የእርሱን ጥቅም የሚያገለግሉ የከበርቴ ግንኙነቶች እንዲፈጥሩ አስገደዳቸው:: ኢምፔሪያሊስት የሆነው ከበርቴ በእነዚህ ህብረተሰቦች ውስጥ ዘመናዊ አርሸዎችን በማስፋፋት፣ ቀላል ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም የተፈጥሮ ሀብት ማውጫዎችን የማእድን ኢንዱስትሪዎች በማስፋፋት ለሸቀጡ ገበያዎችን በመፍጠር በማስፋፋት ሀብትን በአዲስ ማካበት ጀመረ:: ይህም ሁኔታ የአገሮች በአገሮች መበዝበዝን አስከተለ:: ይህ በኢኮኖሚ በኩል ሲታይ ነው:: በፖለቲካም የጎዱ መሠረትን የኢኮኖሚውን ስርአት የሚስማማ ላአላይ መዋቅር መፍጠር ያስፈልገ ነበርና የእነዚህን አገሮች ላአላይ መዋቅሮች ወይ በሙሉ ቀጥጥሩ ስር በማድረግ ወይ ደግሞ ለእርሱ በሚያመች መንገድ በአዲስ በማቋቋም የእርሱ ፖለቲካ አንፀባራቂ አደረጋቸው:: በባህልም እንደዚሁ:: በዚህ መልክ ከበርቴው እነዚህን ህብረተሰቦች የራሱ መልክ አንፀባራቂ አደረጋቸው::

በዚህም መልክ የየአገሩን ወዝ አደር በመበዝበዝ እያደረሰ የከበርቴውን ስርአት በአገር አቀፍ እንዲጠናከረና ሀብትን እንዲካበተ የአለምን ደካማ አገሮች በመበዝበዝ እያደረሰ የከበርቴውን ስርአት በአለም አቀፍ ደረጃ እያጠናከረ ሃብትን ማካበት ተያያዘው::

> "Through the export of capital and the formation of international monopolies the magnates of finance capital divide the world among themselves economically, ie divide it into spheres of influence.
> "With the advent of imperialism, the formation of the capitalist world economic system was completed. This was achieved through <u>the subordination of economically weak countries to the strong imperialist powers.</u> The colonial system of imperialism became a constituent part of the capitalist world economic system". 22

በአጭሩ በኢኮኖሚ ስርአት በምርት ግንኙነቶችና ሃይሎች ወደ ኋላ መቅረትና ማደግ በፊውዳላዊና በከበርቴ ህብረተሰቦች ውስጥ የምርት መጠንና አይነት ልዩነቶች ተፈጠሩ:: የኢኮኖሚ እድገታቸው የሰማይ የመሬትን ያህል ተለያየ:: የከበርቴ ህብረተሰቦች ወደ ኢምፔሪያሊስትነት ተለወጡ:: የኢኮኖሚ እድገታቸው በከፍተኛ ደረጃ ወደፊት የተራመደው የኢምፔሪያሊስት ህብረተሰቦች በኢኮኖሚ እድገታቸው ወደኋላ የቀረውን የፊውዳላዊ ህብረተሰቦች በሃይል ወረሯቸው በቀጥጥራቸው ሥር አዋሏቸው:: ሀብታቸውን፣ ፖለቲካቸውንና በህላቸውን የእነርሱ መገልገያ አደረጓቸው:: በእጅ አዙር ቀኝ ግዛቶቻቸው በማድረግ ብሔራዊ ነፃነታቸውን ገፈፏቸው::



ደርግ ለሰፊው አርሶ አደር ለማደል ያቀደው የማዳበሪያ ጉዳይም የሚከሄደው በዱሮው ስልትና መስመር ስለሆነ ሊያመጣ የሚችለው መሠረታዊ ለውጥ አይኖርም:: ምክንያቱም የአርሶ አደሮችን በማዳበሪያዎች መጠቀምና አለመጠቀም ማዳበሪያዎች በሚሸጡበት ዋጋ፣ በሚከፈለው የወለድ መጠን፣ በብድር መኖር አለመኖርና መክፈያ ጊዜው ማጠርና መርዘም፣ ወዘተ ይወሰናል:: በክፍል 2:2 ውስጥ በማዳበሪያዎች የመሸጫ ዋጋና ወለድ ከፍተኛ መሆን፣ ለመበደር በመንግሥት የሚደረደሩት ሁኔታዎች በሰፊው አርሶ አደር ሊሟሉ የሚችሉ አለመሆን፣ የብድር መክፈያ ጊዜው አጭር መሆን፣ ወዘተ ሰፊውን አርሶ አደር ከመንግሥቱ መጋዘን ማዳበሪያ ገዝቶ እንዳይጠቀም እንዳደረጉት ተመልክተናል:: የደርግ ዘመቻ እነዚህን ችግሮች አያነሳም:: ይታደላል የተባለው ማዳበሪያ በዱሮው የመሸጫ ዋጋ፣ ወለድ የብድር ሁኔታ፣ ወዘተ መልክ ይሆናል ማለት ነው:: ይህ ማለት ደግሞ ሰፊው አርሶ አደር አሁንም ማዳበሪያ ሊጠቀም አይችልም ማለት ነው:: ከዚህም ሌላ የራሱ የማዳበሪያው ማምረት ጉዳይ ችግር ስለሆነና በማመላለሻ ተሽከርካሪዎች እጥረት መኖርና በመንገዶች አለመስፋፋት የተነሳ በለው የማመላለሻ ችግር የተባለው ማዳበሪያ ሊደርስ የሚችለው ለተወሰነ አካባቢና አርሶ አደር ይሆናል:: በዚህ ላይ የቢሮክራሲው አሻጥር አለ:: ሁኔታው ይህ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የደርግ ማዳበሪያም እንደወትሮው በየመጋዘኖቹ ይበሰብሳል:: የማዳበሪያ ማደሉ ብሎም የምርት ማሳደጉም ዘመቻም የአፍ ሆኖ ይቀራል::

ትራክተሮችን በሚመለከተው በኩል ከቀደሞው መንግሥት፣ የመሬት ከበርቴዎችና የውጭ አገር ከበርቴዎች የተወረሱት የመሬት እቃዎች እንደታወጁና አብዮታዊ መንፈስ በየደረጃው በነገሰበት ወቅት በእርሻ ሚኒስቴር አማካይነት እንዴት ለአርሶ አደሮች ጥቅም ሊውሉ እንደቻሉና በዚያ የምርት ውጤት ይከተሳል ተብሎ በተፈረበት ሁኔታ ምርት ለጠመር እንደቻለ በክፍል 2:2 ቀናታችን አይተናል:: በኋላም አብዮታዊ መንፈስ እየቀዘቀዘ ሲሄድ እነዚህ ትራክተሮች ለሰፊው አርሶ አደሮች ጥቅም መዋላቸው ቀርቶ ለጥቂት ሀብታም ገበሬዎችና ለመንግሥት እርሻዎች እንደዋሉም አይተናል:: ይህም ሁኔታ ከዚያ ወዲህ ተከታትለው ለመጡት አመታት ምርት እንዲቀንስ አድርጓል:: የአሁኑ የደርግ የምርት ዘመቻ ይኸን ሁኔታ ለውጦ 98 በመቶ ለሆነው የህብረተሰቡ ምርት ሃላፊ የሆነው ሰፊው አርሶ አደር ትራክተሮች በሰፊው ወይም በተቻለ መጠን እንዲጠቀም በማድረግ ፋንታ በቃልም ሆነ በገበር የቀደሞው ፖሊሲ ቀጥያ /ኮንቲኒዌሽን/ ነው:: 98 በመቶ የሚያመርተውን ክፍል ቸል ብሎ 2 በመቶ የሚያመርተው ላይ ያለ የሌለን ገንዘብና ጉልበት ማሰማራት ደግሞ ምርትን በመጨመር ብዙም ፈቀቅ አያደርገም:: እናብራራ:-

አሳይ ከጠቀስነው አጭር ታሪካዊ ገለጻ ሳንሳሳት የሚከተለውን ለመደምደም እንችላለን፡፡ በኢኮኖሚ ስርአት ወደኋላ መቅረት የተነሳ የተፈጠረው የእድገት ልዩነት የአገሮችን በአገሮች መወረር፣ መበዝበዝ፣ መጠቃን ብሎም ጥገኛ መሆንና ብሎም ብሔራዊ ነፃነት መደፈር አስከተለ፡፡ ያስከትላልም፡፡ በዚህ በኩል የሚመጣውን ጥገኝነትና የብሔራዊ ነፃነት መደፈር መቋቋም የሚቻለው በደገ ኢኮኖሚ ብቻ ነው፡፡

> "Industrialization has the task not only of increasing the share of manufacturing industry in our national economy as a whole, it has also the task....of ensuring economic independence for our country,...of safeguarding it from being converted into an appendage of world capitalism. ....The land of the dictatorship of the proletariat cannot remain economically independent if it does not itself produce instruments and means of production in its own country". [23]

ይላል እስታሊን፡፡

ይህ የእስታሊን አባባል በአንድ በኩል ከላይ የጠቀስነውን የኢኮኖሚ ስርአትና ብሔራዊ ነፃነት ታሪካዊ ግንኙነት ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ አገር በኢኮኖሚ ነፃ ብሎም ብሔራዊ ነፃነቷን አስከብራ ለመኖር በኢኮኖሚ ማደግና ራሷን መቻል እንዳለባት ያስረዳል፡፡ ይሄን የእስታሊንን አሳብ ዘርዘር አድርገን እንመልከተው፡፡

ኢንዱስትሪ አንድ የምርት ክፍል ነው፡፡ በአንድ ህብረተሰብ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚኖረው ድርሻ ግን የሚወሰነው ህብረተሰቡ በደረሰበት የኢኮኖሚ ስርአት ነው፡፡ ኢንዱስትሪ በጣም በመስፋፋት ያደገው ለመጀመሪያ ጊዜ በከበርቴው የኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ ነው፡፡ በሶሻሊስት የኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ ደግሞ ከከበርቴው ስርአት የበለጠ በፍጥነትና በማያቋርጥ ሁኔታ የመስፋፋትና የማደግ እድል ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የኢንዱስትሪ ምርት በጠቅላላው ኢኮኖሚ ምርት ውስጥ የሚኖረው ድርሻ ዝቅተኛ ከሆነ የአንድን አገር የእድገት ደረጃ ዝቅተኛነት ያመለክታል፡፡ ከፍተኛ ከሆነ ደግሞ ከፍተኛ እድገት ያመለክታል፡፡

በኢንዱስትሪ እድገት ወደፊት የተራመዱ የኢምፔሪያሊስት አገሮች ህልውናቸውን ለማራዘም ምርትን ሳያቋርጡ ለማሳደግ ሲሉ አዲስ ገበያዎች፣ አዲስ የጥሬ እቃ ምንጮች፣ አዲስ የኢንዱስትሪ ቦታዎች ወዘተ ለማግኘት በደረጉት ሩጫ የኢንዱስትሪ እድገታቸው ዝቅተኛ የሆኑትን አገሮች በታሪክ እንዴት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል ጥገኞቻቸው በማድረግ ብሔራዊ ነፃነታቸውን እንደገፈፏቸው ከላይ በጭሩም ቢሆን ጠቀስናል፡፡

አሁን ባለንበት ዘመንም አንድ አገር የኢኮኖሚ እድገት ከሌላትና ራሷን ካልቻለች ባደጉ አገሮች ላይ ከመመካት ብሎም በኢኮኖሚ ጥገኛ ከመሆን አትድንም፡፡ እናብራራ፡፡



አንድ በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ስርአት እድገት የምትገኝና በተለይ ''ቶሎ የማደግ'' ጉጉቶች ያሉባት ያልበለጸገች አገር ዘመናዊ የምርት መሣሪያዎችን ራሷ ስለማታፈራና ዘመናዊ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለማቋቋም በቂ ካፒታል ስለሌላት ያደጉ አገሮችን የሁለቱ የቴክኒክና የካፒታል ምንጮች አድርጋ ትወስዳለች፡፡ የተዘበ የውጭ ንግድ ታዳጊ የውጭ ካፒታል ኢንቨስትመንት፣ ታዳጊ የውጭ ብድር፣ ወዘተ ይከተላሉ፡፡ ለምትገዛቸው የምርት መሣሪያዎች፣ ኤክስፐርቶችና ቴክኒሺያኖች በብዛት ስለሌሏት የውጭ ኤክስፐርቶችና ቴክኒሺያኖች መጠቀም ይኖርባታል፡፡ ይህ ሁኔታ በተራው የዚች ያልበለጸገች አገር ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ባህል በበለጸጉ የእርዳታ አድራጊ አገሮች ጥገኞች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ አገሪቱ የምታካሄዳቸው የኢኮኖሚ ክንውኖች/ንግድ፣ እርሻ፣ ኢንዱስትሪ፣ ማእድን ማውጣት ወዘተ/የእርዳታ አድራጊዎችን ጥቅም በሚያሟሉ መንገዶች ይተለማሉ፡፡ ሳእሳይ መዋቅሩም/የመንግሥት መኪና፣ ርእዮተአለሙ፣ ፍልስፍናው፣ ባህሉ፣ ወዘተ/የእርዳታ አድራጊዎቹ ርእዮተአለም እንፀባራቂ ይሆናል፡፡ በሌላ አነጋገር በኢኮኖሚ ጥገኛ የሆነችው ያልበለጸገች አገር የውስጥም ሆነ የውጭ ፖለቲካ አቋሟ እርዳታ የሚያደርጉላት አገሮች አቋም ይሆናል፡፡ እርዳታ ተቀባይዋ ደካማ በመሆኗና የማያቋርጥ እርዳታ ለማግኘት የሰጪዎችን ፍላጎቶች ማሟላት ስላለባት የተቃውሞ ድምጽዋ ይዘጋል፡፡ በዚህም ብሔራዊ ነፃነቷ ይገፈፋል፡፡

> "Without an independent national economy, independences national construction or survival is out of question". [24]

ነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ደግሞ ካለነፃና ያደገ የኢኮኖሚ ስርአት ሊኖር አይችልም፡፡ አንድ አገር ለመኖር ወይም በይበልጥ ለማደግ የሚያስፈልጋትን ምርት በራሷ ካላመረተችና በውጭ ሃይሎች ላይ የምትመካ ከሆነች ብሔራዊ ነፃነቷንና ክብሯን ለማስጠበቅ ያዳግታታል፡፡ ዝቅተኛና ደካማ የኢኮኖሚ ስርአት ደካማና ጥገኛ የኢኮኖሚ እድገት ስለሚያስከትል ለብሔራዊ ነፃነት መከበር ዋስትና አይኖረውም፡፡ ከፍተኛና ጠንካራ የኢኮኖሚ ስርአት ደግሞ ውጤቱ የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ይሄ ሀቅ ልዩ ልዩ ስርአቶችን ያሏቸውን አገሮች ሁሉ በሚመለከት ነው፡፡

> "The realization of the principles of complete equality and independence in the relations between countries calls for the economic independence of each country". [25]

የኢኮኖሚ እድገትና የብሔራዊ ነፃነት ግንኙነት በአጭሩ ይሄ ነው፡፡

ይህን ክፍል ከመዘጋታችን በፊት መሠረታዊ ናቸው የምንላቸውን አሳቦች ደግመን በማገባት አንድ ማጠቃለያ ለመስጠት እንወዳለን፡፡

## 1፡ 4 ማጠቃለያ

የኢኮኖሚ ስርአትና ህብረተሰብ በሚል ንዑስ ርእስ ስር ካቀረብነው ጥናት የሚከተሉትን ስድስት መሠረታዊ ነጥቦች ልናወጣ እንችላለን፡፡

1 — የህብረተሰብ እድገትና የእድገት አቅጣጫ የሚወስነው የምርት ሃይሎች የእድገት ደረጃ በጠቅላላውና በተለይ ሰዎች ነው፡፡

2 — ህብረተሰቦች ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርጉት እድገት በተወሰኑና እንደየደረጃው በተለያዩ ህጋጋት ይገዛል፡፡

3 — የአንድ ህብረተሰብ ብሔራዊ ነፃነትና ክብር መጠበቅ የሰትና የሚኖረው ጠንካራና ነፃ ብሔራዊ የኢኮኖሚ እድገት ሲኖረው ነው፡፡ እነዚህን ሶስት መሠረታዊ ሃሳቦች በጥር በጥሩ በማብራራት ይህን ክፍል እናጠቃልላለን፡፡

1 — የህብረተሰቦች እድገትና የእድገት አቅጣጫ የሚወስነው በምርት ሃይሎች እድገት በጠቅላላውና በተለይ በሰዎች ነው፡፡ የህብረተሰብን ህይወትና የእድገት ደረጃ የሚወስነው ምርት ነው፡፡

"The production of material wealth is the basis of the life and development of any society. Any society will collapse if it ceases to produce material wealth". 26

አንድ ህብረተሰብ ምርት የሚያስፈልገው ለመኖር ብቻ ሳይሆን ለማደግም ጭምር ነው፡፡ ምርት ማምረት ማለት ህብረተሰብ የሚያስፈልገውን ቁሳቁሳዊ ሀብት ለማፍራት በተፈጥሮ ላይ ጉልበት የማፍሰስ ተግባር ወይም ከተፈጥሮ ጋር የሚደረግ ትግል ማለት እንደሆነ ገልጠናል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ከተፈጥሮ ትንሽ/ዝቅተኛ/ብዙ/ከፍተኛ/ ቁሳቁሳዊ ሀብት ማምረት ይቻላል፡፡ የምርት መጠን የሚወስነው በምርት መሣሪያዎች አይነትና መጠን ነው፡፡ ካለምንም መሣሪያ ማምረት እንደማይቻል ሁሉ ያደጉ የተሻሻሉ የምርት መሣሪያዎች እየተጠቀሙ በተፈጥሮ ጉልበትን ማፍሰስ ከተፈጥሮ ብዙ ከፍተኛ ሀብት ለማምረት ያስችላል፡፡ ለምሳሌ 10 ሄክታር ስፋት ያላቸው ማሳዎች እንውሰድ፡፡ በአንደኛው ማሳ ላይ በአንበሳ የሚጎተት ከተራ ብረት የተሰራ ማረሻ እንደምርት መገልገያ እንጠቀም፡፡ በሌላው ላይ ደግሞ ዘመናዊ ትራክተር እንገልገል፡፡ በትራክተሩ መገልገል መሬትን ጠለቅ አድርጎ ለመሰንጠቅ ስለሚያስችል ትራክተር ተገልገለን ጉልበታችንን ያፈሰስንበት ማሳ የበለጠ ምርት ያስገኛል፡፡ እንግዲህ እኩል ከሆኑ ማሳዎች በምርት መሣሪያዎች አይነት ዝቅተኛነትና ከፍተኛነት የተነሳ ዝቅተኛና ከፍተኛ ምርት ለማምረት ይቻላል ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ አገረ መንገዳችን የምርት መሣሪያዎች በምርት ሂደት ብሎም በህብረተሰብ ውስጥ ምን ያህል ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ለመገንዘብ እንችላለን፡፡ ማርክስ ስለምርት መሣሪያዎች ሚና ከፍተኛነት ሲናገር፤



"Economic epochs are distinguished one from another not by what is produced but by the instruments that are used to produced material wealth". ይላል፡፡ እንግዲህ የህብረተሰብን ህይወትና እድገት ደረጃ የሚወስነውን የቁሳቁሳዊ ሀብት ማርባትን ተግባር ዝቅተኛና ከፍተኛነት በተራው በምርት መሣሪያዎች አይነት ዝቅተኛና ከፍተኛነት የእድገት ደረጃ ይወሰናል ማለት ነው፡፡ ይህ እዚህ የጠቀስነው የምርት መሣሪያዎች ሚና የምርት ሃይሎች በምርት ሂደት ብሎም በህብረተሰብ እድገት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና አንደኛው ክፍል ነው፡፡ ሌላው ክፍል ሰዎች የሚጫወቱት ሚና ነው፡፡

"Material production...is the basis of social life, and the working people are the chief productive forces. The people consquently are the decisive force in social development, the real makers of history... It is they who produce all the material wealth...the towns and vi villages, factories, roads, bridges, motors, machines clothing and footwear, food and household utensils,in a word, everything without which mankind could not exist painstakingly and perseveringly from day to day, from year to year from century to century...., they have divided and...the implements of labour, and this in the final count has led to radical technical revolutions, to changes in the productive forces.... Even under the most burdensome oppression, the labour of the ordinary people in a society based on exploitation has always prepared the material prerequisities for mankinds progress, for the transition to a new social system". 27

ካለምርት ህብረተሰብ ህይወትና እድገት አይኖረውም፡፡ ካለምርት መሣሪያዎች ይህ የህብረተሰብ እስትንፋስ የሆነው ምርት ሊመረት አይችልም፡፡ ካለሰዎች ደግሞ የምርት መሣሪያዎች ሊኖሩ አይችሉም፡፡ ካለሰዎች የምርት መሣሪያዎች ካለምርት መሣሪያዎች ምርት ካለምርት ደግሞ ህብረተሰብ ሊኖርና ሊያድግ አይችልም፡፡ ሰዎች የህብረተሰብ እድገት ፈላጭ ቆራጮች ናቸው፡፡

"The people are the decisive force in social development, the real makers of history".28 እናብራራ:—

የህብረተሰብ ምርት አይነትና መጠን ወሳኝ የሆኑት የምርት መሣሪያዎች በህብረተሰብ ውስጥ ተበናጅተው አይገኙም፡፡ ወይም እንደመና ከሰማይ ዓብ አይሉም፡፡ መመረት አለባቸው፡፡ ይህም ተግባር የሚከናወው በሰዎች ብቻ ነው፡፡

"No simian hand has ever fashioned even the crudes of stone knives".28 (M X E Vol II P. 81)

ሰዎች ከተፈጥሮ ለኑሯቸው የሚያስፈልጓቸውን ቁሳቁሳዊ ነገሮች ለማምረት የሚገለገሉባቸው መሣሪያዎች ይፈጥራሉ፡፡ ፍላጎቶቻቸውም እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር የሚያስፈልጋቸው የምርት መጠን እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ይህም የምርት መሣሪያዎቻቸውን የሚያስፈልጋቸውን ምርት

ለማምረት ስለሆም የሚያስፈልጋቸውን ጊዜ ለመቀነስ በሚያስችላቸው መንገድ ያሸሽላሉ፡፡ ከአመት ዓመት ከዘመን ዘመን በሚለዋወጠው ልምዳቸው እየተማሩ አሮጌዎችን መሣሪያዎች እያሻሻሉ አዲሶችን ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ መንገድ የምርት መሣሪያዎችን ከአነጠት፣ ከድንጋይ ወዘተ በመጥረብ ከመሰራት ከብረታ ብረት በዘመናዊ ማቀለጫ እያቀለጡ በተወሳሰበና በከፍተኛ ደረጃ እንዲመረቱ አድርገዋል፡፡

ሰዎች በምርት ሂደት ወይም በህብረተሰብ ውስጥ ያላቸው ከፍተኛ ቦታ የሚለካው የምርት መሣሪያዎችን ለመፍጠር ሳያቋርጡ ለማሻሻልና እንደገና ለመፍጠር በሚጫወቱት ሚና ብቻ አይደለም፡፡ እነዚህ መሣሪያዎችን በማንቀሳቀስ እንዲያመርቱ በማድረጋቸውም ጭምር ነው፡፡

"Instruments of labour by themselves, however do not produce material wealth. They must not only be made, but also be put to use. The most perfect machine will eventually turn into a useless pile of metal if no human hand touches it. Only man is capable of setting a tool into motion and organizing material production. That is why he is an essential element of production". 29

ሰዎች አልምተው ምርት የሚያገኙበት መሬት ካለ እንበል፡፡ የሚያርሱበትም ትራክተር አላቸው እንበል፡፡ የፊተኛው ሰዎች ጉልበታቸውን አፍሰው ምርት የሚያፈሩበት ተፈጥሮአዊ ሀብት ነው፡፡ የኋለኛው ደግሞ ሰዎች ለማምረት የሚገለገሉበት የምርት መሣሪያ ነው፡፡ መሬቱ ቀርቶ ካልተለወጠ በራሱ ምርት አያስገኝም፡፡ ትራክተሩም የሚያንቀሳቅሰው ሃይል ከሌለ መሬትን ሊያርስ አይችልም፡፡ የምርት መሣሪያው ትራክተሩ እና የምርት ማፍሪያው መሬት ካለጥቅም ተገትረው ይቀራሉ፡፡ ሀብት ለህብረተሰብ ጥቅም እንዲሰጡ ለማድረግ የሚችሉት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ሰዎች ትራክተሩን አንቀሳቅሰው መሬትን በማረስ ለህብረተሰቡ ጥቅም የሚውል እህል ያመርታሉ፡፡

"Labour is not only the source of material wealth labour is its father and the earth its mother". 30

የሰዎች ሥራ ካልተጠመረበት፣

"The most perfect machine will eventually turn into a useless pile of metal". 31

ካለሰዎች የምርት መሣሪያዎችን መፍጠር፣ ማሻሻል፣ ማስደገና የተፈጠሩትንም ተጠቅሞ ምርት ማምረት አይቻልም፡፡ ህብረተሰብንም ወደ ከፍተኛና አዲስ ደረጃ ሊያራምዷት የሚችሉ ሁኔታዎች ዘገጃቶች ማሰናዳትም አይቻልም፡፡ ሰዎች የህብረተሰብ እድገት ወሳኝ ሃይሎች ናቸው፡፡

"Whatever its form maybe society is the product of mens reciprocal action". ካርል ማርክስ፡፡



የሰዎች በህብረተሰብ ውስጥ ያላቸው የወሳኝነት ሚና የሚለካው በምርት መሣሪያዎች ፈጣሪነታቸውና የተፈጠሩትንም በማንቀሳቀስ ስራ ላይ እንዲውሉ በማድረጋቸው ብቻ አይደለም፡፡ ለምርት ሃይሎች እድገትና እርምጃ የሚስማሙ የምርት ግንኙነቶች ለመፍጠር በየጊዜውና በየደረጃው በሚያካሂዷቸው አብዮቶችም ጭምር ነው፡፡

"The people are also the main force deciding the fate of social revolutions, of political and national libiration movements". 32

በአንድ ህብረተሰብ ሰዎች በተናጠል ምርት አያመርትም፡፡ ምርት በማንኛውም ጊዜና ቦታ ማህበራዊ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ለማምረትም ሰዎች ያለውድ በግድ ግንኙነት ይፈጥራሉ፡፡ ይህም በምርት ሂደት ውስጥ የሚደረግ የሰዎች ግንኙነት የህብረተሰቡ የምርት ግንኙነት ይሆናል፡፡ የምርት ግንኙነት የሚፈጠረው በምርት ሃይሎች ነው፡፡ የሚለወጠውም በምርት ሃይሎች ነው፡፡ የምርት ሃይሎች የምርት ግንኙነቶች የሚፈጥሩትና አሮጌዎችን በአዲስ የሚለውጡት ለማያቋርጥ እድገታቸው አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡ ስለምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ሁለቱ እንዴት እርስ በእርሳቸው ላይ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ከላይ በዝርዝር ስላብራራን እንመለስበትም፡፡

ሰዎች የምርት መሣሪያዎቻቸውን፣ እያሻሻሉ፣ እየፈጠሩና በተግባር ላይ እያዋሉ ምርታቸውን ከጊዜ ጊዜ ለማሻሻል እንደሚጥሩ የምርት ግንኙነቶቻቸውንም ለእድገታቸው በሚስማማ መንገድ በየጊዜውና በየደረጃው ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ለማራመድ ይታገላሉ፡፡ በእርጅና ምክንያት ከምርት ሃይሎች እድገት ኋላ በመቅረት የምርት ሃይሎችን እድገት የሚጉትቱትን የምርት ግንኙነቶች ለማጨን፣ አዲሱንና ተስማሚውን ለመወሰንና ለማምጣት የሚችሉት ሰዎች ናቸው፡፡ በአንድ የተወሰነ ታሪካዊ ወቅትና የእድገት ደረጃ የምርት ሃይሎች በሀሪ ከምርት ግንኙነቶች በሀሪ ጋር የማይጣጣም መሆኑንና ለውጥ የሚያስፈልገ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ምን አይነት ለውጥ የሚለውን የሚወስኑት እንዲሁም የሚያካሄዱት ሰዎች ናቸው፡፡ የህብረተሰብ ጠቅላላ ሹም ሽር አብዮት በማድረግ ህብረተሰቦችን ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያሸጋግሩት ሰዎች ናቸው፡፡ በግል ሀብት ባለቤትነት ላይ የተመሠረቱትን የበዝባዥና የተበዝባዥ፣ የጨቋኝና የተጨቋኝ፣ የበላይና የበታች ግንኙነቶችን በየጊዜውና በየደረጃው እየደመሰሱ በእኩልነት ላይ የተመሠረተና ነፃነት የሰፈነበት የሰዎች ግንኙነቶች ለመፍጠር ሳያቋርጡ የሚታገሉትና በመጨረሻም ይህን እውን ሊያደርጉ የሚችሉት ሰዎች ናቸው፡፡

በአጭሩ ሰዎች የምርት መሣሪያዎችን በመፍጠር፣ በየጊዜው በማሻሻል፣ የፈጠሯቸውንም በተግባር ላይ በማዋል፣ ለእነዚህም እድገት የማይስማሙትን ግንኙነቶች በአብዮት በየደረጃው እየለወጡና በአዲስ እየተኩ ለህብረተሰቡ የሚያስፈልገውን ምርት የሚያፈሩ የህብረተሰብ ፈጣሪ፣ አፍሪና አስባጊ አውታር ሃይሎች ናቸው፡፡ ካለሰዎች ህብረተሰብ አይኖርም፡፡

አያድግም።

ሰዎች ለህብረተሰብ እድገት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ወይም የሚፈጽሙት ተግባር በህብረተሰቡ ውስጥ ባላቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ነፃነት ይወሰናል። ይበልጥ ነፃ ሲሆኑ ይበልጥ ያመርታሉ፣ ይበልጥ ይፈጥራሉ። ከባሪያው ስርአት በፊውዳሉ ስርአት፣ ከፊውዳሉ ስርአት፣ በከበርቴው ከከበርቴው ስርአት በሶሻሊስት ስርአት የመፍጠርና የማምረት ችሎታቸው ሊያድግ የቻለውና ህብረተሰቡም በዚያው ልክ ያደገው የሰዎች ነፃነት ከነዚህ ልዩ ልዩ ስርአቶች እድገት ጋር ተያይዞ ከጊዜ ጊዜ ስለተሻሻለ ነው። በሌላ አነጋገር ከባሪያው በፊውዳሉ፣ ከፊውዳሉ በከበርቴው፣ ከከበርቴው በሶሻሊስት ስርአት የበለጠ ነፃነት ስለሚኖራቸው ነው።

ሰዎች በህብረተሰብ ውስጥ ስላላቸው ሚና ከቀረብነው ገለጻ የሚከተለውን ዋና ነጥብ ለመረዳት ይቻላል። ማንኛውም ህብረተሰብን ለማሳደግ የሚወሰድ እርምጃ ለሰዎችና ነፃነታቸው ቅድሚያ መስጠት ወይም ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ አለበት። እንዲህ ዓይነቱ ፕሮግራም ወይም እቅድ ፍሬ እንዲሰጥ ሰዎች ሳይፈሩ፣ ሳይጠነቀቁና ሳይረበሹ በድፍረት አስበው እንዲያፈልቁ፣ በአሳቦች ላይ ሂስ እንዲያቀርቡ፣ አሳብ ለአሳብ እንዲለዋወጡ፣ ምርምር እንዲያደርጉ፣ ኢንሼቲቭ እንዲወስዱ፣ ችሎታውን እንዲጠቀሙና ሙሉ ለሙሉ እንዲሳተፉ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። ለዚህም የስራቸው ፍሬ በቀጥታ ለህብረተሰቡና ለእነርሱ ጥቅም እንዲውል፣ የመንቀሳቀስ፣ የመሰረት፣ የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመደራጀት፣ የሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ወዘተ ነፃነቶቻቸው እንዲከበሩላቸውና እንዲለማመዱባቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ምክንያቱም፣

> "The working people, freed from exploitation and oppression, work with conscious enthusiasm and creative initiative for the country and the people, for society and the collective, as well as their own welfare".

በአጭሩ ለህብረተሰብ እድገት የሚወጣ እቅድ ለዚህ እድገት ወሳኝ የሆኑትን ሰዎችን በከፍተኛ ደረጃ ማሳተፍ አለበት። ይህን ለማድረግ ደግሞ ሰዎች ከብዝበዛ ነፃ ወጥተው የስራቸው ፍሬ ጌቶች እንዲሆኑና ሰፊና ወጥ ተው ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶቻቸውን እንዲለማመዱ መደረግ አለባቸው።

አሁን የማጠቃለያችን ሁለተኛ ነጥብ ወደሆነው እንመለስ።

2 — ህብረተሰቦች ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርጉት እድገት በተወሰኑ እንደየደረጃቸው በሚለያዩ ህጎች ይገዛል።



> "All contradictory things are interconnected, not only do they coexist in a single entity in given conditions, but in other, given conditions, they also transform themselves into each other". 33

> "Before it explodes, a bomb is a single entity in which opposites coexist in given conditions. The explosion takes place only when a new condition, ignition, is present. An analogous situation arises in all those natural phenomena which finally assure the form of open conflict to resolve old contradictions and produce new things". 34

እንደማንኛውም ነገር ህብረተሰብም የቅራኔዎች ውህደት/ቅንጅት/ነው። እነዚህ ቅራኔዎች የመቃቃድ ብቻ ሳይሆን የመታገልም ባህሪ አላቸው። ውህደታቸው ከሁኔታ ላይ የተመሠረተ፣ ጊዜያዊና ተለዋዋጭ ሲሆን ትግላቸው ግን ፍጹም ነው። ውህደታቸው የቅራኔዎችን በአንድ በተወሰነ ጊዜና ሁኔታ በመቻቻል አብሮ መኖርን ሲያመለክት ትግላቸው ደግሞ በሌላ በተወሰነ ጊዜና ሁኔታ መለያየትንና አንዱ በአንዱ መተካትን ያመለክታል። የቅራኔዎች በዚህ መልክ በውህደትና በትግል መኖር ለአንድ ህብረተሰብ ህይወት ሲሰጥ መሰቀጣቸው ደግሞ የአንዱን ህብረተሰብ በሌላ ህብረተሰብ መተካትን ያስከትላል።

ይሁን እንጂ ማኦ እንደሚለው አንዱ ተቃራኒዎችን ያቀፈ ቦምብ ለመፈንዳት የተወሰኑ ሁኔታዎች እንደሚያስፈልጉት በህብረተሰብም ውስጥ ያሉ ቅራኔዎች በግልጽ ፈንድተው የህብረተሰብ ለውጥ ለማስከተል የተወሰኑ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው።

ህብረተሰቦች እንደ እድገት ደረጃቸው የሚለያዩ ብዙ ቅራኔዎች ያቀፉ ናቸው። እድገታቸውም የእነዚህ ቅራኔዎች በየጊዜው በየደረጃውና በየመልኩ መፈንዳት ቦታ መውሰድ ውጤት ነው። የእድገታቸውም ፍጥነትና ደረጃ በቅራኔዎቹ ዓይነትና ደረጃ ይወሰናል። ከእነዚህ ብዙ ቅራኔዎች ዋናውና የህብረተሰብ እድገት አሽከርካሪ የሆነው በመደቦች/በምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች መካከል/ያለው ቅራኔ ነው። እስከአሁን ድረስ በደረግነው ገለጻ ይህን አረጋግጠናል። ሌሎቹ ቅራኔዎች የሁለተኛ ደረጃና የእዚህ የዋናው ነፀብራቅ ናቸው። መልካቸው፣ እድገታቸው፣ ተጽእኖዎቻቸውና ሚናቸው በዋናው ቅራኔ እድገት ይወሰናል። ስለሆነም ህብረተሰቦች ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርጉት እድገት የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች ቅራኔ ውጤት ነው። በሌላ አነጋገር አዲስ የምርት ሃይሎች አሮጌ የምርት ግንኙነቶችን በኃይል ደምስሰው አዲስ በፈጠሩ ቁጥር ህብረተሰቦች ከአሮጌ ወደ አዲስ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ይሸጋገራሉ። እድገታቸው በሁለቱ መካከል ያለውን ቅራኔ ህይወት አድገትና መለዋወጥ በሚገዙ ህጎች ይገዛል ማለት ነው።

በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በሚገኙ የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች መካከል ያለ ቅራኔ በተራው በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ አይፈነዳም። በአጭር ጊዜ ውስጥ ወይም

በተፈለገ ወቅትም አይፈነዳም፡፡ የሚገዛበቸው ህጎች ወይም ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡ ለማብራራት ያህል የሚከተለውን ለማለት ይቻላል፡፡

የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች በአንድ በተወሰነ የእድገት ደረጃ ለተወሰነ ጊዜ አብረው ተቻችለው እንደያውም ተጣጥመው ይኖራሉ፡፡ ተጣጥመው ሊኖሩ የሚችሉበት ጊዜ የሚወስነው የምርት ግንኙነቶች በምርት ሃይሎች እድገት ላይ በሚያደርጉት ተጽእኖ ነው፡፡ ተጽእኖአቸው የምርት ሃይሎችን እድገት የሚያበረታታ ማለት አዎንታ ተጽእኖ እስከሆነ ድረስ አብረው እየበሰሉ ይሄዳሉ፡፡ አዲስ ሃይሎችም በየጊዜው ይፈጠራሉ፡፡ የምርት ግንኙነቶች ደግሞ በእኩል እርምጃ ስለማይለዋወጡ ለአዲሶቹ አያረጁና እንቅፋት እየሆኑ ይሄዳሉ፡፡ በዚህን ጊዜ አዲሶች የምርት ሃይሎች በአሮጌዎቹ ግንኙነቶች ላይ ያምጻሉ፡፡ በዚህም አመጽ አዲስ ግንኙነቶች ይፈጥራሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አዲስ ህብረተሰብ ይወለዳል፡፡

> "Up to a certain period the development of the productive forces and the changes in the realm of the relations of production proceed spontaneously, independently of the will of men. But that is so only up to a certain moment, until the new and developing productive forces have reached a proper state of maturity. After the new productive forces have matured, the existing relations of production and their-upholders the ruling classes become that "insuperable" obstacle which can only be removed by the conscious action of the new classes, by the forcible acts of these classes, by revolution". 35

ከላይ ከጠቀስነው ሃሳብ እንደምንረዳው አንድ ህብረተሰብ ከአሮጌው ወደ አዲስ ወይም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ለመሸጋገር የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች በባህሪያቸው ከመጣጣም አልፈው ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ በአሮጌው ወይም በዝቅተኛው ህብረተሰብ ውስጥ አዲሶች የምርት ሃይሎች መፈጠር፣ ማደግና መብሰል አለባቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ባይሟላ ህብረተሰቦች ከአሮጌ ወደ አዲስ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ሊሸጋገሩ አይችሉም፡፡

> "No social order ever perishes before all the productive forces for which there is room in it have developed, and new, higher relations of production never appear before the material conditions of their existance have matured in the womb of the old society itself". 36

በአጭሩ ህብረተሰቦች ከአንዱ ወደ ሌላው፣ ከዝቅተኛው ወደ ከፍተኛው ከአሮጌው ወደ አዲሱ ደረጃ ለመለዋወጥና ለለውጡም መሰረት የሚያስፈልጉት ቁሳቁሳዊ ሁኔታዎች በዝቅተኛው በአሮጌው ህብረተሰብ ውስጥ አስቀድመው ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የፊውዳሉ ህብረተሰብ ወደ ከበር



ቴ ህብረተሰብ ለመለወጥ በፊውዳሉ መደብ ጎን የከበርቴው መደብ መኖርን፣ በፊውዳሉ የምርት ግንኙነት ጎን የከበርቴው የምርት ግንኙነት መኖርን፣ የፊውዳሉ ባህል ጎን የከበርቴው ባህል መኖርን፣ በፊውዳሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ጎን የከበርቴው የፖለቲካ ድርጅት መኖርን ወዘተ ይጠይቃል፡፡ የከበርቴውም ህብረተሰብ ወደ ሶሻሊስት ህብረተሰብ ለመሸጋገር በከበርቴው የምርት ግንኙነት ጎን ለጎን የሚሄድ የሶሻሊስት መፍጠር አይቻል እንጂ የምርት ሃይሎች በከፍተኛ ደረጃ መገኘትንና የኢንዱስትሪ ምርት ማደግን የወዝአደሩ መደብ መኖርን፣ የወዝ አደሩ ኮሚኒስት ፖርቲ መኖርን፣ የወዝአደሩን ርእዮተአለምና ባህል መኖርን፣ ወዘተ ይጠይቃል፡፡

ስለሆነም ሰዎች የሚመሯቸውን የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች የኢኮኖሚ ስርአት ብሎም ህብረተሰብ በመምረጥ በፈለጉት ጊዜ ሊፈጥሩ አይችሉም፡፡ ሊያውቹም አይችሉም፡፡ ከአንዱን አንዱን ዘለውም ወደሌላ ህብረተሰብ ሊገቡም አይችሉም፡፡ የህብረተሰቦች የእድገት ሂደት በኢኮኖሚ የእድገት ህጎች የሚገዛና ከሰዎች ፍላጎት ነፃ በሆነ መንገድ የሚፈፀም ነው፡፡

> "Are men free to choose this or that form of society? By no means....Men are not free to choose their productive forces which are the basis of all their history--for every productive force is an acquired force, the product of former activity. The productive forces are therefore the result of practical human energy, but this energy is itself conditioned by the circumstances in which men find themselves, by the productive forces already acquired, by the social form which exists before they do, which they do not create, which is the product of the preceding generation". 37

ይሁን እንጂ አሁን ባለንበት ዘመን በተለይም ከ1960ዎቹ መጠረሻና በ1970ዎቹ ውስጥ ሰዎች የህብረተሰቦች የኢኮኖሚ ስርአቶች ምርጫዎች ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡ አየታዩም ናቸው፡፡ በተለይ በከፊል ፊውዳልና ከፊል ከበርቴ የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ ውስጥ የሚገኙ ''የሶስተኛው ዓለም''ህብረተሰቦች ለሶሻሊስት ስርአት መፈጠር የሚያስፈልጉት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ባይሟሉ ከቀኝ ገዛት ነፃ ሲወጡ ወይም በመፈንቅለ መንግሥት መዘራ የመንግሥት ለውጥ ሲያካሄዱ ''ሶሻሊስትነን''እያሉ በማወጅ የወጡ ህብረተሰቦች ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ይህ ድርጊት ከላይ ከጠቀስነው ህብረተሰብ እድገት ሂደትና የሚገዛበት ህጎች ጋር ወርስ የማይጣጣምና ስህተተኛ ድርጊት ነው፡፡ ፀረ ታሪካዊ ቁስአካላዊነትና አደገኛ ዝንባሌ ነው፡፡ ስለኢት ሁኔታ በምናወስበት ጊዜ ስለምንመለስበት እዚህ ዝርዝር ውስጥ አንገባም፡፡ ቀጥለን ስትኛውን የመጠረሻውን የማጠቃለያ ነጥብ እናነሳለን፡፡

3 — የአንድ ህብረተሰብ ብሔራዊ ነፃነትና ክብር መጠበቅ ዋስትና የሚኖረው ጠንካራና ነፃ ብሔራዊ የኢኮኖሚ እድገት ሲኖር ነው።

አሁን ባለንበት ዘመን ህብረተሰቦች/አገሮች/በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በባህል፣ በወታደራዊ ደረጃዎች የተሳሰሩ ግንኙነቶች አሏቸው። ያደጉ ሀብታም ህብረተሰቦች ካላደጉ ከድሀ ህብረተሰቦች፣ ያደጉ ከያደጉ ጋር፣ ያላደጉ ካላደጉ ጋር ሶሻሊስት የሆኑ ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር በእነዚህ ሰንሰለቶች ተያይዘዋል። እርስ በእርሳቸው አንዱ በአንዱ የሚመካ/ኢንተር ዲፔንደንት/ሆነዋል። ግንኙነቶቻቸው በሳቸው የእድገት ደረጃና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚገኙት የሀብት ማፍሪያ ምንጮችና መሣሪያዎች ላይ ባላቸው ቁጥጥር ላይ ተመስርቶ የበላይነትና የበታችነት፣ የበዝባዥና የተበዝባዥነት ወዘተ ግንኙነት ነው። ያደጉት የበላዮችና በዝባዦች ሲሆኑ ያላደጉት ደግሞ የበታችና ተበዝባዦች ይሆናሉ። ያደጉት ይበልጥ እየበለፀጉ ሲሄዱ ያላደጉት እየደኸዩ ይሄዳሉ። ያላደጉት በደጉት ላይ ይበልጥ ጥገኞች እየሆኑ ይሄዳሉ።

በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ብሔራዊ ነፃነትና ክብርን ለማስጠበቅ የሚቻለው ነፃና ያደገ ኢኮኖሚ ሲኖር ብቻ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጥገኛና ያላደገ ኢኮኖሚ የሚያስከትለው የፖለቲካ ጥገኝነትን በሙሉ የብሔራዊ ነፃነትና ክብርን መደፈር ነው። ካለነፃና ያደገ ኢኮኖሚ በአገሮች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች በእኩልነት ላይ የተመሠረተና ደካማ የኢኮኖሚ እድገት ያላቸውን አገሮች ብሔራዊ ነፃነትና ክብር ጠንካራ ኢኮኖሚ ባላቸው አገሮች እንዳይደፈሩ ለማድረግ አይቻልም። በቁጥር 1:3 ስር የጠቀስነውን ብናስታውስ:—

> "No country can ensure its firm political independence and realize its full equality and sovereignty in international relations without building an independent national economy".

በዚህ ክፍል ውስጥ ስለምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች፣ ስለላዕላይ መዋቅርና ስለብሔራዊ ነፃነት ወዘተ በማንሳት አንድ የተወሰነ የኢኮኖሚ ስርአት በህብረተሰብ እድገት ላይ ስላለው ቀጥታና ዘዋዋሪ ተጽእኖዎች ማለት የሁለቱን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ለማሳየት ሞክረናል። በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ይህን መሠረት በማድረግ ስለኢት ኢኮኖሚ ስርአትና ህብረተሰብ ሁኔታ እናጠናለን።



## ክ ፍ ል ሁ ለ ት

## የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ስርአትና የህብረተሰብ እድገት

የኢኮኖሚ ስርአትንና የህብረተሰብን እድገት ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት በሚመለከተው በኩል በክፍል አንድ ካቀረብነው ጥናት ውስጥ የሚከተለውን ተምረናል። የአንድ ህብረተሰብ እድገት ደረጃ በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት የሚወሰነው በዚያው ወቅት የህብረተሰቡ የኢኮኖሚ ስርአት መሠረት በደረሰበት ደረጃና ይኸን ደረጃ በሚያንፀባርቀው ላዕላይ መዋቅር እድገት ነው። የኢኮኖሚው ሥርአት መሠረት በተራው በምርት ሃይሎች የእድገት ደረጃና እድገታቸውን በሚያንፀባርቁት የምርት ግንኙነቶች ይወሰናል።

ስለዛሬይቱ ኢት የኢኮኖሚ ስርአትና የህብረተሰብ እድገት ከዚህ በታች የምናቀርበውን ጥናት የምንመሠርተው በክፍል አንድ ውስጥ መጠነኛ በሆነ ዝርዝር ትንተና በቀረቡት በዚህና በሌሎች ትምህርቶች ላይ ነው።

በታህሳስ 11 ቀን 1967 ዓ.ም በጊ ወ መ ከተሰጠው አዋጅ ወዲህ ኢት የምትታወቀው ''በሶሻሊስት''በመባል ነው። ኢት አሁን ባለችበት ማቴሪያላዊና ፖለቲካዊ የእድገት ደረጃ ሶሻሊስት ልትባል ትችላለች ወይ? የኢኮኖሚ ስርአቷ ምንድን ነው? ሶሻሊስት ወይስ ካፒታሊስት? ከዚህ ቀጥለን እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመመለስ በመጀመሪያ የጊዜውን የኢኮኖሚ ስርአት ምንነት፣ ከዚያም ያሉትን የኢኮኖሚ ችግሮች አይነቶችና ጥልቀቶች ከነምክንያቶቻቸው ጥምር እናጠናለን።

### 2:1 የኢት ኢኮኖሚ ስርአት ሶሻሊስት ወይስ ካፒታሊስት?

> "Socialism cannot be decreed from above'. Its spirit rejects the mechanical bureaucratic approach, living, creative socialism is the product of the masses themselves". (Lenin, CW, Vol 26, P. 288)

ሌኒን የሶሻሊስት ስርአት ከላይ ሊታወጅ አይችልም፣ የሶሻሊስት ስርአት የሰዎች ሥራ ውጤት ነው ያለው፣ ማርክስ ሰዎች ይህን ወይም ያን ህብረተሰብ ለመምረጥ አይችሉም፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ህብረተሰብ ቀድሞ በነበረው ህብረተሰብ ውስጥ ያለው የሥራ ውጤት ነው ካለውና በክፍል አንድ ውስጥ ከጠቀስነው ጋር ይመሳሰላል።

በክፍል አንድ ውስጥ አንድ አዲስ ስርአት ከመወለዱ በፊት በአሮጌው ስርአት ውስጥ መፀነስ እንዳለበትና የፊተኛው የሚኖረው ደረጃ በኋለኛው የእድገት ደረጃ እንደሚወሰን አጥንተናል። ለማስታወስ ያህል የባሪያው የኢኮኖሚ ስርአት በፊውዳሉ የተተካው የኋለኛ

Notes

1 Marx & Engels Sw Vol. 1 P 509
2 ቃለ ጉባ ቁ 2 1966 781
3 Marx & Engels Sw Vol. I P 1 82
4 Ibid.
5 Stalin Marxism & Problems of Linguistics P 3
6/5 Ibid. P7
7/9 Ibid. P 5
8 Ibid.
9 Marx & Engels Sw Vol I P 509
10 P Nikiti Fundamentals of Poletical Economy P 9
11 Marx Engels Sw Vol 1 P 89
12 Nikitin P11
13 Marx & Engels Sw Vol I P 503-4
14 V Afancow Marxist Philosophy P 209
15 Marx Engels SW I Vol I P 113
16 Marx quoted from anti During P159 — 60
17 Kim Il Sung On the theoretical problems of the Socialist Economy P 2 — 4
18/19 Ibid P4
19 Self reliance & National Independence Peking Riview 1963 P 6
20 Marx & Engels Communist Manifesto
21 Ibid.
22 Nikitin P 158 — 59
23 Stalin Cw vol 8 P128
24 Peking Riview 1963 P13
25 Ibid P 7
26 Marx quoted from Nikitin P 8
27 V Afanasyv
28 Marx & Engels Sw VOL II P 81
28/29 Op. cit. p 19?—93
30 Marx Capital Vol I P 43
31
32 V Afanasjev P 193
33–40 Mao Sw Vol I P 340
35 Stalin Dialectical & Historical Materialism P 43
36 Marx & Engels SW Vol I 04
37 Ibid P 518
34 Ibid P 343



ው በፊተኛ ውስጥ ተጸንሶ፣ ጉን በጉን ኑሮ እያደገ ሲሄድና በገፃሩ የፊተኛው እያረጀ ሲሄድ ነው ብለን ነበር፡፡ የባሪያው ስርአት የከበርቴ ወይንም የሶሻሊስት ስርአት ሊፀነስና ሊወልድ አይችልም ነበር ማለት ነው፡፡ የፊውዳሉም ስርአት በበኩሉ ወደኋላ ሄዶ የባሪያ ወይም አንድ ደረጃ ዘሎ የሶሻሊስት ስርአት ሊወልድ አይችልም፡፡ የፊውዳሉ ህብረተሰብ ማህፀን የሚችለው የከበርቴውን ህብረተሰብ መፀነስና መውለድን ነው፡፡

በክፍል አንድ ውስጥ የጠቀስነውን የማርክስን አሰብ ብናስታውስ በውስጡ ሊያድጉ የሚችሉት የምርት ሃይሎች ሁሉ ሳያድጉ፣ ማንኛውም ማህበረዊ ሥርአት ሊፈርስ አይችልም፡፡ አዲስና ከፍተኛ የምርት ግንኙነቶችም ለመኖር የሚያስፈልጓቸው ቁስአካላዊ ሁኔታዎች በአሮጌው ስርአት ማህፀን ውስጥ ሳይበስሉ ሊፈጠሩ አይችሉም፡፡

"No revolt can bring about socialism unless the economic conditions for socialism are ripe...state monopoly capitalism is a complete material preparation for socialism, the threshhold of socialism, a rung on the ladder of history between which and the rung called socialism there are no intermediate rungs". (Lenin ,SW, Vol 2, P 270).

የሶሻሊስት ስርአት በህብረተሰብ የእድገት ታሪክ ውስጥ ከፍተኛው ደረጃ ነው፡፡ እንዲህም በመሆኑ ለመፈጠር ብቻ ሳይሆን ለመኖርም የምርት ሃይሎችን ከፍተኛ እድገት ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም በህብረተሰብ እድገት ታሪክ ቀደም ተከተል ሊመጣ የሚችለው የምርት ሃይሎች ከሌሎች ስርአቶች የበለጠ ሊያድጉ በሚችሉበት ከከበርቴው ስርአት መደምሰስ በኋላ ነው፡፡ በሌኒን አባባል የሶሻሊስት ስርአት ሊፈጠር የሚችለው የሚያስፈልጉትን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በከፍተኛ ደረጃ ሊያሟላ ከሚችለው ከከበርቴው ስርአት በኋላ ብቻ ሳይሆን ይህ ስርአት በሞኖፖል|በኢምፔሪያሊስት| ደረጃ ላይ ሲገኝ ነው፡፡ የሶሻሊስት ህብረተሰብ ለመፈጠርም ሆነ ለማደግ ከእርሱ በፊት በነበረው ስርአት ውስጥ በነበሩት የምርት ሃይሎች እድገት ስለሚወሰን ያን ጊዜ ሶሻሊዝምን ለማምጣትም ሆነ ለመገንባት ይቀላል፡፡ እንዲያውም ሌኒን ..."Socialism is merely state capitalist monopoly which is made to serve the interest of the whole people and has to that extent ceased to be capitalist monopoly". (ibid P. 269) ይላል፡፡

እንግዲህ በኢኮኖሚ አነጋገር የተመለከትነው እንደሁ ሶሻሊዝም ማለት የምርት ማፍሪያዎችን የህብረተሰቡ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ህብረተሰቡን በከፍተኛ የኢንዱስትሪ እድገት ደረጃ ማስገኘትም ማለት ነው፡፡ ሌኒን የሶሻሊዝም ኢኮኖሚያዊ ይዘት ሌላ ሳይሆን "The electrification of the whole country" ነው ይላል፡፡ የሶሻሊዝም ዋና ኢኮኖሚያዊ መሠረት ከባድ ኢንዱስትሪ ሲሆን የእርሻንም በዘመናዊ የኢንዱስትሪ መኪናዎች መታረስን ይጠይቃል፡፡ እንግዲህ ዓይነተ የምርት ሃይሎች እድገት የሚገኘው ደገም በፊውዳ

ሉ ስርአት ውስጥ ሳይሆን በከበርቴውም አገዛዝም የሞኖፖል የእድገት ደረጃ በደረሰው ስርአት ውስጥ ነው። ይህ ማለት ግን የከበርቴው ስርአት በፊውዳሉ ውስጥ እንደተፀነሰ የሶሻሊስትም በከበርቴው ስርአት ውስጥ ይፀነሳል ማለት አይደለም። የከበርቴው በፊውዳሉ ውስጥ ሊፀነስ የቻለው የግል ሀብት የሁለቱ ስርአቶች የጋራ መሠረት ስለሆነ ነው። የሶሻሊስትና የከበርቴው ስርአቶች ግን መሠረታቸው የተለያየ ነው። የመጀመሪያው ፀረ የግል ሀብት ስለሆነ መሠረቱ በማህበራዊ ወይም በህብረተሰቡ ባለቤትነት ሥር የሆነ የምርት ማፍሪያ ሀብት ነው። ስለሆነም ምንም አይነት መሠረታዊ የጋራ ባህሪ በሌለው በከበርቴው ውስጥ አይረገዝም። ይሁን እንጂ ሶሻሊዝም ከመና አይፈጠርም። የተወሰኑ ማቴሪያል ሁኔታዎች ያስፈልጉታል። እነዚህንም ለመፍጠር የሚያስፈልጉትን ኢኮኖሚያዊ ቴክኒካዊ ሁኔታዎች ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ምርት ማፍሪያ መሳሪያዎች ምርትና በከፍተኛ ደረጃ የተሰበሰበ የተከማቸ እና ማህበራዊ የሆነ ሥራ፣ ከፍተኛ ሳይንሳዊና ቴክኒካዊ እድገት ወዘተ የሚያገኘው እንደመጨረሻውም ስርአት ከእርሱ በፊት ከነበረው ከከበርቴው ስርአት ነው። ሶሻሊዝምን ለማምጣትና ለመገንባት ብቸኛ የሆነው የወዝ አደሩ መደብም የሚወለደው፣ የሚያድገውና ድርጅታዊም ሆነ ርእዮተዓለማዊ ጥንካሬ የሚያገኘው በዚሁ በከበርቴው ስርአት ውስጥ ነው።

የኢኮኖሚና የቴክኒካዊ ሁኔታዎች በከፍተኛ ደረጃ መሟላት ግን ብቻውን የሶሻሊስት ስርአትን አያስገኝም። እንደዚህ ቢሆንማ በዛሬዎቹ የምእራብ አውሮፓና የሰሜን አሜሪካ ህብረተሰቦች ሶሻሊዝምን በመሠረቱ ነበር። ሶሻሊዝምን ለመፍጠርና ለመገንባት የፖለቲካ ሁኔታዎችም መሟላት አለባቸው። የፖለቲካ ስልጣን ማንኛውንም ነገር ስለሚወስን የሶሻሊስት ስርአትም የሚስማማው ሳአሳይ መዋቅር ማግኘት ይኖርበታል። በሶሻሊስት ስርአት ውስጥ የምርት ማፍሪያዎች የህብረተሰቡ ቶስቶሲ ሀብት ባለቤትነትና ምርት ማህበራዊ እንደመሆናቸው መጠን የሚፈጠረው ሳአሳይ መዋቅርም ግለሰባዊ ባለቤትነትን የሚቃወም ብሎም የኢኮኖሚውን መሠረት የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት። እንዲህ አይነት ሳአሳይ መዋቅር ማግኘት የሚቻለው ደግሞ መሠረታቸው የግል ሀብት የሆነው የፊውዳሉ፣ የከበርቴው ወይም የንዑስ ከበርቴው መደቦች የፖለቲካ ስልጣን ሲይዙ አይደለም። እንዲህ ዓይነቱን ሳአሳይ መዋቅር መፍጠር የሚቻለው ከሌሎቹ መደቦች ሁሉ የግል ሀብትን ለማጥፋት፣ ሶሻሊዝምን ለማምጣትም ሆነ ለመገንባት ከበርቴውን ፊት ለፊት ገጥሞ በቆራጥነት እስከመጨረሻው ሊታገል የሚችለው የግል ሀብት መጥፊያው የሆነው የወዝ አደሩ መደብ ብቻ ነው። ስለሆነም የወዝአደሩ መደብ በፖርቲ ደረጃ ተደራጅቶ ባይታገል፣ የሶሻሊስት ስርአት ለመፍጠር አይቻልም። ይህ መደብ በፖርቲው አማካይነት የፖለቲካ ስልጣን ሳይዝም የሶሻሊስት ስርአትን መገንባት አይቻልም።



"Socialism is inconceivable without large-scale capitalist engeneering based on the latest discouveries of modern science. It is inconceivable without planned state organization, which keeps tens of millions of people to the stricter observance of a unified standard in production and distribution....<u>At the same time socialism is inconceivable unless the proletariat is the ruler of the state</u>".
(Lenin SW vol 2 p. 694)

ባጭሩ ካለወዝ አደሩ መደብ የፖለቲካ ሥልጣን መያዝና ካለምርት ሃይሎች ከፍተኛ እድገት የሶሻሊስት ስርአት ህልም ነው። በሌኒን ታላቅ ሕይወትና የመፍጠር ችሎታ ያለው የሶሻሊስት ስርአት ለመፈጠርና ለመገንባት የእነዚህን ሁለት መሠረታዊ ሁኔታዎች መሟላት ይጠይቃል። እነዚህ ሁኔታዎች ባይሟሉ የክፍ እንጂ እውነተኛ የሶሻሊስት ስርአት ሊኖር አይችልም።

በኢት የሶሻሊስት ስርአት የተፈጠረው ከላይ ባጭሩ በጠቀስነው ማርክስና ሌኒን በሚያስተምሩት መንገድ አይደለም። ከዚህ ተፃራሪ በሆነ ነው። ሌኒን በጣም ዘመናዊ በሆነ የሳይንስ እውቀት ላይ የተመሠረተ ከፍተኛ የካፒታሊስት እድገት ባይኖርና የወዝ አደሩ መደብ የፖለቲካ ስልጣን ባይጨብጥ ሶሻሊዝም ሊኖር አይችልም ሲል በኢት "የሶሻሊስት ስርአት የተፈጠረው" የከበርቴው የምርት ሃይሎች ከፊውዳሉ ስርአት ቀንበር ስር ገና ነፃ መውጣት ቢጀምሩና እድገታቸው ገና ጠቅላ እንደሆነና የፖለቲካ ሥልጣን በወዝ አደሩ እጅ ሳይገባ ነው። ሌኒን ሶሻሊዝም ከላይ የሚታወጅ ሳይሆን ከታች የሚመጣ የሰፊው ህዝብ ትግል ውጤት ነው ሲል የኢት ኢኮኖሚ ስርአት ብሎም ህብረተሰብ ''ሶሻሊስት''በመባል የተሰየመው ጊ ወ መ በታህሳስ 1967 ዓ ም በሰጠው አዋጅ ነው። ማርክስ ሰዎች የፈለጉትን ህብረተሰብ ሊመርጡ አይችሉም፣ ምክንያቱም እያንዳንዱ ህብረተሰብ ከበፊቱ ያሉት የምርት ሃይሎች እድገት ደረጃ ውጤት ነው ሲል የኢት ህብረተሰብ ''ሶሻሊስት'' የሆነው ለሶሻሊዝም መሠረት የሆኑት የከበርቴ የምርት ሃይሎች ባያድጉ የከበርቴው ስርአት በአሁኑ ወቅት መጠሳቱንና የሶሻሊስት መወደቁን በወቀው በንዑስ ከበርቴው የገዥ መደብ ምርጫ ነው። ሁለቱም መንገዶች ስህተተኛና ፀረ—ማርክሲስት ሌኒኒስት ናቸው። ስለሆነም በደርግ አዋጅና ምርጫ የህብረተሰብን የእድገት ህጋጋት በመጣስ በኢት የተፈጠረው የሶሻሊስት ስርአት የንዑስ ከበርቴው እንጂ እውነተኛው የወዝ አደሩ ሶሻሊስት ስርአት ሊሆን አይችልም።

ነገሩን ይበልጥ ዘርዘር አድርጎ ለመረዳት ይረዳን ዘንድ ከዚህ ቀጥሎ ኢት በደርጉ ''አዋጅ'' ወይም ''ምርጫ'' ''ሶሻሊስት''ከመባሏ በፊት የነበረችበትን የኢኮኖሚ ስርአት የምርት ሃይሎችና ግንኙነቶች የእድገትና ይህንም እድገት በማንፀባረቅ ላይ የነበረውን የሳአሳይ መዋቅር ሁኔታ በአንዱ በኩልና ለሶሻሊስት ስርአት መፈጠርና መገንባት

የሚያስፈልጉትን ''ኢሎመንተሪ''ሁኔታዎች በአጭሩ ለማሰየት እንሞክራለን። በዚህም አርጊውን የኢት ኢኮኖሚ ስርአትና በእርሱም ውስጥ ሊታነጽና ሊወለድ የሚችለውን አዲሱን የኢኮኖሚ ስርአት/የዛሬውን ማለት ነው/እናገኛለን።

የየካቲት አብዮት በ1966 ዓ ም ከመፈንዳቱ በፊትና በፈነዳበት ወቅት የኢት ኢኮኖሚ ስርአት ''ፅርበ'' /ጽዋል/ ነበር። በአንድ በኩል የፊውዳሳዊ የኢኮኖሚ ስርአት ሲኖር በሌላ በኩል ደግሞ የከበርቴው የኢኮኖሚ ስርአት ይገኝ ነበር። በዚህም ምክንያት የኢት የኢኮኖሚ ስርአት ከፊል ፊውዳል ከፊል ከበርቴ ወይም ፊውዳ ከበርቴ/ፊውደ ቡርዡዋ/በመባል ይጠራ ነበር።

ሁለቱ ስርአቶች ጉን ለጉን ይኑሩ እንጂ በእድሜአቸውና በተጽኖአቸው እኩል አልነበሩም። የፊውዳሉ ስርአት የብዙ መቶ አመታት እድሜያለው ሲሆን ከከበርቴው በጣም ያረጀና የበሰጠ ተጽእኖ ነበረው።

በሰኢት ታሪክ የፀሩ አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ የፊውዳሉ ስርአት በኢት ህብረተሰብ ውስጥ መታየት የጀመረው እአአ 1200 ዓ ም ገደማ ጀምሮ ነው። እስከየካቲት 1966 አብዮት ድረስ ከ800 ዓመታት በላይ የሆነ እድሜ የነበረው ማለት ነው። የከበርቴው ስርአት ግን በኢት መታየት የጀመረው የምእራብ አውሮፓ የከበርቴ ህብረተሰቦች የኢምፔሪያሊስት የእድገት ደረጃ በደረሰበትና በኢኮኖሚ ደካማ የሆኑትን ህብረተሰቦች መውረር በጀመሩበት በምኒሊክ ዘመን ነው። ይበልጥ መስመር በያዘ መንገድ ራሱን የቻለ ስርአት ሆኖ መታየት የጀመረው ግን በጠቅላላው ከጣሊያን ወረራ ወዲህ ሲሆን በተለይ በ50ዎቹ፣ በ60ዎቹና በ70ዎቹ መጀመሪያ ነው። እስከየካቲት አብዮት ፍንዳታ ድረስ 100 ዓመት የማይሞላ እድሜ ነበረው። ስለሆነም ከሁለቱ ስርአቶች የፊውዳሉ ስርአት በጣም አርጊ የከበርቴው ደግሞ በጣም አዲስ ሆነው እናገኛቸዋለን። ነገሩን ይበልጥ ዘርዘር አድርጎ ለማየት ያህል የሚከተለውን ለማለት ይቻላል።

ኢምፔሪያሊዝም ባደረገው አለም አቀፋዊ መስፋፋት ወደ ኢት ከመግባቱና የከበርቴ የምርት ግንኙነት ከመፈጠሩ በፊት ዋናው የምርት ማፍሪያ መሬት ነበር። በመሆኑም በኢት የነበረው የሰዎች ግንኙነት መሉ በሙሉ በመሬት ዙሪያ ያተኮረ ነበር። በሌላ አነጋገር በህብረተሰቡ ውስጥ የነበረው የምርት ግንኙነት ሙሉ በሙሉ መሬት ባላቸውና በሌላቸው ማለት በባላባቶችና በጪሰኞች መካከል ያለው ነበር። በዚህ የምርት ግንኙነት ውስጥ በአንድ በኩል 1/ የንጉሣዊያን ቤተሰቦች፣ ባላባቶች፣ ታላላቅ ካህናት፣ ታላላቅ ወታደሮችና ነጋዴዎች ከ90 በመቶ የሚበልጠውን መሬት የግል ሀብታቸው በማድረግ፣ 2/ ላእላይ [illegible] በሁሉን ወዘተ/



በቀጥተራቸው ስርና የመደብ ጥቅማቸው ማስጠበቂያ በማድረግ፣ 3/በምርት ሂደት ውስጥ ምንም አይነት የጉልበት ሥራ ሳያበረክቱ አምራችን ህዝብ በመጠቀንና በመበዝበዝ የህብረተሰቡን አብዛኛውን ምርት በሥልጣናቸውና በባለቤትነታቸው እየወሰዱ የተንደላቀቀ ኑሮ ይኖሩ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ ለኑሮው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በእርሻ ላይ ተመኪ ከሆነው 90 በመቶ የኢት ህዝብ ከ80 በመቶ የሚበልጠው ህዝብ ምንም መሬት ሳይኖረው በጪሰኝነት 1) 50—75 በመቶ የሚደርስ የምርቱን ክፍል ለባለ መሬቶች እንዲሰጥ ይገደዱ ነበር። ይህ በአይነትም ሆነ በመጠን ከባለ መሬቶች ፍላጐት መለወጥና መጨመር ጋር አብሮ ይለወጥና ይጨምር ነበር። 2) በጪሰኛውና በባለመሬቱ መካከል የሚደረጉት ውሎች አብዛኛውን ጊዜ በቃል ስለነበረና ለባለመሬቱ በሚጠቅም መንገድ የሚፈጸሙ ስለነበሩ በባለመሬቱ ፍላጐት ጪሰኛው በሳሰበው ወቅት ይበረር ነበር። እህሉን ዘርቶ ያፈራውን ሊሰበስብ ሲል የሚበረረው ጪሰኛ ቍጥር ጥቂት አልነበረም። 3) ጪሰኛው ለባለመሬቱ የግል ጥቅም የጉልበት አገልግሎትና ልዩ ልዩ ''ስጦታዎች'' ዘወትር ይሰጥ ነበር። ከዚህም ሌላ በግብርና በልማት መልክ የሚያወጣቸው ልዩ ልዩ ወጪዎች በጣም ብዙ ነበሩ።

በተጠማሪም ጪሰኛው ለማምረት የሚገለገልባቸው የምርት መሣሪያዎች ወደኋላ የቀረ ከመሆናቸውም ሌላ ለማሻሻልም የሚያበረታቱ ሁኔታዎች አላጋጠሙትም። ከላይ እንዳመለከትነው ጪሰኛው የሚያምርትበት ሁኔታዎች መሻሻሉን ለማድረግ፣ ለመፍጠርና በርትቶ ለመሥራት የሚያመቹ አልነበሩም። እንዲያውም ተቃራኒ ሁኔታ የሚፈጥሩ ነበሩ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ፣

> "The tenant is not very interested inimproving the land since since he cannot be sure of ever enjoying the fruits of his effort and investment, if a share cropper, he will be reluctant to invest money in technological innovations or increase his labour imput unless he is convinced that his share in the marginal increase in output will actually augment his income"(E. jacoby, Man & Land, P. 225)

በመሆኑም የኢት አርሶ አደር የሚያርስበት በበሬ/በፈረስ የሚጎተት ወደኋላ የቀረ ማረሻ፣ ከማስ ወደ ውደማ የሚያገዘው በሸክም፣ የሚወቃው በበሬ ኮቴ በመፈቃ፣ ምርቱን ከገለባ የሚለየው ወደኋላ በቀረ ዘዴ ነበር።

የአርሶ አደሩ የማምረቻ መሣሪያዎች እጅግ ወደኋላ የቀሩ ከመሆናቸው የተነሳ በህብረሰቡ ውስጥ የሚመረተውም ምርት መጠኑ ዝቅተኛ ነበር። ከዚሁ ዝቅተኛ ምርት አርሶ አደሩ ለባለመሬቱ በኪራይ፣ ለግብርና በስጦታ መልክ ከፍሎ፣ ለባላባቱ መንግሥት በገባር ግብርና በልማት መልክ ከፍሎ፣ በየጊዜው ለሚበደራቸው ብድሮች ከከፍተኛ ወለድ ጋር

ከፍሉ ፣ ወዘተ ሰፊው የሚተርፈው ለአለት ኑሮው የሚበቃ ወይም ከሚበቃው በታች ነበረ፡፡
በዚህም ምክንያትም ረሀብ፣ እርዛና ድንቁርና በሽታ የአርሶ አደሩ ህዝብ የማይለቅ የኢሰ
ት ተለት ልማደቹ ሆኑ፡፡ በበዝበዛው መብዛትና መጠናከር፣ በመሬት ሳይ የመኖየት አድሉ
ያልተረጋገጠ በመሆኑ፣ ነፃነቱ የተረገጠ በመሆኑ፣ የአርሶ አደሩ የሚገለገልባቸውን የምር
ት መሣሪያዎች ለማሻሻል አዳዲሶች ለመፍጠር፣ ብሎም የተሻለና የበለጠ ምርት ለማምረት ያለ
ው ፍላጎቱና ችሎታ እየተበሳሸና እየተገታ ሄደ፡፡ በፊውዳሉ የኢኮኖሚ ስርአት የምርት
ሃይሎችን በተለይም የሰዎችን እድገት መገታት ሥራው ሆነ፡፡ ተጽእኖው አሉታ እየሆነና
አሉታነትም በጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የሚሄድ ሆነ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የከበርቴ የምርት ግንኙነት በመቀሳሳው ከጣሊያን ወረራ
ወዲህ መታየት ሲጀምር በተለይ በ60ዎቹና በ70ዎቹ መጀመሪያ ውስጥ በጣም መስፋፋት ጀመ
ረ፡፡ በባለቤትነታቸው በውጭ አገር ከበርቴዎችና ታሳሳቅ ባላባቶች ስር የሆኑ ከኮሜርሺያ
ሊስት አገሮች በገቡ ዘመናዊ የምርት መሣሪያዎች የሚገለገሉ ዘመናዊ እርሻዎች፣ ገዶቦች፣
ቀላል ኢንዱስትሪዎችን፣ ወዘተ በአገሪቱ ውስጥ መፍለቅ ጀመሩ፡፡ አርሶ አደሮች ከሚያርሱ
በት በሃይል መባረርና ከጋጠማቸው አዲስ በተቋቋሙት የከበርቴ ሀብት ማፍሪያ ኢንዱስትሪያ
ችና እርሻዎች የሚሰሩ ነባ ወዝአደሮች ወይም አዲስ በተዋረዳረፉት ከተማዎች በሥራ አጥነት
የሚንቀሳቀሱ ሃይሎች መሆን ጀመሩ፡፡ የሸቀጥ ማስወጫያና ማስገቢያ ወደቦች የአየር፣
የጓብስና የምድር የሸቀጥ ማመሳለሻ መንገዶች ተዘረጉ፡፡ ባንኮችና የመድህን ኩባንያዎች
ተቋቋሙ፡፡ በዚህ መልክ በፊውዳሉ የምርት ግንኙነት ጎን የከበርቴው የምርት ግንኙነት
ተፈጠረ፡፡ በሌላ አነጋገር በጪሰኛና በባላባት መካከል ብቻ ለብዙ መቶ አመታት ተወስኖ
የኖረው ያረጀ የሰዎች ግንኙነት በከበርቴና በወዝአደሩ መካከልም የሸቀጥ ምርት መሆን ጀመረ፡፡ የህ
ብረተሰቡ ምርት ተፈጥሮአዊ/ናቹራል ገበያ በሸቀጥነት መሆንም ጀመረ፡፡ የሚደረገውም የሸቀጥ ል
ውውጥ በአይነት ብቻ ከመሆን አልፎ በገንዘብም መሆን ጀመረ፡፡ በጭሩ የከበርቴው ስርአ
ት በፊውዳሉ ስርአት ውስጥ ተፀነሰ፡፡ ኢኮኖሚውም ድርብ ሆነ፡፡ የፊውዳሉና የከበርቴ
ው የምርት ግንኙነቶች ነፀብራቅ ሆነ፡፡ ስለዚህም ነው የኢት ኢኮኖሚ ከፊል ፊውዳል ከፊ
ል ከበርቴ ወይም ''ፊውደቦርዥዋ'' የተባለው፡፡ ተጽእኖአቸውን በሚመለከተው በኩል የፊተኛው
አብዛኛውን የሰዎችን ግንኙነት ስለሚያጠቃልልና የህብረተሰቡን ምርት ስለሚያስገኝ ከኋለኛ
ው በጣም የበለጠ ተጽእኖ አለው፡፡ ድርብ ተጽእኖአቸው ገን በህብረተሰቡ ላይ ጭቆናን
ብዝበዛን፣ ጭሁንነትን፣ ረሀብንና ድንቁርናን ማስከተል ነበር፡፡ ፊውዳሉ በተለይ የገን
ዘብ ኢኮኖሚ እየተስፋፋ ሲሄድ ፍላጎቱ ወደ ኢንዱስትሪ በልዋልጭ ሸቀጦች ሲሸጋገር ከጪሰ
ኛው ብዙና በገንዘብ እንዲከፍለው መጠየቅ ጀመረ፡፡ በዝበዛውን አባባሰ፡፡ ከበርቴውም
የውጭ አገዶሙኑ መጠን በአርባሽ ዋጋ ተቀር ከሚያሰፈው ወዝአደርና በሸቀጥ ሽያጭ በገፍ
የሚዘረፈውን ትርፍ ወደ የአገሩ በማንበስ ከገፊትን ርሀፊጌ በሌላው መንገድ ያራቀታት
ጀመረ፡፡



በዚህ ''ድርብ'' የኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ አሮጌው የፊውዳሉ ስርአት እና አዲሱ
የከበርቴው ስርአት ለተወሰነ ጊዜ ተቻችለው ቢኖሩም የፊተኛው የኋለኛው ከጊዜ ወደ ጊዜ
እነቀፋት እየሆነና በዚያውም ልክ ቅራኔአቸው እየጠመረ ሄደ፡፡ እያረጀ በሄደው የፊውዳ
ል የምርት ግንኙነት እድገታቸውና ነፃነታቸው የታገደው በዚሁ ስርአት ውስጥ ማደግ የጀመ
ሩት አዲሶቹ የከበርቴ የምርት ሃይሎች በአሮጌው ላይ ማመፅ ጀመሩ፡፡ ይህም አመፅ በየ
ካቲት 1966 ዓ ም በተወለደው አብዮት ተከሰተ፡፡ ስለሆነም፣

"The economic charcter of the present movement in Ethiopia is the struggle of the capitalist productive forces against the feudal mode of production. It is a question of primarily at least historically seen, of destroying feudalism, since it lies in the interest of the bourgeoisie (petty bourgeoisie).

a) to open the vista for the development of commodity production,for its freest and widest development, and correlatively.

b) to create the internal home market" (T.3 sept 1974 P.27 ቅንፍ ተጨማሪ)

የየካቲቱ አብዮት ኢኮኖሚያዊ መሠረት በፊውዳሉ የምርት ግንኙነትና በከበርቴው የ
ምርት ሃይሎች መካከል ያለው ግጭት ከሆነ፣ አሮጌውና አዲሱን ያረገዘው የፊውዳሉ የምርት
ግንኙነት ከሆነ፣ አዲሶቹና አሮጌውን የሚደመስሱት ደግሞ የከበርቴው የምርት ሃይሎች ከሆ
ኑ የሚወለደው የኢኮኖሚ ስርአት ብሎም ህብረተሰብ የበሪያ ወይም የሶሻሊስት አይደለም፡፡
ሊወለድ የሚችለው በፊውዳሉ የምርት ግንኙነት ውስጥ የተረገዘው የከበርቴው የምርት ግንኙ
ነት ነው፡፡ የሶሻሊስት የምርት ግንኙነት ከየካቲት በፊት በነበረው የፊውደ ከበርቴ
ኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ ሊረገዝ አለመቻሉ እርግጥ በማንኛውም ስርአት ውስጥ አይረገዝም
ብቻ በይሆን የሚፈለጉትን ማቴሪያላዊና ቴክኒካዊ ሁኔታዎች በዚህ ስርአት ውስጥ እንኳን
ተሟልተውና በከፊልም አልነበሩም፡፡ ሊኖሩም አይችሉም ነበር፡፡ ዋናው ቅራኔም በወዝ
አደሩና በከበርቴው መካከል ሳይሆን በአሮጌው የፊውዳል የምርት ግንኙነትና በአዲሶቹ የከ
በርቴ የምርት ሃይሎች መካከል ስለነበረ ከየካቲት አብዮት በኋላም የተወለደውና ማደግ የ
ጀመረው ይኸው ስርአት ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከየካቲት አብዮት በፊት የነበረውን የኢኮኖሚ ስርአት ባጭሩ በመጥቀ
ስ አብዛኛውን ፊውዳላዊ እንደነበረና የዛሬይቱ ኢት የኢኮኖሚ ስርአት ይህ አሮጌው ፊውዳ
ላዊ ስርአት ፅንሶት የነበረው የከበርቴ እንጂ የሶሻሊስት ሊሆን እንደማይችል አሳይተና
ል፡፡ ከዚህ ቀጥሎን ከየካቲት አብዮት በኋላ ባለፉት አራት ዓመታት በየጊዜው የተወሰዱ
ት ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎች ፀረ ፊውዳል እንጂ ፀረ ከበርቴ እንዳልነበሩና ቀጥታ ውጤታቸው
የፊውዳሉን የኢኮኖሚ መሠረት ማፍረስና የታፋነውን የከበርቴ ኢኮኖሚ መሠረት ማጠናከር
እንደነበረ እንደሆነ በአጭሩ ለማሳየት እንሞክራለን፡፡

<u>አንደኛ</u> የመሬት አዋጁን እንውሰድ:— ከ90 በመቶ የሚበልጠው የኢት መሬት ተይዞ የነበረው በጥቂት ባላባቶች እጅና ጥናው የሰዎች ግንኙነት መሬት ባላቸው ባላባቶች እና መሬት በሌላቸው ጪሰኞች እንደነበር ከላይ አመልክተናል። ይህም ግንኙነት በዝበዛና በጭቆና ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለምርት ሃይሎች እድገት እንቅፋት እንደነበር አስይተናል። የካቲት አብዮት በፈነዳ ከአንድ ዓመት በኋላ ግን ሁኔታው ስር ነቀል በሆነ መንገድ ተለወጠ። በየካቲት 1967 ዓ ም በወጣው የመሬት አዋጅ የፊውዳሉ ስርአት መሠረት የሆነው መሬት በመንግሥት ሥር ሆኗል። የማይሸጥ፣ የማይለወጥና የማይወረስ ሆኗል። የጋራ ሀብት መሆን ተርቷል።

መሬት ከባላባቶች ተነጥቆ በመንግሥት ስር መዋል የሚያስከትለው ቀጥታ ውጤት ደግሞ የፊውዳሊዝምና ስርአት ስር ነቀል በሆነ መንገድ ማናጋትና የእርሱ ተኪ ለሆነው ለከበርቴው ስርአት እድገት አመቺ ሁኔታ መፍጠር ነው። በተለይ የኢኮኖሚዋ ዋና እምብርት መሬት ሊሆነው ኢት የመሬት ከግል ሃብትነት መውጣትና በመንግሥት ስር መሆን ለከበርቴ የምርት ሃይሎች እድገት በሩና አመቺ ሁኔታዎች ይፈጥራል። ሌኒን "Nationalization is not only an effect of, but also a condition for, the rapid development of capitalism". (Lenin,CW, 13 P319) ይላል። መሬት ከባላባቶች ተነጥቆ ለአምራቾች ሲሰጥና አምራቾች የሥራቸው /የምርታቸው/ ጌቶች ሲሆኑ ብሎም ለባለ መሬቶ የሚከፍሏቸው ልዩ ልዩ ወጪዎች ሲቀሩላቸው የሚያመርቱት ከሆዱ አልፎ ለገበያ ይተርፋል። የተረፋቸውን እህልም ገበያ አውጥተው በመሸጥ ሌላ ሸቀጦች የኢንዱስትሪ ወይም የእጅ ጥበብ ምርቶች ይገዙበታል። እህል ወደ ገንዘብ ይለወጣል። በገንዘብ የኢንዱስትሪ ሸቀጥ ይገዛል። የእርሻ ውጤቶችን በኢንዱስትሪ ውጤቶች የሚደረገው ለውውጥ ይስፋፋል። ይህም የሸቀጥ ምርት /የከበርቴው ስርአት/ መስፋፋትን ያስከትላል። አርሶ አደሮችም ከፊውዳሉ ጭቆናና በዝበዛ ስለሚወጡ የማምረት ችሎታቸውን ለማሻሻልና ይበልጥ ለማምረት አመቺ ሁኔታዎች ይፈጠሩላቸዋል። ማቴሪያላዊ ፍላጎታቸውም እየተለወጡና እያደጉ ስለሚሄዱ እነርሱን ለማርካት ይበልጥ እህል መሸጥ ስለሚያስፈልጋቸው ምርታቸውን ለመጨመር ይገደዳሉ። በዚህ መልክ የመሬት የግል ሀብት መሆኑ ቀርቶ በመንግሥት ስር መዋልና ለአርሶ አደሮች መታደል የከበርቴውን ስርአት ለመፍጠር መቻል ብቻ ሳይሆን በፍጥነት ያሳድጋል። ስር ነቀሉ የየካቲት የመሬት አዋጅ የከበርቴ ስርአት ለማሳደግ ያለው ችሎታ ሰፊና ጠንካራ ነው። ምክንያቱም

> "The fearer that farming is from land congestion landlord oppression, the pressure of medieval relations and system of landownership, bondage and tyramy, the more strongly do capitalist relationships develop within that peasant farming". (Lenin CW, vol,13 p.296)



የዛሬይቱ የኢት ኢኮኖሚ የከበርቴ እንጂ የሶሻሊስት ሊሆን አይችልም ያልነውም የኢት ኢኮኖሚ ዋና መሠረት መሬት በመሆኑና የዚህ መሬት ከፊውዳላዊ ልዩ ልዩ ተጽእኖዎች ነፃ መውጣት ሌኒን እንደሚለው ሊያስከትል የሚችለው የከበርቴ ግንኙነቶች መሆኑን በመረዳት ነው። ከመሬቱ አዋጅ በኋላ ይህ ሁኔታ በሚገባ ታይቷል። በተለይ የመሬቱ አዋጅ ከሞላ ጎደል ሥራ ላይ በዋለበት በደቡብ ኢት ክፍል አርሶ አደሩ የማምረት ኃይሉ መጨመሩ ከሆዱ አልፎ ለገበያ የሚተርፍ ማምረት መጀመሩ፣ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ለመግዛት ፍላጎትና ችሎታው ማደግ፣ ብሎም የሸቀጥ ምርት መስፋፋትን ማበረታታት መጀመሩ ይታወቃል።

አንድ በእርሻ ሚኒስቴር ይሠራ የነበረ የስዊድሽ ኤክስፐርት በ1977 ዓ ም ባደረገው ጥናት የመሬቱ አዋጅ የአርሶ አደሩን የማምረት ኃይል ከፍ እንዳደረገውና ምርት እንደጨመረ ሲናገር እንዲህ ይላል።

> "The reform did eliminate one of the major structural hindrances to economic development in the country-side by making it possible for the large part of the rural population that formerly were tenants to retain for themselves the fruits of their labour thereby providing prima facie incentives for an increased production". (Holmgren, Grain Marketing & Land Reform in Ethiopia, P. 9

መሬት የመንግሥት ይሁን እንጂ አርሶ አደሮች እህል ለማምረት የሚገለገሉባቸው የምርት መሣሪያዎች ዘር፣ በሬ፣ ማረሻ፣ ወዘተ የአርሶ አደሮች የግል ሀብት ናቸው። ከመሬቱም የሚገኙት ውጤት ምርት የራሳቸው የግል ሀብት ነው። ግብርና ሌሎች ወጪዎችን ለመንግሥት ከከፈሉ በኋላ የተረፋቸውን እንደፈለጉት ሊያደርጉት ይችላሉ። ቢሻቸው ሊያጠራቅሙት ይችላል። ቢሻቸው ደግሞ በፈለጉበት ወቅትና ገበያ አውጥተው ሊሸጡት ይችላሉ። በነፃ ምርታቸው እየጨመረ ሲሄድ ደግሞ ለፈለጉት አላማ በእህል ለማጠራቀም ወይንም ሸጠው በገንዘብ መልክ ለማጠራቀም ወይንም እነርሱ ሊያመርቱ የማይችሏቸውን ሸቀጦች ለመግዛት ሊያውሉት የሚችሉት ክፍል ይጨምራል። በኢት የሚደረገው የሸቀጥ ለውውጥ በነፃ የገበያ ኢኮኖሚ ስርአት ስለሚገዛ እየተስፋፋ የሚሄደው የከበርቴው ስርአት ይሆናል። ሌኒን አርሶ አደሩ ካፒታሊዝምን በየቀኑ፣ በየሰዓቱ በያደርጥ እንደሚያስፋፋ ያስተምራል።

<u>ሁለተኛ</u> ኢንዱስትሪንና ባንኮችን፣ ኢንሹራንሶችንና የውጭ ንግድን እንውሰድ:—

ከየካቲት በፊት አብዛኞቻቸ የኢት ኢንዱስትሪዎች፣ የውጭ ንግድ፣ ባንኮችን፣ ኢንሹራንሶች በውጭ አገር ከበርቴዎች፣ በፊውዳሎችና በታላላቅ የቢሮክራት ከበርቴዎች የጋራ ባለቤትነት ስር ነበሩ። አብዛኛው ጥሬ ሀብት የውጮቹ ከበርቴዎች ስለነበረ ኢሰብአዊ በሆነ በዝበዛ አማካይነት የሚዛቀው ወሰን የሌሽ ትርፍ የሚጉረፈው ወደእነዚሁ የውጭ ከበርቴዎች ኪስ ነበር። የውጭ ከበርቴዎች የአገሪቱን ኢኮኖሚ እንደፈለጉት ለማስኬድ፣ የፈለጉትን ለማውጣትና ለማስገባት ይችሉ ስለነበረ የአገር ውስጥ የሸቀጥ ምርት እንዳያድግ

ተሰብስቦ በቀጦችን በማስገባት፣ የዋጋ ቁጥጥር ስላልነበረ የፈለጉትን ዋጋ በመወሰን፣ የ
አገሪቱ ውስጥ ካፒታል እንዳይጠራቀም ትርፋቸውን በየጊዜው ወደ የአገሮቻቸው በመላክ፣
የአገሪቱ ከበርቴ በንግድና በኢንዱስትሪ እንዳይሰተፍ በባንኮችና በኢንሹራንሶች የሚንቀሳ
ቀሰውን አብዛኛውን ካፒታል በስልጣናቸው ለእነርሱ ጥቅም በማዋል፣ ወዘተ የኢኮኖሚውን እ
ድገት አግደውት ነበር፡፡ በተግባር የከበርቴውን ስርአት የሚያስፉን ቢሆንም በቀጥታና
የውጭ የከበርቴ ስርአት ተቀጥያ አገልጋይ ሆኖ እንዲያድግ ነበር የሚጣጣሩት፡፡

ከየካቲት አብዮት በኋላ እነዚህ ሁሉ ከምሳ ጉደል ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል በመ
ንግሥት ቁጥጥር ስር በመሆናቸው ለከበርቴው የምርት ሃይሎች እድገት የተሸለ ሁኔታ ተፈጥ
ሯል ለማለት ይቻላል፡፡

የኢንዱስትሪዎች የንግድና የልዩ ልዩ የገንዘብ ተቋሞች በመንግሥት መወረስና ቁጥ
ጥር ስር መዋል፡-

1—በውጭ ከበርቴዎች በትርፍ መልክ በተፈለገው ጊዜና መጠን የሚወጣው ካፒታል
እንዲቆርና በአገር ውስጥ እንዲያገለግል ያደርጋል፡፡

2—በትርፍ መልክ ለንጉሣዊ ቤተሰቦች በታላላቅ ባላባቶችና የቢሮ ከበርቴዎች የሚ
ደርሰውና ለቅንጦት ኑሮ ማሳበሪያ በመዋል የሚባክነው በስዊስና በለንደን ባን
ኮች የሚቀመጠው ሀብት ለህብረተሰብ ጥቅም እንዲውል ለማድረግ ያስችላል፡፡

3—የውጭ ሸቀጦችን በመቆጣጠር የአገር ውስጥ ገበያ እንዲስፋፋ በሎም የአገር ው
ስጥ ኢንዱስትሪዎች የአገሬ ከበርቴዎች እንዲያድጉ ለማድረግ ያስችላል፡፡

4—የሸቀጥ ዋጋዎችን ለመቆጣጠር፣ ብድሮችን ለማስፋፋትና የገንዘብን እንቅስቃሴ
አጥጋቢ በሆነ መንገድ ለመቆጣጠርና ለመከታተል ይረዳል፡፡ እናስተረው እንጂ
ሌሎች ብዙ ነጥቦች መጥቀስ ይቻላል፡፡

እነዚህ የጠቀስናቸው ሁሉ በገበሬ ኢኮኖሚ በተገዛው ኢት ውስጥ የሚዝወትር ግና
የከበርቴውን ስርአት ማሳደግ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ አብዛኛው ንግድ፣ ማመሳሰሽ እንልገሎት፣ ከፍፍል፣ ትናንሽ ኢንዱስት
ሪዎች፣ ወዘተ በግል ከበርቴዎች ቁጥጥር ስር ነው፡፡

ከላይ ከተረብነው አጭር ገለጣ የዛሬው የኢት ኢኮኖሚ ስስት ገጽታዎች ቅርጾች አ
ንዳሉት እንገነዘባለን፡፡ እነዚህም የንዑስ ከበርቴ የሸቀጥ ምርት/አብዛኛውን ጊዜ አር
ስ አደሩን ይመለከታል፣ የግል ካፒታሊዝምና፣ የመንግሥት ካፒታሊዝም ናቸው፡፡



የኢት ኢኮኖሚ የገበሬ ኢኮኖሚ በመሆኑ ከስስቱ ገጾች አይነተኛውና ዋናው የንዑስ
ከበርቴው ካፒታሊዝም ነው፡፡ ስስቱም በድምር በመስፋፋት ላይ ያለውን "ወጣቱን" የከበርቴ
ስርአት ያስገኛሉ፡፡- በልዩ ልዩ የአገሪቱ ክፍሎችም የተፈጥሮ/ናቹራል ወይም ፓትሪያሪካ
ል/ኢኮኖሚም አለ፡፡ የሶሺሊስት ገን እንኳን እንደ ዋና የአገሪቱ ኢኮኖሚ ስርአት ይቅ
ርና እንደ አንዱ ክፍል እንኳን አይገኝም፡፡

ከዚህ በላይ ከየካቲት አብዮት ወዲህ የተወሰዱትን አንዳንዱ ዋና ዋና ለውጦች ያሳ
ቸውን ኢኮኖሚያዊ ይዘቶች በጣም በጥሩ ባሳየነው መሠረት በኢት ውስጥ በማደግ ላይ ያለው
የሶሺሊስት ሳይሆን የከበርቴ ስርአት መሆኑን እንደገና ለማረጋገጥ ሞክረናል፡፡ አንባቢ
ም ከእኛ ጋር እንደሚስማማ እንጠራጠርም፡፡ ጊ ወመ ባለፉት አራት አመታት ውስጥ የወሰ
ዳቸው እርምጃ የፈጠሩትና በማደግ ላይ ያሉት በፈታው የመረጠውን ''ሶሺሊዝምን'' ሳይ
ሆን ካፒታሊዝምን ነው፡፡ በኢሲተማ 15ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በዚህ ጥያቄ ላይ እን
ዲህ ይላል፡፡

> "The present government...is paving the way for a freer and wider development of capitalism. It has taken various measures that break the economic backbone of feudalism and clear the way for capitalist development (T.Z. No 75 P 10)

ለአሳይ መቀቀሩንም ወስደን የተመለከትን እንደሁ የዚሁ ነፀብራቅ ሆኖ እናገኘዋለ
ን፡፡ ከየካቲት በፊት የነበረው ለአሳይ መቀቅሩ አይነተኛ ባህሪ ፊውዳላዊ ይሁን እንጂ
ከከበርቴው የኢኮኖሚ ስርአት ጋር ተያይዞ ላአሳይ መቀቀሩም የከበርቴ ባህሪ እየወሰደ
መጥቶ ነበር፡፡ በሌላ አነጋገር የፊውዳሉ ላአሳይ መቀቅር በከበርቴው ርእዮተዓለም
በህል፣ ፍልስፍና ወዘተ እየተበረበረ መሄድ ጀምሮ ነበር፡፡ በኢንዱስትሪ ወደኋላ መቅረ
ት የተነሳ ወዝአደሩ በቀጥሩ አነስተኛ በርእዮተአለሙና በባህሉ ደካማና በነፃነት ማጣት
የነበረውም ያልተደራጀና የተበታተነ መደብ ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የኢት ወዝአደር መደብ የየካቲት አብዮት ሲፈነዳ የተሰተፈው
በመሪነት ሳይሆን በተመሪነት ደረጃ ነበር፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ብቃ
አልነበረም፡፡

የከበርቴው ኢኮኖሚ አብዛኛው ክፍልም በውጭ አገር ከበርቴዎች ባለቤትነት ቁጥጥር
ስር በመሆኑ ብሔራዊ ከበርቴውም እንደዚሁ ያላደገ፣ ደካማ፣ ለፈስፋባና ጥገኛ መደብ
ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የራሱን አብዮት ለመምራት የፖለቲካ ሥ
ልጣን መያዝ የማይችልበት ደረጃ የደረሰው የብሔራዊ ከበርቴው መደብ ሳይሆን የዲሞክራቲክ
አብዮት ሃይሎች በሆኑት ሃይሎች ሁሉ የተሸለ ደርጅትና ትጥቅ የነውስ ከበርቴው መደብ

ክፍል ወታደራዊ ሥልጣን ያዘ።

የንዑስ ከበርቴው መደብ ሥልጣን መያዝ ደግሞ በሳአሳይ መቆር ደረጃ የዛሬው የኢት የኢኮኖሚ ስርአት የከበርቴ አገኚ የሶሻሊስት ሊሆን የማይችል ለመሆኑ ሌላ ማረጋገጫ ነው። ምክንያቱም በሦስተኛው አለም ውስጥ፣

> "The petty bourgeois intelligenz (in Ethiopia it also includes the military S.B) which stands at the head of these parties, puts up national revolutionary demands, but is simulteneously-either more or less conscious-the representative of the capitalist development of its land".
> (ከ ት ዘና መስከረም 1967 የተወሰደ)

የፖለቲካው ሥልጣን በንዑስ ከበርቴው ስር እስከሆነ ድረስ ደግሞ የኢት ኢኮኖሚ ስርአት በሶም ህብረተሰብ በምንም አይነት ሶሻሊስት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ሶሻሊዝም ካለወዛአደሩ መደብ ሥልጣን መያዝ ተምኔታዊ ነው። የማይታሰብም ነገር ነው። ስለሆነም በንዑስ ከበርቴው አገዛዝ የኢት ኢኮኖሚ ስርአት በሶም ህብረተሰብ የከበርቴ አገኚ የሶሻሊስት አይሆንም።

በጥሬ ሶሻሊስት ስርአት መፈጠር የሚያስፈልጉትን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች መነሻ አድርገን የኢትን ህብረተሰብ የኢኮኖሚ መሠረትና ሳአሳይ መቆር ከየካቲት በፊትና በኋላ ስንመረምር የዛሬይቱ ኢት የእውነተኛ ሶሻሊዝም አራማጅ በሆነው በወዛአደሩ መደብ አገዛዝ ስር የከበርቴውን ስርአት በሶሻሊስት ለመተካት በሽግግር ላይ የምትገኝ አይደለችም። በኢምፔሪያሊዝም ዘመን የከበርቴው ስርአት ወኪል/አራማጅ/በሆነው በንዑስ ከበርቴው መደብ አገዛዝ ስር የፊውዳሳዊውን ስርአት በከበርቴው ለመተካት በሽግግር ላይ የምትገኝ ህብረተሰብ ናት በመሆኑም የኢት ኢኮኖሚ ስርአት ብሶም ህብረተሰብ አሁን ባለበት ደረጃ ሶሻሊስት ሊሆን አይችልም። የሶሻሊስት ኢኮኖሚም በአሁኑ ሁኔታ ለመገንባት አይቻልም። የየካቲት አብዮት ፍንዳታ ያስከተለው ውጤት የፊውዳሉ ስርአት በከበርቴው እየተተካ መሄዱን ነው። ከአብዮት በኋላ የምናየው የፊውዳሉ የኢኮኖሚ መሠረትና የእርሱ ነፀብራቅ የሆነው የፊውዳሉ ሳአሳይ መቆር እየተዳከመና የከበርቴው ኢኮኖሚ መሠረትና የእርሱ ነፀብራቅ የሆነው የከበርቴው በንዑስ ከበርቴው ወታደራዊ መንግሥት ይወክሳል ሳአሳይ መቆር እየተገነባ ሲሄድ ነው። የዛሬይቱ ኢት የኢኮኖሚ ስርአት ብሶም ህብረተሰብ ከምሳ ጉደል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የከበርቴ ስርአት ነው ለማለት ይቻላል። ተወደደም ተጠላም ከሰዎች ፍላጎት ነፃ በሆነ መንገድ በዛሬይቱ ኢት ውስጥ በአይናችን ፊት በማደግ ላይ የሚገኘው ስርአት በንዑስ ከበርቴ የሸቀጥ ምርት በሌላ አነጋገር የገበሬ ካፒታሊዝም የታየለ/ደሚኒትዎ የሆነ/የከበርቴ ስርአት ነው። ወቅቱ የሽግግር ስለሆነ ይህ ስርአት ገና አልበሰለም። "ወጣት" ነው። ይህን ሃቅ አሌ የሚል ከሰው ፍላጎት



ውጭ ስለሚያድጉት የኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች የማያውቅ በፊቱ ያለውን የማያይ ወይም ሃቅን የማይቀበል ወይም በአገራችን ውስጥ የሚካሄደውን ሽግግር ሊረዳ የማይችል ብቻ ነው።

## 2፤ 2 የዛሬይቱ ኢት ኢኮኖሚ ችግሮች አይነቶቻቸው፣ ጥልቀቶቻቸውና ምክንያቶቻቸው፦

በክፍል ሁለት ቁጥር 2፤1 ስር ከየካቲት አብዮት በፊት ለነበረው የኢኮኖሚ ችግርና ውድቀት ዋናው ምክንያት የመሬት በጥቂት ባላባቶች በባለቤትነት ስር መያዝና አብዛኛው ምርት ለነዚህ ባላባቶች ግላዊ ጥቅም በመዋሉ፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ዘመናዊ እርሻዎች፣ ባንኮች ኢንሹራንስ ኩባንያዎችና የውጭ ንግድ አብዛኛውን ጊዜ በውጭ ከበርቴዎችና በገዢው መደብ አባሎች በባለቤትነት ስር ስለነበሩ በብዝበዛ የሚዘረፈው ትርፍ ወደ ውጭ አገር በመውጣቱ የውስጥ ኢንዱስትሪዎችና ገበያ ባለመስፋፋቱ እንደነበረ አጥንተናል። የፊውዳላዊ ሳአሳይ መቆርም በማርጀቱ የእድገት እንቅፋት መሆኑ አንዱ ምክንያት እንደነበረ አሳይተናል። በዚሁ ክፍል ከየካቲት በኋላ ለኢኮኖሚ እድገት በር ሊከፍቱና በዚያን ወቅት የነበረውን የኢኮኖሚ ችግር ሊያስወግዱ የሚችሉ ብዙ እርምጃዎች እንደተወሰዱ ብሶም ከቀድሞው የበለጠ ለእድገት ''ጉጉና'' በር ከፋች የሆነ የንኡስ ከበርቴ መንግሥት እንደተፈጠረ ጠቁመናል። እነዚህ አዲስ ሁኔታዎች የእድገት ጉታችና የችግሮች ወሳኝ የሆነውን የፊውዳሉን ስርአት እንዴት ሊገረስሱ እንደሚችሉና እንደጀመሩም በጥሬ አሳይተናል።

ነገሩ የሚያቆረን ይመስላል። ሃቅ ግን የመሬት ከባላባቶች ተነጥቆ ለአርሶ አደሩ መሰጠቱ፣ የኢንዱስትሪ፣ የገንዘብ ተቋሞችና የውጭ ንግድ ከውጭ አገር ከበርቴዎችና የገዢ መደብ አባሎች ተነጥቆ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መዋሉ፣ የተፈጠረው የገዢ መደብ ለእድገት ''ጉጉ'' ብቻ ሳይሆን የዋና ዋና ምርት ማፍሪያዎች ባለቤት በመሆኑ ከእርጌው መንግሥት የበለጠ ገቢ ያለው መሆኑ የኢት የኢኮኖሚ ችግር እየዛያው በዚያው እየተጣጣ እንዲቀር እንጂ ሥር ነቀል መፍትሄ እንዲያገኝ እምብዛም አልረዳትም፤ኢኮኖሚው የተጠበቀውን ያህል አላደገም። እንዲያውም ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ ተባብሶዋል። አገሪቱ በጠቅላላው የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ በመዋዠቅ ላይ ትገኛለች። እጥረት በእጥረት ሆናለች። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

ከዚህ ቀጥለን በምናቀርበው አጭር ጥናት በአሁኑ ወቅት አይነተኛ የሆኑትን የኢኮኖሚ ችግሮች በማንሳት አይነቶቻቸውን ጥልቀቶቻቸውንና ምክንያቶቻቸውን ለማሳየት እንሞክራለን።

ኢትን በአሁኑ ጊዜ እንደ ሸረሪት ድር የተበተቧት የኢኮኖሚ ችግሮች አይነቶቻቸው ብዙ፣ ጥልቀቶቻቸው ሰፊና ምክንያቶቻቸው በጣም ውስብስብ የሆኑ ናቸው። ችግሮች መልካቸውና ቅርፃቸው እጅግ በመብዛቱ የማይያዙ በመሰሉም ለሰው ልጅ ኑሮ መሠረታዊ በሆኑ በምግብ፣ በልብስና በመጠለያ ጥያቄዎች አከባቢ የሚጠቃለሉ ናቸው። በዚህ ጥናታችን

ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ችግሮች አንስተን እንመለከታለን፡፡

<u>፪.፪.፩ የምግብ ሸቀጦች እጥረት</u> /ጥሬ እህልን ጨውን፣በርበሬን፣ ዓቦን፣ የወጥ ዘይትንን፣ የምግብ አትክልትን፣ ወዘተ ይጨምራል/ በአገሪቱ ውስጥ የተፈጠረው የእህል እጥረት አገር አቀፍ አይደለም፡፡ ገና የሚታየው ይበልጥ በከተሞች፣ በተፈጥሮ አደጋ በተጎዱ በምእራብ ወሎና ትግራይ፣ በጦርነት በተጎዱ በኤርትራና በሐረር ክፍለ አገሮች ሲሆን የመሬት አቅች አጥጋቢ በሆነ መንገድ/አርገጥ በየትም ቦታ አጥጋቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ አልዋለም/ወይም አስከሚፈለግ ስራ ላይ ባልዋለባቸው ቦታዎችም ጭምር ነው፡፡ ከሌሎች ቦታዎች ጋር ሲነፃፀር የመሬት አቅች በተሻለ መንገድ ሥራ ላይ በዋለባቸው በአብዛኛዎቹ የደቡብ ኢት ክፍለ አገሮች አልፎ አልፎ የእህል እጥረት ቢኖርም በአጠቃላይ ደህና ሁኔታ አለ ለማለት ይቻላል፡፡ የጨው፣ የዘይትና የበርበሬ እጥረቶች ግን አብዛኛውን ክፍል በመንካታቸው አገር አቀፍ ችግሮች ናቸው፡፡

በልዩ ልዩ አደጋዎች በተጎዱት ክፍለ አገሮች በተለይ በምእራብ ወሎ የተፈጠረው የእህል እጥረት ፀፋ ረሀብ ሲያስከትል ለብዙ መቶ ሺ ሰዎችም ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል፡፡

በከተሞች የተፈጠረው የእህል እጥረትም በበኩሉ ''የተደበቀ ረሀብ''አስከትሏል፡፡ በዚህ እጥረት ይበልጥ የተጎዳው አነስተኛ ደመወዝ ያለው ወዝአደሩ በተለይ የከተማው ሠርቶ አደር በጠቅላላው ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ህብረተሰብ ክፍል ረጅም የወር የሁለት ወር ወረፋ እህል ለማግኘት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የተገኘውንም አውጥቶ ለመግዛት ያለው ችሎታ የተወሰነ ነው፡፡ ደመወዙ መጠን የእህል ዋጋ ሰማይ ሆነውበት አንደምንም ብሎ እህል ሲገኝ እንኳ ለመግዛት አይችልም፡፡ በዚህ ምክንያት አንዳይምት አንዳይሸር አንድ አፍኝ ቆሎ ቆርጥሞ፣ ወይም አንድ ኩርማን ዳቦ በልቶ ውሃውን ተጎንጭቶ የእለት ኑሮውን እንዲገፋ የተገደደው የከተማ ሠርቶ አደር በጣም በጣም ብዙ ነው፡፡ በጠቅላላው የከተማ ኗሪው በተለይ ያገኘውን ለመግዛት የገንዘብ ገቢው የሚፈቅድለት ክፍል ለእንጀራ የሚሆኑ እህሎች ጤፍ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ ማሽላ ወዘተ በመጥፋታቸው የምግብ ልምዱን እንዲለውጥ ተደርጓል፡፡ ከቤት ዳቦ የፋብሪካ፣ ከእንጀራ ፓስታና መኮሮኒ እንዲመገብ አድርጎታል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህም ቢሆኑ እንደልቡና የትም ሱቅ አይገኙም፡፡ በትናንሽ ዳቦ መጋገሪያ ቤቶች ከሌሊቱ 10ሰአት ጀምረው እስከሚተጥሰው ቀን ድረስ ወረፋ ቆመው አንድ ቅሬጭ ዳቦ ሳያገኙ የሚመለሱ ብዙ ናቸው፡፡

ከዚህም ሌላ ለጠላ፣ለከረፋና ለዘህላ የሚውሉ ጥሬ እህሎች በተለይ ገብስና ማሽላ በመጥፋታቸው ጠላና ከረፋ በመጥፋቱና ለዘህላ በማወጣት ኑሮአቸውን የሚገፋ ትምራቸው



ወሰን የሌለው የከተማ ሠርቶ አደሮች በእህል እጥረት መኖር አዳገ ተጐድተዋል፡፡ ትናንሽ የምግብ ቤቶችና ቡናቤቶች ከፍተው የሚኖሩም እንደዚሁ፡፡

በጭሩ በአገሪቱ በጠቅላላውና በከተማዎች በተለይ የደረሰው ጠቅላላ የምግብ ሸቀጦች እጥረት ከገጠው መደብ ከቢሮ ከበርቴው፣ ከከፍተኛው ገውስ ከበርቴና ነጋዴዎች በስተቀር ያልነካውና ያልጐዳው መደብና የህብረተሰብ ክፍል የለም፡፡

ከችግሮች አንዱ የሆነውን የምግብ ሸቀጦች እጥረትን ጥልቀትና ስፋት በጭሩ ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ እንዲኖር ወዳበቁት ምክንያቶች እንመለስ፡፡

በኢት ውስጥ ለደረሰው ከፍተኛ የምግብ ሸቀጦች እጥረት ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ይህን ጥያቄ ለመመለስ የሞከሩ አንዳንድ ድርጅቶችና ግለሰቦች ''መጥፎ''አርሶ አደሮችና ነጋዴዎች ናቸው ይላሉ፡፡ አርሶ አደሮችን እንደምክንያት የሚወስዱት አርሶ አደሩ የሚያመርተውን በእህል መልክ ስለሚያጠራቅም ነው፣ ገበሬው ''ስነፍ''በመሆኑ የተሰጠውን መሬት ሳያርስ ጦም በማሳደሩ ነው፣ ወዘተ ይላሉ፡፡ ''መጥፎ''ነጋዴዎችን እንደምክንያት አድርገው የሚወስዱት ደግሞ የእህል ነጋዴዎች በልዩ ልዩ መንገድ ስለሚያሸጥሩ ነው ይላሉ፡፡ የመጥፎ አርሶ አደሮችና ነጋዴዎች የተቀነባበረ ሴራ ውጤት ነው የሚሉም አሉ፡፡ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሰበቦችና ነፀብራቆች እንጂ መሠረታዊ ምክንያቶች አይደሉም፡፡ ከዚህም ሌላ በአርሶ አደሩ ላይ የተሰነዘሩት ''ክሶች''ስህተተኛ ከመሆናቸውም በላይ ተገቢ ያልሆኑ ናቸው፡፡ የነጋዴዎች አሻጥርም ውጤት ነፀብራቅ እንጂ እራሱን የቻለ መሠረታዊ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ በኢት ለደረሰው የምግብ ሸቀጦች እጥረት ምክንያቶች እንደዚህ በቀላሉ የሚወሰኑ አይደሉም፡፡ ብዙና የተወሳሰቡ ናቸው፡፡ የምርት/ፕሮዳክሽን/፣ የክፍፍል/ዲስትሪቡሽን/ና የልውውጥ/ኤክስቼንጅ/ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው፡፡

<u>እንደምርት ጥያቄ፡-</u> በክፍል አንድ ውስጥ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሰዎች የኑሮ ደረጃ ማደግና የቁስቁሳዊ ፍላጐቶች መሟላት የሚወሰነው በህብረተሰቡ ውስጥ የሚመረተው የምርት መጠን መሆኑንና ይህም በተራው በምርት ሃይሎች/ሰዎችና ሰዎች ለማምረት በሚገለገሉባቸው መሣሪያዎች/እና ግንኙነቶች የእድገት ደረጃ እንደሚወሰን አጥንተናል፡፡ በኢት የደረሰውን የምግብ ሸቀጦች እጥረት፣ ብሎም የሰዎች መራብ የምናጠናው ከዚሁ አንፃር በማየት ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በኢት ለደረሰው ወሰን የለሽ የምግብ ሸቀጦች እጥረት መሠረታዊ ምክንያቱ የምርት መጠን ከህብረተሰቡ ፍላጐት ጋር በተመጣጠነ ፍጥነት አለማደጉ

ነው፡፡ መሬት ለአምራች ተሰጥቶ ምርት ለምን አላደገም? ጥያቄውን ለመመለስ እንደገና በክፍል አንድ ውስጥ ወደ አቀረብነው ጥናት እንመለስ፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የምግብ ሸቀጥ ለማምረት መሬት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ነገሮችም እንደሚያስፈልጉ መጥቀሳችን ይታወሳል፡፡ ከእርሻ መገልገያ መሣሪያዎች ምርት ማምረትና ካለ የተሻሻሉ የስራ መገልገያ መሣሪያዎች ምርትን ለማሳደግ/የበለጠ ለማምረት/እንደማይቻል አመልክተናል፡፡ የኢት አርሶ አደር ስለሚገለገልባቸው የምርት መሣሪያዎች ማጥናት ከመጀመራችን በፊት ስለመሬት ለአምራች መሰጠት ትግበ ስለመሬቱ አዋጅ ሥራ ላይ መዋል በአጭሩ እናንሳ፡፡

በየካቲት 1967 በወጣው አዋጅ መሠረት አብዛኛው የኢት አርሶ አደር አርሶ የሚኖርበት መሬት አግኝቷል፡፡ በማህበራት ተደራጅቷል፡፡ እልፍ አልፎም የህብረት ሱቆች አቋቁሟል፡፡ ሁኔታውን ጠለቅ አድርጎ ለመረመረው ግን ምንም መሬት ያላገኘና እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች ለሚመጣው ዓመት ታገኛለህ ገበር መክፈል ጀምር እየተባለ እንኳን ፍሬውን በአይኑ ሳላየው መሬት ከዓመት ዓመት ገበር እየከፈለ ወይም ሳይከፍል ወረፋ የሚጠብቀው አርሶ አደር ብዙ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ መሬት ለአራሹ ሁሉ አልታደለም ማለት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ደገበኛ የመሬት ድልድል ባለመደረጉና አርሶ አደሮች የወሰዱት ቀደም የሚያርሱትን ስለነበረ በአብዛኛው ቦታ የመሬት ጥበት አለ፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች ያለው የመሬት ጥበት ከኗሪው ቁጥር ጋር ሲወዳደር ሊታረስ የሚችለው መሬት በሃቅ መጥበቡ ሲሆን በሌሎች ቦታዎች ደግሞ ሰው ሰራሽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አንድ አንድ ገበሬዎች ከ20–30 ሄክታር መሬት ይዘው ሌሎች ደግሞ 2–3 ሄክታር አያርሱ እንዲሁም ሌሎች ምንም መሬት ሳይኖራቸው ለማግኘት እየጠበቁ የሚኖሩባቸው አካባቢዎች ጥቂት አይደሉም፡፡ እንግዲህ በአንድ አካባቢ ወይም በብዙ አካባቢዎች ውስጥ አዋጁ ከሚፈቅድላቸው በላይ ብዙ መሬት የያዙ አርሶ አደሮች ይገኛሉ ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በአንድ ወገን ከአቅም በላይ መሬት በያዙት አርሶ አደሮች በኩል የመሬት ጦም ማደርን ወይም በሚገባ አለመታረስን ሲያስከትል የመሬት ጥበት ባላቸው በጠቀሳሳውና መሬት ለማግኘት በሚጠባበቁት አርሶ አደሮች በኩል ደግሞ የሰዎች ጉልበትና የማምረት ችሎታ በከንቱ መባከንን ያስከትላል፡፡ የሁለቱ ድምር ውጤት ደግሞ የህብረተሰቡ የምግብ ምርት እንዳያድግ ያደርጋል፡፡ የመሬት ድልድል ከሞላ ጎደል ሥራ ላይ የዋለበት የደቡቡን ክፍልና የመሬቱ አዋጅ ጠርሶ ሥራ ላይ ያልዋለበትን ወይም ''በተልከሰከሰ''መንገድ ለይስሙላ የዋለበትን የሰሜኑን ክፍል ብንወስድ የምግብ ሸቀጦች ምርት ከኋለኛው በፊተኛው ይበልጥ አድጎ እናገኘዋለን፡፡

ጊ ወ መ ይህን ለምግብ ሸቀጦች ምርት አለመጠመር አንዱ ምክንያት የሆነውን በልዩ ልዩ ክፍለ ሃገሮችም ሆነ በአንድ ክፍለ ሃገር ውስጥ የሚገኘውን የተዛባ የመሬት ድልድል በማስተካከል ችግሩን ለማቃለል ጥረት አላደረገም፡፡ እንዲያውም በተባራሪው የመሬት ድልድል ማስተካከሉ/የመሬት አዋጅ ሥራ ላይ መዋል/እንዲቆም አድርጓል፡፡



እስከ በ1967 የመሬትን አዋጅ ሥራ ላይ ማዋል ለሚያገባቸው መሥሪያ ቤቶች ባስተላለፈው ምስጢራዊ ዜና እነዚህ መስሪያ ቤቶች የተስተካከለ የመሬት ድልድል (equitable land redistribution) ለማካሄድ እንዳይጠነቁና ብዙ መሬት ለማልማት ለሚችሉ ገበሬዎች የበለጠ እንዲሰጧቸውና እንዲያበረታቷቸው አሳስቧል፡፡ (Michael Stähl: New seeds in old soil P, 32)

በጥሩ የመሬትን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል በተካሄደው ከነውን የተዛባ የመሬት ድልድል በመደረጉ የመሬት አዋጁ በሚገባ ሥራ ላይ ባለመዋሉ እና ደርግም ይህን ዓይነት ሁኔታ በማበረታቱ ''እውነተኛም''ሆነ ''ሰው ሰራሽ''የመሬት ጥበት መሬትና ጉልበት በከንቱ እንዲባክኑ ብሎም የምግብ ምርት ፍላጎትን በሚያረካ እንዳያድግና የምርት ሸቀጦች እጥረት እንዲኖር አድርጓል፡፡ ከዚህም ሌላ የመሬት አዋጁ ሥራ ላይ መዋል እንደጀመረ በይድረስ በይድረስ የተቋቋሙት የህብረት እርሻዎች እየተዳከሙ በመምጣታቸው ለመሬት ጦም ማደርና የምግብ ምርት አለመጠመር ሚና ተጫውተዋል፡፡ ይህም ሲሆን የቻለው በማህበራቱ አባል ገበሬዎች መካከል ዘወትር በሚነሰው የሂሳብ ጭቅጭቅ፣ የክፍፍል ችግር፣ የዘርና የጉልበት መዋጮ ችግር ወዘተ ምክንያት ነው፡፡ በብዙ የህብረት እርሻዎች ዘንድ በህብረት ለማምረት ልዩ ልዩ ገበሬዎች በልዩ ልዩ መልክ የሚያበረክቷቸውን የምርት ማካሄጃዎች ጉልበት፣ ዘር፣ በሬ ጥሬ ገንዘብ ወዘተ ለመመዘንና፣ የተመረተውን ለማከፋፈልና የወጪ ገቢ ሂሳብ ለመያዝ ትልቅ ችግር በመፈጠሩ የህብረት እርሻዎችን እየለቀቁ ብዙ ገበሬዎች ወጥተዋል፡፡ በዚህ ብቻ ሳይሆን በግል የሚያርሱት የበለጠ ጥቅም ስለሚያስገኝላቸውና ከህብረት እርሻው የሚያገኙት የእለት ፍላጎታቸውን ስለማያረካላቸው በየጊዜው በየቦታው የሚለቀቁ ብዙ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት በብዙ ቦታዎች በህብረት እርሻነት ተሰይመው በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ጦም ያደሩ ለም መሬቶች ብዙ ናቸው፡፡ ጦም ያደሩ መሬቶችን ካነሳን አይቀር በአገር ጥሪ ምክንያት በጦር ግምባር በግዳጅ እንዲዘምቱ በተደረጉት ብዙ መቶ ሺ አርሶ አደሮች ምክንያትም ከጥቅም ውጭ ያደሩት ማሳዎች ብዙ ናቸው፡፡ እንዲቀጉ በዘመቻ ብቻ ሳይሆን ጦርነቱ በተካሄደባቸው ቦታዎች በሰላም ጉድለት በተሰደዱ አርሶ አደሮችም ምክንያትም ብዙ መሬት ጦም አድሯል፡፡

በወሎ በትግራይ፣ በሐረርና በሌሎች ሰሜን ክፍለ አገሮች በየጊዜው የደረሱት ልዩ ልዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ድርቅ፣ አንበጣ፣ ጎርፍ፣ ወዘተ በአገሪቱ ለሚመረተው የምግብ ሸቀጦች ምርት አለመጠመር ሌሎች ምክንያቶች ናቸው፡፡

አላይ ከጠቀስናቸው የበለጠ ለምግብ ሸቀጦች አለመጠመር ምክንያት የሆነው አርሶ አደሮች ለማምረት የሚገለገሉባቸው መሣሪያዎችና የእርሻ ዘዴዎች እጅግ በጣም ወደኋላ

የቀረና ያረጁ መሆናቸው ነው፡፡

በዚሁ ክፍል ቁጥር 2:1 ስር ከየካቲት በፊት ሰፊው የኢት አርሶ አደር ለማምረት የሚጠቀምበት የእርሻ መሣሪያዎችና ዘዴዎች በጣም ጥንታዊ/ፕሪሚቲቭ/ እንደነበሩና በዚህም ምክንያት የሚያመርተው ምርት መጠን ከአሥር ጕርስ የማያልፍ በጣም ዝቅተኛ እንደነበረ ገልጠናል፡፡ ከየካቲት በኋላም ሁኔታው አልተሻሻለም፡፡ የሚያርሰው መሬት ቢያገኝም 90 በመቶ የሚሆነውን የአገሪቱን የምግብ ሸቀጥ የሚያመርተው ሰፊው የኢት አርሶ አደር ከመሬት ጋር የሚታገለው በዚያው በጥንታዊው የእርሻ መሣሪያውና ዘዴው ነው፡፡

ሰፊው አርሶ አደር አሁንም የሚያርሰው በትራክተር ሳይሆን በጥንድ በሬዎች ወይም በፈረስ ወይም በሰው በሚጐተት ከተራ ብረት በጥንታዊ መንገድ በተሰራ ማረሻ ነው፡፡ እንዲያውም በአንዳንድ ቦታዎች በዶማና በአንካሴ ቆፍረው በማምረት የሚኖሩም አሉ፡፡ የሚያጭዱበት ማጭድ፣ የሚወቁበት ዘዴ፣ ወዘተ ሁሉም ጥንታዊ ናቸው፡፡ ሰፊው አርሶ አደር የተሻሻለ የአፈር አያያዝ ትምህርት የለውም፡፡ በዚህ ምክንያት ዝናም ሲጥል በጉርፍ፣ ነፋስ ሲነፍስ በነፋስ አፈሩም ሆነ የዘራው እየተጠረገ ይወሰድበታል፡፡ በዚህ በኩል የእውቀት ብቻ ሳይሆን ገደቦች ለመስራት፣ ዘመናዊ የቦይ ውሃ ለመጠቀም፣ ደን ለማልማት ወዘተ የቴክኒካልና የገንዘብ አቅም የለውም፡፡ የተሻሻለ ዘር፣ የአፈር ማዳበሪያና ሌሎች እርሻውን ለማሻሻል የሚያስፈልጉትን ሁሉ ለመግዛት የገንዘብ ችሎታ የለውም፡፡

መንግሥት የአርሶ አደሩ የእርሻ መገልገያ መሣሪያዎችንና ዘዴዎችን እንዲያሻሽል የወሰደውን እርምጃ የሰጠውን አገልግሎት የተመለከትን እንደሆ በጣም ውስን ከመሆኑም በላይ ለሰፊው ደሀ አርሶ አደር ተስፋ አስቆራጭ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

እንደነገሩ ከሆነ መንግሥት በገጠሩ ተሰማርተው አርሶ አደሩን ''የሚረዱ'' ወኪሎች አሉት፡፡ ከእነዚህ የመንግሥት ወኪሎች ይበልጥ በሰፊው ተሰራጭቶና አርሶአደሩን ተጠግቶ የሚሠራው ኢፒድ የሚባለው የእርሻ ሚኒስቴር የአገልግሎት ክፍል ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የእድገትና አብዮት ኮሚቴዎች፣ የእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክ ወዘተ አሉ፡፡

ከሁሉም የበለጠ ከአርሶ አደሮች ጋር ግንኙነት ያለውን ኢፒድን ወስደን እንመልከት፡፡ ኢፒድ የመሬት አዋጅን ሥራ ላይ በማዋል በኩል የማይካድ ታላቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ በተለይ በመጀመሪያው ጊዜ በከፍተኛ መንፈስ ጋር አርሶ አደሮችን ለማደራጀት፣ ለአርሶ አደሮች መሬት ለማደልና የእርሻ መሣሪያዎቻቸውንና ዘዴዎቻቸውን ለማሻሻል ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ የመጠረሻዎችን በሚመለከት በኩል ገበሬ ከገበሬ ሳይለይ፣ ማሰው



ትንሽ ነው ትልቅ ነው ሳይል ከመሬት ከበርቴዎች የተወረሱትን በዝቅተኛ ዋጋ በማከራየት በሬ ገዝቶ በመስጠት ወይም በማበደር፣ ማዳበሪያና ዘር በማደል፣ ልዩ ልዩ ብድሮችን በመፍቀድ፣ ስለእርሻ ዘዴዎች ትምህርት በመስጠት ወዘተ ለማሻሻል ረድቷል፡፡ ይህም ሁኔታ አርሶ አደሮች በከፍተኛ መንፈስ በምርት ሂደት ውስጥ እንዲሰማሩ አድርጓቸዋል፡፡ ስለ ኢት የመሬት አዋጅ የፃፉ አንዳንድ ኤክስፐርቶች ሲናገሩ የመሬት አዋጁ ሥራ ላይ መዋል እንደተጀመረ እንደተፈራው የምግብ ሸቀጥ ምርት ያልቀነሰውና በአገሪቱ እጥረት ያልተከተለው በዚህ ምክንያት ነው ይሳሉ፡፡

የኋላ የኋላ ግን ሁኔታው እየተለወጠ ሄደ፡፡ በኢፒድ አማካይነት ለአርሶ አደሮች ጥቅም ውለው ከነበሩት ትራክተሮች አብዛኛዎቹ ወደ መንግሥት እርሻዎች መሠማራት ጀመሩ፡፡ ለአርሶ አደሮች አገልግሎት እንዲውሉ የተደለደሉትም ጥቂት ትራክተሮችም ከ10—15 ሄክታር በላይ ለሚያርሱ አርሶ አደሮች ብቻ መከራየት ጀመሩ፡፡ ይዘት ከዚህ በታች የሆነው ብዙሀኑ አርሶ አደር ''ማሳያቻቸሁ ትራክተር ለመጠቀም አያመችም''መባል ጀመረ፡፡ በጥሬ ገንዘብ የሚሰጠውም ብድር የዚሁ አይነት ፈለግ ተከተለ፡፡ የእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክ ብድር የሚሰጠው ከ15—20 ሄክታር መሬት ለሚያርሱ አርሶ አደሮች ብቻ ሆነ፡፡ ኢፒድ ከዚህ በታች ላሉትም ለመስጠት ቢሀን በይስከልም የሚጠይቀው ወለድ በጣም ከፍተኛ 13 በመቶ/— የነገድ ባንክ 9 በመቶ ነው/በመሆኑ ድሃ አርሶ አደሮች ለመበደር አይችሉም፡፡ በዚህ ምክንያት በተደምው ሰርክ በነበራቸው ይዘትና የመሬት ዱልዱል በለመስተካከሉ አዋጅ ከሚፈቅዱላቸው በላይ ብዙ መሬት ያላቸው ጥቂት ''አዱሳና''ገበሬዎች ብቻ የመንግሥት ''እርዳታ'' ተጠቃሚዎች ሆኑ፡፡ ከየካቲት በፊትም እንደነዚህ አይነቶቹ የመንግሥት አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች የነበሩት ሃብታም ገበሬዎች ነበሩ፡፡ የማይመስል ሊሆን ይችል ይሆናል ሐቁ ግን ይህ ነው፡፡

ምርታቸውን ለማሻሻል አርሶ አደሮች እንደየቦታቸው አዘወትረው ወይም አልፎ አልፎ የሚያገኙት ብዙ ወይም ጥቂት መንግሥታዊ አገልግሎቶች ማዳበሪያና ዘር ነው፡፡ በዚህ ረገድ እንኳ በድሀና በሀብታም ገበሬዎች መካከል ልዩነቶች ይደረጋሉ፡፡ የኋለኞቹ ብዙና አዘወትረው ሲያገኙ የፊተኞቹ ግን ጥቂትና ሲያሙች አልፎ አልፎ ያገኛሉ፡፡ ከዚህም ሌላ ወለዳቸው|ኪራያቸው|ከፍተኛና የከፍያው ጊዜ አጭር በመሆኑ ድሀ ገበሬዎች ብዙውን ጊዜ ለመበደር ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ በእንደዚህ ዓይነት የብድር ሁኔታዎች ውስጥም አዱናቸውን ጠፍነው የተበደሩና በእዳ ተዘብትበው በሀዐት የሚኖሩ አርሶ አደሮች በጣም ብዙ ናቸው፡፡ በአካባቢያቸው ያሉ ሌሎች ደሀ ገበሬዎችም ከእነዚህ ትምህርት በመውሰድ ተመሳሳይ ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት ከመበደር እጃቸውን ለማሰረፍ የወሰኑ እንደዚሁ ብዙ ናቸው፡፡

ሚካኤል አስቶል በሰወለጋ ክፍለ ሃገር ባደረገው ጥናት ብዙ አርሶአደሮች በሬ፣ ዘርና ማባበሪያ ለመግዛት ከመንግሥትና ከገበሬ ማህበራት የሚወስዷቸውን ብድሮች መክፈል አቅቷቸው በእዳ እንደሚቆዩ ይናገራል::

ምርቱን ለመጨመር ሰፊው አርሶ አደር ያለበት ችግር የሚገለገልባቸው መሣሪያዎችና የሚጠቀምባቸው የእርሻ ዘዴዎች ጥንታዊና ወደኋላ የቀረ መሆናቸው ብቻ አይደለም:: የእነዚህ መሣሪያዎች እጥረት መኖሩም ጭምር ነው::

ለምሳሌ ዋና የእርሻ መገልገያ መሣሪያ የሆነውን በሬ ወስደን ብንመለከት ታላቅ የእጥረት ችግር እንዳለ እንገነዘባለን:: ይህ እጥረት ሊኖር የቻለው በመጀመሪያ የመሬት ከበርቴዎች የመሬት አዋጁን ለማሸጠር በወሰዱት የበሬ ጭፍጨፋ እርምጃ ነው:: የተፈጥሮ አደጋ በደረሰባቸውና ጦርነት በተካሄደባቸው ቦታዎች የደረሰው የከብቶች እልቂትም ለዚህ እጥረት ምክንያት ሆኗል:: መርዛማ በሆኑ ዝንቦች/ስስ ፍላይ/ በመነከስም ይህ ችግር በተለይ በደቡብ ምእራብ ኢት አይነተኛ ነው/በሬዎች ማለቃቸው ሌላው ምክንያት ነው:: ከዚህም ሌላ መንግሥቱ በሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ ታላላቅ ድግሶችና በተለይ በ1969 ዓ ም በእናት አገር ጥሪ ስም በየቦታው የተጨፈጨፈው በብዙ ሺ የሚቆጠር በሬ ለዚህ እጥረት ከፍተኛ ምክንያት ነው:: በእነዚህና በሌሎች ልዩ ልዩ ምክንያቶች በአገሪቱ ጠቅላላ የበሬ እጥረት በመኖሩ ይህ እጥረት ደግሞ በተራው ቢያንስም በበዛም በገበያ የሚወጣውን በሬ ዋጋ እንዲጨምር ስላደረገውና ሰፊው ድሀ አርሶ አደር ደግሞ ከላይ እንዳመለከትነው የገንዘብ አቅሙ ዝቅተኛ ስለሆነ ምርቱን እንደፈለገው ሊጨምር የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ገብቷል::

አሁንም ሚካኤል አስቶል ስለወለጋ ገበሬዎች ያጠናውን ጥናት ወስደን ለምሳሌ ያህል ብንመለከት እንዲህ ይላል:—

''የመሬት አዋጁ ከመታወጁ በፊት የአርሶአደሩ 2/3 በበሬ በኩል ራሱን የማይችል ነበረ:: ከአዋጁም በኋላ በሳቦቶች በልዩ ልዩ መንገዶች በቀንድ ከብቶች ላይ እልቂት ስላደረሱ የበሬ እጥረት ተባባሰ:: እስከ 1977 ዓ ም መጀመሪያ ድረስ የበሬ እጥረት የአርሶአደሩ አይነተኛ ችግር ሆኖ ቆይቷል::'' (ገጽ 39–41)::ከዚያ ወዲህ ሁኔታው ተባባሰ እንጂ አልተሻሻለም::

በጭሩ ሰፊው አርሶ አደር የሚጠቀምባቸው የእርሻ መሣሪያዎችና ዘዴዎች በጣም ወደኋላ የቀሩ ከመሆናቸውም ሌላ እንደልብ አለመገኘታቸው በአይነትም በመጠን ለማሻሻል የቴክኒካል ሆነ የማቴሪያል ችግር ስላለበት፣ ችግሩንም ለማቃለል በቂ ወይም ምንም መንግሥታዊ ድጋፍ ስላልተሰጠው ከእለት እለት ከዓመት ዓመት እያደገ የሚሄደውን የህብረተሰቡን የምግብ ሸቀጥ ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ምርት ሊያመርት አልቻለም:: የምግብ



የምግብ ሸቀጥ የምግብ ሸቀጥ ምርት እድገት ከህብረተሰቡ ፍላጎት እድገት ጋር እኩል ወይም ተደምሮ እንዲያድግ ካላስቻሉት ብሎም የምግብ እጥረት እንዲፈጠር ካደረጉት ብዙም ምክንያቶች ዋናው ይኸ የእርሻ መሣሪያዎች በአይነትም ሆነ በመጠን በዝቅተኛ ደረጃ መገኘት ነው::

ይህ ሲባል ግን በኢት ያለው የእርሻ ዘርፍ ሁሉ የሚገለገለው በጥንታዊ የእርሻ መሣሪያዎችና ዘዴዎች ነው ማለት አይደለም:: በመንግሥት ይዞታ ስር ያሉትን የመንግሥት እርሻዎች ብንወስድ በዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች፣ ዘዴዎች፣ አስተዳደሮች፣ ወዘተ የሚሰሩ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ይሁን እንጂ እነዚህ እርሻዎች ለውጭ አገር ገበያ የሚውሉ የእርሻ ሸቀጦች ማምረት ላይ ከፍተኛ አተኩሮ በማድረጋቸውና ለአገር ውስጥ ጥቅም በተለይ ለህዝባዊ ቀጥታ ጥቅም የሚውሉ ማምረቱን ዝቅተኛ ቦታ በመስጠታቸው የህብረተሰቡን የምግብ ምርት በማሳደጉ በኩል የተጫወቱት ሚና እምብዛም ነው:: እንዲያውም በአንዳንድ ጉናዊ ተጽእኖቻቸው አሉታ ሚና ተጫውተዋል::

## እንደ ለውጥ ጥያቄ

አርሶ አደሩ ባለው የእርሻ አውቀት መሣሪያ የሚያመርተውን እህል ወይም ሌሎች የምግብ ሸቀጦች ለሆዱ የሚያስፈልገውን አስልቶ ከጎተራው ካስገባ በኋላ የተረፈውን እንካችሁ ብሎ በነፃ አያድልም:: የአርሶ አደሩ ትርፍ እህል በሌላ ሥራ ለሚኖረው የከተማው የህዝብ ክፍል የሚደርሰው በለውጥ ነው:: እዚህ ላይ ለውጥ የሚለው ቃል የገበያ ጥያቄ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

አርሶ አደሩ የተረፈውን እህል ገበያ አውጥቶ የሚሸጠው ከምግብ ውጭ የሆኑትን ፍላጎቶቹንና ህብረተሰባዊ ግዴታዎቹን ለማሟላት ነው:: ህብረተሰባዊ ግዴታዎች የሚለው ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ግብሮችን ያመለክታል:: ከምግብ ውጭ የሆኑትን ፍላጎቶች የሚለው ደግሞ እርሱ ሊያመርታቸው የማይችላቸውን ለምሳሌ የእጅ ጥበብ ሥራ ውጤቶች፣ ለቤት እገልግሎት የሚውሉ የኢንዱስትሪ እቃዎች፣ የእርሻ መሣሪያዎች፣ ወዘተ ሸቀጦች ያጠቃልላል:: እነዚህን በሁለት ክፍሎች ያጠቃለልናቸውን ግዴታዎችና ፍላጎቶች ለማሟላት አርሶ አደሩ ገንዘብ ያስፈልገዋል:: በመጀመሪያ ገንዘብ፣ ገንዘብ ካገኘ በኋላ ደግሞ እነዚህን ሁለት ሁኔታዎች ለማሟላት ሲል በሚያካሂደው የልውውጥ ተግባር ነው፣ የአርሶ አደሩ እህል ለማያርሰው የህብረተሰብ ክፍል የሚደርሰው:: እዚህ ላይ ገንዘብ የልውውጥ/በእርሻና በኢንዱስትሪ ሸቀጦች መካከል/ማካሄጃ እንጂ ግብ አለመሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው::

አርሶ አደሩ ህብረተሰባዊ ግዴታዎችን ለማሟላት ብዙና በየጊዜው እህል መሸጥ አያስፈልገውም፡፡ አብዛኛዎቹ ግዴታዎች የተወሰኑና የታወቁ ስለሆነ የተወሰነ እህል በመሸጥ ሊያጠናቅቃቸው ይችላል፡፡ ስለሆነም አርሶ አደሩ ህብረተሰባዊ ግዴታዎችን ለማሟላት በሚያካሂደው የልውውጥ ድርጊት ለማያርሰው ከተሜው ክፍል የሚደርሰው የምግብ ሸቀጥ የተወሰነና በጣም አነስተኛ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ግን የአርሶ አደሩ ፍላጎቶች ብዙና ባያቋርጡ የሚያድጉ ናቸው፡፡ በክፍል አንድ ውስጥ የሰዎች ፍላጎቶች በአይነትና በመጠን በየጊዜው ባያቋርጡ እንደሚያድጉ አጥንተናል፡፡ አርሶ አደሩ ከበሬ በትራክተር፣ ከተራ ብረት ከጠራ ብረት በተሰራ ማረሻ፣ ከደማ በበሬ ኩትራ የተመረጠ ዘር፣ ከተቃጠለ አፈር ዘመናዊ ማዳበሪያ፣ ወዘተ በመጠቀም ማረስን፣ ከመራብ መጥገብን ብቻ ሳይሆን የተሻለ መብላትን ከመታረዝ መልበስን ብቻ ሳይሆን የተሻለ መልበስን ጠለላ አጥቶ ከመንከራተት በቤት መኖርን ብቻ ሳይሆን የተሻለ መልበስን፣ ጠለላ አጥቶ ከመንከራተት በቤት መኖርን ብቻ ሳይሆን በተሻለ ቤት መኖርን፣ ወዘተ ይፈልጋል፡፡ እነዚህን ውስብስብና እያደጉ የሚሄዱትን ፍላጎቶችን ለማሟላት ሲል ደግሞ ባያቋርጥ በገበያ አውጥቶ የሚሸጠውን ምርት ያሳድጋል፡፡ የሚሸጠውን ሲጠምርና የሚፈልጋቸውን ሲያገኝ ደግሞ ምርቱን ጠቀሳሳ የኑሮ ሁኔታውን ያሻሽላል፡፡ ይኸ ደግሞ በተራው እንደገና የሚሸጠውን እንዲጨምር ያደርገዋል፡፡ እንደዚህ እያለ በማያቋርጥ መንገድ የአርሶ አደሩ ፍላጎቶች በዚያም ምርትና በገበያ ላይ አውጥቶ የሚሸጠው ብሎም የማያርሰው ክፍል የሚያገኘው የምግብ ሸቀጥ እየጨመረ ይሄዳል፡፡

በጥሩ ለማያርሰው ለከተሜው ከአርሶ አደሩ የሚደርሰው እህል ወይም ሌሎች የምግብ ሸቀጦች መጠን ወይም እድገት አብዛኛውን ጊዜ አርሶ አደሩ በራሱ የማያመርታቸው ሸቀጦች በማግኘት ገላዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት በህብረተሰቡ ውስጥ የሚፈጸመው የልውውጥ ድርጊት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የሚፈልገው ሸቀጥ ለእርሱ ተቀባይነት ባለው ዋጋ በገበያ ባያቋርጥ የሚገኝ ከሆነ ይኸን ሸቀጥ ለመግዛት ባያቋርጥ የእርሻ እያዎች ይሸጣል ብሎም የከተሜው ኗሪ የሚያስፈልገውን የምግብ ሸቀጥ ያገኛል፡፡ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ካላገኘ አርሶ አደሩ አይሸጥም፡፡ ካልሸጠ ደግሞ ከተሜው እህል አያገኝም፡፡

በኢት ያለውን ሁኔታ ስንመለከት የልውውጡ ሁኔታ የተዛባ በመሆኑና በተቀነባበረ መንገድ ባለመካሄዱ ለተፈጠረው የምግብ ሸቀጥ እጥረት አንዱ ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በመጀመሪያ በገጠሩ ክፍል/አርሶ አደሩ አብዛኛውን የልውውጥ ድርጊቱን በሚፈጽምበት/ከፍተኛ የሸቀጥ እጥረት/በዚህ ጥያቄ ላይ በኋላ እንመለስበታለን/ አለ፡፡ አርሶ አደሩ ለመግዛት የሚፈልጋቸው እንደ ጨው፣ ስኳር፣ ሳሙና፣ ምሳጥ፣ መርፌ፣ ዶማ፣ ጣቃ፣



ወይም የተሰሩ ልብስ፣ ጥለታ ጥለት፣ ባሙና፣ ሬዲዮ፣ በትሪዶንጋይ፣ ጥላ፣ ጫማ፣ ጭልፋ፣ ብርጭቆ፣ ምስማር፣ የቤት ቆርቆሮ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ለእለት ተእለት ጥቅምና እንዲሁም ለእርሻ መጌልገያ የሚውሉ ሸቀጦች አዘውትረው የማይገኙ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ቢገኙም ለይስሙላ እንጂ የአርሶ አደሩን ፍላጎት በሚያረካ መጠን አይደለም፡፡

ያም ሆነ ይህ በገጠሩ የደረሰው የኢንዱስትሪ ሸቀጥ እጥረት በተዘዋዋሪ መንገድ የምግብ ሸቀጦች እጥረት እንዲኖር ፈጥሯል፡፡ እላይ እንደጠቀስነው አርሶ አደሩ የተረፈውን እህል ወይም ሌሎች የምግብ ሸቀጦች በገበያ አውጥቶ የሚሸጠው ለእለት እለት ጥቅምና ለማምረቻ የሚውሉ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ለመግዛት ስለሆነ የእነዚህ ሸቀጦች በገበያ መጥፋት የመሸጥ ፍላጎቱን አዳክሞታል፡፡ ለእንዲሁ ለምን ይሸጣል?

በዚሁ በልውውጥ ሂደት ውስጥ የተያያዘ አርሶ አደሩን የመሸጥ ፍላጎት ያዳከመ አንድ ሌላ ምክንያት ማንሳት ይቻላል፡፡ ይኸውም የእርሻና የኢንዱስትሪ ሸቀጦችን ዋጋ የሚመለከት ነው፡፡

የሁለቱ ሸቀጦች ዋጋዎች ያልተመጣጠኑ ናቸው፡፡ የኢንዱስትሪ ከእርሻ ሸቀጦች ጋር ሲወዳደር በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ዋናው ምክንያት የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት ሲሆን "ኢስፔኩሌቲቭ" የሚያደርጉና ''አሻጥረኛ'' ነጋዴዎች፣ አውሀሪ ቢሮ ክበርቴዎችና በመንግሥት በኩል የተቀነባበረ የዋጋ ቁጥጥር አለመደረጉ ሌሎች ምክንያቶች ናቸው፡፡ የኋላ ኋላ የተደረገውም የዋጋ ቁጥጥር የኢንዱስትሪ ሸቀጦች የሚያስሁና የእርሻዎችን የሚቀንስ በመሆኑ ችግሩን አባብሶታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ አርሶ አደሮች ለአንዱ ቀንጣት የኢንዱስትሪ ሸቀጥ ብዙ እህል የሚከፍሉበትና ተመረው እህል አለ መሸጡን ግን ሁኔታ መጠበቅን የሚመርጡበት ሁኔታ ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል፡፡ የኋለኛውን በመምረጣቸውም የተዛባው የልውውጥ ስርአት ለምግብ ሸቀጦች እጥረት ምክንያት ሆኗል፡፡

አሻጥረኛ ነጋዴዎችና ቢሮክራቶች በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ የሚፈጥሩትን እጥረት ለመቋቋም የተመሰረቱት የአምራቾችና የተጠቃሚዎች የህብረት ሱቆችም ከእነርሱ ቁጥጥር ውጭ የሆኑትን ችግሮች በተለይ የማመሳለሽ፣ የቢሮክራሲ ጣጣዎች ወዘተ ለመፍታት ባለመቻላቸውና ጊ ወመ የእርሱ ተቀጥያ ለማድረግ ባደረሰባቸው የተቀነባበረ መገፋ በመደከማቸው ምንም አይነት አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ገብተዋል፡፡

እንደ ክፍፍል /እንደ አጠቃቀም/ ጥያቄ

አርሶ አደሮች ከአመረቱት ልዩ ልዩ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት በገበያ አውጥተው የሚሸጡትንና በግብርና ለማይከፈለው ተጠቃሚ የሚደርሰውን የምግብ ሸቀጥ ክፍፍል ወይም

አጠቃቀም በጥሩ አንፃልከት፡፡

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ አርሶ አደሮች ለሆኑቸው የሚያስፈልጋቸውን ይዘው ለል ዩ ልዩ አሳማዎች የሚሸጡት የምግብ ሸቀጥ ለልዩ ልዩ ጥቅም ይውሳል፡፡ በልዩ ልዩ ዘርፎች ይከፋፈላል ማለት ነው፡፡ ለማያርሰው የህብረተሰብ ክፍል/በምርት ውስጥ በቀጥ ታ ለሚሳተፍ/ለምሳሌ ወዘአደሩ/ወይም ለማይሳተፍ/ለምሳሌ ቢሮክበር ቴ፣ ከበር ቴ፣ ወታደር ወዘተ/ ቀለብ፣ ለልዩ ኍሳያዊ ጥቅሞች/ታሳሳቂ ገበሸዎች ወይም ፀርነቶች፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ እቃ፣ ለውጭ አገር ገንዘብ፣ ሊውል/ሊከፋፈል ይችሳል፡፡ የተቀነባበረ ፕላን በሌለ በትና ክፍፍሉ በነፃ ገበያ ህግጋት የሚገዛ ከሆነ በልዩ ልዩ ዘርፎች መካከል የተዛባ ክፍፍል ይፈጠሬል፡፡ ለምሳሌ ብዙ ለውጭ ንግድ ቢውል በአገር ውስጥ ሳለው የማያርሰው ክፍል ተለብ የሚተርፈው ነበስ፡፡ ወይም ለልዩ ልዩ ኍዚያዊ ዱግቦች ፀርነቶች ያለአ ግባብ ከፍተኛ የምግብ ሸቀጥ ቢባከን ለብዙሃኑ ሸምቶ አዓሪ የኢሰት ተለት ኑሮ ማስኬጃ የሚተርፈው ያንበል፡፡ ዛሬን ወትት የምግብ ሸቀጥ እጥረት በህብረተሰብ ውስጥ ይፈጠ ራል፡፡

በኢት ለኍዜያዊ ቅሞች(ታሳሳቂ ዱግቦች፣ ፀርነቶች ወዘተ)በለፉት ዓመታት በተ ለይም ባለፈው አመት የጠፋውን የምግብ ሸቀጥ ብንወስድ ከፍተኛ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በፀርነት የተሰፉትን ኅዘዙ መቶ ሺ የሚቆጠሩትን ወታደሮችና ዘማቾች እንደሁም የተሰደ ትትን ለመቀለብ የተደረገው ብቻ የሊሳውን ሸምቶ አዓሪ የምግብ ሸቀጥ ማግኘት ሁኔታ የሚያናጋ ነበር፡፡ ፀርነቱ የተደረገው ዱልዱል ትክክል ቢሆንም በዚህ ሥራ ውስጥ በ ተከማሩ በቢሸልና ሚሊታሪ ቢሮክራቶች አሸጥር የገዱላሽነት አጠቃቀም የተነበ ለወታደሩ፣ ለዘማችና ለስደተኛው ነይደርስ በየሚዓው እየበሰበሰ ወይም እየተደፋ የተበላሸው የምግብ ሸቀጥ(በሰሎ/ባይበሰል)በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ ቢያንስ ለአንድ አመት ያህል በተካሄደው የእናት አገር ጥሪ ታሳሳቂ ዱግቦች በሚገነገሸገሸ ሁኔታ የተደረገው መረን የለሽ የምግብ ሸቀጥ አጠቃቀም ኍዜያዊ ቢሆንም በአገሪቱ የምግብ ሸቀጥ ሳይ በአጭር ኍዜ የማይስተካከል መዛባት አስከትሏል፡፡ ''ሁሉም ለድግሱ''በሚል መፈክር በየቦታው የተደረገው የጥሬጥሬ አህሎ ች የቀባቶች፣ የቀመማቀሞዎች፣ የአትክልቶች ወዘተ አይን አውጣ ሟጠጣዎች በዚያውም ኍዜ ሆነ በኋላ የሸምቶ አዓሪውን የምግብ ሸቀጥ የማግኘት እዱል አጁነ እናገኘውታል፡፡

## 2፡2፡2 የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ በኢንዱስትሪው የኢኮኖሚ ክፍል የሚመረቱትን ለእለት ተእለት ጥቅምና ለማምረቻ የሚውሉትን ሸቀጦች ሁኔታ በአጭሩ እንመለከታለን፡፡



የኢንዱስትሪ ሸቀጥ እጥረት እንደሁኔታውና እንደቦታው በመጠን ከምላ ጉደል እ ልፍ እልፍ ቢለያይም አገር አቀፍ ነው፡፡

በገጠሩ ያለው የሳምበ፣ የሰሙና፣ የጠው፣ የስኳር፣ የመርፌ፣ የልብስ ወዘተ እ ጥረት በከተማም አለ፡፡ የብርዱልብስ፣ የአንበሳ፣ የጧማ፣ የቤት እቃዎች (household utensils) በጥሩ ከኢንዱስትሪ የተሰሩ የእለት ተእለት ጥቅም ሸቀጦች በተፈለጉበ ት ቦታ ሁሉ እንደልብ አለመገኘት ብቻ ባይሆን አስከነጭራሹም አይገኙም፡፡ ከዚሁም ሌ ሳ የማምረቻ መሣሪያዎች ሙሉ ለሙሉም ሆነ በመገጣጠሚያ ደረጃ እጥረት ያለው በየቦታው፣ በአገሪቱ በሙሉ ነው፡፡

ይህ ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት በተራው ጠቅላላ የዋጋ ንረር በማስከ ተሉ በሰሬው ሠርቶ አደር ኑሮ ሳይ ከፍተኛ ውድቀት አስከትሏል፡፡ በዚህ ችግር ያልተ ጉዱት የገዥው መደብ አባሎች፣ የከፍተኛ ቢሮ ከበርቴዎች ከፍተኛ ንዑስ ከበርቴዎችና ነ ጋዴዎች ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ የህብረተሰቡ ክፍሎች የፖለቲካ ስልጣናቸውና የገንዘብ ገቢአቸው ስለሚፈቅዱሳቸው የውጭ አገር ተወሳጆች ከሚገዙባቸው ሸቀጦች ሁልኍሌ ታሽቀው ከሚገኙባቸው ታሳሳቂ ሱቆች የፈለጉትን መጠን በፈለጉት ኍዜ የሆነውን ዋጋ ከፍለው ሊገዙ ስለሚችሉ ምንም ችግር የለባቸውም፡፡ የፖለቲካ ስልጣናቸውና የገንዘብ ገቢአቸው አብዛኛውን ኍዜ በሸቀጥ እጥረት ተራቀተው ከሚገተሩት የህብረት ሱቆች ብቻ እንዲገዙ የሚያስገድዳቸው ሠርቶ አደሮች ግን የቀንና የሌሊት ልብስ አጥተው ወይም መገዛት አቅቷ ቸው፣ የሚታረዙ፣ መታጠቢያና ማጠቢያ ሳሙና አጥተው አዱፈው የሚኼቀኙለሩኖስ የሚሆን ሳ መብ አጥተው በጠለማ ውስጥ የሚቀመጡ፣ ወዘተ ብዛታቸው ቀጥር ስፍር የለውም፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ታሳሳቂ ኢንዱስትሪዎች ለአድገት ''ጉጉና''''አብዮታዊ''በሆነ መንግሥት ቀጥጥር ሥር ሆነው እንዴት ይህን ያህል ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት ሊፈጠር ቻለ? ይህን ጥያቄ በመመለስ በአሁኑ ወቅት በኢት በደረሰው የኢንዱስትሪ ሸቀ ጦች እጥረት ምክንያቶችን በጥሩ እናቀርባለን፤፡

እንደ ምግብ ሸቀጥ እጥረት የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት ምክንያቶችም በልውውጥ በክፍፍል/አጠቃቀምና በምርት ጥያቄዎች ስር የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥያቄዎች ስር የሚጠቃለሉት ምክንያቶች ለምግብም ሆነ ለኢንዱስትሪ ሸቀጦች አንድ ዓይነት ስለሆኑ እንደገና እዚህ ማንሳት ፉጋሚ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ቀና በሆኑት በምርት ጥያ ቄ ስር በሚጠቃለሉት ምክንያቶች ሳይ እናተኩራለን፡፡

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ በልውውጥ ሂደት ውስጥ የሚገተሰተሰውም ሆነ ለልዩ

ልዩ አላማዎች በልዩ ልዩ ዘርፎች የሚከፋፈለው የኢንዱስትሪ ሸቀጥ በዚያ ህብረተሰብ ውስጥ ባሉት ኢንዱስትሪዎች መጠን አይነትና አድገት ይወሰናል:: የኋለኛው ደግሞ በተራው በኢንዱስትሪ በምርት ላይ በሚውለው ካፒታል ገንዘብ፣ በሚገለገልባቸው የማምረቻ የሥራ መሣሪያዎች፣ በሂደት ውስጥ በሚሰተፉት ሰዎች ወዝአደሮች የቴክኒካል እውቀትና የፖለቲካ ንቃት እንዲሁም በማመራበት የአስተዳደር ችሎታና ብቃት ይወሰናል::

በኢት ውስጥ ኢንዱስትሪ አዲስ የምርት ክፍል ነው:: በአድገቱም በጣም ዝቅተኛ ነው:: ከአገሪቱ ጠቅላላ ዓመታዊ ምርት የሚይዘው 10—12 በመቶ ብቻ ነው:: ያሉት ኢንዱስትሪዎች ከአብዮቱ በፊት ከነበረው ስርአት የተወረሱት ብቻ ሲሆኑ በቁጥራቸው በጣም ትንሽ ናቸው:: ከአብዮቱ ወዲህ አዚህ ግቡ የሚሏቸው አዲስ ኢንዱስትሪዎች አልተቋቋሙም:: ለዚህ ለኢንዱስትሪዎች መጠን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ለኢንዱስትሪዎች በቁጥር አለመስፋፋት ዋናው ምክንያት ለኢንዱስትሪው የኢኮኖሚ ክፍል የሚውለው የህብረተሰቡ ካፒታል በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ነው:: መንግሥቱ በኢንዱስትሪው ክፍል ላይ ብዙ ካፒታል/ገንዘብ/አላሰማራም ማለት ነው::

በቁጥር ማነሳቸው ብቻ ሳይሆን ያሉት ኢንዱስትሪዎች የሚገለገሉባቸው የሥራ መሣሪያዎች ያረጁ ወደኋላ የቀሩና፣ ጉልበትና ጊዜ የሚጨርሱ ናቸው:: እርግጥ በኢት የተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎች አብዛኛዎቹ የ20—የ25 ወይም ከዚያ በታች እድሜ ያላቸው ናቸው:: ስለሆነም የሚገለገሉባቸው የምርት መኪናዎች ያረጁ ወደኋላ የቀሩ፣ ጉልበትና ጊዜ የሚጨርሱ ሳይሆን ዘመናዊ እንዲሁም ጉልበትና ጊዜ የሚቆጥቡ መሆን ነበረባቸው:: የፊተኛው ሊሆንና የኋለኛው ሳይሆን የቻለው አሁን ያሉት ኢንዱስትሪዎች ከሞላ ጎደል ሁሉም የተቋቋሙት በውጭ አገር ከበርቴዎች ስለነበረ ነው:: እነዚህ የውጭ አገር ከበርቴዎች ዋና ፍላጎታቸው በዝቅተኛ ካፒታል/ገንዘብ/በሌላ አነጋገር በዝቅተኛ የምርት ዋጋ ከፍተኛ ትርፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጋበስ ስለነበረ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁ ዘመናዊ የማምረቻ መኪናዎች በሥራ ላይ ለማዋል አልፈለጉም:: ይኸን በማድረግ ፋንታ በአውሮፓ ውስጥ ብዙ አመት ያገለገሉና ሊጣሉ የደረሱ የተጠጋገኑ አሮጌ የማምረቻ መኪናዎች ገዝተው ተከሉ:: አፍኘ የማይሞሉት የኢት ኢንዱስትሪዎች የሚንቀሳቀሱት በእነዚህ በአሁኑ የኢንዱስትሪ ዘመን ''ጥንታዊ''/ፕሪሚቲቭ/ በሆኑ የማምረቻ መኪናዎች ነው:: በምርት ማምረቻ መኪናዎችና በቴክኒካል እውቀት ወደኋላ መቅረት የተነሳ የወዝ አደሩ የማምረት ችሎታም/ሊበር ፕሮዳክቲቪቲ/በጣም ዝቅተኛ ነው:: በመሆኑም የተወሰነ ሸቀጥ ለማምረት የሚፈጀው ጊዜና ጉልበት ጣም ከፍተኛ ነው::



ይህ ብቻ አይደለም በጣም ከማርጀታቸው የተነሳ አዘወትረው ይበላሻሉ:: ለማደስ የሚያስፈልጉት መገጣጠሚያዎች ደግሞ በአገር ውስጥ ስለማይመረቱ በገበያ ላይ እንደልብና በቀላሉ አይገኙም:: ከውጭ አገር መምጣት አለባቸው:: ከውጭ አገር ማስመጣቱ ደግሞ የሚወስደው ጊዜ አጭር አይደለም:: በዚህ ምክንያት እየተበላሹ ከሥራ ውጭ ሆነው የተገተሩት የማምረቻ መኪናዎች ብዙ ናቸው::

በመገጣጠሚያ ብሎም በማምረቻ መሣሪያዎች እጦት ብቻ ሳይሆን በጥሬ እቃዎችም በአጭር ጊዜ ወይም ለረጅም ጊዜ ሥራቸውን በከፊልም ሆነ በሙሉ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎች ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ የምግብ ቅባት/ዘይት/የሚያወጡ ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች የቅባት እህሎች ወደ ውጭ አገር ገበያ በብዛት ስለሚላኩ በአገር ውስጥ ገበያ ላይ ባለመገኘታቸው በብዙ የዘይት ፋብሪካዎች ሳይወዱ በግድ ሥራቸውን አቁመዋል:: የጥቄትና የዳቦ መጋገሪያ ፋብሪካዎችም እንደዚሁ::

በጦርነትም ምክንያት በተለይ (1/3 የሚሆኑት የአገሪቱ ኢንዱስትሪዎች በሚገኙበት በኤርትራ ክፍለ አገር በተካሄደው) ብዙ ፋብሪካዎች ከሥራ ውጭ እንዲሆኑ ተደርገዋል::

ከዚህም ሌላ ኢንዱስትሪዎች የሚተዳደሩት በፊውዳል ቡርዥዋ ቢሮክራሲያዊ የአስተዳደር ዘዴ ነው:: ወዝአደሩ በአስተዳደር ውስጥ ያለው ተሳትፎ ዜሮ ነው:: ለመሳተፍም የሚያደርገው ትግል እየተጨቆነ ነው:: ፈላጭ ቆራጮች ምርት በመጨመር በይጨመር ግድ የሌላቸው አንዲያውም በሚቻላቸው መንገድ ሁሉ ምርት አንዳያድግ የሚያሻጥሩ ''ቴክኖክራቶች'' ናቸው:: ወዝአደሩ የአስተዳደር ተሳትፎ ማጣቱ ብቻ ሳይሆን በሥራው ሁኔታና በደመወዙ እድገት ለስም እንጂ በእውነት አይነተኛ የሆነ ለውጥ አላገኘም:: እንደነገሩ ዝቅተኛ ደመወዝ በወር አምሳ እንዲሆን ታውጇል:: ኮዓርው መጠነኛ ለውጥ ተደርጋል ማለት ነው:: ይህ ለውጥ በምግብና ሬሱ በሚያመርታቸው የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ዋጋ መናር የተነሳ ወዝአደሩ በአሁኑ ወቅት ለመኖር ከሚያስፈልገው ወጭ ጋር ሲነፃፀር ለስም የተደረገ እንጂ እውነተኛ ለውጥ አይደለም:: ከኑሮ ዋጋ መናር ጋር ሲወዳደር ደመወዝ ቀንሷል ለማለት ይቻላል:: የሥራ መገልገያ መሣሪያዎችን ለማሻሻል አዲሶች ለመፍጠርና ምርትን ለማሳደግ ያለው ችሎታ ታፍኗል ማለት ነው::

በጭሩ ከላይ እንደጠቀስነው በአሮጌው ስርአት የተወረሱት ኢንዱስትሪዎች በቁጥራቸው አነስተኛ በመሆናቸውና አዲሱ መንግሥትም ቁጥራቸውን ለመጨመር በኢኮኖሚው የኢንዱስትሪ ክፍል ላይ ብዙ ካፒታል ባለማሠማራቱ፣ ያሉትም ኢንዱስትሪዎች የሚገለገሉባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች በጣም በማርጀታቸው ጊዜና ጉልበት የሚፈጁ በመሆናቸው ብሎም የወዝአደ

ሩ የማምረት ችሎታ/ፕሮዳክቲቪቲ በማሳደጉ በጣም በረጅና የምርትን እድገት በሚያፋጥር በቢሮክራሲ አስተዳደር ስር ስለሚመራና የወዝአደሩ ሞራል ባለው ጥኖና በመዳከሙ በኪት ውስጥ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ምርት የህብረተሰቡን ፍላጎት ሊያሟላ በሚችል ደረጃ ሊያድግ አልቻለም፡፡ ዛሬ አገሪቱ ውስጥ ለደረሰው የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት ዋናው ምክንያት እንደሚባለው የነጋዴዎች ወይም የቢሮክራቶች ''አሻጥር'' አይደለም፡፡ ከላይ በጠቀስናቸው ምክንያት የምርት አለማደግ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን በልዩ ልዩ ደረጃዎችና ዘርፎች የተፈጸሙት ''አሻጥሮች'' ችግሩን አላባበሱትም ማለት አይደለም፡፡ ለችግሩ መፈጠር ዋና ምክንያቶች አይደሉም፤ ሊሆኑም አይችሉም ማለት ነው፡፡

## 2፡2፡3 የውጭ ንግድ ችግር

አንድ ህብረተሰብ የሚያመርተውን የሚሸጠው በሁለት ገበያዎች ላይ ነው፡፡ አንደኛው አለም አቀፍ ሲሆን ሌላው የአገር ውስጥ ገበያ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረገው የሸቀጥ ልውውጥ ንግድ/ገበያ/ ያ ህብረተሰብ ለኢኮኖሚው ተጨማሪ ሀብት የሚሆን የውጭ ምንዛሬ ወይም ጥሬ ገንዘብ ማግኘት ብቻ ሳይሆን በራሱ የማያመርታቸውን ለልዩ ልዩ አላማዎች የሚያስፈልጉትን ሸቀጦችም ያገኛል፡፡

የአንድ ህብረተሰብ የውጭ ንግድ ይዘት፣ የደንበኞች ብዛት፣ ለህብረተሰቡ የሚያስገኘው የውጭ ምንዛሬ መጠን፣ በእድገት ላይ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ያ ህብረተሰብ በደረሰበት የእድገት ደረጃ ይወሰናል፡፡ የህብረተሰቡ እድገት ወደኋላ የቀረና መሠረቱ የእርሻ ኢኮኖሚ ከሆነ በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ለሽያጭ የሚያቀርባቸው ሸቀጦች የእርሻ ውጤቶች(ቡና፣ ጥጥ፣ ስኳር፣ ሸይቅጠል፣ ፍራፍሬ፣ ጥራጥሬዎች፣ ወዘተ)፣ የደን ውጤቶች (እጣን፣ ጥሬ ጎማ፣ ለጣውላ የሚውሉ እንጨቶች፣ ወዘተ)፣ የማእድን ውጤቶች(ወርቅ፣ መዳብ፣ ነዳጅ ዘይት፣ ወዘተ)ወይ ሙሉ በሙሉ ጥሬ እንደሆኑ ወይም በግማሽ ተፈብርከው (Semi-processed) ይሆናሉ፡፡ እነዚህ የጥሬ እቃ ሸቀጦች በመባል ይታወቃሉ፡፡ ህብረተሰቡ በጣም ያደገና መሠረቱ የኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ከሆነ ደግሞ በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ለሽያጭ የሚያቀርባቸው ሸቀጦች ጥሬ እቃዎችም በኖሩባቸው አብዛኛውን ጊዜ የኢንዱስትሪ ውጤቶች (ትራክተሮች፣ ተሽከርካሪዎች፣ የጦር መሣሪያዎች፣ የተጠቃሚ ሸቀጦች ኮንቢውተር ጉዳስ ወዘተ)ይሆናሉ፡፡ እነዚህ የተፈበረኩ ሸቀጦች በጥሬ እቃዎች ይለወጣሉ ማለት ነው፡፡

የሁለትን ሸቀጦች ዋጋዎች ወስደን የተመለከትን እንደሆ የጥሬ እቃዎች ዋጋ በጣም ዝቅተኛ የኢንዱስትሪ(የተፈበረኩ) እቃዎች ዋጋ ግን በጣም ከፍተኛ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የተፈበረኩ እቃዎች ዋጋ ግን ሳያቋርጥ በከፍተኛ ፍጥነት



ዘሁሌ ሁሌ እየጨመረ ሲሄድ የጥሬ እቃዎች ዋጋ ግን አንድ ጊዜ ከፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዝቅ እያለ አብዛኛውን ጊዜ ባለበት የሚረግጥ ቢመስልም ከፊተኛው እድገት ጋር ሲነፃፀር እያሽቆለቆለ የሚሄድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህም ምክንያት በሁለቱ ሸቀጦች አቅራቢዎች መካከል የሚደረገው የንግድ ልውውጥ ያልተመጣጠነ ይሆናል፡፡ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች አቅራቢዎች በጥቂት ሸቀጦቻቸው ብዙ የጥሬ እቃ ሸቀጦች ሊገዙ ሲችሉና ይህም ከአመት አመት እየተሻሻለ ሲሄድላቸው የጥሬ እቃ ሸቀጦች አቅራቢዎች ግን በብዙ ሸቀጦቻቸው ጥቂት የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ለመግዛት ሲገደዱ ይህም ከአመት አመት እየተባባሰባቸው ይሄዳል፡፡

እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በኢንዱስትሪ ሸቀጦችና በጥሬ እቃ ሸቀጦች አቅራቢዎች መካከል የተዛባ ልውውጥ ያስከትላል፡፡ የተዛባው ልውውጥ ደግሞ በተራው ለፊተኞች የውጭ ምንዛሬ መጠን የውጭ ንግድ ገቢ እየጨመረ፣ ብሎም የንግዱ ሚዛናቸው እየተሻሻለና የውጭ ንግድ በኢኮኖሚያቸው ላይ የሚኖረው አስተዋጽኦ እያደገ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ የኋለኞች ግን የውጭ ምንዛሬ መጠን የውጭ ንግድ ገቢ እየቀነሰ ብሎም የንግዱ ሚዛናቸው እየተበላሸ፣ እዳቸው እየጨመረና የውጭ ንግድ በኢኮኖሚያቸው ላይ የሚኖረው አስተዋጽኦ አሉታ እየሆነ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡

ሁለቱ ሸቀጥ አቅራቢዎች በአለም አቀፍ ገበያ ላይ የሚኖራቸውን የደንበኞች ብዛት የተመለከትን እንደሆ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች አቅራቢዎች ብዙ ደንበኞች ብሎም የበለጠ የማማረጥና የመከራከር እድል ሲኖራቸው የጥሬ እቃ ሸቀጦች አቅራቢዎች ግን በጣም የተወሰኑ አብዛኛውን ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ዋና ደንበኞች አገዳሷቸው ብሎም ምንም ዓይነት የማማረጥና የመከራከር እድል እንደሌላቸው እንመለከታለን፡፡ የጥሬ እቃዎች አቅራቢዎች የውጭ ንግድ ደንበኞቻቸው በተለይ ትልቅ ደንበኞቻቸው በቁጥራቸው በጣም ውስን፣ ለንግድ የሚያቀርቧቸው ዋና ዋና ሸቀጦቻቸው ከአንድ ወይም ከሁለት አይነት የማይበልጡ በመሆናቸውና የሚሸጡበትና የሚገዙበት ዋጋ የሚወሰነው በነዚሁ ጥቂት ደንበኞቻቸው ስለሚሆን የንግዳቸውና የኢኮኖሚያቸው እድገቶች በእነዚህ ጥቂት ደንበኞቻቸውና ጥሬ እቃቻቸው ላይ ይመካሉ፡፡ እርግጥ አንዳንድ ጥሬ እቃ ሸቀጦች አቅራቢዎች ብዙ ደንበኞች/ከፍተኛ የማማረጥና የመከራከር እድል) አላቸው፡፡ለዚሁ ጥሩ ምሳሌ የነዳጅ ዘይት አቅራቢዎች ናቸው፡፡

በኢኮኖሚ እድገቷ ኢት በጣም ወደኋላ የቀረች አገር ናት፡፡ ዋናው የኢኮኖሚዋ መሠረት እርሻ ሲሆን በእድገቱ ወደኋላ የቀረ ነው፡፡ በኢኮኖሚ እድገቷ ወደኋላ የቀረ በመሆኑ የውጭ ንግዷም ያልተስፋፋና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ እንደማንኛውም ወደኋላ የቀረች አገር ኢት በአለም አቀፍ ገበያ ላይ ለሽያጭ የምታቀርባቸው

ሸቀጦች የአርሻ ውጤቶች ጥሬ እቃዎች ሲሆኑ በቁጥርም የተወሰኑ ናቸው፡፡ አምስት ጥሬ እቃዎች ቡና፣ ቆዳ፣ ሥጋ፣ የቅባት እህሎችና ጥራጥሬዎች ብቻ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን ይይዛሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ ደግሞ ቡናን ነጥለን ብንወስደው ከ60 በመቶ በላይ የሚይዝ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በአለም አቀፍ ገበያ ላይ የምትገዛቸው ሙሉ በሙሉ ነው ለማለት በሚያስደፍርም በጣም በጣም ከፍተኛው ክፍል በኢንዱስትሪ ሸቀጦች የተያዘ ነው፡፡

የውጭ ንግድ ይዘት እንዲህ አይነት መሆን ደግሞ አጋጣሚ ሆኖ ለምሳሌ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት የቡና ምርት በበረዘል ወይም በአንጉሳ መበላሸት የጥሬ እቃዎች ዋጋ ከጨመረባቸው ወቅቶች በስተቀር ከሚሸጠው የሚገዛው ዋጋ ስያደርጥ ስለሚጨምር በአገሪቱ ላይ የማያቋርጥ የንግድ ሚዛን መዛባትን አስከትሎበታል፡፡ የንግድ ሚዛን መዛባት ደግሞ ብድር ውስጥ እንድትገባ ብሎም ጥገኛ እንድትሆን አድርጓታል፡፡

የማን ጥገኛ? በንግድ በኩል የሚመጣ የኢኮኖሚ ጥገኝነት አብዛኛውን ጊዜ ከንግድ ደንበኞች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከየካቲት በፊት የኢት ዋና ዋና የውጭ ንግድ ደንበኞች ሰሜን አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ጣሊያንና ጃፓን ነበሩ፡፡ ከነዚህ ውስጥ በተለይ በገዢነት ደረጃ ሰሜን አሜሪካን አንደኛ ደንበኛ ነበር፡፡ ከ75 በመቶ በላይ የሚሆነው የኢት ዋና የውጭ ንግድ ሸቀጥ ቡና የሚሸጠው ለሰሜን አሜሪካን ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ኢትዮ ኢኮኖሚ በሰሜን አሜሪካ ቡና በሚኖረው ዋጋ የሚመካ ነበር፡፡ በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች፣ የፖለቲካ ተጽእኖዎች ወዘተ በመያዟም በሌላ ቦታ የቡና ዋጋ ቢጨምር እንኳ ለአሜሪካ የተወሰነ ''ኮታ''ማቅረብ ግዴታዋ ስለነበረባት የመከራከርና የመምረጥ አቅሟም የተወሰነ ነበረ፡፡ ዋረቷ አሜሪካን በሰጣት ዋጋ ከአሜሪካ ጋር የተስማማችውን ውል ማለት የተወሰነ ኮታ ማቅረብ /መፈጸም/ ነበረ፡፡ ባጭሩ በዚያን ወቅት የኢት ህልውና በሰሜን አሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ላይ የወደቀ ነበር፡፡ የሰሜን አሜሪካ ጥገኛ ነበረች፡፡

ከየካቲት አብዮት በኋላ የኢት የውጭ ንግድ ደንበኞች ተለውጠዋል፡፡ ከሰሜን አሜሪካና ከላይ ከጠቀስናቸው የኢምፔሪያሊስት አገሮች ጋር የምታካሂደው የንግድ ልውውጥ ሙሉ በሙሉም ባይሆን ከቀድሞው ጋር ሲወዳደር በጣም ቀንሷል፡፡ ለምሳሌ በሰሜን አሜሪካና ከሌሎች ምእራብ አገሮች ይገዛ የነበረው የጦር መሣሪያ አብዛኛው ከሶቪየት እንዲሁም ከምሥራቅ ጀርመን፣ ቼኮዝሎቫኪያ ይገዛል፡፡ ሌሎችም ሸቀጦች እንደዚሁ፡፡ ዛሬ በኢት ውስጥ በጋዜጣ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሚካሄዱት ማስታወቂያዎች የምእራብን ባይሆን የምስራቅ አውሮፓ አገሮችን ሸቀጦች ለማስተዋወቅ የአገር ውስጥ ገበያ እንዲያገኙ ለማድረ



ግ ነው፡፡ አገሪቱ የምትሸጣቸውንም ሸቀጦች የተመለከትን እንደሆነ ተመሳሳይ ሁኔታ እናገኛለን፡፡ ቀድሞ ወደ አሜሪካ ይሄድ የነበረው ዛሬ ወደ ሶቪየት ህብረትና ለምስራቅ ጀርመን በመሄድ ላይ ነው፡፡ አብዛኛው የሚሄደው ቡናም ሆነ ሌላ ጥሬ እቃ ኢትዮ ከእነዚህ አገሮች የምትገዛቸውን የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ለመክፈል ነው፡፡ ይህም በአዲስ የኢት የንግድ ደንበኞች እያነሱ እንዲሄዱ ብሎም ኢትዮ ለመከራከርና ውድ ከርካሽ ገበያ ለማማረጥ ያላት ችሎታ እየቀነሰ እንዲመጣና የአገሪቱ የንግድ ሚዛን እንዲዛባና፣ በእነዚህ አገሮች ላይ እንድትመካና ጥገኛቸው እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ባጭሩ አገሪቱ የምትሸጣቸው ሸቀጦች የአርሻ ውጤቶች፣ የምትገዛቸው ደግሞ የኢንዱስትሪ ውጤቶች በመሆናቸው ደንበኞቿ የተወሰኑ በመሆናቸውና የመምረጥና የመከራከር ችሎታዋ በመወሰኑ እንዲሁም አብዛኛው የውጭ ንግዷ ገቢ እዳ ለመክፈል ስለሚውል ኢትዮ በአሁኑ ወቅት የማይናቅ የውጭ ገበያ ችግር አለባት፡፡

ይህ የውጭ ገበያ ችግር በአገሪቱ ለተፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ በሶስት መንገዶች አስተዋጽኦ አለው፡፡

አንደኛ፡— በአሁኑ ጊዜ በአለም አቀፍ ገበያ ላይ የሚሸጠው ሸቀጥ መጠን ዝቅተኛ በመሆኑም በላይ አቅጣጫው ወደ ተወሰኑ የምስራቅ አገሮች ነው፡፡ አላማውም አገሪቱ በልማት ላይ ልታውለው የምትችለው የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ባይሆን ከነዚህ አገሮች በዱቤ ለተገዛው ቁጥር ስፍር ለሌለው የጦር መሣሪያ እዳ ለመክፈል ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በአንድ በኩል ለሌሎች አላማዎች ሊውል የሚችል ብዙ ገንዘብ ለልማት ያልዋለ ሸቀጥ የጦር መሣሪያ እዳ በመክፈል ''ይጠፋል''፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለእነዚህ አገሮች የሚሸጡት ሸቀጦች እዳ ለመክፈል ስለሆነ አገሪቱ ውድ ገበያ ፈልጋ ወይም መርጣ ሸቀጧን ለመሸጥ እድል ስለማይኖራት በዚህ በኩል ለአገሪቱ ሊገባ የሚችለው ገቢ ይጠፋል፡፡ በሌላም ገበያ የምትሸጠው ያው ጥሬ እቃ በመሆኑ ከምትገዛው ጋር ሲነፃፀር ዋጋው እየቀነሰ እንጂ እየጨመረ ስለማይሄድ የንግድ ገቢዋ ይቀንሳል፡፡ ባጭሩ በንግድ የሸቀጦች ይዘት በሚመጣው ክስረት፣ በንግድ ደንበኞች የተወሰኑ የእነርሱም ጥገኛ ከመሆን የተነሳ የመምረጥና የመከራከር እድል በመጥፋት በሚከተለው ክስረት ከውጭ ንግድ የሚገኘው ገቢ ቀንሷል፡፡ ከተገኘው ገቢም ላይ አብዛኛው ለልዩ ልዩ ትልቅ አላማዎች ክፍያ በመዋሉም የውጭ ንግድ ለሌሎች ልዩ ልዩ የእድገት ሥራዎች የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀንሷል፡፡ ይህ አገሪቱ ለልዩ ልዩ አላማዎች ከምታውለው ገንዘብ ከፍተኛውን ክፍል የሚያስገኘው የውጭ ንግድ በእንደዚህ ሁኔታ ውስጥ መገኘቱ ደግሞ የአገሪቱን ዘላቂ እድገት አዳከሟል፡፡

ሁለተኛ፡— የኢኮኖሚ እድገቷ እንዲዘብ አድርጓል፡፡ አዲሶቹን ደንበኞች ለማስደሰት ሲባል በተወሰኑ የንግድ ሸቀጦች ላይ ብዙ ገንዘብ፣ ብዙ የማምረቻ መሣሪያ፣ ብዙ የሰው ጉልበት ወዘተ በመሠማራቱ በሌሎች የኢኮኖሚ ክፍሎች በተለይ ለህዝቡ አሰታዊ ኑሮ የሚያስፈልጉ ምርቶች ላይ አነስተኛ አተኩሮ ተሰጥቷል፡፡ ለምሳሌ ለህዝቡ ኑሮ የሚያስፈልገው እህል ማምረት ላይ ብዙ ገንዘብ፣ ጉልበትና የማምረቻ መሣሪያ ማሠማራት ሲያስፈልግ በቡናና በሌሎች የንግድ ሸቀጦች ላይ የበለጠ ወጥቷል፡፡ ይህ ለውጭ ገበያ በሚውሉ ሸቀጦች ላይ ሁሉን ነገር ማሠማራትና በአገር ውስጥ በሚያስፈልጉ ሸቀጦች ላይ ንቀት ማሳየት በአንድ ወይም በሁለት ሸቀጦች ላይ የተመሠረተ የጥገኛ አገር የውጭ ንግድ ውጤት ነው፡፡

ሶስተኛ፡— ለሸቀጦች እጥረት መባባስ ምክንያት ሆኗል፡፡ በውጭ ገበያ ላይ ለሽያጭ የሚቀርቡት ሸቀጦች በአገር ውስጥ ገበያ ላይ የሚፈለጉ ናቸው፡፡ በሁለቱ ዘርፎች መካከል የሚደረገው የሸቀጦች እንቅስቃሴም የሚወሰነው በዕቅድ ሳይሆን በነፃ የገበያ ህጋጋት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የውጭ ንግድ፣ ንግዱ በአገር ውስጥ የሸቀጦች እጥረት አስከትሏል፡፡ ለምሳሌ ያህል የመንግሥትን እስታትስቲክስ እንጥቀስ፡፡ በአገሪቱ ውስጥ ታላቅ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች እጥረት እያለ በ1969 ዓ ም 20 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ጥራጥሬዎችና 15 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የቅባት እህሎች የውጭ ንግድ ከአገር ውስጥ ገበያ ወስዷል፡፡

ለማጠቃለል ያህል ኢትዮ በዓለም ገበያ የምትሸጣቸው የእርሻ ውጤት ሸቀጦች ዋጋቸው ከምትገዛቸው የኢንዱስትሪ ውጤት ሸቀጦች ጋር ሲመጣጠን እያሽቆለቆለ የሚሄድና በደንበኞቿም ማነስና የእነርሱም ጥገኛ በመሆኗ የማማረጥና የመከራከር አቅሟ የተወሰነ በመሆኑ የንግድ ሚዛኗ ከጊዜ ጊዜ እየተበላሸና እዳዋ እየጨመረ መጥቷል፡፡ መንግሥትም እየጨመረ የሚሄደውን የአገሪቱን እዳ ለመክፈል እያደገ የሚሄድ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ስለሚያስፈልገውና ይህን ለማድረግ ደግሞ ይበልጥ በእነዚህ የውጭ ንግድ ሸቀጦቿን ማምረት ላይ ይበልጥ አተኩሮ በማድረጉ በአገሪቱ የውስጥ ገበያ በተለይም በህዝቡ አሰታዊ ኑሮ የሚያስፈልጉት ላይ ለሚውሉ ሸቀጦች አነስተኛ አተኩሮ አድርጓል፡፡ ይህም እንደገና የአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት እየተዘበ፣ ችግሮች እየጨመሩና ጥገኝነት እየተጠናከረ እንዲሄድ ራሱን የቻለ ምክንያት ሆኗል፡፡



## 2.2.4 ሌሎች ችግሮች

### 2.2.4.1 የመኖሪያ ቤቶች ችግር

ጤናማ ኑሮ ለመኖር ለአንድ ሰው ቢያንስ መታጠቢያ፣ ሽንት ቤትና የምግብ ማብሰያ ያለው አንድ ክፍል ያሻዋል ከሚለው ከተመለከትነው በኢት ያለው የቤት ችግር አገር አቀፍ ነው ልንል እንችላለን፡፡ .በአገራችን ከሄድን ማለት 10—15 ሆኖ ሰው በሰው ላይ እየተኛ ከከብቶቹ በአንድ ክበብ ጎጆ ውስጥ የሚኖረውን ብዙውን የገጠሩን ህዝብ 6:6:7ም ሆኖ በአንድ ክፍል ውስጥ ለ10—15 ቤተሰብ አንድ ሽንት ቤት፣ አንድ ማብሰያ ቤት፣ አንድ የውሀ መቅጃ ወዘተ እየተጠቀመ የሚኖረውን ብዙውን የከተማውን ሠርቶ አደር መጠለያ ቤት ያለው አድርገን ከወሰድን ገን በአሁኑ ጊዜ በኢት ውስጥ ያለው የቤት ችግር በከተሞች በጠቅላላውና በተለይ ደግሞ በታላላቅ ከተሞች ውስጥ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በአሁኑ ወቅት የሚከራየው ቤት በማጣት በሆቴል ወይም ከዘመድና ከጓደኛ ጋር መተገፈሽ እስኪጠሩ ድረስ ጠፍንገው የሚኖረው ሰው ቁጥር በከተሞች በተለይ በታላላቆች በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ እጥረት ይበልጥ የተሰቃየው የንዑስ ከበርቴው ክፍል ሲሆን ብዙዎቹ ከ12ኛ ክፍል ትምህርታቸው እየጠረሱ በታላላቅ ከተሞች በተለይ በአዲስ አበባ ሥራ የሚፈልጉ ወይም የሚይዙ ከልዩ ልዩ ክልሎች ትምህርታቸውን ጨርሰው እንደዚሁ ሥራ የያዙ፣ በሥራ ዝውውር ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ከውጭ አገር ትምህርታቸውን ጨርሰው የሚመጡ ናቸው፡፡ በዚህ መልክ የቤት ፈላጊው ቁጥር ከዓመት ዓመት እየጨመረ በመሄዱና የቤቶች ምርት ከፍላጎቱ ጋር ሲነፃፀር በጣም ወደኋላ ስለቀረ ቤት ለማግኘት በቀበሌና በቤቶች ሥራ ሚኒስቴር አከራይ ድ ቤቶች ደረጃ ከ1967ና 68 ዓ ም ጀምረው አመልክተው ወረፋ የሚጠብቁ ቁጥራቸው በጣም ብዙ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሆቴሎች እንኳ ያለውን ፍላጎት ለማሟላት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡

ይህ እጥረት ለምን ተፈጠረ? የከተማ ቦታ በመንግሥት ሥር ሆኖ የቤት ሥራ ለትርፍ መሆኑ ቀርቶ እንዴት የቤት ችግር በመፈታት ፈንታ ሊባባስ ቻለ? አንዳንድ ምክንያቶች እንስጥ፡—

1/ የሚከራዩ ቤቶች ሊካሄዱ የሚችለው በመንግሥትና በቀበሌዎች በመሆኑና በሁለቱም በኩል አዲስ ቤቶች አለመሠራታቸው፡፡ በመንግሥት ችልተኝነትና በቀበሌዎች አቅም ማጣት እነዚህ ብዙ አዲስ ቤቶች ሊሰሩና ከአብዮቱ በፊት በጅምር የተወረሱት ብዙ ታላላቅ የመኖሪያ ህንፃዎችና ከአብዮቱ በኋላም በቀበሌዎች የተጀመሩት የቁጠባ ቤቶች ተገትረው ቀርተዋል፡፡ መንግሥት የገንዘብ አቅምና የሚያስፈልጉትን ጥሬ እቃዎች ለማግኘት

ችሎታ እያለው እነዚህን አዱሶችን ተጠቅሞ ከእለት እለት የሚያብጠውን ችግር ለመፍታት ምንም አይነት ተግባራዊ እርምጃ አልወሰደም:: ቀበሌያች ደግሞ በገንዘብ ችግር ብቻ ሳይሆን/ገንዘቡ ትልቅ ችግር ነው/ ለቤት ሥራ የሚያስፈልጉ እቃዎች እንጨት፣ ቆርቆሮ ምስማር፣ ሲሚንቶ፣ ጣውላ፣ መገጣጠሚያ፣ ባንቧ፣ ወዘተ ማግኘት ስለማይችሉ ፍላጎት ያላቸው እጃቸውን አጣጥፈው እንዲቀመጡ ተገደዋል:: እዚህ ላይ እንበብ ለእናት አገር ጥሪ በአሎች መደገሻ የተጣሉት ብዙና ታላላቅ ዛፎች የባከነውን እንጨት፣ ምስማር፣ ቆርቆሮ፣ ወዘተ እንዲሁም ለደርጉ ለተሰራው ዱልዱይ ትሪቢዩንና አደባባይ የፈሰሰው ሲሚንቶ ጣውላ፣ አሸዋ ወዘተ ሲታወስ ምነው በነዚህ እቃዎች እጥረት ምክንያት ለብዙ ሺ የሚያገለግሉት በጅምር የተገተሩት ቤቶች እንዲያልቁ አልተደረገም? ብሎ ሊጠይቅ ይችላል:: የእኛም ጥያቄ ይኸ ነው:: መልሱም የመንግሥት ለህዝብ ጥያቄዎች መሟላት አለመጠነቅ ነው::

2/ የከተማ ቤቶች እቅድ የመኖሪያ ቤት ለማሠራት የሰጣቸውን መብት ተጠቅመው ማሠራት የጀመሩ፣ በአንድ በኩል ከላይ የጠቀስናቸው ችግሮች በሌላ በኩል ደግሞ ባለው ጠንካራ ቢሮክራሲያዊ አሠራር ምክንያት ከፍተኛ ስቃይ የደረሰባቸው ብቻ ሳይሆን ለማስራት ረጅም ጊዜ ወሰደባቸዋል:: ይኸም እንደገና ማሠራት ከጀመሩት አንዳንዶች እንዲያቆሙ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ላይ መጥፎ ተጽእኖ ስላሳደረ የየራሱን ቤት ለማስራት የሚችለው እንኳ ተስፋ ቆርጦ እንዲቀመጥ ተገዷል::

3/ብዙ የመኖሪያ ቤቶች የእስር ቤቶች፣ የልዩ ልዩ አስተዳደር ጽ ቤቶች፣ የድግስ መደገሻዎች፣ ወዘተ መሆናቸውም የረጅምና የአጭር ጊዜ የቤት እጥረት አስከትሏል::

2:2:4:2 የማገዶ ችግር:—

የአንድን አገር እድገት ለመለካት እንደምልክት ሆነው ከሚወሰዱት ነገሮች በዚያ ህብረተሰብ ውስጥ ሰዎች ለማምረትም ለምበሊ የኢንዱስትሪ መኪናዎችን ለማንቀሳቀስ ሆነ ለእለታዊ ኑሮአቸው ለምበሲ ምግብ ለማብሰል የሚገለገሉበት የነዳጅ ኃይል አይነት አንዱ ነው:: ህብረተሰቦች እያደጉ ሲሄዱ ሰዎች እንደነዳጅ ሃይል የሚገለገሉባቸው ምንጮች ከእንጨት ወደ ከሰል ድንጋይ፣ ከከሰል ድንጋይ ወደ ጋስ፣ ከጋስ ወደ ኤሌክትሪክሲቲ እየተለወጡ ይሄዳሉ:: በሌላ አነጋገር ዋናው የሃይል ምንጩ የእንጨት ሃይል የሆነ ህብረተሰብ ወደ ኋላ የቀረ ሲሆን ኤሌክትሪክሲቲ ዋና ምንጩ የሆነ ህብረተሰብ ደግሞ በከፍተኛ እድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ይሆናል::



ኢትዮ ወደኋላ የቀረች አገር በመሆኗ ዋናው የማገዶ ምንጭ እንጨት ነው:: እርገጥ አንዳንድ ኢንዱስትሪያዎችና በትላልቅ ከተሞች የሚኖሩ የአውሮፓ ኑሮ የቀመሱና ደህና ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ኤሌክትሪክሲቲ ወይም ጋስ ይጠቀማሉ:: በህብረተሰቡ ውስጥ አብዛኛው ህዝብ የሚጠቀምበትን ስንመለከት ግን ይኸ እንዳለ ለመቁጠርም አያስደፍርም:: ምክንያቱም በገጠር የሚኖረውን የአገሪቱን 90 በመቶ ህዝብ የወሰድን እንደሁ ምግቡን ለማብሰል የሚገለገለው ጭራሮ፣ ኩበት፣ ፍግ ወዘተ ሲሆን በከተማ የሚኖረውም አብዛኛው ሠርቶ አደር የሚጠቀመው በልዩ ልዩ መልኮች የሚቀርቡ የእንጨት ውጤቶች ናቸው:: ምግቡን የሚያበስለው፣ ልብሱን የሚተኩሰው፣ ወዘተ በእንጨትና በቅጠል አብዛኛውን ጊዜ የባህርዛፍ፣ በእንጨት ከሰል በባህርዛፍ ፍሬ፣ ወዘተ ነው:: አብዛኛዎቹ የአገሪቱ ኢንዱስትሪያዎችም የማምረቻ መኪናዎችም የሚንቀሳቀሱት እንጨትንና የእንጨት ከሰልን እንደማገዶ በመጠቀም ነው:: በሌላ አነጋገር አገሪቱ የምትጠቀምበት የማገዶ ነዳጅ ሃይል በጣም ጥንታዊና ወደኋላ የቀረ ነው::

ማገዶን በሚመለከተው በኩል የኢት ህብረተሰብ ዝሁያዊ ችግር የሆነው ጥንታዊና ወደኋላ የቀረ መሆኑ ብቻ አይደለም:: በዚሁ ደረጃውም እንደልብ አለመገኘቱ ነው:: የማገዶ ችግር ያለው በገጠርም በከተማም ቢሆን በጣም ገኖ የሚታየው ግን በከተማዎች በተለይ በታላላቅ ከተማዎች ነው::

በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ፣ በሐረር፣ በመቀሌ፣ በአስመራ፣ በደሴ በጎንደር ወዘተ ታላቅ የማገዶ እንጨትና ከሰል እጥረቶች አሉ:: ይኸም እጥረት ከፍተኛ የዋጋ መናር አስከትሏል:: በመሆኑም ወይ ለመግዛት ገንዘብ እያላቸው እንጨትና ከሰል በገበያ ላይ ለማግኘት ባለመቻላቸው ወይ ዋጋ ተወደባቸው በገበያቸው ማነስ የተነሳ ማገዶ አጥተው በችግር የሚሰቃዩ ሰዎች በጣም ብዙ ናቸው:: በማገዶ እጦት ምክንያት ብቻ ምግብ ለማብሰል ባይችሉ ቀርተው ገንዘብ ካላቸው ሆቴል የሚበሉ፣ ገንዘብ ከሌላቸው ደግሞ የሚራቡም ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም:: በሆቴልና በልዩ ልዩ ተመሳሳይ አገልግሎቶች ተሰማርተው የሚሠሩ ነጋዴዎችም ተመሳሳይ ችግር አለባቸው:: እንዲህ ዓይነት ጠቅላላ የማገዶ እጥረት ለምን ተፈጠረ? አንዳንድ ምክንያቶች እንጥቀስ:—

1/ በአገሪቱ በጠቅላላውና በከተማዎች አካባቢ በተለይ ደን መጥፋት፣ በቀደሞው ስርአት ስርአት በሌለው መንገድ በደን የተሸፈኑ መሬቶች እየተመነጠሩ ለእርሻ በመዋላቸው፣ ከገዥው መደብ አበሎች ጋር በመሻረክ በአገሪቱ የሚገኙትን የእንጨት ሥራ ፋብሪካዎች በሞኖፖል የያዙት ኢምፔሪያሊስቶች በተለይ ጣሊያኖች የአገሪቱን ደኖች በግዴለሽነት በመጨፍጨፋቸውና በምትካቸው ምንም ዓይነት የተከላ ስራ ስላልተደረገ በጠቅላላው በአገሪቱ በተለይም በከተማዎች አካባቢ ሰዎች ለማገዶ በቀጥታም ሆነ በከሰል መልክ እንጨት ሊቆር

ጡ የሚችሉበት ደን የለም፡፡ አልፎው አልፎው ለቅሪት የሚታዩት ደኖችም አብዛኛዎቹ የሚገኙት ሰዎች በቀላሉ ሊደርሱባቸው በማይችሉ ሩቅና መገናኛ በሌለባቸው ቦታዎች ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ለማገዶ እጥረት አንዱ ምክንያት የጥሬ እቃ /በአገጠት መልክ የሚቆረረጥና የሚከስል ዛፍ/ እንደልብ አለመገኘት ነው፡፡

ሁኔታውን ለማሻሻል በደን ልማትና በዱር አራዊት በለስልጣን መስሪያ ቤት መጠነኛ የደን ልማት ዘመቻዎች ተደርገዋል፡፡ ነገር ግን አንዱ ዛፍ /በጣም ፈጣን እድገት ያለው በሃርዘፍ እንኳ/ ለጥቅም ከመዋሉ በፊት ብዙ አመታት ስለሚያስፈልጉት ለጊዜው ችግር መፍትሄ ሊሆን አልቻለም፡፡

2/ የተቀነባበረ የማገዶ ምርት አለመካሄድ በየቦታው ያሉትን የከሰልም ሆነ የማገዶ አገጠት አምራቾች አደራጅቶ ትምህርትና አመራር እየሰጡ ያለውን የደን ሀብት በብልሃትና በጥንቃቄ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገዱ እየተጠቀሙ እንዲያመርቱ ማድረግ ሲያስፈልግ በአንዳንድ ቦታዎች መንግሥት እንዲህ አይነቱ ምርት እንዲቆም አድርጓል፡፡ የረጅም ጊዜ አሳማው ደንን ለመጠበቅ ሲሆን የአጭር ጊዜ ውጤቱ ግን የማገዶ እጥረት መፈጠር ሆኗል፡፡ በተደረገው ክልከላና በከልከላው የጉደለውን ምርት ለማሟላት መንግሥት ተጠብጥ አርምጃ በለመውሰዱ የማገዶ እቃ ምርት ቀንሷል፡፡ የናው የእጥረቱም ምንጭ ይኸው የማገዶ እቃ ምርት ከፍላጎት ጋር እኩል አለማደጉ ነው፡፡

3/ የማመሳለሻዎች እጥረት ከከተማዎች ይራቀ እንጂ ደን በሉባቸው ቦታዎች የማገዶ አገጠቶችም ሆነ ከሰል እንደልብ ይገኛሉ፡፡ እንዲያውም ብዙ ገንዶች በየጫካው ተጋደመው የምበጥ ቀለብ ሲሆኑና ሲበሰብሱ ይታያሉ፡፡ የደን ልማት በለሥልጣን መስሪያ ቤት ሠራተኞች ይሆን ሁኔታ በደንብ ያውቃሉ፡፡ በየጫካው ውስጥ ተኝተው በመበስበስ ላይ ያሉትን ገንዶች ቆራርጦ ወይም አክስሎ ለከተማው እራሪ ማቀረብ ሲቻል በማመሳለሽ መኪናዎች ጉድለት ብቻ ሊደረግ አልቻለም፡፡ የማመሳለሽ እጥረትም ሊኖር የቻለው ህዝቡ ለደረሰበት የማገዶ ችግር መንግሥት ደንታ በለመስጠቱና የማመሳለሽ መኪናዎች በለመደልደሉ ነው፡፡ ስለሆነም በኢት ለደረሰው የማገዶ ችግር የማመሳለሻዎች እንደልብ አለመገኘት ሌላው ምክንያት ነው፡፡

## 2፡2፡4፡3 የአገልግሎቶች ችግር፡—

የት ቤቶች፣ የሆስፒታሎች፣ የመገናኛዎችና የሌሎች አገልግሎቶች እጥረቶች ሌሎች የህብረተሰብ ዝኔያዊ ችግሮች ናቸው፡፡



ከየካቲት አብዮት በኋላ ብዙ መለስተኛ አንደኛ ደረጃ ት ቤቶች መሠራታቸው እሙን ነው፡፡ በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ ት ቤቶች ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ከየነው ገን ከየካቲት በኋላ በተለይ በመጠረሸዎች ሁለተ ደረጃ ምንም አልተሰራም፡፡ ያሉት በሙሉ ከየካቲት በፊት ከነበረው ስርአት የተወረሱ ናቸው፡፡ የት ቤቶች ምርት በህብረተሰቡ ውስጥ እየጨመረ የመጣውን የመማር ፍላጎት ሊያረካ በሚችል ፍጥነት ከሳደገም፡፡ ይህም በአገሪቱ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ የት ቤቶች እጥረት አስከትሏል፡፡

በት ቤቶች እጥረት ምክንያት በየቦታው በተለይ በታላላቅ ከተማዎች ተማሪዎች የሚማሩት በሁለት በበስት ፈረቃዎች /ሽፍትስ/ ነው፡፡ ይህ ለት ቤቶች እጥረት አይነተኛ ምልክት ነው፡፡

የሆስፒታሎችም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡ በምርት በኩል ብዙ አልተሰራም፡፡ ያሉት ሆስፒታሎች የዱሮዎች ናቸው፡፡ በእነዚህም ውስጥ የአልጋዎች፣ የመድሃኒቶች፣ የሀኪሞች፣ የነርሶች፣ የአስታማሚ፣ ወዘተ እጥረቶች አሉ፡፡ በእነዚህ እጥረቶች የተነሳ የገጠሩን እንኳን ትተን የከተማውን እራሱ ብንወስደው አልጋ አጥቶ በየሆስፒታሉ ገቢና በየቤቱ የሚደፋው ብዙ ነው፡፡

ለዚህ ችግር መሠረታዊ ምክንያቱ የሆስፒታሎችና ከእነርሱ ጋር የተያያዙ ነገሮች ምርት እድገት ከፍላጎት እድገት ወደኋላ መቅረት ሲሆን ህኔያዊ ምክንያቱ ደግሞ ሆስፒታሎች በጦርነት በቆሰሉት መሞላታቸውና ብዙ ሐኪሞች፣ ነርሶችን ዶክተሮችም በየጦር ግንባሩ መዝመታቸው ነው፡፡

የማመሳለሽ ሁኔታዎችን የወሰድን እንደሁ እንደዚሁ ተመሳሳይ ችግር እንዳለ እናያለን፡፡ የጭነት መኪናዎች፣ የህዝብ ማመሳለሽ ከአንድ ከፍለ አገርም ሆነ ከከተማች ውስጥ ተሽከርካሪዎች፣ ወዘተ እጥረት የህብረተሰቡ ሌላው ህኔያዊ ችግር ነው፡፡ በዚህ እጥረት ምክንያት ሰዎችንም ሆነ ሸቀጦችን ከቦታ ቦታ በተፈለገው ጊዜ ለማመሳለስ ባለመቻሉ በሰዎች መጉላላት የተነሳ የሚጠፋው ጉልበት፣ በሸቀጦች በአንድ ቦታ ተከምረው መቀመጥ የተነሳ ባልደረሱባቸው ቦታዎች የሚፈጠረው እጥረት አያሌ ነው፡፡ አንድ ሰው ከአ አ መቀሌ ለመሄድ ቢያስብ የ5—6 ቀናት ወረፋ መጠበቅ ያስፈልገዋል፡፡ እህል ደብረማርቆስ እያለ አ አ መውሰጃ ትራንስፖርት ጠፍቶ የአ አ ህዝብ በእህል እጥረት ይሰቃያል፡፡ ጥጥ ቲንዳሆ እያለ ወይም ከውጭ አገር የሚመጣ ቀለም በአሰብ ወደብ ተከምሮ በትራንስፖርት እጦት ምክንያት የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሥራውን በሙሉም ሆነ በከፊል ያቋርጣል፡፡ ወዘተ ወዘተ፡፡

መንግሥትም ይህን ችግር የተረዳው ይመስላል፡፡ ለምሳሌ የመንግሥት መዋቅር የ
ሆነው የፕሮፖጋንዳና የማስታወቂያ ኮሚቴ በመስከረም በ1971 ዓ.ም ''ገጠሬቶ ኢት ከ
ትናንት እስከ ዛሬ''በሚል ርእስ በዘጋጀው ጽሑፍ የሚከተለውን ይናገራል ''በትራንስፖ
ርት ችግር የተነሳ ቡና ወደ አ አ ለማጓጓዝና ብሎም ለውጭ ገበያ ለማቀረብ ችግር አሰኘ
በአንዳንድ ሥፍራ ጥጥ ተበላሽቶ ከፍተኛ ኪሣራ ያስከተለበት ጊዜ አለ፡፡ በብዙ ቦታዎ
ች የከሰል፣ የሣንቃና፣ የማገዶ ከምችት ተትረፍርፎ አያሉ ወደ ገበያ ለማጓጓዝ ስላልተ
ቻለ በከተሞች ውስጥ የከሰል የሣንቃና የማገዶ እጥረት ይታያል፡፡ በመልካ ሰዲ ተመር
ቶ ወደ ውጭ መላክ የነበረበት አትክልት በማጓጓዣ እጦት የተበላሸበትና ኪሣራ የደረሰበ
ት ጊዜ አለ፡፡ አሁንም በማጓጓዣ እጥረት በጾሙ ወረት በጣም ተፈላጊ የነበረውን አሳ
ህዝቡ በሚፈልገው መጠን ለገበያ ለማቅረብ ትራንስፖርት ገቺ ሃይል ነበር፡፡

የማመላለሻዎች ትራንስፖርት እጥረት ለምን ተፈጠረ? ይህ እጥረት ሊፈጠር
የቻለው፡—

1/ ማመላለሻዎች በአገር ውስጥ አይመረቱም ከውጭ መግዛት አለብቸው፡፡ ዋጋቸ
ው በጣም ውድ ነው፡፡ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ከተወሰነ ቀጥር በላይ ለመግዛት ባለመፍቀዱና
መንግሥትም ከአመታዊ በጀቱ የማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በአገሪቱ ለማስገኘት የሚወስነው
በጀት ዝቅተኛ በመሆኑ ከውጭ አገር ተገዝተው በህብረተሰቡ ውስጥ በአገልግሎቱ ላይ የሚ
ውሉት ማመላለሻዎች ከህብረተሰቡ ፍላጎት ጋር ሲወዳደር በጣም በጣም ጥቂቶች በመሆናቸው፣

2/ የመገጣጠሚያና የመለዋወጫ ተቋሞች ካለመስፋፋታቸውና እያያችም በአገር ውስ
ጥ ገበያ ላይ ካለመገኘታቸው የተነሳ በልዩ ልዩ ብልሽቶች ምክንያት ብዙ የጭነትና የህ
ዝብ ማመላለሻ መኪናዎች በየመንገዱና በየጋራዡ ተገትረው ሥራ በመፍታታቸው፣

3/ ብዙ ማመላለሻዎች ሰርአት በሌለው መንገድ ከሲቪል አገልግሎት ወጥተው በየ
ጦር ግንባሩ በመደልደላቸው ወዘተ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ባቀረብነው ጥናት የኢት ህብረተሰብ ዘተወሳሰበ የኢኮኖሚ ችግር እ
ንደተተበተበና ብዙ የእድገት ችግሮች እንዳሉበት ለማሳየት ሞክረናል፡፡ በጥናቱ ውስ
ጥ የሚከተለውን ለማጤን ችለናል፡፡ ለጠቀስናቸውና ለሌሎች የአገሪቱ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ
ችግሮች ዋናው ምክንያት የቀስ አዘሳዊ ምርት /ማቴሪያል ፕሮዳክሽን/ በፍጥነት ከሚያድ
ገው የህብረተሰቡ ቁሳቁሳዊ ፍላጎት/ማቴሪያል ሪኳየርመንት/ ጋር እኩል ወይም ተደጋ
አለማደጉ ነው፡፡ ከኋላኛው ጋር ሲወዳደር የፊተኛው በዝቅተኛው ደረጃ በመገኘቱ ነው፡፡
ለዚህ ደግሞ ሰበቦች በተለይ የእርሻ እደሩና የወዝ አደሩ የምርት ማምረቻ መሣሪያዎ



የሥራ መገልገያዎች ወደኋላ መቅረትና ቢሮክራሲያዊ ነባነቶች አለመሟላት ዋና ዋና ዎ
ከንያቶች ናቸው፡፡ ለነዚህ ሁኔታዎች አለመሟላት ምክንያቶች የሆኑት ከአገሪቱ እድገት
ጋር ተያይዞ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚደረገው የሀብት ክምችት /ካፒታል አኩሙሌሽን/ በጣ
ም ዝቅተኛ በመሆኑና ይኸም ህብረተሰቡን በሚጠቅሙ ነገሮች ላይ አቀፅ ባለውና ኢኮኖሚያ
ዊ በሆነ መንገድ በሚገባ ባለመሠማራቱ ነው፡፡ ለሁለተኛው ምክንያት ተጠያቂው መንግሥት ነ
ው፡፡

መንግሥቱ የአገሪቱን ሀብት በይንበዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል የተ
ቀነባበረ የኢኮኖሚ እቅድ ባለማውጣቱ /እርግጥ እንዲህ አይነት እቅድ ለማውጣት መደበዊ
ይዘቱ አይፈቅዱለትም/፣ የምርት ሃይሎችን የመፍጠርና የመንቀሳቀስ ችሎታ እንደሩቸው
የሚያስችሉ ነባነቶች ባለመልቀቁ ለምርት እድገት ወደኋላ መቅረት ምክንያት ሆኗል፡፡
ከዚህም ሌላ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚመረተው ሀብት አንደ አንዱ ተካፋይ በመሆኑ፣ ከጽር
ከዚህም ሌላ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚመረተው ሀብት እንደ አንዱ ተካፋይ በመሆኑ፣ ከጽር
ሽውም አብዛኛውን ለህዝብ ጥቅም በሚውሉ ነገሮች ላይ ባይሆን በሌላኛ ላይ /ለጦር መሣ
ሪያ፣ ለዘወትር ታላላቅ ግብዣዎች፣ ለማያስፈልጉ ሥራዎች ለምሳሌ 7 1 2 ሚሊዮን ብር
አውጥቶ የተሰራ አደባባይ እንደገና ማሽብረቅ፣ ለሉክስ መኪናዎች ወዘተ ገንዘቦች ላይ/
አለአግባብ ያወፋል፡፡ መንግሥቱ የህብረተሰቡ ካፒታል ዋና ተካፋይ ብቻ ሳይሆን ያለአ
ገባብ በግዲለሽነት የሚያባክን ክፍል በመሆኑ እንደገና ለችግሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ የኢት ኢኮኖሚ ሥርአት የነውስ ከበርቴ በተለይ የገበሬ
ኢኮኖሚ የሚያይልበት የከበርቴ እንጂ የሶሻሊስት እንዳልሆነ በቁጥር 2፡1 ውስጥ
እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ያሉትን ዋና ዋና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እስከነ ምክንያቶቻቸው
በቁጥር 2፡2 ውስጥ ተመልከተናል፡፡

ከዚህ ቀጥለን በምናቀርበው የጥናታችን ሶስተኛና የመጨረሻ ክፍል ደግሞ በክፍል
አንድና ሁለት ውስጥ ያደረግናቸውን ጥናቶች መሠረት በማድረግ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግ
ሥት በኢት የደረሰውን የኢኮኖሚ ቀውስ ለመፍታት በቅርቡ ያወጣውን የምርት ዘመቻ ፕሮግ
ራም ሂሳዊ በሆነ መንገድ ለማጥናት እንሞክራለን፡፡ በዚያውም ባለው ተጨባጭ ሁኔታ
ውስጥ የኢት ጊዜያዊ ኢኮኖሚ ችግሮች ለመቋቋም በእኛ አስተያየት መደረግ ያለባቸውን
እንጠቁማለን፡፡

## ክ ፍ ል ሦ ስ ት

### የጊ ወ መ  የምርት ዘመቻ–ሂሳዊ አመለካከት–

"If it is not to err in policy the party of the proletariat must both in drafting its program and in its practical activities proceed primarily from the laws of development of production from the laws of economic development of society". (Stalin Dialectical & Historical Materialism, p, 30–31)

በመጀመሪያ የጥናታችን ክፍል በያቹ ያን ወይም ይህን የፈለጉትን አይነት የህብረተሰብ የእድገት ደረጃ ለመርጡ አንደማይችሉና ለእድገታቸው ደረጃ ወስኝ የሆነው ምርታቸው ወይም የሚያካሄዱት የኢኮኖሚ እድገታቸው በተወሰኑ ህጎች እንደሚገዛ አጥንተናል:: ይህንን ጥናታችንን መሠረት አድርገን የኢትን ኢኮኖሚ እድገት ለመመርመር በሁለተኛው የጥናታችን ክፍል በደረግነው ጥናታችን ደግሞ የኢት ኢኮኖሚ ስርአት የነውስ ከበርቴ/የገበሬው/ካፒታሊዝም የሚያይልበት ያሳደገ የከበርቴ ስርአት መሆኑንና እድገቱም የሚገዛው በዚሁ ስርአት ህጎች መሆኑን ተረድተናል::

ጊ ወ መንግሥት ያወጣውን የምርት ዘመቻ የምንመለከተው በነዚህ በሁለቱ ክፍሎች ካደረግናቸው ጥናቶች ባገኘናቸው ውጤቶች ላይ ተመሥርተን ነው:: በሌላ አነጋገር የደርግን የምርት ዘመቻ ትክክለኛነትና ተገበራዊነት የምንመረምረው አስታሊን እንደሚያስገነዝበን ከኢት ህሪያዊ የኢኮኖሚ እድገትና ከሚገዙት ህጎች አንፃር ተነስተን ነው:: ጥናታችንም በሚከተሉት አራት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ያተኩረ ይሆናል::

1 — ዘመቻውና አላማዎች
2 — ዘመቻውና የአዲሱ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ
3 — ዘመቻውና የደርጉ ፖለቲካ
4 — ዘመቻውና ሃቀኛ ተራማጆች

### 3:1 ዘመቻውና አላማዎች

"As was pointed out in the programme of the NDR the surest way for enabling the Ethiopian masses to defeat imperialism, feudalism and bureaucratic capitalism and free their means of production from feudalist and imperialist control will be the <u>building of a socialist economy under the co-ordination of a central planning body.</u>



"<u>To this end an economic development plan for 1971–72</u>
<u>has been drawn up with the aim of charting out the</u>
<u>long path towards economic development and with the</u>
<u>aim of solving the current problems</u>" ( a speech by PMAC,
E. H. Jan 21, 1979 መስመር የና)

የጊ ወ መ የምርት ዘመቻ ሁለት አላማዎች አሉት:: አንደኛው አላማ የሶሻሊስ ''ነፍስ ለማዛን'' የኢን ህሪያዊ የኢኮኖሚ ለመገንባት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የኢኮኖሚ ችግሮች ለመፍታት ነው:: ከዚህ ቀጥለን ሁለቱን አላማዎች አያንዳንዳቸውን በመውሰድ የዘመቻውን ተገበራዊነት ለመመርመር እንሞክራለን::

### 3:1:1 ''ሶሻሊዝምን ለመገንባት''

"የአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የኢት ህዝቦች በስቶን አበይ ወሳቶቻቸውን ለማሸነፍና የምርት ማፍሪያ መሣሪያዎችንም ከአነርሱ ነፃ ለማውጣት ያሳቸው አርገጠኛ መንገድ በማእከላዊ ፕላን የሚመራ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ መገንባት ነው ስለሳ አነሀ ይህን ለማሟላት ስንል የሁለት አመት የኢኮኖሚ ፕላን ይዘን ተርበናል" ይላል የጊ ወ መ የምርት ዘመቻ ሰነዱ::

ሶሻሊዝም የሚገነበው በሶሻሊስት ስርአት ነው:: የሶሻሊስት ስርአት ማለት ደግሞ ወዘደራዊ ሳአሳይ መቆቅርና ማህበራዊ የኢኮኖሚ መሠረት ያለው ማለት ነው:: አንዲህ ዓይነት ሳአሳይ መቆቅርና መሠረት በሌለበት ስርአት ውስጥ ሶሻሊዝምን ለመገንባት ፈጽሞ አይቻልም::

"<u>The socialist system... begins its chronology with</u>
<u>the seizure of power by the proletariat.</u> This follows
from the very essence of the socialist economy as a
single complex which cannot be built up molecularly
within the world of capitalism". (socialist primitive
accumulation, E. preobrazhensky, 1926 funted from
socialist economic P. 130)

ሌኒን ለማንኛውም ነገር ወሳኙ የፖለቲካ ስልጣን ነው፣ ስልጣን የያዘ የፈለገውን ሊያደርግ ይችላል፣ በፖለቲካ ይዘቱ ሶሻሊዝም ማለት የወዝ አደሩ አምባገነንነት ማለት ነው፣ ወዘተ በማለት ያስተማረን የሶሻሊዝም መገንባት የሚጀመረው የወዝአደሩ መደብ ስልጣን ከያዘ በኋላ መሆኑን ለማመልከት ነው:: ከሰወዝአደሩ የፖለቲካ ሥልጣን መያዝ በሌሎች መደቦች ስልጣን ስር የሚገነባ ሶሻሊዝም የአነዚያ መደቦች ሶሻሊዝም አንጂ አውነተኛው፣ ማለት ወዘደራዊው ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም አይሆንም:: በሌላ አነጋገር ለምሳሌ የነውስ ከበርቴው መደብ በስልጣን ላይ ሆኖ ሶሻሊስት ነኝ በሚል ሶሻሊዝምን አገነባለሁ

ቢል የሚገነባው ሶሻሊዝም አውነተኛውን ማለት ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ሳይሆን የራሱን የገውስ ከበርቴው ሶሻሊዝም ይሆናል፡፡

"የኢት ኢኮኖሚ ስርአት ሶሻሊስት ወይስ ካፒታሊስት?" በሚል ነውስ ርእስ በክፍል 2፡1 ስር ስለኢትዮ ሳእሳይ መዋቅርና ኢኮኖሚያዊ መሠረት ሁኔታዎች አድገት ደረጃዎች በቀረብነው ጥናታችን የዘሬይቶ ኢትዮ ስልጣን በገኡስ ከበርቴው መደብ የተያዘ ብትና የኢኮኖሚ ስርአትም የንውስ ከበርቴው/የገበሬው/ካፒታሊዝም የሚያይልበት"ወጣት" የከበርቴ ስርአት እንደሆነ አብይተናል፡፡ ከፊውዳል ወደ ከበርቴ ህብረተሰብ በመሸጋገር ላይ የምትገኝ መሆኗንና የሶሻሊስት ህብረተሰብ እንዳልሆነች ብሎም አሁን ባለችበት ሁኔታ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ለመገንባት እንደማይቻል ጠቀስናል፡፡ እዚህ እንመለስበትም፡፡

የደርግ ዘመቻ ገን ከዚህ የተለየ መነሻ አለው፡፡ ሶሻሊዝምን ለመገንባት ስላሰው ጠቀሳሳ ሁኔታ ሲገልጥ /መነሻው መሆኑ ነው/ እንዲህ ይላል፡—

"Now there is a favourable condition to construct socialism and lay down a sound economic base".
(The campaign P. 10)

ለሶሻሊዝም መገንባት አስፈላጊ ሁኔታዎች በፖለቲካ በኩል የፖለቲካ ስልጣን በወዝአደሩ ስር መገባትና በኢኮኖሚ በኩል ደግሞ የምርት ሃይሎች በከፍተኛ ደረጃ ላይ መገኘት ናቸው፡፡ በዘሬይቶ ኢትዮ ገን በክፍል 2፡1 ስር እንደጠቀስነው ሁለቱም ሁኔታዎች የሉም፡፡ የፖለቲካ ስልጣን በገውስ ከበርቴው መደብ ነው፡፡ የምርት ሃይሎች እድገትም አጅግ ወደ ኋላ የቀረ ነው፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የእነዚህ ሁኔታዎች በአሁኑ ጊዜ ተሟልተው አለመገኘታቸው ብቻ አይደለም፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሁኔታዎች እንዳይሟሉም ብዙ ውስብስብ ሴራዎች እየተካሄዱ ናቸው፡፡ በፖለቲካ ወዝአደሩ የተጀመረውን አዲሱን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መርቶ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን ከሌሎች ፀረ ሶስቶ መደቦች ጋር በመሆን መስርቶ፤ ወደ ሶሻሊዝም የሚያራምደውን ማቴሪያላዊ መሠረት ጥሎ ሶሻሊዝምን ለመገንባት እንዳይችል በልዩ ልዩ ስውርና ገሀድ ጭቆናዎች ተደርገውበታል፡፡ እየተደረጉበትም ነው፡፡ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የሚያነቃቁትንና የሚያደራጁትን ተራማጅ ምሁራን ወይ በመታሰር፤ ወይ በመረሸን ወይ በመሰደድ፤ ወይ በክትትል የተነበ አጥቷል፡፡ ሊደርጅቶቹ ወይ ፈረርሶዋል ወይ በፍርሃትና በገዶቻ የቀኝ አደርባዮች ተገዥዎች ሆነውበታል፡፡ ሌሎች ብዙ ሁኔታዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በአሁኑ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለወደፊትም ወዝአደራዊ ሶሻሊዝም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዳይገነባ የሚያጉሉ ናቸው፡፡ በኢኮኖ



ሚም በኩል የተመለከትነው እንደሆነ አሁን ያለው ሁኔታ በክፍል ሁለት ውስጥ በተለይም በ2፡2 ንውስ ደረጃ ዝቅተኛ ብቻ ሳይሆን በክፍል 2፡2 ውስጥ በጠቀስናቸው ልዩ ልዩ ችግሮች የተነሳ እርምጃቸው ታግዷል፡፡

ኢሁንም ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ገ ወ መ እነዚህን ሁኔታዎች በምርት ዘመቻው አኳኋን አያሸሻቸውም፡፡ እንዲያውም ፖለቲካን በሚመለከተው በኩል በሃቀኛ ተራማጆች /እርገጥ ለእርሱ ''ፀረ አብዮታውያን ናቸው/ ላይ ጭቆናው እንደሚቀጥል ያረጋግጣል፡፡ ዘማቸችም አስማርቷል፡፡ ኢኮኖሚን በሚመለከተው በኩል ሶሻሊዝምን ለመገንባት ዋና መሠረት የሆነውን የከበድ ኢንዱስትሪ መስፋፋትን ትልቅ ዋጋ አይሰጠውም ሊሰጠውም አይችልም ቢሰጠውም ሊያረጋግጠው አይችልም፡፡ እንዲያውም የሚያተኩረው ያሉትን ኢንዱስትሪዎች "በሙሉ ኃይል እንዲሰሩና እንዲበሩ" በማድረግ ላይ ነው፡፡ አሁን ያሉት ደግሞ ተሳል ሸቀጦች የሚያወጡና ለሶሻሊዝም መሠረት የሆነውን ከበድ ኢንዱስትሪን ሊተኩ የማይችሉ ናቸው፡፡

ሃቀ ይህ ሆና ሳለ ደርግ የምርት ዘመቻውን በአንድ በኩል ሶሻሊዝምን ለመገንባት ብሎ ሲጀምር አሁን ባለንበት ወቅት ''ሶሻሊዝምን ለመገንባት አመቺ ሁኔታ አለን'' በሚልም መነሻ ጭምር ነው፡፡ የደርግ መነሻ ከላይ ከጠቀስነው የኢት ጠበጭ ሁኔታ ጋር ጠርስ የማይጣጣም ነው፡፡ ከጠበጭ ሁኔታ፤ ማለትም ከህብረተሰብ የኢኮኖሚ እድገት ህገጋት ተነስቶ የማይነደፍና ወደተግባራዊነት የማይለወጥ ፕሮግራም ደግሞ አስታሊን እንደሚለን ትክክል አይደለም፡፡ ስለሆነም ገ ወ መ ሶሻሊዝምን ለመገንባት በሚል የሚያደርገው ዘመቻ ከኢት የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ ጋር ስለማይጣጣም ከቶ ትክክል ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ''በመገንባት ላይ ያለው ሶሻሊዝም''አሁን ባለንበት ጠበጭ ሁኔታ ሊሆን የሚችለው በደርግ አመራር የተወከለው ''የንውስ ከበርቴው ሶሻሊዝም''ነው፡፡ የምርት ዘመቻውም በአፍ ሶሻሊስት ቢባልም የሶሻሊስት ይዘት ከቶ የለውም፡፡ ደርግም ''ሶሻሊዝምን ለመገንባት በአሁን ጊዜ አመቺ ሁኔታ አለ'''' ሶሻሊዝምን ለመገንባት ችሳን ይዘን ቀርበናል'' የሚለው ይኸው''የንውስ ከበርቴውን ሶሻሊዝም''ነው፡፡ በእርግጥም ለእዚህ አይነቱ ሶሻሊዝም አመቺ ሁኔታ አለ፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ እየተጠናከረ የመጣው ይኸው ንውስ ከበርቴው መደብ ነው፡፡ ሶሻሊዝም አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ግቡን ከመምታቱ በፊት ሊመሠረት አይችልም፡፡ ከአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጋርም ተጠፍሎ ሊካሄድ አይችልም፡፡ የሬተኛው ከኋለኛው በኋላ የሚመጣ እንጂ ከእርሱ በፊት ወይም ጎን በጎን የሚሄድ አይደለም፡፡ አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ግቡን ከመምታቱ በፊት ስለሶሻሊዝም መገንባት ማውረት ወይም የሶሻሊዝም መገንባት እንደ ጊዜያዊ ተግባር አድርጎ መውሰድ አይቻልም፡፡ ይህ ከሉ

አርሱ ገብ ሙያተኞች ሶሻሊዝምን መገንባት የማይቻለው አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በኢት መካሄድ ከጀመረ አመታት ቢያልፉትም ገና አልተፈፀመም:: እንዲያውም አሁን ያለበት ሁኔታ ሲታይ የመፈፀሚያው ጊዜ እየተራዘመ በመሄድ ላይ ነው:: ምክንያቶቹን ከላይ ጠቅሰናል::

ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ተቀዳሚው ተግባር ሶሻሊዝምን በባዶ ሜዳ ላይ ለመገንባት መሯሯጥ ሳይሆን የተጀመረውንና ለሶሻሊዝም መገንባት ወሳኝ የሆነውን አዲሱን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ያሉበትን ችግሮች/የሃቀኛ ወዝአደር ፓርቲ፣ የነቁ ህዝባዊ ድርጅቶች፣ አብዮታዊ ህዝባዊ ግንባርና ሠራዊት፣ የዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች አለመኖር፣ ወዘተ/ መፍታትና ግቡን እንዲመታ መታገል ነው::

ሃቅና አጣዳፊው ተግባር ይህ ሆኖ ሳለ የደርግ ዘመቻ አንድ እርምጃ ወደፊት ዘሎ ስለ ሶሻሊዝም መገንባት ያወራል:: እንዲህ ዓይነቱ ዘመቻ ደግሞ ከተጨባጩ፣ ሊሠራ ከሚችለውና ከሚገባው ተግባር ለመሸሽ መፈለጉን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ለወደፊት ለሚገነባው ሶሻሊዝም አደጋ ያስከትላል:: ደርግ ''ሶሻሊዝምን ለመገንባት'' የሚያደርገውን ዘመቻ ጠለቅ ብሎ ለተመለከተው ወይ አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እንደተፈፀመ ወይ ደግሞ ይህንን ከሶሻሊስት አብዮት ጋር አጣምሮ ለማካሄድ እንደሚቻል አድርጎ ያየዋል:: በየትኛውም መንገድ ይመልከተው ሁለቱም ከኢት ተጨባጭ ሁኔታዎች የማይጣጣሙ ትምኒታዊ፣ ከተጨባጩ ስራ የሚያሸሹና በአብዮቱ ህልውና ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ናቸው:: ማኦ በቻይና አብዮት ላይ ከዚህ ተመሳሳይ የሆነ አስተሳሰብ በነበራቸው የሰጠውን መልስ እንመልከት:—

> "They do not understand that our revolution is divided into stages, that we can only proceed to the next stage of revolution after accomplishing the first, and that there is no such thing as "accomplishing both at one stroke". Their approach is like wise very harmful because it confuses the steps to be taken in the revolution and weakens the effort directed towards the current task.... It is a utopian view rejected by true revolutionaries to that the democratic revolution does not have a specific task and period of its own but can be merged and accomplished simultaniously with another task, ie, the socialist task (which can only be carried out in another period)...." (Mao SW. Vil 2 P. 360)

ባጭሩ ደርግ ''ሶሻሊዝምን ለመገንባት'' የሚያደርገው ዘመቻ ከኢት ፖለቲካዊና ማቴሪያሳዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች የራቀና ሰማይና መሬት ቢገለባበጡ ተግባራዊ ሊሆን የማይችል እንዲያውም አሁን በሚካሄደው አብዮት ላይ ውዥንብር በመፍጠር ጉዳት የሚያስከትልና ለወደፊት በኢት የሚገነባውን የሶሻሊዝም መምጫ ጊዜ የሚያራዝም ዘመቻ ነው:: በአሁኑ ጊዜ መዝመት የሚያስፈልገው የተጀመረውን አዲሱን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከግቡ ለማድረስ መሆን ሲገባው ይህ እንደተፈፀመ አድርጎ ''ሶሻሊዝም ለመገንባት'' ዘመቻ ማድረግ በደርግ በኩል ውዥንብር ለመፍጠር፣ ትጥቅ ለማስፈታት፣ አቅጣጫ ለመቀየር በሱም አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ግቡን እንዳይመታ ለማድረግ የተጠነሰሰ ሴራ ነው::



## 3:1:2 ''የኢትዮጵያን ህዝባዊ የኢኮኖሚ ችግሮች ለመፍታት''

ሁለተኛው የደርግ ምርት ዘመቻ አላማ ''የኢትን ህዝባዊ የኢኮኖሚ ችግሮች በመፍታት ነፍስ ለማዳን ነው::'' ይህኛው የአጭር ጊዜ አላማው ነው፡፡

ኢት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ እንደምትገኝ ያሉትን ዋና ዋና ችግሮች በማንሳት ጥልቀቶቻቸውንና ምክንያቶቻቸውን ዘርዝረን በክፍል 2:2 ውስጥ አሳይተናል:: በአንዳንድ ቦታዎች በተለይ በከተሞች፣ በጦርነትና በተፈጥሮ አደጋ በተጎዱ አካባቢዎች የተፈጠሩት ችግሮች የሰዎች ደህና ኑሮ ብቻ ሳይሆን የህልውናቸውን መኖርና አለመኖሩ ጭምር የሚወስኑበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ጠቅሰን ሁኔታውን ለመቋቋም አስቸኳይ እርምጃዎች መውሰድ እንደሚያስፈልግ አመልክተናል:: በዚህ በኩል ደርግ ዘመቻ ማድረጉ የሰፊውን ህዝብ ጥያቄ ለመቀበል በሰፊው ህዝብ ትግል መገደዱን ያመለክታል፡፡ ዋናው ጥያቄ ግን የሰፊውን ህዝብ በመፍራት ደርግ የህዝቡን ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ችግሮች ለመፍታት ''የነፍስ አድን''ፕሮግራም አውጥቶ የምርት ዘመቻ ለማካሄድ ጉዱ ጉዱ ማለቱ አይደለም:: ዋናው ጥያቄ ደርግ የሚያካሂደው ዘመቻ ''የኢን ህዝባዊ የኢኮኖሚ ችግሮች በመፍታት ነፍስ ለማዳን''ተግባራዊነት/ብቃትነት/ አለው የለውም የሚለው ነው፡፡ በማንኛውም ሰው የሚታዘዝ መድሃኒት የአንድን በሽተኛ ነፍስ ሊያድን አይችልም:: የበሽተኛውን ነፍስ ለማዳን የሚወስነው የመድሃኒቱ አይነት ሲሆን የመድሃኒቱን አይነት የሚወስነው ደግሞ የመድሃኒቱ አዘዥ አይነት ይሆናል::

ፕሮግራም፣ጥሩ ፕሮግራም በማንኛውም ሊነደፍ ይችላል:: ከተነደፈ በኋላ በስራ ሊረጋገጥም ሳይረጋገጥም ይችላል:: ትታች/ማታለያ/ሊሆን ወይም አራማጅ/እውነተኛ/ሊሆን ይችላል:: የችግር መፍትሄ ወይም አባባሽ ሊሆንም ይችላል:: ምን ሊሆን እንደሚችል የሚወስነው ይዘቱና ሥራ ላይ የሚውልበት ሁኔታ ነው:: የደርግን ''የነፍስ አድን''ዘመቻ የምንመለከተው ከዚህ አንፃር ነው::

### 3:1:2:1 ዘመቻውና አመራሩ

የአንድን ፕሮግራም በስራ መተርጎምና አለመተርጎም ወይም መፍትሄ ለመስጠት

መቻልና አለመቻል ከሚወስኑት ሁኔታዎች አንዱ የአመራር ጉዳይ ነው:: አመራር ስንል የፖለቲካውን ስልጣን ከጨበጠው መደብ አንስቶ የፕሮግራሙ ሥራ አስፈጻሚ እስከሆነው አካል ያለውን ሁሉ ይጠቀልላል:: በጥሩም ከደርግ አንስቶ እስከ ቢሮክራሲው ማለት ነው::

ለህዝብ ችግሮች ዘላቂና አጥጋቢ መፍትሄ ሊሰጡ የሚችሉ ፕሮግራሞች በማንኛውም መደብ ሊታወጁ ቢችሉ በማንኛውም መደብ አመራር ስር ስራ ላይ አይውሉም:: ዘላቂና አጥጋቢ መፍትሄዎች ሊሰጡ በሚችሉበት መንገድ በተግባር ሊረጋገጡ አይችሉም:: ለዚህም ነው ከለአብዮታዊ የፖለቲካ ለውጥ አብዮታዊ የኢኮኖሚ ለውጥ ከስራ ላይ አይውልም የሚባለው::

ኢት በአሁኑ ወቅት ከገባችበት የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ የውስጥ ቅልቀትና ውስብስብነትና ሰፊው ህዝብ ይህን ችግር ለመወጣት ከሚያደርገው ትግል አንፃር ቢታይ ጊ ወ መ ያወጣው ዘመቻ ጉድለቶች ቢኖሩበትም በፕሮግራም ደረጃ ''ተራማጅነት'' አለው:: የአጭር ጊዜ ፕላን ወጥቶ የህዝቡን ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ችግሮች ለመቋቋም ዘመቻ እንዲካሄድ ሃቀኛ ተራማጆችም ሳይታክቱ ታግለዋል:: ለሃቀኞችና ለሰፊው ህዝብ ዋናው ጥያቄ ደርግ ያወጣውና የሚያካሄደው የምርት ዘመቻ አሁን ባለው አመራር ስር ስራ ላይ ውሎ የህዝቡን ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ችግሮች ሊፈታ ይችላል አይችልም የሚለው ይሆናል:: ከዚህ ቀጥለን ለዚህ ጥያቄ አጭር መልስ እንሰጣለን::

የዘመቻው የበላይ መሪው ደርግ ነው:: የዘመቻውን ድርጅታዊ መዋቅር እንዳየነው በርእሰ ብሔር ደረጃ ሊቀ መንበሩ የደርጉ ሊቀመንበር ም ሊቀመንበሩ የደርጉ ቋሚ ኮሚቴ የኢኮኖሚ ኃላፊ ሲሆን ከወረዳ አንስቶ እስከ ክፍለ ሃገርም የሊቀ መንበርነቱን ቦታ የያዙት አብዛኛዎቹ የደርግ አባሎች ናቸው:: በአሁኑ ወቅት ደግሞ ደርግ የት እንደቆመ ለብዙው እውቅ ነው:: ቢያንስ ሙሉ በሙሉ ከሰፊው ህዝብ ወገን እንዳልቆመ ሁሉም ያውቃል:: የአሁኑ ደርግ በአፍ አሁንም ከሰፊው ህዝብ ጎን የቆመ፣ በተግባር ግን ሰፊውን ህዝብ የሚቃጋ የገዥ መደብ ነው:: ባለፉት አመታት ይህን ውጊያውን ያካሄደው በሚያወላውል ሁኔታ ነበር:: አሁን ግን በማያወላውል መንገድ ሆኗል:: እያወላወለ በባለፉቸው በለፉት አመታት ለተደረጉት አብዮታዊ ለውጦች ሁሉ ሥራ ላይ መዋል ምንያህል እንቅፋት ሆኖ እንደነበርና ወደ መጨረሻውም እስከነጭራሹ እየተቃወማቸው እንደመጣ የኢትን አብዮት በጥሞና ለተከታተለ ሁሉ እንግዳ ነገር አይደለም:: ታዲያ በዚህ መልክ የሰፊውን ህዝብ ድሎች ሥራ ላይ መዋል እያደናቀፈና በመጨረሻም እየተቃወመና ፀረ ህዝብ እየሆነ በመጣው በደርግ የበላይነት የሚመራው ዘመቻ እንዴት አድርጎ "የሰፊውን ህዝብ የኢኮኖሚ ችግሮች ሊፈታና ነፍስ ሊያድን" ይችላል? አይችልም:: በሌሎች ለውጦች ላይ



ያጋረውን ያህል ካጋራ በኋላ ከወረቀት ስያልፍ ይህንም ዘመቻ በሳበት እንዲቀር ያደርገዋል:: የአሁኑ ደርግ ሰፊውን ህዝብ የሚጠቅሙ እርምጃዎች እንደባርቁ በቆራጥነት በስራ ላይ የማያውል ብቻ ሳይሆን መዋላቸውን በቆራጥነት የሚቃወም ነው:: ይህን የማይቀበሉ ለአብዮታዊ/ለህዝቡ ዘላቂና አጥጋቢ ጥቅም ለሚሰጡ/ እርምጃዎች ሥራ ላይ መዋል አብዮታዊ አመራር አያስፈልገም የሚል እምነት ያላቸው አድርባዮች ብቻ ናቸው::

የዘመቻው ሥራ አስፈጻሚ /የሁለተኛ ደረጃ መሪው/ ቢሮክራሲ ነው:: የዘመቻውን ድርጅታዊ መዋቅር እንዳየነው ከወረዳ አንስቶ እስከ ርእሰ ብሔር በአስፈጻሚነት ዘመቻውን የሚመሩት ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው ወታደራዊና ሲቪል ቢሮክራቶች ናቸው:: ዘመቻውን ከስራ ላይ ለመዋል ''ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለበት'' ቢሮክራሲው የሰፊውን ህዝብ ጥቅሞች በአንደኛ ደረጃ የሚፃረር ለመሆን ጥርጥር የለውም:: ባለፉት አራት ዓመታት የተደረጉትን ለውጦች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ስልጣኑን በመጠቀም በልዩ ልዩ አሻጥሮች እንዳደናቀፈ ማንም የማይዘነጋው ነው:: ራሱ ጊ ወ መ ባለፉት አራት አመታት ባደረጋቸው ፕሮፓጋንዳዎች ይቅርና በዚሁ በዘመቻው ፕሮግራም ውስጥ እንኳ በቢሮክራሲው አሻጥር የ 80 ሚሊዮን ብር ሃብት ሊጠፋ እንደቻለ ይናገራል:: ቢሮክራሲው ይህን የተባለውን የሀብት ጥፋት ያስከተለው ያውም አብዮቱ በየለበት፣ በቢሮክራሲው ላይ በደርግ ሆነ በተራማጅ ሃይሎች አብዮታዊ እርምጃዎች አልፎ አልፎ ቢሆንም በሚወሰዱበትና ቢሮክራሲው በታላቅ ሽበር ውስጥ በተከተተበት ወቅት ነበር::

በአሁኑ ወቅት ቢሮክራሲው ሰፊውን ህዝብ ሊጠቅሙ የሚችሉትን እርምጃዎች ሁሉ ሥራ ላይ እንዳይውሉ ሊያደርግ የሚያስችለው አመቺ ሁኔታዎች አሉት:: በመጀመሪያ ከደርግ በኩል አልፎ አልፎ በተጠበጥም ሆነ በፕሮፓጋንዳ ይሰነዝርበት የነበረው እርምጃ እነምሰታል:: እንዲያውም በደርግ ወደቀ እንደሚሰበር እቃ እየተንከባከበ ነው:: ሁለተኛ አብዮታዊ ሃይሎች በመመታታቸውና ሰፊው ህዝብ ነፃ እርምጃዎች የሚያካሂዱበትን ህዝባዊ ድርጅቶች በመፈራረሳቸውና ከሥራ ውጪ በመሆናቸው የሚቀናቀነው ኃይል ለህሙ በመጥፋቱ እንደልቡ የፈለገውን እያከናወነ ነው:: ታዲያ ይህ እየተመናከረና እየተደላደለ የመጣው የሰፊው ህዝብ ምንደኛ ጠላት የሆነው የሃይለሥላሴ ፊውዳል ቡርዡዋ ቢሮክራሲ እንዴት አድርጎ ነው ዘመቻውን በስራ ላይ በማዋል የሰፊውን ህዝብ ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ችግሮች ለመፍታትና የሰፊውን ህዝብ ''ነፍስ ለማዳን'' የሚችለው? መልስ አሁንም አሉታ ነው::

በጥሩ ደርግ ያወጣው ፕሮግራምና የሚያካሄደው ዘመቻ ከነደፈ አንስቶ በተግባር እስከመዋል ድረስ የሚመራው አብዮቱን በዘላቂው ደርግና ከመጀመሪያው ጀምሮ የአብዮቱ

ጠሳት በሆነው ወታደራዊና ሲቪል ቢሮክራሲ ''የተቀደሱ ህብረት''ነው:: ''ዘመቻው
ሥራ ላይ የሚውለው በሰፊው ህዝብ ተሳትፎ ነው'' ፣ ''ዘመቻው ራሱ ህዝባዊ ነው''
ወዘተ እየተባለ በአፍ ቢለፈፍም ሰፊው ህዝብ/አብዮታዊ ምሁራን፣ ወዝአደሩና አርሶ አ
ደሩ፣ ወዘተ/ይህ ነው የሚባል የፍርማል ተሳትፎ እንኳን አልተሰጠውም:: ለዚህም ዋና
ው ምክንያት የደርግ አብዮታዊነት በሀሰ እያከሰመ መሄዱና በሰፊው ህዝብና በአብዮታውያ
ን ላይ እምነት እያጣ መሄዱ ነው:: ስለሆነም ይህ በፀረ—አብዮታዊው ደርግና ቢሮክራ
ሲው ህብረት አመራር ስር ከለሰፊው ህዝብ አብዮታዊና ነፃ ተሳትፎ የሚካሄደው ዘመቻ ከተ
ገባራዊነት የወረቀት፣ ከዘጠጭነት የአፍ ብቻ ሆኖ ይቀራል:: ከለአብዮታዊ አመራርና
ከለሰፊው ህዝብ ሰፊና ነፃ ተሳትፎ የሰፊውን ህዝብ ጥልቅና ውስብስብ የኢኮኖሚና ማህበ
ራዊ ችግሮች ለዘላቂም ሆነ ለጊዜው አጥጋቢ በሆነ መንገድ ለመፍታት አይቻልም:: ከዚ
ህ ውጭ በሆነ መንገድ የሚደረግ ማንኛውም አይነት ሙከራ ሁሉ ዘር ዘር ከማታለያነት አ
ያልፍም:: የደርግም የምርት ዘመቻ ከዚህ አያልፍም:: ደርግ ''ሶሻሊስት''ነው በ
ማለት ያቋቋመውን ያስተዋወቀው ከላይ እስከታች ወታደራዊና ሲቪል ቢሮክራቶች የተሰገሰጉ
በት ''ቶንጆ''ቀርጽ ያለው የዘመቻው መምሪያም ከሰፊው ህዝብና ከአብዮታዊ ኃይሎች ተ
ጽእኖ ነፃ ሆኖ በሚሰራበት በአሁኑ ወቅት በማንኛውም ደረጃ የሰፊውን ህዝብ ጠሳቶች
የሚያገለግል አንድ ዘጠማሪ ድርጅታዊ መዋቅር ከመሆን አያልፍም:: ቢሮክራሲውን ''እ
ለኘታ''አድርጎ የሚካሄደው ይህ ዘመቻ ለቢሮክራሲው አዲስ የመጠናከሪያ መስክ ይሆናል::

3:1:2:2 ዘመቻውና የምርት ኃይሎች

ሰዎች ጉልበታቸውን አፍሰው ምርት የሚያመርቱባቸው ማንኛቸውም ተፈጥሮአዊ ነገሮ
ች ለማምረት የሚገለገሉባቸው መሣሪያዎችና የእነዚህ መሣሪያዎች ፈጣሪዎች አበጃዮች እነ
ደገና ፈጣሪዎች የሆኑት ሰዎች እራሳቸው በአንዱ ህብረተሰብ ውስጥ በሚከናወን የምርት
ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ብቻ ሳይሆን ወሳኝ ሚናዎች እንደሚጫወቱ በክፍል አንድ ውስጥ በደ
ረግነው ጥናታችን አይተናል:: የምርት ኃይሎች/የሰዎች የማምረቻ መገልገያዎችና ሰዎች
ራሳቸው/የሚያድጉበት ሁኔታዎች ካልተፈጠሩ ማንኛውም ዓይነት የምርት ዘመቻ ዋጋ ቢስ
ይሆናል:: የምርት ኃይሎች የሚያድጉበት ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ደግሞ ማንኛውም አይነት
የምርት ዘመቻ አውንታ ውጤት ይኖረዋል:: ከዚህ ቀጥለን የደርግ ዘመቻ በምርት ኃይሎ
ች ላይ ያለውን ተጽእኖ በመመርመር ምርትን በማሳደግ ብሎም የኢኮኖሚ ችግሮችን በመፍታ
ት ምን ያህል ''ነፍስ ለማዳን''እንደሚችል እናያለን::

የምርት መሣሪያዎችን እንውሰድ:-

በክፍል 2:2 ስር እንደጠናነው የሰፊው አርሶ አደር የማምረቻ መገልገያዎች



በጣም ወደኋላ የቀሩ ናቸው:: 98 በመቶ የሚሆነውን የአገሪቱን የእርሻ ምርት የሚያ
ፈራው አርሶ አደር የሚጠቀምባቸው የእርሻ ዘዴዎች ሰዎች ከብዙ መቶ አመታት በፊት ይገ
ለገሉባቸው የነበሩ ጥንታዊ ዘዴዎች ናቸው:: አርሶ አደሩ ከመሬቱ አዋጅ በኋላም የአ
ርሻ ምርት እንዲቀንስ ካደረጉት ምክንያቶች ዋናው አርሶ አደሩ ዘመናዊ የእርሻ ዘዴ ለ
መጠቀም አለመቻሉ ነው:: ዘመናዊ የእርሻ ዘዴ ስንል በበሬ በሚጎተት የተሬ ማረሻ ከ
ማረስ በትራክተር ማረስ፣ ከዘልማዱ ዘሮች በምርምር የተመረጡ ዘሮች መጠቀም፣ ማዳበሪያ
ዎችን መጠቀም፣ ዘመናዊ ገድቦችንና ቦዮችን መጠቀም፣ ወዘተ ማለታችን ነው፡፡ ሌላው
ምክንያት ደግሞ የመሬት ድልድል ካለመደረጉ የመሬት ጥበት በመኖሩ ብዙ አርሶ አደሮች
ጉልበታቸውን የሚያፈሱበቸው ማሳዎች አነስተኛ መሆናቸውና ጠርሶም መሬት ያላገኙ አርሶአ
ደሮች መኖራቸው ነው::

የደርግ ዘመቻ ለእነዚህ ችግሮች ዘጠጭ መልስ አይሰጥም፡፡ በአሁኑ ጊዜ የመ
ሬት አዋጁን በሚገባ ስራ ላይ ማዋሉን ቀጥሎ የዚህ ሂደት የመጀመሪያ ክፍል የሆነውን
የመሬትን ድልድል ሥራ መፈፀምና በመሬት ጥበት የተቸገሩ፣ ወይም ምንም መሬት ያላገኙ
አርሶ አደሮች መሬት እንዲያገኙ ማድረግ ሲያስፈልግ ደርግ በዘመቻው ጥያቄውን ጠርሶ አ
ያነሳውም:: እንዲያውም የመሬቱ አዋጅ ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ እንደዋለና አርሶ አደሮች
የመሬት ችግር እንደሌለባቸው አድርጎ ነው ለማቀረብ የሚሞክረው:: ችግርን በመደበቅ
ደግሞ ችግር ሊፈታ አይችልም:: ይህ በአንድ በኩል ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ አርሶ አደሮች የሚገለገሉባቸውን የምርት መሣሪያዎች እንዲያ
ሻሽሉ ማለትም፣ በበሬ ከማረስ በትራክተር እንዲያርሱ፣ ዘመናዊ ማዳበሪያዎችና የተመረጡ
ዘሮች እንዲጠቀሙ፣ ገድቦችና ቦዮች እንዲሰሩ፣ ብሎም ጥንታዊ የእርሻ ዘዴአቸውን በዘመ
ናዊ እንዲለውጡ በዘጠጭ በመርዳት ፋንታ የደርግ ዘመቻ ያተኮረው በባዶና ደረቅ ፕሮፓ
ጋንዳ ነው:: ''ከግል ጥቅም ለጋራ በሚል መንፈስ ጀርቻችን ሳይተሩ እረንጋዴ
እናድርጋቸው!''በሚል ማራኪ ግን ባዶ ፕሮፓጋንዳ የአርሶአደሩን መንፈስ ''ለመለወጥ
ና''በዚህ ''አዲስ መንፈስ''ምርት ለመጨመር ነው የደርግ ዘመቻ ጥረት፡፡ ይኸም
ቢሆን እውነተኛ ችግርን መደበቅ ነው:: በአሁኑ ወቅት ለምርት መቀነስ ምክንያቱ የአ
ርሶ አደሮች ''መንፈስ''አለመለወጥ አይደለም:: የሚገለገሉባቸው የማምረቻ መሣሪያዎ
ቻቸው አለመለወጥ ነው:: የመንፈስ አስተሳሰብ ችግር በአርሶ አደሩ ዘንድ ቢኖርም
እንኳን ለመለወጥ የሚቻለው በደረቅ ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን በዘጠጭ የአርሶ አደሮችን
የማምረቻ መሣሪያዎች በመለወጥ ነው::

> "The only way to solve this problem of the small farmer to improve, so to speak, his mentality - is through the material basis techniqual equipment, the extensive use of tractors and other farm machinery and electrification on a mass scale. This would remake the small farmer fundamentally and with tremendous speed". (Lenin SW Vol 3 P. 570)

እንገዲህ ለምርት አለመጠመር ምክንያቱ የአርሶ አደሩ አስተሳሰብም/ በዘረው የኢት ሁኔታ ምክንያቱ ይህ አይደለም:: አርሶ አደሩ ከፍተኛ የማምረት ፍላጎትና አስተሳሰብ አለው።/ሆነ የማምረቻ መሣሪያዎች አይነት ወደኋላ መቅረት/በዘረው የኢት ተጠባጭ ሁኔታ ዋናው ምክንያት ይህ ነው:: አርሶአደሮች የሚገለገሉበቸው መሣሪያዎች ወደኋላ የቀሩ ብቻ ሳይሆን እንደልበም አይገኙም::/ መፍትሄው ደረቁ ፕሮፖጋንዳ ሳይሆን የአርሶ አደሩን የማምረቻ መሣሪያዎች ማሸሸል ነው:: መፍትሄው አርሶ አደሩ በትራክተሮችና በሌሎች ዘመናዊ የእርሻ መኪናዎች ሊያመርት የሚችልበትን ማቴሪያላዊ ሁኔታ ማመቻቸትና ይህንም በተጨባጭ ማረጋገጥ ነው:: ይህ ማለት ደግሞ ትራክተሮች፣ ማዳበሪያዎች፣ ምርጥ ዘሮች፣ ወዘተ ለሰሬው አርሶ አደር በቀላል ዋጋ ሊገዙ የሚችሉበትን፣ በቀላል ኪራይ ሊከራዩ የሚችሉበትን፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሊደርሱ የሚችሉበትን፣ ወዘተ ሁኔታ ማዘጋጀት ያስፈልጋል ማለት ነው::

የደርገን ዘመቻ ስንመለከተው ገን የሰፊውን አርሶ አደር / 98 በመቶ የሚሆነውን የአገሪቱን የእርሻ ምርት የሚያመርተውን/ የእርሻ ዘዴ ዘመናዊ ለማድረግ መሠረታዊ አሳማው እርምጃ አይወስድም:: እንዳውም አሳማው የማህበራዊና የመንግሥት እርሻዎችን እንጂ ትናንሽ የግል እርሻዎችን ለመርዳት እንዳልሆነ በይፉ ይገልጣል:: የኋለኞችን ምርታቸውን እንዲያሳድጉ ''የሚያበረታታ''መሆኑን ቢገልጥም ዘመናዊ ለማድረግና ለማስፋፋት ይበልጥ ካፒታልና ጉልበት የሚያፈስው በሬ ተኞች ላይ እንደሆነ ከወጣው ፕሮገራምና ከዘመቻው ለመረዳት ይቻላል:: ይህ ፖሊሲ በምርት እድገት ላይ ምን ያህል ተጽእኖ ይኖረዋል? እንመልከት::

ደርግ ትናንሽ የግል እርሻዎችን ''ለማበረታታት'' የሚወስደው እርምጃ 90 በመቶ የሚሆነው ማዳበሪያ በማደልና ፕሮፖጋንዳ በማካሄድ ላይ ያተኮረ ነው::

ደርግ ''በምርት ዘመቻ''ስም በምርቁ ክፍሎቻች የሚያካሄደው ፕሮፖጋንዳ ባይነበቢ የሆነ የኢኮኖሚ ዘመቻ ሳይሆን እድሀሪ የፖለቲካ ዘመቻ በመሆኑ በምርት እድገት በኩል የሚያስከትለው ውጤት አሉታ ነው:: ተራማጅ እንኳን ቢሆን ከተጨባጭ ማቴሪያላዊ ለውጥ ጋር እስካልተያያዘ ድረስ ተጨባጭ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም::



የከበርቴው ህብረተሰብ የእድገቱ የመጠረሻ ደረጃው/የኢምፔሪያሊስት ደረጃ/ከደረሰበት ጊዜ ገን እንዚህ በከበርቴውና በወዝአደሩ መደቦች መካከል የነበሩት የበሳይና የበታች ግንኙነቶች ባደጉት የከበርቴ ህብረተሰቦች እና ባላደጉት/ገና ከፊውዳላዊ የምርት ግንኙነቶች ውስጥ በሚቀዥቁት/ወደ መሆኑም ተሸጋገሩ:: የከበርቴው የምርት ግንኙነት እያደገና የኢምፔሪያሊስት ደረጃው በደረሰበት ወቅት ከአገር አቀፍ ግንኙነቶች አልፎም አለም አቀፍ ግንኙነቶችን መሠረተ::

> "The bourgeoisie cannot exist without constantly revolutionizing the instruments of production, and thereby the relations of production, and with them the whole relations of society". 20 ይላል ማርክስ::

የከበርቴ የምርት ግንኙነቶች በተፈጠሩባቸው ህብረተሰቦች ውስጥ ሁሉ የከበርቴው መደብ መደባዊ ተሰትሰዊ ፍላጎቱን ለማሟላት/ትርፍ በመሰብሰብ ሀብት ለማካበት/በዚህ መልክ የምርት መሣሪያዎች እንዲያድጉ አድርጓል:: እያረጀ ሲሄድ ገን ይህ እርምጃው እየተገታ ሄደ:: የአርስ በአርስ ውድድሩም ለአያንዳንዱ የከበርቴ ተቋሞች እያስቸገረ ሄደ:: ካፒታል/ሀብት/ ከበዙ ከበርቴዎች ወደ ጥቂት ከበርቴዎች እጅ እየገባ ሄደ:: ካለሰፊና እያደገ የሚሄድ ገበያ ሊኖር የማይችለው ከበርቴ የአገሩ ገበያ ጠበበው:: ካለገደብ የለሽ የተፈጥሮ ሀብት መኖር ኢንዱስትሪ ማስፋፋት የማይችለው ከበርቴ የአገሩ ተፈጥሮ ሀብት ለመሰሊ ጥሬ እቃ አነሰው:: ከሚመረተው ምርት የሚገኘው ቀርፍ ከፍ ዘቀ ማለት ብቻ ሳይሆን አስቸጋሪ እየሆነበት ሄደ:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ የከበርቴው መደብ እጁን አገሩን አጣምሮ አልተቀመጠም:: የሀብት ማካበት ፍላጎቱን ለማሟላት ሌሎች መንገዶችን መፈለግ ጀመረ:: አዲስ ገበያዎች አዲስ የጥሬ እቃ ምንጮች አዲስ የኢንዱስትሪ ቦታዎች፣ ወዘተ ለማግኘት እንደ አበዶች ውሽ በአለም አቀፍ ደረጃ መሯሯጥ ጀመረ:: የሩጫው አቀጣጫ ወደየት ነበር? የሩጫውስ ውጤት ምን ሆነ?

> "The need of a constantly expanding market for its products chases the bourgeoisie over the whole surface of the globe. It must nestle evereywhere, settle everywhere, establish connexions everywhere....It compels all nations, on pain of extinction, to adopt the bourgeois mode of production, it compels them to introduce what it calls civilization into their midst ie,ie to become bourgeois themselves. In one word, it creates a world after its own image". 21

ማርክስም እንደሚለው የከበርቴው መደብ አዲስ ገበያዎች አዲስ የጥሬ እቃ ምንጮች አዲስ የኢንዱስትሪ ቦታዎች ለማግኘት የሮጠው በእድገት ደረጃ ከእርሱ በታች የነበሩት ገናኛ ሪውዳላዊ የሆኑበቸው ወደኋበሩት-ህብረተሰቦች ነበር:: በዚህም ከሰማ

በመጀመሪያ በየቦታው ከመሬት አዋጁ ጋር ተያይዘው በግዱም ሆነ በውዴ በችኮላና በሆያ ሆዩ የተቋቋሙት ደርግ ብዙ የሚያወራላቸውና ከፍተኛ አተኩሮ በመስጠት ለመርዳት ቃል ኪዳን የሚገባላቸው የህብረት እርሻዎች በጥረታቸው አነስተኛ ከመሆናቸው ሌላ በልዩ ልዩ ተገባራዊና ጠበጥ ሁኔታዎች ፈራርሰዋል:: የተረፉትም በተወሰኑ አካባቢዎች የሚገኙ ብቻ ባይሆን በቴክኒካል፣ በአስተዳደርና በማቴሪያላዊ ችግሮች የተነሳ ሊሰሩ የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል:: ይህንን በክፍል 2:2 ጥናታችን ውስጥ በዝርዝር አስይተናል:: እዚህ አንመለስበትም::

ከዚህ ጠበጥ ሁኔታ ስንመለከተው በአሁኑ ወቅት መደረግ የሚገባው በአንድ በኩል ትናንሽ ገሳዊ አርሶ አደሮች የግል እርሻቸውን ለማዳበር እንዲችሉ በሁሉም ደረጃ መርዳት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የነፃ ህብረት ፈጥረው በጋራ እንዲያርሱ ማድረግ ነው:: የደርግ የምርት ዘመቻ ግን በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ድርጅታዊና ፖለቲካዊ ብስለት በሳቸው የህብረት እርሻዎች እንደተጥለቀለቀች አድርጎ ያያል:: በአንድ በኩል ጥረት፣ ብቃትና ትእግሥት በጎሳበት መንገድ የህብረት እርሻዎችን ማቋቋምና በሌላ በኩል ደግሞ ትናንሽ የግል እርሻዎችን ለመርዳት ያልተቆጠበ ጥናት ማድረግ በሚያስፈልግበት በአሁኑ ወቅት ደርግ የምርት ዘመቻ የሚሠራው ተቃራኒውን ነው::

> "The pursuit of self-enrichment is an obstacle to the development of collective farming".
>
> "We give priority to collective welfare over individualistic interests".
>
> "There is no doubt that collective farming will be enhanced by the support the government gives it. In accordance with its capability, the government will provide long-term loans to the development of collective farming. It will provide fertilizers will levy lower taxes on collective farms, and will provide various types of services at very low cost". (The campaign P. 10)

ደርግ ለማስመሰል እንደሚሞክረው አገሪቱ በህብረት እርሻዎች ተጥለቅልቃና የዘመቻው አመራር አብዮታዊ ሆኖ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ቢሆን ኖሮ ይህ የደርግ ''ቃልኪዳን'' ምርት ለማሳደግ አወንታዊ ሚና በኖረው ነበር:: አሁን ባለው ሁኔታ ግን አመራሩ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ስር በመሆኑና በአገሪቱ ያሉት የህብረት እርሻዎች ከጥር የማይገቡ በመሆናቸው በእነርሱ ላይ ሊፈስ የታሰበው ማቴሪያልና ሊደረግ የታቀደው የማምረቻ መሣሪያዎች ለውጥ በምርት እድገት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተጽእኖ የውቅያኖስን ውሃ በጭልፋ ጠልፍ ለመጠረስ ከሚደረግ ጥረት ጋር ተመሳሳይ ነው:: ከዚህም ሌላ ያለውንና ቢረዳ በምርት እድገት ላይ ከፍተኛ ውጤት ሊያስከትል የሚችለውን የበሬውን አርሶ አደር



የግል እርሻ ለመርዳት መወሰንና የሌለን እንዳለና እንዳይፈጠር አድርጎ ከፍተኛ አተኩሮ በማድረግ በማንኛውም ደረጃ አረዳለሁ ብሎ ማስወቅ ያልጠበጠ ነገር ለማድረግ ብሎም መቁጠት ይሆናል::

የመንግሥት እርሻዎችንም በሚመለከተው በኩል ''የተለየ አተኩሮ'' እንደሚሰጣቸው ዘመቻው ይናገራል:: በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙት ትራክተሮች ከሞላ ጎደል በጥቅም ላይ የሚውሉት በመንግሥት እርሻዎች ላይ ነው:: በእርሻ ምርት ስም በሚንቀሳቀሰው ካፒታል፣ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ወዘተ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው እነዚህ የመንግሥት እርሻዎች ናቸው:: እነዚህ እርሻዎች እንደኛ በጥረታቸው አነስተኛ በመሆናቸው፣ ሁለተኛ የሚያመርቱት አብዛኛው ለውጭ ገበያ የሚውል በመሆኑ፣ ሶስተኛ የሚንቀሳቀሱት ብዙ የአስተዳደር ጉድለቶች ባሉት ብቻ ባይሆን የምርትን ማደግ በሚቃወም አድሃሪ ቢሮክራሲ ስለሆነ ምንም አይነት ''ልዩ አተኩሮ'' ተደርጎ የተፈለገውን ያህል የካፒታል ስምሪት፣ የጉልበት መፍሰስና የቴክኒካል መሻሻል ቢደረግ መሠረታዊ የሆነ የምርት እድገት ለማሳየት አይቻልም::

ከዚህም ሌላ አሁን በስራ ላይ ያሉትም ሆኑ በእርዳታና በግዢ ከሶሻሊስት አገሮች በመግባት ላይ ያሉት የእርሻ መሣሪያዎች አሮጌዎች በመሆናቸው አዘውትሮ የሚመጣ የብልሽት ችግር ሊፈጠር ይችላል:: በመገጣጠሚያዎችም ሆነ በገጣጣሚዎች በተሳሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ መገኘት ስለመቻል ደግሞ የመሣሪያዎች አዘወትረው ሥራ እንግፌት ያደርጋቸዋል:: በዚህ ሁኔታ የእርሻ ምርት የገብታዊነት በህሪ ይኖረዋል:: እስከአሁን የታየው ሁኔታ ይኸ ነው:: ብዙ የእርሻ መኪናዎች መገጣጠሚያዎችና ገጣጣሚዎች በተሳሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊገኙ በለመቻላቸው በእርሻ ቦታው ከጥቅም ውጭ ሆነው እንደተገተሩና ለምርት መቀነስም ምክንያቶች እንደሆኑ የእርሻ መሃንዲሶች ይናገራሉ:: ይህ ችግር ሊፈታ የሚችለው ኢት የራሷ የእርሻ መኪናዎች ፋብሪካ፣ የራሷ መገጣጠሚያዎችና ገጣጣሚዎች ስናፈራ ነው:: ይህን ደግሞ ደርግ አሁንም ሆነ ለወደፊት ሊያደርግ አይችልም::

በጥሩ ደርግ የእርሻ ምርትን ለማሳደግ የሚያደርገው ዘመቻ በጠቅላላው የእርሻ መሣሪያዎችን ለማሻሻል የሚወስደው ጠበጥ እርምጃ የለም:: የሚያደርጋቸው ለውጦችና የሚሰጣቸው እርዳታዎች የሚያተኩሩት የአገሪቱን 2 በመቶ የሚሆነውን የእርሻ ምርት በሚያመርቱ በመንግስትና በህብረት እርሻዎች ላይ ነው:: በዘመቻው ሰበብ የሚሰበሰበው ማቴሪያል ጉልበትና ቴክኖሎጂ ከሞላ ጎደል የሚውለው በእነዚህ ዘርፎች ላይ ነው:: አመቺው ሁኔታ ሁሉ ለእነዚህ ክፍሎች ነው:: እነዚህ ዘርፎች ደግሞ በጥረታቸው ማነስ፣ የሚያመርቱት ምርት ለውጭ ገበያ መሆኑ፣ አስተዳደራቸው፣ ብቃት በሌለውና አድሃሪ ቢሮክራሲ መሆኑ፣ የመኪናዎች ብልሽቶች መኖርና የመገጣጠሚያዎች መጥፋት፣ ወዘተ በምርት

እድገት ላይ የሚኖራቸው ተስእና ዝቅተኛ ነው:: 98 በመቶ የሚሆነውን የአገሪቱን የአርሻ የሚያመርተው ሰፊው አርሶ አደር ግን በዘመቻው መረሰቱ ብቻ ሳይሆን የዘመቻው አሳማ ሆኗል:: የአርሻ መሣሪያዎችን ሊያሻሽል የሚያስችሉት ሁኔታዎች አልተፈጠሩለትም:: እንደዘመቻው ከሆነ ''ከተከፈቱለት'' አንዳንድ ሁኔታዎች ዋናው ማዳበሪያ የማግኘት ችሎታ ነው:: ይኸም ቢሆን በዋጋውና በወለድ ከፍተኛነትና በመከፈያው ጊዜ ማጠር የተነሳ ምንም ሊደርሰው አይችልም:: ሰፊው አርሶ አደር በዚያው በረጃው የምርት መሣሪያውና ዘዴው ማምረቱን ይቀጥላል ማለት ነው:: ይኸ እስከሆነ ድረስ ደግሞ የተለፈፈውን ያህል ቢለፈፍ የፈለገውን ያህል አብዮታዊ ፕሮግራም ቢወጣና ዘመቻ ቢደረግ ምርትን ለማሳደግና የኢኮኖሚ ችግሮችን ለመፍታት አይቻልም::

> "It is impossible to increase the production and collection of grain and the storage and delivery of fuel except by improving the condition of the peasantry, and raising their productive forces." (SW, vol 3 P. 599 Lenin)

በኢንዱስትሪም በኩል ያሉትን በሙሉ ችሎታቸው እንዲሰሩ እንዲስፋፉና ተጨማሪም አዲስ ኢንዱስትሪዎች እንደሚቋቋሙና የሰፊውን ህዝብ የሸቀጥ ፍላጎት ለማሟላት እንደሚሰራ የደርግ ዘመቻ ይናገራል:: ጥሩ ነው:: ግን በዚህ በኩል የሚደረገው ውጤት በእርግጥ ''ነፍስ ለማዳን'' የሚደርስ ነወይ?

ያሉት ኢንዱስትሪዎች የሚንቀሳቀሱባቸው መኪናዎች እጅግ በጣም ያረጁና ወደኋላ የቆዩ በመሆናቸው አብዛኛዎቹ ከተወሰነ ጊዜ በላይ ሊሰሩ የማይችሉ ናቸው:: ከዚህም ሌላ በብዙ ኢንዱስትሪዎች በብልሽት ምክንያት የተገተሩ መኪናዎች መገጣጠሚያቸው በአገር ውስጥ ገበያ ላይ ስለማይገኝ በውጭ አገር ገበያ ላይ መግዛት አለባቸው:: ይኸ ደግሞ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊሰራ አይችልም:: ሊገኝ ሳይገኝ መቻሉ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ሂደቱ ጊዜ ይወስዳል:: ስለሆነም የአሁኖቹ ኢንዱስትሪዎች በሚንቀሳቀሱባቸው መኪናዎች በሀሪና በመኪናዎች ላይ የሚደርሱን ብልሽቶች በቀላሉና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማቃናት ስለማይቻል በሙሉ ችሎታቸው ማለትም ያላቸውን መኪናዎች ሁሉ በማንቀሳቀስ በተቻለ መጠን ረጅም ጊዜ እንዲሰሩ ለማድረግና በዚህ መንገድ የኢንዱስትሪ ምርትን ለመጨመር አይቻልም::

ከዚህም ሌላ አሁን ያሉት ኢንዱስትሪዎች የሚጠቀሙት ጥሬ እቃዎች የእርሻ ውጤቶች በመሆናቸውና የሚንቀሳቀሱባቸውም ሃይሎች/ማገዶች/ የደን ውጤቶች በመሆናቸው የሆነውን ያህል የምርት እድገት በደርጉ ቁጥር በአሁኑ የተቀነበበረ ክፍፍልና ቁጥጥር በሚደረግበት ወቅት ለህዝቡ በሚያስፈልጉ የጥቅም እቃዎች ላይ እጥረት ያስከትላሉ:: በኢንዱስትሪያ



ኛና በሸምቶ አዳሪው የከተማው ሠርቶ አደር መካከል ሽሚያ ይፈጠራል ማለት ነው:: ይኸም በልዩ ልዩ አቅጣጫዎች የሚደረጉትን ''የምርት ጭማሪዎች'' እዚያው በዚያው እንዲጠጡና ችግሩ ባይፈታ ነፍስም ባይዳን እንዲቀር ያደርጋል::

አሁን ያሉትን ኢንዱስትሪዎች ማስፋፋት የሚለውም በአጭር ጊዜ ነፍስ የሚያድን አይደለም:: አሁን ያሉትን ማስፋፋት ማለት አዲስ የማምረቻ ህንፃዎች በመገንባትና አዲስ መኪናዎች በመግዛት ወይ አሁን ባሉባቸው ቦታዎች ወይ ደግሞ በሌሎች ቦታዎች ተቀጥያዎች/ቅርንጫፎች/ መክፈት ማለት ነው:: በዚህ በኩል ይኸ አዲስ ኢንዱስትሪዎች ማቋቋም ከሚለው ጋር የሚሄድ ነው:: እነዚህ ሁለቱ ''ነፍስ ለማዳን'' የሚደረጉት ዘመቻዎች ባይሆኑ የረጅም ጊዜ እቅዶች ናቸው:: የካፒታሉና የምርት መሣሪያዎች መገኘት ጉዳይ በተለይ የኋለኛው አመታት ሊወስድ ይችላል:: ስለሆነም በእዚህ መንገድ በኢት የተፈጠረውን የኢንዱስትሪ ሸቀጥ እጥረት በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈትቶ ''ነፍስ አድናለሁ'' በማለት የሚያካሄደው ዘመቻ ፍርሽና ፈጽሞ በተጠበጥ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ነው:: እኛም ለማረጋገጥ የምንፈልገው ኢንዱስትሪዎች ቢስፋፉ ችግር አይፈቱም የሚለውን ሳይሆን ደርግ ከሁለት አመት በነስ ጊዜ ውስጥ ኢንዱስትሪ አስፋፍቶ የኢትን ህዝቦች የኢኮኖሚ ችግር እፈታለሁ በማለት የሚያደርገው ዘመቻ ከሃቅ የራቀና ከማታለያነት ሊያልፍ የማይችል መሆኑን ነው::

## የምርት አምራቾችን /የሰዎችን/ ጉዳይ እንውሰድ:-

በአንድ ህብረተሰብ የምርት ሂደት ውስጥ ሰዎች የሚጫወቱት ሚና ወሳኝ ነው:: ሰዎች የሚጫወቱት ሚና ደግሞ በላቸው ነፃነት ይወሰናል:: ነፃነት ካላቸውና የምርታቸው ጌቶችና ተጠቃሚዎች ከሆኑ ያላቸውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም በከፍተኛ የስራ መንፈስ ምርታቸውን ለማሳደግ ይሰራሉ:: አዲስ አሰቦች ማፍለቅን፣ የተሰበቱ አሰቦችን መንቀፍን፣ መወያየትን፣ መከራከርን፣ መፃፍን፣ ማንበብን፣ መመራመርን፣ ነፃ እርምጃ መውሰድን ወዘተ ሳይፈሩ እንደልብ አሰባቸውን እያንሸራሸሩ ለማምረት የሚገለገሉባቸውን መሣሪያዎች ባያቋርጡ ያሻሽላሉ:: ከልማዳቸውና ከእርስ በእርሳቸው በመማርም አዲሶች ይፈጥራሉ:: ሙሉ ነፃነት ካላቸው በሷቸው ብቻ ሳይሆን የምርት መሣሪያዎቻቸውን እያሻሻሉ አዳዲሶች እየፈጠሩ በአብዮታዊ ስሜት በመስራት ምርታቸውን ያሳድጋሉ:: ነፃነት ከሌላቸው ግን እነዚን ወደኋላ በቀሩ የምርት መሣሪያዎች ይቀሩና እነዚን መሣሪያዎቻቸውን እያሻሻሉ አዲሶች አየፈጠሩ ሊሰሩና በጣም ያረጁ የምርት መሣሪያዎች በመጠቀም እነዚን የማምረት ወኔ ስለማይኖራቸው ለምርት ማደግ ችግር ይፈጠራል:: ለማስታወስ ያህል ነው እንጂ ይኸን ሁሉ በክፍል አንድ ውስጥ አጥንተናል::

በዛሬይቱ ኢት ሰፊው አምራች አርሶአደርና ወዝአደር ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች የሉ
ትም፡፡ ለመወያየት፣ አስቡን ለመግለጥ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ተሳትፍ ለማድረግ፣ ወ
ዘተ ወዝአደሩ በፋብሪካ አርሶአደሩ በእርሻ ላይ ያለው ነፃነት ተፃፍኖበታል፡፡ ልሳኑ
በቢሮክራሲው የበላይነት ማገኘት ተዘግቶበታል፡፡ ድርጅቶቹ ወይ እየፈረረሱ እንዳልነበሩ
ሆነውበታል ወይ እየተሰቀወጡ የአድሃሪያች መመሸጊያ ሆነውበታል፡፡ አብዮታዊ መሪያች ወ
ይ ተረሽነዋል ወይ ታስረዋል ወይ ተሰደዋል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ተጠቃለው የወዝአ
ደሩንና የአርሶአደሩን የማምረት፣ የማሸሸልና አዲስ የመፍጠር ችሎታዎች እንዲዳከሙና እን
ዲታፈኑ አድርገዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ለምርት እድገት ማዘቅዘቅ የአምራቾች ዲሞክራሲያዊ መብቶች አለመከ
በር አንደኛውና ዋናው ምክንያት ሆኖ ሳለና ምርትንም ለማሳደግ በቅድሚያ መወሰድ የሚገባ
ው እርምጃ የሰፊውን ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ ማክበር ሲሆን የደርግ የምር
ት ዘመቻ ይህን ችግር አይቶ እንዳላየ እያለ እንደሌለ አድርጎ ይወስደዋል፡፡ ይህን አ
ቢይና ወሳኝ ጥያቄ በዚህ መልክ ማየት ደግሞ የደርግ የምርት ዘመቻ ተገበራዊ አለመሆኑን
ብቻ ሳይሆን ደርግ ዘመቻውን ተገበራዊ ለማድረግ ፍላጎት እንደሌለው ያመለክታል፡፡ ስጋውን ሰጥ
ቶ ቢላዋውን መንሳት እንዳሉ ነውና፡፡

የደርግ የምርት ዘመቻ የአምራቾን ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች ያለገደብ አውቆ ለአምራ
ቹ የማምረትና የመፍጠር ችሎታ እንዲሁም እንደልብ ሲንቀሳቀስበት የሚያስችለው አመቺ ሁኔ
ታ መፍጠር በሚያስፈልገበት በአሁኑ ወቅት ተቃራኒውን ያደርጋል፡፡ አርሶ አደሮችን ወዝ
አደሮችን "የምርት አጥቃረኞች" "የአድሃሪ ተባባሪዎች" "ቀኝ መንገደኞች" ወዘተ በሚል መሠ
ረተ ቢስ ክስ ይወነጅላል፡፡ያሸብረል፡፡ በተለይ አርሶ አደሮችን "የከበርቴው ስርአት
ምንጠቾ" "ስንፎች፣" "ከአጥቃረኛ ነጋዴዎች ጋር ተባባሪዎች፣" "አደገኞች" ወዘተ በሚል እየወነ
ጀለ አስፈላጊውን እርምጃ እንደሚወስድበቸው የሚዝት ዘመቻ ነው፡፡ የሚወስደውም እርምጃ
ከመሬት ማጣት አንስቶ እስከ መረሸን ይደርሰል፡፡ ታዲያ በእንደዚህ አይነት የሽብርና
ያልተረጋገጡ ሁኔታ ወዝ አደሩና አርሶ አደሩ እንዴት አድርገው ነው አሁን ያሏቸውንም
መሣሪያዎች ሆነ አዳቦች እየፈጠሩ ምርታቸውን ለማሳደግ የሚችሉት? መልሱ አሉታ
ነው፡፡

ከዚህም ሌላ የእርሻ ገብርን እየቀነሱ፣ የወዝአደሩን ደመወዝ እየጠመሩና የእርሻ
ንና የኢንዱስትሪ ሸቀጦችን ዋጋዎች እያስተካከሉ በገጠርና በከተማው መካከል የሚደረገው
የንግድ ልውውጥ የተዛባ እንዳይሆን እየጣሩ የወዝአደሩንና የአርሶ አደሩን የማምረት
ፍላጎትና ወኔ ማጠናከር በሚያስፈልገበት በአሁኑ ወቅት የደርግ ዘመቻ የሚሰራው ተቃራኒው



ን ነው፡፡ ዘመቻውን ተከትሎ ደርግ በሰፊው አርሶ አደር ላይ በነፃ ብር ገበር ጠምሯ
ል፡፡ በእለት ተእለት ጥቅም በሚውሉ የኢንዱስትሪ ሸቀጦችም ላይ ዋጋ ጠምሯል፡፡ ለዘ
መቻው ስራ ማስኬጃም 71 ሚሊዮን ብር ህዝቡ እንዲያዋጣ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ መዋጮው በ
ውዴ ሳይሆን በግድ ነው፡፡ እነዚህ እርምጃዎች በአንድ በኩል የእህል ዋጋ መጠመርን ስ
ለሚያስከትሉ ደመወዝ ዝቅተኛ በሆነው ወዝአደሩ ዘንድ የእህል እጥረት ያስከትላሉ፡፡ በ
ሌላ በኩል ደግሞ አርሶ አደሩ በኢንዱስትሪ ሸቀጦች ዋጋ መጠመር የተነሳ ፍላጎት ቢኖረው
ም ለመግዛት የገንዘብ አቅሙ ስለማይፈቅድለት በአርሶ አደሩ ዘንድ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች
እጥረት ይኖራል፡፡ በመጠረሻም ዘመቻው ለመፍታት አሳማው አድርጎ የወሰዳቸው የምግብና
የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ችግሮች ባይፈቱ ይቀራሉ፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ሲደመሩ በደርግና በምርት አምራቾ ሃይል መካከል መታጋር
የጀመረውን ገንቾነት ያባብሱታል፡፡ የዚህም ገንቾነት መሸከር ለደርግ የምርት ዘመቻ
አለመብከት ራሱን የቻለ ሌላ ምክንያት ነው፡፡

## 3፡1፡2፡3 ዘመቻውና ወጪው

የዘመቻው መምሪያ ስለ ዘመቻው ወጪ ማለትም ዘመቻውን ከስራ ላይ ለማዋል የሚያስ
ፈልገው ገንዘብ እንዴትና ከየት እንደሚገኝ በቀጥታ አይገልጥም፡፡ ስለሆነም በተጥታ ስ
መቶች ያስቸግራል፡፡ በልዩ ልዩ መግለጫዎችና በመመሪያውም ጭምር ከተሰነዘሩት ነገሮች
ችና በተጠባጭም ደርግ ከወሰደው እርምጃ ሲታይ ግን የዘመቻው ማካሄጃ ገንዘብ የሚመጣው
እንዲም በብድር ከውጭ አገር መንግሥታት ሁለትም በመዋጮና በገብር መልክ ከሰፊው ህዝብ
መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአርሶ አደሩ የተጠመረው ገብር፣ህዝቡ እንዲያዋጣ የተወሰነው 71 ሚሊዮን ብር፣
ከሶሻሊስት አገሮች ጋር በመተባበር 600 ሚሊዮን ካፒታል የሚኖራቸው የስኳር፣ የጠርታ
ጠርቅና የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለማቋቋም የወጣው እቅድ፣ በአዲስ አበባ ተከፍቶ የነበረው
ታላቅ ባዘር፣ ወዘተ የዚህ ዘመቻ አፃ ከሰፊው ህዝብ ጫንቃና ከውጭ አገር እርዳታ እንደ
ማይለፉ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ዘመቻው የሸቀጦችን ዋጋ መናር ያስከትላሉ፡፡ አርሶ አደሩ
የገብርና የመዋጮዎች መጠመር የሸቀጦችን ዋጋ መናር ያስከትላሉ፡፡ አርሶ አደሩ
የተጠመረበትን ገብርና የተጫነበትን መዋጮ ለመክፈል እንዲሁም የሚያስፈልጉትን የኢንዱስት
ሪ ሸቀጦች ለመግዛት ይችል ዘንድ ያለው አንዱ የእህሉን ዋጋ መጠመር ነው፡፡ በሸቀጥ
ንግድም በልዩ ልዩ ደረጃ የተሰማሩ ነጋዴዎችም የተጠመረባቸውን ገብርና የተጫነባቸውን መ
ዋጮ ለመክፈል እንዲሁም የሚገዙ ሸቀጦች ለመግዛት ይችሉ ዘንዱ የሚሸጧቸውን የኢንዱስትሬ

ሸቀጦች ዋጋ መንግሥት ከደረጋቸው ጭማሪዎች ሌላ ይጠምራሉ፡፡ በአዚህ መልክ የሸቀጦች ዋጋ ይንራል ከዋጋ መናር ጋር ደግሞ የሸቀጦች እጥረት ይከተሳል፡፡ በከተሞች በጕልበተ በስተቀር ሌላ መንገድ የሌለውና ደመወዙ ከሸቀጦች ዋጋ እድገትና መቀጦች ጋር እየተስተካከለ የሚያድገው ወዝአደሩ የመግዛት ችሎታው እየቀነሰ ስለሚሄድ በሸቀጦች እጥረት በጠቅላላውና በምግብ ሸቀጦች በተለይ ይበልጥ ይሰቃያል፡፡ አርሶ አደሩም በምርት መሣሪያዎቹም ወደኋላ መቅረት የተነሳ የፈለገውን ያህል ምርትን ለማብዛት ስለማይችልና በኢንዱስትሪ በአርሻ ሸቀጦች የልውውጥ ሚዛን ለፊተኞቹ በማዳላቱ የሆነውን ያህል ዋጋ ለመጠመር ጥረት ቢያደርግም የሚያስፈልጉትን የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ሁሉ ሊገዛ አይችልም፡፡ በገጠርም የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት ይናራል፡፡ የዘመቻው ወጪ በህዝቡ ላይ መጫኑ የሸቀጦች እጥረት እንዲባባስ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ይኸ ደግሞ የወዝአደሩና የአርሶ አደሩን አንድነት ያሸክራል፡፡

የብድር መጠመር ደግሞ የአገሪቱን ኢኮኖሚ በብድር ሰጪ አገሮች ላይ ጥገኛ እየሆነ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ ይህ የጥገኝነት ግንኙነት በተፈው የአገሪቱ አዳ እየጠመረ፣ የአገሪቱ የውጭ ንግድ በብድር ሰጪ አገሮች መካከል ብቻ እየተወሰነ የአገሪቱ የውጭ ንግድ ሚዛን የተበላሸ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡ አስፈላጊውን ብድር ለማግኘትና እያደገ የሚሄደውን የውጭ አዳ ለመክፈል ሲባል ደግሞ የውጭ ንግድ ሸቀጦች ቡና፣ ስኳር፣ የቅባት እህሎች ወዘተ ላይ ብዙ የካፒታልና የሰው ጉልበት እንዲፈስ ከመደረጉም ሌላ በአገር ውስጥ ገበያ ላይ እየተነጠቁ ወደ ውጭ እንዲላኩ ይደረጋል፡፡ ቀስ በቀስም በአገር ውስጥ የሚቋቋሙት ኢንዱስትሪዎችን ዘመናዊ አርሻዎች ለእርዳታ ሰጪ አገሮች ጥቅም በሚሰጡበት መንገድ ይቀየሳሉ፡፡ የሰፊው ህዝብ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮችም በይፋት ይቀራሉ፡፡

ከዚህ በላይ በጥሩ ለማስየት እንደሞከርነው የደርግ የምርት ዘመቻ በምርት ሂደት ውስጥ ወሳኝ በሳቸው የምርት ሃይሎች እድገት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ እዚህ ግባ የማይባል ነው፡፡ ዘመቻው አምራቾች ሰፊ ማቴሪያላዊ ድጋፍ፣ ሰፊ ማበረታቻዎችና ሰፊ ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች አግኝተው የምርት መሣሪያዎቻቸውን እያሻሻሉና አዳዲስ እየፈጠሩ የማምረትና የመፍጠር ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ስለማያደርግ በምርት እድገት ላይ ደርግ የሚደነፋውን ያህል ተገባራዊ ውጤት አይኖረውም፡፡ ''አመርታ''እያሰኘም፡፡ ይህ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ አገሪቱን የተበተቧት የምግብና የኢንዱስትሪ ሸቀጦች፣ የቤቶች፣ የት.ቤቶች፣ የሆስፒታሎች፣ የማገዶ፣ ወዘተ እጥረቶች የንግድና የመሳሰሉ ችግሮች ወዘተ በአሁኑ አመራር በአሁኑ መንፈስ ተጠባጭ ሁኔታ ደርግ እንደሚለው ዘላቂና አጥጋቢ በሆነ መንገድ ሊፈቱ አይችሉም የደርግ ፕሮግራም የወረቀትና የማታለያ ዘመቻ ሆኖ ይቀራል፡፡



## 3.2. ዘመቻውና የአዲሱ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ

የአዲሱ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ የአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውጤት ነው፡፡ አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ደግሞ በኢምፔሪያሊዝም ዘመን በአደጉታቸው ወደኋላ በቀሩ ከፊል ፊውዳልና ከፊል ከበርቴ ህብረተሰቦች ውስጥ በወዝአደሩ አመራር በአርሶአደሩና በሌሎች ፀረ ቦስት ሃይሎች ከበርቴው ጥምር አጋርነት የሚካሄድ ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮ ካፒታሊስት አብዮት ነው፡፡ ከዚህ ሂደት መፈፀም በኋላ የሚፈጠረው ሳአሳይ መቀቀርም እነዚህ ፀረ ቦስት ሃይሎች ሁሉ የሚሳተፉበት በወዝአደሩ መደብ ፓርቲ የሚመራ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ይሆናል፡፡ በዚህ ወቅት ከዚህ ሳአሳይ መቀቀር ጋር ተጣጥሞ የሚሄደው የኢኮኖሚ መሠረት የከበርቴው የኢኮኖሚ ሰርአት ነው፡፡ ከህበረተሰቦች የእድገት ህገጋት አንፃር ስንመለከተው ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ''የከበርቴው''ወይም ''የገበሬው''እየተባለ የሚጠራውም ለዚሁ ነው፡፡

የአዲሱ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ በመሠረቱ የከበርቴ ኢኮኖሚ ይሁን እንጂ ''ከአውሮፖው'' ወይም ''ከአሮጌው'' የከበርቴው ኢኮኖሚ ይለያል፡፡ በገል፣ ሳአሳይ መቀቀሩ በከበርቴው መደብ ቀጥጥር በሆነበት በ''አሮጌው''የከበርቴ ኢኮኖሚ ሰርአት ውስጥ የህብረተሰቡ የምርት ማፍሪያ ሀብቶች በገል፣ በተለይ በጥቂት ከበርቴዎች ባለቤትነት ስር በመሆኑ ካፒታሊዝም ካሳንዳች ቀጥጥር በነፃ ያድጋል፡፡ እንዲህ አይነቱ እድገት ደግሞ የትንሾችን በትልቶች መገዛትንና መቀጥን፣ የብዙሃኑን መበዝበዝ መደህየትን፣ በመሠረቱም የሀብትን አያደር በጥቂት ገለሰቦች ቀጥጥር ስር እየተከማቸ መሄዱን ያስከትላል፡፡

ሳአሳይ መቀቀሩ በወዝአደሩ መደብ ፓርቲ በሚመራ ህዝባዊ መንግሥት ቀጥጥር ስር በሆነበት በአዲሱ የዲሞክራሲ ከበርቴ ኢኮኖሚ ገን የህብረተሰቡ ዋና ዋና የምርት ማፍሪያ ሀብቶች በመንግሥት ቀጥጥር ስር ይሆናሉ፡፡ ይኸ ማለት ገን ካፒታሊዝም ተደምስሶ በሸሊዝም ተመሰረተ ማለት አይደለም፡፡ የህብረተሰቡ ዋና ዋና የምርት ማፍሪያ ሀብቶች በወዝአደሩ መደብ በሚመራው ህዝባዊ መንግሥት ቀጥጥር ስር መዋል ማለት ካፒታሊዝምን በመንግሥት ደረጃ/ እስቴት ካፒታሊዝም/ ወይም በመንግሥት ቀጥጥር ስር ማሳደግ ማለት ነው፡፡ ይኸ ማለት ደግሞ ህዝባዊ መንግሥት በቀጥጥሩ ስር ያደረጋቸውን የምርት ማፍሪያዎች በመጠቀም ብቻ ካፒታሉን እየተቆጣጠረ ሲያሳድግ ከእነዚህ ውጪ የሆኑትን የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ገንነቶች በእንጭጭነታቸውም ሆነ በጉልምስናቸው ይደመስሳቸዋል ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም አስፈላጊውን የማቴሪያልና የቴክኒክ እርዳታ፣ እንዲሁም የልውውጥ ነፃነት እየሰጠ ተዝናንተው እንዲሰሩ ይረዳቸዋል፡፡ ይህ የሚደረገው ደግሞ የአዲሱ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ ለሶሻሊዝም መገንባት የሚያስፈልጉትን የማቴሪያላዊ መሠረቶች የሚጣለበት ሰርአት ስለሆነ

የምርት ሃይሎችን እድገት ለማፋጠን ነው:: የአዲሱ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ አበይና ታሪካዊ ተግባር ካፒታሊዝምን በግልና በመንግሥት ደረጃ እንደየሁኔታው ችሎን በማውጣት ሙሉ በሙሉ ለቀቅ ባይሆን በቁጥጥር ስር የዋለ /ሬጉሌትድ ካፒታሊዝም/ የዘበርቴ ኢኮኖሚ በማሳደግ ለሶሻሊዝም ማቴሪያላዊ መሠረቶች መጣል ነው:: ስለሆነም ወዲያውና በማንኛውም ሁኔታ ፀረ ካፒታሊስት ሶሺሊስት ኢኮኖሚ ሊሆን አይችልም:: ኢኮኖሚያቸው ወደኋላ የቀረ የገበሬ ኢኮኖሚ በሆኑ አገሮች ካፒታሊዝም በቁጥጥር ሳይውል ለሶሻሊዝም ማቴሪያላዊ መሠረቶች መጣል አይቻልም:: በዚህ መልክ ለሶሻሊዝም መሠረት ለመጣል የሚወስደው ጊዜ በህዝባዊው መንግሥት በሚደረገው ጥረትና በምርት ሃይሎች እድገት ፍጥነት እንጂ በሰዎች ፍላጎት አስቶዶም የሚወሰን አይደለም:: እነሌኒን በ1921 ዓ ም ባወጡት ''አዲሱ የኢኮኖሚ መምሪያ'' እነማኦ በ1940 ባወጡት የአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መምሪያ በዝርዝር ያረጋገጡት ይኸው ካፒታሊዝም በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሳይውል የሶሻሊዝምን መሠረት መጣል አለመቻልና ይኸም ተግባር በአንድ ሌሊት ወይም በአንድ አመት የሚፈፀም ባይሆን ረዘም ያለ የተወሰነ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ነው::

ከአዲሱ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ ይዘት አንፃር ስንመለከተው የደርግ ዘመቻ የዚህ የኢኮኖሚ እድገት ተፃራሪ ሆኖ እናገኘዋለን::

በዛሬይቱ ኢት የምርት ሃይሎች እድገት ወደኋላ የቀረውና የሸቀጦች እጥረት በየደረጃውና በየህዝቡ የሚደርሰው የካፒታሊስት ኢኮኖሚ በማደጉ አይደለም:: ባለማደጉ ነው:: ስለሆነም የኢትን ህብረተሰብ ኢኮኖሚ እድገት ህጋጋት በመከተል በግል ከበርቴው ክፍል በገበሬው ጥምር የሚከናወነውን የሸቀጥ ምርት፣ የንግድ ልውውጥ እየተቆጣጠሩና እያበረታቱ እንዲዳብር ማድረግ ያስፈልጋል:: አምራቾች የሚያመርቷቸውን በቀላሉና ፍሬያማ በሆነ መንገድ እንዲለዋወጡ ማመላለሻዎችን፣ ገበያዎችን፣ ማስፋፋትና፣ የእንቅስቃሴና የልውውጥ ነፃነቶችን መስጠት፣ የበለጠ እንዲያመርቱ በካፒታልና በጥሬ እቃዎች መርዳት ያስፈልጋል:: በጥሩ ካፒታሊዝምን እየተቆጣጠሩ ማስፋፋት ያስፈልጋል:: ይህ ደግሞ የሸቀጥ ምርት መስፋፋትን፣ የምርት ሃይሎችን ማደግንና የኢኮኖሚ ችግሮች መቃለልን ያስከትላል:: ጥቅም አለው ማለት ነው::

"Exchange is freedom to trade, it is capitalism. It is useful to us inasmuch as it will help us overcome th dispersal of the small producer, and to a certain degree combat the evils of bureaucracy, to what extent this can be done will be determined by practical experience.

"The fight against profiteering must be transformed into a fight against stealing and the evasion of state supervision, accounting and control. By means of this control we shall direct the capitalism that is to a certain extent inevitable and necessary for us into the channels of state capitalism.



"The development of local initiative and independent action in encouraging exchange between agriculture and industry must be given the fullest scope". (Lenin, SW, Vol 3, P. 618)

ሌኒን በዚህ መልክ የካፒታሊዝም ማደግ አስፈላጊና ግዴታ /የማይቀር/ መሆኑንና ትክክለኛውም መንገድ እንዲያድግ መታገሉ ባይሆን ለሶሻሊዝም በከፍተኛ ደረጃ መሠረት በሆነው የመንግሥት ካፒታሊዝም ቁጥጥር ስር እንዲውል ማድረግ እንደሚያስፈልግ የተናገረው የአራት አመት እድሜ ያለው የወዝአደሩ መንግሥት ነበር:: የአራት አመት እድሜ ያለው የእኛ የንዑስ ከበርቴ መንግሥት ግን ተቃራኒውን ለማድረግ በመዝመት ላይ ነው::

ደርግ በአሁኑ ታሪካዊ ወቅት በኢት ማደግ የሚችለውንና የሚገባውን ካፒታሊዝምን በመቀሳሳውና የገበሬውን ካፒታሊዝም በተለይ በአንገቱ ለመቁረጥ መዝመት ይዟል:: ደርግ ከአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መሠረተ አሳቦች ውጭ የሆነ ፀረ ካፒታሊስት ዘመቻ በማካሄድ ላይ ነው:: የደርግ ፀረ ካፒታሊስት ዘመቻ ያተኮረው በገጠሩ ክፍል በአርሶ አደሩ ላይ ነው:: በዚህ በኩል ደርግ በገጠር የሚካሄደውን ማንኛውም አይነት የካፒታሊስት ግንኙነት ለመደምሰስ ቆርጦ የተነሳ ይመስላል:: እንዲህ ይላል፦

"Here and there, we see individualism on the part of the peasant producer...This individualism on the part of the peasantry has manifested itself in relation to the food market....the situation of the peasantry could lead us not towards socialism but towards capitalism. This drift towards individualism or self...enrichment can be very dangerous unless it is nibbed in the bud".
(The Campain P.9)

የደርግ ዘመቻ በገጠሩ ካፒታሊዝም ማደግ እንደሌለበትና አስፈላጊ እንዳልሆነ ብቻ ሳይሆን አደገኛ እንደሚሆን አድርጎ ያቀርባል:: ይህ አቀራረብ በጣም አደገኛ ነው::

የኢት ኢኮኖሚ የምርት ሃይሎች እድገት ወደኋላ የቀረበት ከፊል ፊውዳል ከፊል ከበርቴ ኢኮኖሚ ነው:: ከሁለቱ ክፍሎች የፊውዳሉ ስለሚያይል የኢት ኢኮኖሚ የገበሬ ኢኮኖሚ ነው:: በእንደዚህ አይነቱ የኢኮኖሚ ስርአት ውስጥ አርሶ አደሩ መሬት ሲያገኝ የግል ሀብቱ በሆኑት የእርሻ መሣሪያዎች የሚያመርተው ምርት ጊዜ ሲሆን፣ ለመሬት ባለቤቶች በልዩ ልዩ መልኮች የሚያደርጋቸው ክፍያዎች ሲቀነሱ ተርፎ በገበያ ላይ አውጥቶ ሊሸጠው የሚችለው ይተርፈዋል:: የሚተርፈውን እህል በገበያ ላይ አውጥቶ ወደ ገንዘብ ከለወጠ በኋላ ሌሎች እርሱ ሊያመርታቸው የማይችላቸውን ነገሮች ይገዛል:: የመሸጥና የመግዛት የልውውጥ ክንውኖች ይስፋፋሉ:: ተበታትነው የሚኖሩ አምራቾች ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች ይፈጥራሉ:: የስራ ክፍፍሎች ይስፋፋሉ:: በአይነት የሚደረግ ልውውጦች በገንዘብ ይካሄዳሉ:: ይህም ሂደት የካፒታሊስት ኢኮኖሚ መሠረት ነው:: የገንዘብ ኢኮኖሚ ወደኋላ በቀረበት፣ የሸቀጥ ምርት ዝቅተኛ በሆነበት ማመላለሻዎችና ገበያ

ቾ በለተሰሩፉበት ሚዛየሸል ኢት አገዲህ አይነቶ ሂደት አሰፈላጊም ገኒታም ነው። በአ
ነጸዘህ አይነቶ ሁኔታ ውስጥ መደረገ የሚገበው ከፒታሊዝም አገዓያዱነ፣ ወይም ማደገ የ፫
መሪውናና ያደገውን ለመደምሰስ መታገል ባይሆን አገደየሁኒታው በተወሰነ ቀጥር ሰር አገ
ዲሰሩሩና ከመንግሥት ከፒታሊዝም ጋር ሊቶናበር የሚችልበትን መንገዱ መሸት ነው።

"Capitalism is a bane compared with socialism. Capitalism is a boon compared with medievalism small production, and the evils of bureaucracy which spring from the dispersal of the small producers. In as much as we are as yet unable to pass directly from small production to socialism, some capitalism is inevitable as the elemental product of small production and exchange, so that we must utilize capitalism (particularly by directing it into the channels of state capitalism) as the intermeditary link between small production and socialism, as a means, a path, and method of increasing the productive forces". (Lenin, SW, Vol 3, P.607)

ስለሆነም ደርግ ከዚህ ውጭ በሆነ መንገዱ በመሰረት በአሁኑ ወቀት በኢት በሚደገ
ሳይ ያለውን ከፒታሊዝምን ''በአንጭጩ ለመቅጨት'' የሚያደርገው ዘመቻ በትናንሽ ሸቀጥ አ
ምራቾች፣ በተለይም በአርሶ አደሩ ሳይ የሚከሄዱ ዘመቻ ነው። ይኸም ዘመቻ ከኢት ህብ
ረተሰብ እድገት ህገጋት ውጭ የሚከሄዱ የአዲሱን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ኢኮኖሚያዊ
ይዘት የሚያሪገ፣ የምርት ሃይሎችን እድገት የሚቀጭና ወደ ስሸሊዝም የሚደረገውን ጉዞ የ
ሚያስተጓጉልና የሚያሬዝም ነው።

## 3:3 ዘመቻውና የደርግ ፖለቲካ

የደርገን የምርት ዘመቻ በኢኮኖሚያዊ ይዘቶ ብቻ ማየት በቂ አይደለም። ፖለቲ
ካዊ ይዘቱንም ማየት ያስፈልጋል። ከዚህ ቀጥለን ደርግ የሚያካሄደው የምርት ዘመቻ ም
ን አይነት ፖለቲካዊ ይዘት እንዳለው በጥሩ ለማስየት እንሞክራለን።

የምርት ዘመቻውን መምሪያ ድርጅታዊ ተቋም፣ ስለአዲሱ ዲሞክራሲና ስሸሊስት ኢኮኖሚ
ያቾ መገንበት የሚነተሳቸውን ፖሊሲያቾ፣ ዘመቻውን ከስራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን የቴ
ክኒካል የማቴሪያል ምንጮችን፣ ወዘተ ስንመለከት ደርግ አንዱ ቅልጥ ያለ ትልቅና ወሰኝ የ
ፖለቲካ ለውጥ እንዳደረገ እናያለን። ደርግ የአዲሱ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት
ፍልስፍናን ሽሮ ''የከበርቴ-አልባ እድገት''/ነገ-ካፒታሊስት ዲቨሎፕሚንት/ፍልስፍናን
የአብዮቱ መመሪያ አድርጓል። ይህ ነው የደርግ ምርት ዘመቻ ፖለቲካዊ ይዘት።
ከዚህ ቀጥለን የአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት
ነና ''የከበርቴ አልባ እድገት''ጉዳናን አገዓገዱ በህሪያቸንና የደርገን የምርት ዘመቻ



ፖለቲካዊ ነፀብራቆች በአጭር በጥሩ በማወዳደር ሰምን ጊ ወ — የአብዮት ፍልስፍናን ሽሮ
''የከበርቴ አልባ እድገት''ፍልስፍናን መመሪያው አድርጓል ለማለት እንደበቃን እናብራራ
ለን።

## 3:3:1 "የከበርቴ-አልባ እድገት"ፍልስፍና ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ ካለወዝአደሩ መደብ አመራር ገቡን ሊመታ ይችላል ብሎ ያምናል።

የአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፍልስፍና ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ ገቡን እንዲ
መታ ወዝአደራዊ አመራር ማግኘት አለበት ይላል። በዚህ ፍልስፍና መሠረት ወደኋላ በቀ
ሩ ከፊል ፊውዳል ከፊል ከበርቴ አገሮች ውስጥ ለዲሞክራሲና ለብሔራዊ ነፃነት የሚደረጉት
ህዝባዊ ንቅናቄዎች በማያወላውል መንገድ ከፍጻሜ እንዲደርሱ ብቸኛ አብዮታዊ በሆነው በወ
ዝአደሩ መደብ መመራት አለባቸው ብሎ ያምናል። እርግጥ በኢንዱስትሪ [illegible] የተ
ነሳ የወዝአደሩ መደብ በቁጥሩ አነስተኛ በድርጅቱ ደካማ ነው። [illegible] ከበርቴ
ው መደብ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ደካማ፣ በመሆኑ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር [illegible]
ባበረ የኋላ የኋላ የመታረቅ ዝንባሌ ስላለውና የአብዮቱ ገብ መምታት ስለሚያስፈራው፣
እንዲሁም የገጠሩ ከበርቴው መደብም በመሳቀይ ባህሪው የተነሳ [illegible] አብዮትን ለመም
ራትና ከተወሰነ ደረጃ በኋላም የመክዳት ዝንባሌ ስላለው በማያወላውል መንገድ አብዮትን
እስከመጨረሻው በመምራት ከግቡ ለማድረስ መደባዊ ባህሪው የሚፈቅድለት [illegible] ስለ
ሆነ የቀጥሩን ማነስ በድርጅታዊና ንቃታዊ ጥንካሬ ሽፍኖ መምራት አለበት። ይህ ማለት
ግን ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ በሌሎች ሃይሎች አይጀመርም ወይም የወዝአደሩ መደብ አብዮትን
ለብቻው ማካሄድ አለበት ማለት አይደለም። ሊጀመር ይችላል። [illegible]
ሚና እንዲጫወት ታሪክ ሃላፊነት ቢጥልበትም የዲሞክራሲው አብዮት [illegible]
ሆኑ አብዮቱ ገቡን ሊመታ የሚችለው በወዝአደር፣ አርሶ አደር [illegible]
አደሩ መደብ ፓርቲ የሚመራ ፀረ ቡስት ሃይሎችን ሁሉ የሚያቅፍ [illegible]
መንግሥት ይሆናል። በጥሩ የአብዮት ፍልስፍናን ለአብዮቱ ገብ [illegible]
ርቲ አመራር ወሰኝ ነው ብሎ ያምናል። በዚህ ፍልስፍና መሠረት [illegible]
ገኘ አብዮቱ ገቡን ይመታል። ከሳገኘ ደግሞ ይከሳሸል። ''የከበርቴ አልባ እድ
ገት''ፍልስፍና ይኸን ከላይ የጠቀስነው አስብ ይቃረናል።

"....The assertion that in all cases in countries where the working class does not have direct leadership, where it has not assumed power, it is impossible to carry out the tasks in the general-democratic stage of the revolution... leads to a tacit recommendation to sit back and wait for the day when a local industry and proletariat come into being"

> in those Afro-Asian countries where no full fledged proletariat has as yet taken shape, for the day when this proletariat will come to lead the movement, to assume power". (ulyanovsky, Socialism & the Newly Independent Nations, P. 44)

ይህን አባብ የጠቀስነው ለመተቸት አይደለም:: ትችት ከጀመርን ብዙ ነገር ውስጥ ያስገባናል:: የጠቀስነው ከላወዝአደሩ መደብ አመራር አዲስ ብሔራዊ ዲሞክራሲ አብዮት ግቡን አይመታም የሚለውን የአብዲኮ ፍልስፍናን ''የከበርቴ-አልባ አድገት'' ፍልስፍና እንዴት አድርጎ እንደሚያንቋሽሽና እንደሚቃረን ለማሳየት ያህል ነው:: "የከበርቴ-አልባ አድገት" ፍልስፍና የሚለው ባሳደጉ አገሮች ውስጥ በኢንዱስትሪዎች አለማደግ የተነሳ ወዝአደሩ በቁጥርና በድርጅት ወደኋላ የቀረ ስለሆነ አብዮትን ሊመራ አይችልም:: ኢንዱስትሪዎችን አስፋፍቶ ቁጥሩን ለማብዛት ቁጥሩን ወሳኝ አድርጎ ይወስደዋል ማለት ነው ፣ ያለውንም አንቅቶና አደራጅቶ የወዝአደሩን መንቃትና መደራጀት አይፈልግም ማለት ነው፣ አብዮትን እንዲመራ ለማድረግ ጊዜ ይወስዳል ነው:: ሁኔታውን በዚህ ካስቀመጠ በኋላ አመራሩን ''የሶሻሊስት ዝንባሌ'' ያለው የህብረተሰብ ክፍል /አብዛኛውን ጊዜ የሚሆነው የንዑስ ከበርቴው መደብ/ መውሰድ እንዳለበትና በዚህም ግቡን ሊመታ እንደሚችል ይናገራል:: ለምሳሌ ኮልያኖቭስኪ "The contemporary national liberation movement and the peasantry" በሚለው ስራው ውስጥ በገለፀ ''ወዝአደሩ ገና ያላደገ ስለሆነ አመራሩን የተማረው የንኡስ ከበርቴ ክፍል መያዝ አለበት'' ይላል:: የሚመሠረተውም መንግሥት የዚሁ መደብ እንደሚሆንና ሌሎች ሃይሎች ህብረት ፈጥረው ሊያጠናክሩት እንደሚገባ ይናገራል::

ኢ.ሠ.ፓ በአሁኑ ወቅት የሚለው ይህን ነው:: በምርጫ ዘመቻው ስለ አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ ሳይሆን ስለሶሻሊስት መገንባት ማውራት፣ በንዑስ ከበርቴው በደርግ አመራር አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ግቡን እንደመታ፣ ለዚህ ተግባር የወዝአደሩ መደብ አመራር እንዳላስፈለገና እንደማያስፈልግ ለማስመሰል ነው:: እንዲያውም በምርጫ ዘመቻው በተሰጡት ልዩ ልዩ መግለጫዎች ''ያለወዝ አደሩ ፓርቲ በደርግ መሪነት እዚህ ደርሰናል፣ የኢኮኖሚ ዘመቻውም ቢሆን ያለወዝአደሩ ፓርቲ ወደ ሶሻሊዝም በሚገባ ሊያመራ ይችላል'' የሚሉ አሳቦች ተሰንዝረዋል:: ከዚህም ሌላ በአሁኑ ወቅት የሚደረገው ዝግጅት ሁሉ ወዝአደሩን አንቅቶና አደራጅቶ ለአመራር እንዲበቃ ማድረግ ሳይሆን ንዑስ ከበርቴውን ''አብዮታዊ ፓርቲ'' አድርጎ የአብዮትን አመራርና የፖለቲካ ስልጣኑን እንደያዘ ለማቆየት ነው:: በዲሞክራሲ አብዮቱ አመራር ጥያቄ ላይ የደርግ መመሪያ የአብዲኮ ፍልስፍና ሳይሆን ''የከበርቴ-አልባ አድገት'' ፍልስፍና ሆኗል ማለት ነው::



### 3:3:2 "የከበርቴ-አልባ አድገት" ፍልስፍና በንዑስ ከበርቴው መደብ አመራር ሶሻሊዝምን መገንባት ይቻላል ብሎ ያምናል::

የአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፍልስፍና የሚያስተምረን ከላወዝ አደሩ መደብ አመራር ዲሞክራሲ አብዮት ግቡን አለመምታቱን ብቻ ሳይሆን ወደ ሶሻሊዝም የሚደረገው ሽግግርም ሆነ ከሽግግሩም በኋላ ለሚካሄደው የሶሻሊዝም መገንባት ይኸው አመራር እንደሚያስፈልግ ነው:: ምክንያቱም ከሶሻሊስት /የወዝአደሩ/ መንግሥት ሶሻሊዝምን መገንባት አይቻልም::

''የከበርቴ-አልባ አድገት'' ፍልስፍና ግን ዲሞክራሲ አብዮትን ንዑስ ከበርቴው ከግቡ ሊያደርሰው ይችላል ከሚለው እምነቱ በመነሳት የሶሻሊስት ህብረተሰብም በዚሁ መደብ ሊገነባ እንደሚችል ይናገራል::

> "Leadership in effecting non capitalist changes (የሶሻሊስት ለውጦች ማለት ነው) is provided by national revolutionary democrats who generally have a radical petty-bourgeois origin". (Solodovnikov, Non-Capitalist Development: An Historical outline, P. 34 brackets added)

ኢ.ሠ.ፓ በአሁኑ ወቅት ድንገት ተነስቶ ''ሶሻሊዝምን ለመገንባት'' የሚያደርገው ዘመቻ ከዚህ ''ንዑስ ከበርቴው ሶሻሊዝምን ለመገንባት ይችላል'' ከሚለው ''የከበርቴ-አልባ አድገት'' ፍልስፍና የፈለቀ ነው:: የሚመሳሰሉትም እዚህ ላይ ነው::

### 3:3:3 ''የከበርቴ-አልባ አድገት'' ፍልስፍና ከፊውዳሊዝም [illegible] ሳያልፍ በቀጥታ ወደ ሶሻሊዝም መሸጋገር ይቻላል ብሎ ያምናል::

በአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፍልስፍና መሠረት ህብረተሰቦች ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚያድጉት ማርክስ ኤንግልስ በሰቀመጡት ቅደም ተከተል (ጥንታዊ የጋርዮሽ ፣ ባሪያ፣ ፊውዳል፣ ከበርቴ፣ ሶሻሊስት) እንጂ አንዱ ሌላውን በመዝለል አይደለም:: [illegible] ከፊውዳል ህብረተሰብ የከበርቴውን ዘሎ ሶሻሊስት ደረጃ መግባት አይቻልም:: [illegible] አሁኑ የኢምፔሪያሊስት ዘመን በታዳጊ አገሮች ውስጥ ፊውዳሊዝም ተደምስሶ [illegible] ስርቶ አድጎና በቅራኔዎች ተውጦ እስኪወድቅ ድረስ መጠበቅ አይቻልም:: [illegible] ይህ ማለት ግን ከፒታሊዝምን ጠርሶ ዘሎ ማለፍ ይቻላል ወይም [illegible] ማለት አይደለም:: [illegible] ም:: ካፒታሊዝም ያድጋል:: እድገቱ ግን በጥርጡ መልክ አይሄድም:: [illegible] መደብ የሚመራው ህዝባዊ መንግሥት የህብረተሰቡን ዋና ዋና የሀብት ማፍሪያዎችን [illegible]

ባለቤትነት ስር በማድረግ፣ የህዝቡን ኑሮ የማያበላሹ እስከሆነ ድረስ የግል ባለቤትነት ያላቸው የሀብት ማፍሪያዎች እንዲኖሩ በመፍቀድ ካፒታልን እየተቆጣጠረ የመንግሥት ካፒታሊዝምን ያስፋፋል:: ይኸም አዲሱ የከበርቴ ኢኮኖሚ ይባላል:: በዚህ በአዲሱ የከበርቴ ኢኮኖሚ ለሶሺያሊዝም መገንባት የሚያስፈልጉት ማቴሪያላዊና ቴክኒካዊ መሠረቶች ይባላሉ:: በዚህ መልክ በአዲሱ የከበርቴ ስርአት ታልፎ ወደ ሶሺያሊዝም ይገባል::

"የከበርቴ-አልባ እድገት" ፍልስፍና ግን ካፒታሊዝምን ዘሎ ወደ ሶሺያሊዝም መሸጋገር የሚቻል መሆኑ ብቻ ሳይሆን እንደሚያስፈልገም ያስተምራል:: እንዲህ ይላል:–

> "....in the era of imperialism and socialist revolutions, the peoples of backward countries can achieve socialism not through capitalist development, but by-passing it". (V. Solodovnikov, Non capitalist development P. 24)

ይኸ ፍልስፍና ወደ ሶሺያሊዝም ለሚደረገው ሽግግር የሚያስፈልጉትን ማቴሪያላዊና ቴክኒካዊ ሁኔታዎች ለማሟላት ታዳጊ አገሮች በማንኛውም አይነት የከበርቴ ስርአት ማለፍ አያስፈልጋቸውም ለሚለው አስተሳሰቡ የሚሰጠው ምክንያት የሶሺሊስት አገሮችን በአለም ውስጥ መኖር ነው:: በዚህ ፍልስፍና መሠረት ከፍተኛ የማቴሪያል፣ የቴክኒክ፣ የሳይንስ፣ ወዘተ እድገት ያላቸው ሶሺሊስት አገሮች በንፃቸው ስለቆሙ ታዳጊ አገሮች ወደሶሺያሊዝም ለመሸጋገር ሁሉን ነገር በራሳቸው መሥራት አያስፈልጋቸውም:: የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ ከእነዚህ የሶሺሊስት አገሮች 1/ በእርዳታ መልክ 2/ በብድር መልክ 3 የጥሬ እቃ ምርታቸውን በማስደገ ከእነዚህ አገሮች ጋር በሚያደርጉት የንግድ ልውውጥ ሊያገኙ ይችላሉ::

> "Relying on the support of the highly developed socialist countries, the backward countries can pass to socialism without going through the capitalist stage of development". (Nikitin, P.197)

ኢ ወ መ በኢኮኖሚ ዘመቻው ''ሶሺያሊዝምን ለመገንባት'' በሚል የንዑስ ከበርቴ ድንፋታ በአገሪቱ በጠቅላላውና በገጠሩ በተለይ ማደግ የጀመረው ካፒታሊዝም በእንጭጩ መቀጨት አለበት እያለ የሚፎክረው ለመቅጨትም የሚታገለው ''የከበርቴ-አልባ እድገት'' ፍልስፍናን በመከተሉ ነው:: ለውጭ እርዳታም ከፍተኛ ቦታ የሰጠው ለዚሁ ነው::

## 3:3:4: ''የከበርቴ አልባ እድገት'' ፍልስፍና ወደ ሶሺያሊዝም ''በሰላማዊ መንገድ'' መሸጋገር ይቻላል ብሎ ያምናል::

የአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፍልስፍና ''በሰላማዊ መንገድ'' እንደ አንዱ የትግል መንገድ አንዱ እንደ ወሳኝ አድርጎ አይወስደውም:: ይህ ፍልስፍና እንደህው



ና ሁኔታው ሰላማዊ ህጋዊ ና ትጥቃዊ ህገ ወጥ መንገዶችን ማቀነባበር እንደሚያስፈልግና ወሳኙ ግን የኋለኛው እንደሆነ ያስተምራል:: ማንኛውም ገዢ መደብ ስልጣኑን በፈቃዱ ስለማይለቅ አብዮታዊና ወሳኝ የፖለቲካ ስልጣን ለማድረግ የመደብ ትግል ለማካሄድ ማለትም ስልጣን በወዝ አደሩ እጅ በማስገባት ወደ ሶሺሊዝም ለመሸጋገር አመፅ ወይም ሃይል መጠቀም እንደሚያስፈልግ ያስተምራል:: ስለሆነም በሰፊው ህዝብ መንቃትና መደራጀትና መታጠቅ እንዲሁም በወዝአደሩ መደብ የሚመራ ቀይ ሠራዊት መኖር አስፈላጊነት ላይ አተኩሮ ያደርጋል::

''የከበርቴ-አልባ እድገት''ፍልስፍና መሠረት ግን በታዳጊ አገሮች ውስጥ አይነተኛ ነው የሚባል የተወሰነ የምርት ስልት ወይም መደብ ስለሌለ በመጀመሪያ ደረጃ ከሁሉም መደቦች የተውጣጣ መንግሥት ይቋቋማል:: በዚህ ወቅት የዲሞክራሲ ለውጦች ይደረጋሉ:: በካፒታሊዝም ኢንዱስትሪዎች እየተስፋፉ ስለሚሄዱ ወዝአደሩ በቁጥሩ እየጨመረ ይሄዳል:: በካፒታሊዝም ላይ አጥቂ እርምጃዎች ይወሰዳሉ:: የወዝአደሩ ቁጥር እያደገ መምጣትና ካፒታሊዝም እየተዳከመ መሄድ ይኸን የተቋቋመውን መንግሥት ከሳንባች ደም መፍሰስ በሰላም ለወዝአደሩ መደብ ስልጣኑን እንዲለቅ ያደርገዋል:: ስልጣን/የመደብ ትግል/በሃይል ሳይሆን በሰላም በግድ ሳይሆን ብሎም በፈቃዱ ከከበርቴው መደብ ወደ ወዝአደሩ መደብ ሲዛወርና ብሎም ወደ ሶሺሊዝም በሰላም ለመሸጋገር እንደሚቻል ያስተምራል:: ይኸንን እስከንደሮቭ የሚባለው ፀሐፊ በ1970 እአአ በታተመው ''ሶስተኛው አለም''በሚለው ሥራው ውስጥ ያብራራል:: ከእዚህ እምነት የተነሳ ለንቅናቄ፣ ለድርጅትና ለትጥቅ ብዙ አተኩሮ አያደርግም::

ኢ ወ መ ዛሬ ከሲቪሉና ከወታደራዊው ቢሮክራሲ፣ ከብሔራዊ ከበርቴው፣ ከንዑስ ከበርቴው፣ ከወዝአደሩ፣ ከአርሶ አደሩ የተውጣጣና በእርሱ ቁጥጥር ስር የሆነ መንግሥት ለማቋቋም የተነሳ ለመሆኑ በወዝአደሩ ፓርቲ አመሠራረት ጥያቄ ላይ ከወሰደው አቋም ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ዘመቻ መምሪያ ብሎ ከአቋቋመው ድርጅታዊ መዋቅር ለመረዳት ይቻላል:: ዲሞክራሲ መብቶችን በማፈን፣ አንቂዎችን በማሰደድ፣ ሰፊውን ህዝብ ትጥቁን በማስፈታትና ድርጅቶችን በማፈራረስ ሰፊው ህዝብ እንዳይነቃ እንዳይደራጅና እንዳይታጠቅ ለማድረግ የወሰዳቸውና የሚወስዳቸው እርምጃዎች ደርግ ''የከበርቴ-አልባ እድገት''ፍልስፍና መከተሉን ያረጋግጣሉ:: ከላይ የጠቀስነውን ለማጠቃለል የሚከተለውን ለማለት ይቻላል:: ከህብረተሰብ የእድገት ህግጋት አንፃር ሲታይ ፀረ ታሪካዊ ቀስ አክልነት አመለካከት አለው፤ ከወዝአደሩ መደብ አንፃር ሲታይ የወዝአደሩን ሚና ለንዑስ ከበርቴ ይሰጣል:: የወዝአደሩን መደብ ሳይሆን የንዑስ ከበርቴውን የአብዮት መሪና የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ይጥራል፤ ከመደብ ትግል አንፃር ሲታይ በመደቦች መሃል ተባባሪ ቅራኔ እንደሌለና አንዱ መደብ [illegible]

ሉት ሁኔታዎች እንደሚያዘጋጁ አድርጎ ያወራል:: ከቦሸቪዝም አንፃር ሲታይ ለወዝአደራዊ ሳይሆን ለነኡስ ከበርቴያዊ ቦሸቪዝም አተኩሮ ይሰጣል:: ከአብዮት ደትገል ዘዴ አንፃር ሲታይ ለትጥቃዊ /ሀገ—ወጥ/ ሳይሆን ለሰላማዊ /ህጋዊ/ ዘዴ ወሳኝ ቦታ ይሰጣል:: ከብሔራዊ ነፃነት አንፃር ሲታይ በውጭ እርዳታ ላይ ስለሚያተኩር ለተገኘነት ብሎም ለብሔራዊ ነፃነት መደፈር በር ይከፍታል:: ''የከበርቴ-አልባ እድገት'' ፍልስፍና ፀረ ቶስ አካል፣ ፀረ አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲ አብዮት ፣ ፀረ ወዝአደር፣ ፀረ ቦሸቪስት የሆነ የከሳቦች ፍልስፍና ነው:: ኢ ወ መ የአዲሱን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፍልስፍና ሸሮ መመሪያው ያደረገው ''የከበርቴ አልባ እድገት'' ፍልስፍና ይዞት በአጥፉ ይኸ ነው:: ለደርግ ፀረ አብዮታዊነት ባህሪ መጠናከርም ምንጩና ምክንያቱ የዚህ ፍልስፍና ተጽእኖ በኢት አብዮት ላይ እየተጠናከረ መምጣት ነው:: በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሃቀኛ ተራማጆች ምን ማድረግ አለባቸው? ከዚህ ቀጥለን ባጭሩ እንመለከታለን::

3፡4፡ ዘመቻውና ሃቀኛ ተራማጆች

1/ ሃቀኛ ተራማጆች የሰፊው ህዝብ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ችግር ማጥ ውስጥ እንደሚገኝ ያውቃሉ:: ከዚህ ማጥ እንዲወጣ የሚያስችሉት እርምጃዎች መወሰድ እንደሚገባቸው መጠየም ብቻ ሳይሆን እንዲወሰዱም ታግለዋል:: ይታገላሉም:: ለምሳሌም ያህል በውጭ አገር አኢተማ፣ ኢኘአዩና፣ በልዩ ልዩ በአገር ቤት መኢሶን፣ ኢሕወን፣ ኢሰአን፣ ወዘተ በልዩ ልዩ ውሳኔዎቻቸውና መግለጫዎቻቸው ያስቀመጧቸውን ነጥቦች ብንመለከት ሃቀኛ ተራማጆች ምን ያህል ትግል እንዳደረጉ እንገነዘባለን:: ሰፊው ህዝብም በየእለቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳይ ጥያቄዎችን እያነሳ በየሰላማዊ ሰልፉና በየስብሰባው እንደታገለ እናውቃለን:: በመሆኑም ደርግ ያወጣውን የኢኮኖሚ ዘመቻ ሃቀኛ ተራማጆች እንዳለ አይቃወሙት [illegible] እንዳለም አይቀበሉትም::

ሃቀኛ ተራማጆች የደርገን የምርት ዘመቻ ደርግና ቀኝ አድርባዮች እንደሚያዩት አያዩትም:: ብሎም ደርግና ቀኝ አድርባዮች እንደሚሉት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ችግር ይህ የሚደረገው ዘመቻ ''በማያዳግም ሁኔታ'' ይፈታል ብለው አያምኑም:: በዚህ ፋንታ ዘመቻው ያሉበትን ጉድለቶች፣ የሚከተለውን ዘገባ፣ በአብዮቱ ላይ ሊያስከትል የሚችላቸውን ልዩ ልዩ ተጽእኖዎች፣ በስራ ላይ ሊውል መቻሉንና አለመቻሉን፣ ወዘተ ያመለክታሉ::

2/ የተባለው የምርት ዘመቻ የሚካሄደው በህዝቡ በኩል አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ቢሆን ኢ ወ መ ለህዝቡና ለአብዮቱ የሚጠቅመውን የአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፍልስፍና ሸሮ ለህዝቡና ለአብዮቱ ጉዳት የሚያስከትለውን ''የከበርቴ-አልባ እድገት'' ፍልስፍና መመሪያው በአደረገበት ወቅት ነው:: የዘመቻው የበላይ መሪው ደግሞ ይኸው ሰፊውን



ህዝብና አብዮትን የሚጎዳ መስመር የያዘው ደርግ ነው:: ዘመቻውን በበላይ የማስፈጸም ሃላፊነትም በአፍ ''ለሰፊው ህዝብ ተሰጥቷል'' ቢባልም በአንደኛ ደረጃ የተጣለው በወታደሮች፣ በሲቪል ቢሮክራቶችና በውጭ አገር አማካሪዎች፣ ልዩ ልዩ ባለሙያዎች ወዘተ ላይ ነው:: በእንደዚህ አይነት አመራር እስከተመራና የሰፊው ህዝብ ነፃ ተሳትፎ እስከ ሌለበት ድረስ ዘመቻው ስራ ላይ ሊውል አይችልም:: የደርግ ፕሮግራምና ዘመቻ የወረቀትና የአፍ ብሎም የማታለያ ሆኖ ይቀራል:: እንዲያውም በአንድ በኩል ቢሮክራሲውን እንዲጠናከር ይረዳል:: በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ አገር የማቴሪያል፣ የገንዘብ፣ የአማካሪዎች ወዘተ እርዳታ ላይ ብዙ ስለሚመካ አገሪቱን በውጭ ሃይሎች ላይ ጥገኛ እንድትሆንና ብሔራዊ ነፃነትዋን እንዲደፈር ያደርጋታል:: ሃቀኛ ተራማጆች ይህን በሚገባ በመረዳት ለአብዮቱና ለብሔራዊ ነፃነቱ ለሚቆረቆረው ሰፊው ህዝብ በሚገባ መግለጽ ይኖርባቸዋል::

3/ በአሁኑ ወቅት ኢ ወ መ ለመደላደልና አፍዩ ብሎ ''በሰላም'' ለመግዛት ይፈልጋል:: ስለሆነም ይህን ፍላጎቱን ለማሟላት የሚያስችለውን ሁኔታ ሁሉ ለመቷቷምና ለማጥራት ማንኛውንም ጥረት ያደርጋል::

አሁን ባለንበት ሁኔታ የደርግን የመደላደልና በስልጣን ላይ የመቆየትን ፍላጎት በማያዳግም ሁኔታ የሚሰብረው የአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከፍተኛ መድረስ ብቻ ነው:: ምክንያቱም ያን ጊዜ ደርግ ከተቀመጠበት የስልጣን ኮርቻ ላይ ደግሞ በማይመለስበት ሁኔታ ይወርዳል:: ደርግ ይኸን ጠንቅቆ ያውቃል::

ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ደርግ ዋና ተግባሩ አድርጎ የሚወስደው አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ግቡን ሊመታ የማይችልባቸውን ሁኔታዎች ሁሉ መፍጠር ነው:: የምርት ዘመቻው ከዚህ አንፃር መታየት አለበት:: ከዚህ አንፃር ሲታይ በተለይ ''ቦሸቪዝምን ለመገንባት'' በሚል የሚደረገው አጉል ዘመቻ አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እንደተፈፀመ፣ የአሁኑ ተግባር መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ ብሎም የተጀመረውን አብዮትን ከፍጻሜ ለማድረስ መታገል ሳይሆን ''ቦሸቪዝምን መገንባት'' እንደሆነ አድርጎ የሚያቀርብ ነው:: ሃቀኛ ተራማጆች ይህ ለደርግ መደላደል አመቺ ሁኔታ ለማስናዳት፣ ወቶገበር ለመፍጠር፣ ከትግል ለማዘናጋትና ትጥቅ ለማስፈታት በደርግ የተጠነሰሰ ሴራ እንደሆነ መረዳትና ለሰፊው ህዝብ ማስረዳት አለባቸው::

4/ በአሁኑ ወቅት ደርግ ''አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መርቼ እዚህ አድርሻለሁ፣ የቦሸቪስት አብዮቱን ለማካሄድ ቦሸቪስት ኢትን ለማገንባትም ተያይዤአለሁ'' በሚል ፈሊጥ የወዝአደሩን መደብ ሚና ለመንጠቅ እየተዘጋጀ ነው:: ቀኝ አድርባዮችም

''እይዘህ እዚሀ ያደረስክልንን ያህል ለሶሻሊስት አብዮታችንም መሪያችን አንተ ነህ፣ እስከመጨረሻው ከጎንህ ቆመናል''በማለት እያበረታቶት ናቸው፡፡ ይህ ዘገባሌ ከሁሉም የበለጠ አደገኛ ነው፡፡

አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮታችን ገና ገቡን አልመታም፡፡ ወዝአደራዊ አመራር አስከሳገኘ ድረስም ገቡን አይመታም፡፡ የሶሻሊስት አብዮትም እንደዚሁ፡፡ ባለንበት ዘመን ለእነዚህ አብዮቶች የአመራር ሃላፊነት የተጣለው በወዝአደሩ መደብ ላይ ነው፡፡ ይህንን ታሪካዊ ሃላፊነት የንዑስ ከበርቴውም ሆነ የከበርቴው መደብ ሊወስዱት አይችሉም፡፡ ንዑስ ከበርቴው የሚያካሂደው የንዑስ ከበርቴ አብዮት፣ የሚገነባው ሶሻሊዝም ደግሞ ''የንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝም''ነው፡፡ ወዝአደራዊ ሶሻሊዝም በንዑስ ከበርቴው ከቶ ሊገነባ አይችልም፡፡ ንዑስ ከበርቴው ወዝአደሩን ከቶ ሊተካ አይችልም፡፡ ሃቀኛ ተራማጆች ይህን የደርገን ዘገባሌ በሚገባ ማጋለጥና ወዝአደሩ የአብዮቱን አመራር ከንዑስ ከበርቴው ነጥቆ እንዲወስድ ማስረዳትና ለዚህ ታሪካዊ ሚናው የሚያበቃው ሶሻሊስታዊ ንቃት፣ ድርጅትና ትጥቅ እንዲያገኝ ከመቸውም ይበልጥ በልዩ ልዩ መልኮች በወዝአደሩ ውስጥ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

5/ የአርሶ አደሩን ትግል ለማዳከም ደርጉ ከመቸውም ይበልጥ የመሬቱን እቁጁ እንደ መደለያ አድርጎ በመጠቀም ላይ ነው፡፡ በዚህ በኩል ደርጉ ''መሬት የሚሰጥህ እኔን የመሰለ መንግሥት የት ታገኛለህ፣ ላንተ መሬት በመስጠቴ ብዙ ጠላት አፍርቻለሁ፡፡ በእኔ ጎን ቆመህ ካልታገልክ መሬትህን ታጣለህ''በሚል ቀረል አርሶ አደሩ በአርሱ ላይ እንዳይነሳ ለማድረግ ከንቱ የማታለያ ዘመቻ እያካሄደ ነው፡፡ በሌላ በኩል ገን የአርሶ አደሩን ድርጅቶች እያፈራረሰና ትጥቅ እያስፈታ ነው፡፡ ሃቀኛ ተራማጆች ለአርሶ አደሩ በትግሉ ያገኘውን መሬት ዘፍተኛ ጥቅም ሊያስገኝለት የሚችለው አብዮታዊ የፖለቲካ ለውጥ ሲደረግና አርሶ አደሩ ራሱ በህብረተሰቡ ውስጥ ፖለቲካዊ ተሰትፎ ሲኖረው ብቻ መሆኑን እየገለጡ እንዲነቃ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ መታገል ይኖርባቸዋል፡፡

6/ የዘመቻውን ጉድለቶች፣ ሥራ ላይ መዋል አለመቻልና አደገኛ ፖለቲካዊ ይዘቶች ለሰፊው ህዝብ ማሳወቅ እንደሚያስፈልግ መረዳት ብቻ አይበቃም፡፡ ይህ የተቀደሰ ተግባር አጥጋቢ በሆነ መንገድ ሊረጋገጥ የሚችልበትን ሁኔታ መጣልም አስፈላጊ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የኢት ተራማጅ ሃይሎች በሆነ ባልሆነው ተከፋፍለውና እንደየአቋሙ ጉዳት ደርሶባቸው ለአብዮቱ ይህ ነው የሚባል አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ህቡዕ ወታደራዊ መንግሥትና አጭሃሪዎች ሁኔታውን በመጠቀም እየተጠናከሩ ናቸው፡፡ እድሚአቸውን ለማራዘምም ሃቀኛ ተራማጆች ተበታትነውና ተዳክመው



እንዲተፉ የከረፍሰህ ገዘ ፖሊሲአቸውንና የጭፍጨፋ እርምጃቸውን በስለት ስለት እያበቡ ናቸው፡፡ ሃቀኛ ተራማጆች አሁን ባሉበት ሁኔታ ከተጠሉ እንደተበታተኑ ለፀረ—አብዮተ ወገን. እመቺ ሁኔታን እንደፈጠሩ ይቆራሉ፡፡ በገቢርም የአብዮቱ ባይሆን የፀረ—አብዮተ ነገል ''አጋዦች'' ይሆናሉ፡፡ ሃቀኛ ተራማጆች ይህን ሁኔታ ቶሎ በሰው ማየት አለባቸው፡፡ ሁኔታውንም አብዮቱን በሚጠቅም መንገድ ለማስተካከል በአዲስ ሁኔታ በአዲስ መልክ መሰባሰብ አለባቸው፡፡

# ማውጫ


ክፍል 1፡ የኢኮኖሚ ስርአትና ህብረተሰብ ገጽ 1

1፡1፡ የኢኮኖሚ ስርአት ትርጉም 2

1፡2፡ የኢኮኖሚ ስርአትና የህብረተሰብ እድገት 6

1፡3፡ የኢኮኖሚ ስርአትና ብሔራዊ ነፃነት 19

1፡4፡ ማጠቃለያ 24

ክፍል 1፡ የዘሬይቱ ኢት የኢኮኖሚ ስርአትና የህብረተሰብ እድገት 34

2፡1፡ የኢት ኢኮኖሚ ስርአት በሽሊስት ወይስ ከፒታሊስት 34

2፡2፡ የጊዚያዊ ኢት ኢኮኖሚ ችግሮች አይነቶቻቸው ጥልቀቶቻቸውና መከንያቶቻቸው 47

2፡2፡1፡ የምግብ ሸቀጦች እጥረት 48

2፡2፡2፡ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት 58

2፡2፡3፡ የውጭ ንግድ ችግር 62

2፡2፡4፡ ሌሎች ችግሮች 67

ክፍል 3፡ የ ጊ ወ ሙ የሥርት ዘመቻ—ሂብዊ አመለካከት 74

3፡1፡ ዘመቻውና አላማዎች 74

3፡2፡ ዘመቻውና የአዲሱ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚ 93

3፡3፡ ዘመቻውና የደርግ ፖለቲካ 96

3፡4፡ ዘመቻውና ሃቀኛ ተራማጆች 102

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፣

የውጭ ኀይና ከውስጥ ሆኖ ቦርቦር ለማዳከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት እርሱን ከኀይና ቱያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቀርበ ጊዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ያለማቋረጥ ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግል ሲያካሄድ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያለተቋረጠ ነፃነት በመገጠቱ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፲ከየተኖረውም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መቀስቀሻ ሆነው በቆዩት በታጠቅና በትግላችን ስም መጠቀም ጀምረዋል፡፡ የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም ታጠቅና ትግላችን በ14 ዓመት የፈጠ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው፡፡እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያቋቋሙን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማናለስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወኪነገበር በመገዛት ለማፋፋም ነው፡፡ይህም አገደማይባክ የተረጋገጠ ነው፡፡ ለማገናዘም፣የተለመደው የመጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ይዘት፣የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር አባልነትን የማያመለክቱ ጎን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንድታውቁልን እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን፡፡ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው "ዓለም ዓቀፍ ፊኋሪስን" በሚባለው ስም የታወቀው የነ አስፋወሰን — መንገሻ ሥም የወጣቶች ድርጅት ነው፡፡

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአሌተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ